# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ገላትያ ሰዎች

## መግቢያ

### ጸሐፊው

የገላትያ መልእክት ጸሐፊ ሐዋርያው ጳውሎስ መሆኑን የመልእክቱ የመጀመሪያ ቍጥር (1፥1) ያመለክታል፡፡ በ19ኛው ምእተ ዓመት ከተነሡት ጥቂት ምሁራን በስተቀር የመልእክቱ ጸሐፊ ጳውሎስ በመሆኑ ላይ ከሌላ አቅጣጫ የተሰነዘረ ጕልሕ ጥያቄ አልነበረም፡፡

### መልእክቱ የተጻፈበት ጊዜና ተደራስያን

የገላትያ መልእክት የተጻፈበት ጊዜ መልእክቱ በተጻፈላቸው ሰዎች ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ለዚህም ሁለት ዋና ዋና አመለካከቶች አሉ፡-

(1) የሰሜን ገላትያ አመለካከት፤ ይህ አመለካከት ጎሎች በ3ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ወረው በያዙት በትንሹ እስያ የሰሜኑ ማእከላዊ ክፍል ለሚገኙ (ለፔሲነስ፣ አንሲራና ታቪየም) አብያተ ክርስ ቲያናት የተጻፈ መሆኑን ይገልጻል፡፡

የሐዋርያት ሥራ ምንም ፍንጭ ባይሰጥም፣ ጳውሎስ በሁለተኛው ሐዋርያዊ ጕዞው እነዚህን ቦታ ዎች መጐብኘቱ ይታመናል፡፡ በዚህ አመለካከት መሠረት ጳውሎስ ይህን መልእክት በ53/46 እና በ57/50 መካከል በኤፌሶን ወይም በመቄዶንያ ሳለ ሳይጽፈው እንዳልቀረ ይገመታል፡፡

(2) የደቡብ ገላትያ አመለካከት፤ በዚህ አመለካከት መሠረት መልእክቱ የተጻፈው የሮማ ግዛት በሆነችው በገላትያ ደቡባዊ ክፍል ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ነበር፡፡ ጳውሎስ እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት (አንጾኪያ፣ ኢቆንዮን፣ ልስጥራና ደርቤን) የመሠረተው በመጀመሪያው ሐዋርያዊ ጕዞው ነበር፡፡ ይህ መልእክት ከ48-49 ባሉት ዓመታት ከጳውሎስ የመጀመሪያ ሐዋርያዊ ጕዞ በኋላና ከኢየሩ ሳሌም ጉባኤ (ሐሥ15) በፊት በሦርያ ውስጥ በምትገኘው በአንጾኪያ ሳለ እንደ ተጻፈ የሚናገሩ አሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ መልእክቱ በሦርያ በምትገኘው ከአንጾኪያ ወይም ከቆሮንቶስ በ51 እና በ53 መካከል ባለው ዓመታት እንደ ተጻፈ ይናገራሉ፡፡

### ዐላማው

ለመዳን በክርስቶስ ማመን ብቻ ሳይሆን የተለያዩ የብሉይ ኪዳንን ሥርዐቶች መጠበቅ የግድ አስፈላጊ እንደ ሆነ የሚያምኑ አይሁድ ክርስቲያኖች ነበሩ፡፡ እነዚህ ሐሰተኛ መምህራን፣ ጳውሎስ በገ ላትያ አውራጃዎች እየተዘዋወረ የሚያስተምረው ትምህርት ተቀባይ እያገኘና ፍሬ እያፈራ መሄዱን ሲያዩ፣ እግር በግር እየተከተሉ ከአረማዊነት ወደ ክርስትና የመጡትን ወገኖች አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ሥርዐቶ ችን መጠበቅ (በተለይም መገረዝን) አለባቸው በማለት ያውኩ ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች ይህን ያደረጉት ወደ ጌታ ከመጡት አሕዛብ ጋር ጥብቅ የወንድማማችነት መንፈስ በመፍጠራቸው ከሕገ ኦሪት ቀናእያን አይሁድ ስደት እንዳያመጣባቸውና መከራ እንዳይደርስባቸው (6፥12 ይመ) ከመፍራታቸው የተነሣ ነበር፡፡ እነዚህ አይሁድ ክርስቲያኖች ጳውሎስ እውነተኛ ሐዋርያ እንዳይደለ፣ መልእክቱም አሕዛብን ደስ ለማ ሰኘት አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ሕጐችን ከወንጌል ትምህርት እንዳስቀረ እየተቈጩ በመከራከር ለማስረ ዳት ሞክረዋል፡፡ ጳውሎስም እውነተኛ ሐዋርያ መሆኑንና የሚሰብከውም ወንጌል እውነተኛ እንደ ሆነ በሚያሳምን መልኩ በማቅረብ እያስረዳ ይጽፍላቸዋል፡፡ የጳዉሎስ ተቃዋሚዎች፣ "ጽድቅን ለማግኘት ሕግን መጠበቅ የግድ ነው" የሚልና ሌላም ተጨማሪ መመዘኛ በማቅረብ፣ የጸጋ ወንጌልን በማጣመም ዕንቅፋት ሆነው ነበር፡፡ መርዘኛ የሆነው የሐሰት ትምህርታቸው ጨርሶ እንዲወገድ ካልተደረገ በጳውሎስ ስብከት ወደ እምነት የመጡትን ምእመናን የሕግና የሥርዐት ተገዢዎች እንደሚያደርጋቸው ግልጥ ነው፡፡ ማንም ሰው መጽደቅ የሚችለው በጸጋ ብቻ በሚገኝ እምነት ነው፤ ከመንፈስ ቅዱስ በሚገኘው ነጻነት በአዲሱ ሕይወት መመላለስ የሚችለውም በእምነት ብቻ ነው፡፡

### ትምህርተ መለኮቱ

ይህ መልእክት ሰው ሊጸድቅ የሚችለው ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን ብቻ በመሆኑ የሚቀደሰውም ውጫዊውን ሥርዐት በመፈጸም ሳይሆን፣ በክርስቶስ ጸጋና በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ነው የሚለውን ትክክለኛውን የአዲስ ኪዳን ትምህርት ማራኪና ጠንካራ በሆነ አገላለጽ ተንትኖ የሚያስረዳ መልእክት ነው፡፡ ይህ መልእክት ለቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ መንሥኤ የሆነውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡

የቤተ ክርስቲያን ዐዳሽ የነበረው ማርቲን ሉተር፣ በዘመኑ የነበረውን የሐሰት ትምህርት ለመቃወም መሠረት ያደረገው የገላትያን መልእክት ስለ ነበር፣ ብዙ ጊዜ "የሉተር መጽሐፍ" እየተባለ ይጠራል፡፡ የመጽሐፉ መሪ ሐሳብ ያረፈበት ጥቅስ 2፥16 ነው (ያንኑ ማብ ይመ)፡፡

**አስተዋፅኦ**

1. **መግቢያ** (1፥1-9)

   ሀ. **ሰላምታ** (1፥1-5)

   ለ. **ቅዋሜ** (1፥6-9)

2. **ግላዊ:- የዐርነትና የእምነት ሐዋርያ መሆኑ አጠራጣሪ አይደለም** (1፥10-2፥21)

   ሀ. **ጳውሎስ የሚሰብከው ወንጌል በልዩ መገለጥ የተሰጠውን ነው** (1፥10-2፥21)

   ለ. **ጳውሎስ የሚሰብከው ወንጌል በኢየሩሳሌም ከነበሩት ሐዋርያትና ከይሁዳ አብያተ ክርስቲያናት የተገኘ አይደለም** (1፥13-2፥24) **ይኸውም:-**

   (1) **ወደ ክርስትና እምነት እንደመጣ ባከናወናቸው ሥራዎች ተረጋግጦአል** (1፥13-17)

   (2) **በክርስቶስ ካመነ በኋላ በመጀመሪያው የኢየሩሳሌም ጕብኝቱ ተረጋግጦአል** (1-18-24)

   (3) **በክርስቶስ ካመነ በኋላ በሁለተኛው የኢየሩሳሌም ጕብኝቱ ወቅት ከ14 ዓመት በኋላም ተረጋግጦአል** 2፥1-10

   (4) **ጴጥሮስን በአንጾኪያ በገሠጸ ጊዜም ተረጋግጦአል** (2፥11-21)

3. **አስተምህሮአዊ:- የዐርነትና የእምነት ትምህርቱ ትክክለኛ መሆኑ** (ም3-4)

   ሀ. **ወንጌል በገላትያ ምእመናን ሕይወት ልምምድ** (3፥1-5)

   ለ. **የአብርሃም ሕይወት ልምምድ** (3፥6-9)

   ሐ. **የሕጉ ርግማን** (3፥10-14)

   መ. **አስቀድሞ ተስፋ መስጠቱ** (3፥15-18)

   ሠ. **የሕጉ ዐላማ** (3፥19-25)

   ረ. **ልጆች እንጂ ባሮች አለመሆን** (3፥26-4፥11)

   ሰ. **ከሕግ ባርነት ዐርነት እንዲወጡ የቀረበ ልመና** (4፥12-20)

   ሸ. **የአጋርና የሣራ ምሳሌነት** (4፥21-31)

4. **ተግባራዊ:- የዐርነትና የእምነት ሕይወት መኖር** (5፥1-6፥10)

   ሀ. **ስለ ዐርነት የተሰጠ ምክር** (5፥1-12)

   ለ. **በመንፈስ እንጂ በሥጋ አለመኖር** (5፥13-26)

   ሐ. **መተጋገዝ** (6፥1-10)

5- **ማጠቃለያ** (6፥11-18)

1 ከሰዎች ወይም በሰው ከተላከው ሳይሆን፣
በኢየሱስ ክርስቶስና ከሙታን ባስነሣው
በእግዚአብሔር አብ ሐዋርያ ከሆነው ከጳው
ሎስ፤ [2]አብረውኝም ካሉት ወንድሞች ሁሉ፤

### በገላትያ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት

[3]ከአባታችን ከእግዚአብሔር፣ ከጌታም ከኢ
የሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን::
[4]እንደ ፈቃዱ፣ እንደ አባታችን ፈቃድ፣
ከዚህ ክፉ ዓለም ያድነን ዘንድ ስለ ኀጢአ
ታችን ራሱን ለሰጠ፣ [5]ከዘላለም እስከ ዘላ
ለም ለእርሱ ክብር ይሁን፤ አሜን::

### ወንጌል አንዲት ናት

[6]በክርስቶስ ጸጋ የጠራችሁን እርሱን ትታ
ችሁ፣ ወደ ተለየ ወንጌል እንዲህ ፈጥና
ችሁ መዞራችሁ ደንቆኛል፤ [7]እንደ እውነቱ
ከሆነ ሌላ ወንጌል የለም:: የሚያደነጋግሯ
ችሁና የክርስቶስን ወንጌል ለማጣመም ጥረት
የሚያደርጉ አንዳንድ ሰዎች አሉ:: [8]ነገር
ግን እኛም ብንሆን ወይም የሰማይ መል
አክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የተለየ ወንጌል
ቢሰብክላችሁ እርሱ ለዘላለም የተረገመ
ይሁን:: [9]ቀደም ብለን እንዳልነው፣ አሁንም
ደግሜ እላለሁ፤ ማንም ከተቀበላችሁት ሌላ
የተለየ ወንጌል ቢሰብክላችሁ፣ እርሱ ለዘላ
ለም የተረገመ ይሁን::

[10]አሁን እኔ ጉሽ ለመባል የምሻው በሰዎች
ዘንድ ነው ወይስ በእግዚአብሔር ዘንድ? ወይስ
ሰዎችን ደስ ለማሰኘት እየተጣጣርሁ ነው?
ሰዎችን ደስ ለማሰኘት የምጥር ብሆን ኖሮ፣
የክርስቶስ አገልጋይ ባልሆንሁ ነበር::

### ጳውሎስ በእግዚአብሔር መጠራቱ

[11]ወንድሞች ሆይ፤ የሰበክሁላችሁ ወንጌል
ሰው ሠራሽ አለመሆኑን እንድታውቁ እፈ
ልጋለሁ፤ [12]ከማንም ሰው አልተቀበልሁትም፤
ከማንም አልተማርሁትም፤ ይልቁንስ በመገ
ለጥ ከኢየሱስ ክርስቶስ ተቀበልሁት::
[13]ቀድሞ በአይሁድ ሃይማኖት እንዴት
እንደኖርሁ፣ የእግዚአብሔርንም ቤተ ክርስ
ቲያን እንዴት በእጅጉ እንዳሳደድሁ፣ ለማ
ጥፋትም እንዴት እንደ ጣርሁ ሰምታች
ኋል፤ [14]በእኔ ዕድሜ ዘመን ከነበሩት ከብዙ
ዎቹ አይሁድ ይበልጥ በአይሁድ ሃይማኖት
እልቅ ነበር፤ ስለ አባቶቼም ወግ እጅግ ቀና
ተኛ ነበርሁ:: [15]ነገር ግን፣ ከእናቴ ማሕፀን[u]
ጀምሮ የለየኝና በጸጋው የጠራኝ እግዚአብሔር፣
[16]በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ እንድሰብክ
ልጁን በእኔ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ፣ ከማንም
ሥጋ ለባሽ ጋር አልተማከርሁም፤ [17]ከእኔ
በፊት ሐዋርያት ወደ ሆኑትም ወደ ኢየሩ
ሳሌም አልወጣሁም፤ ነገር ግን ወዲ

1፥1 ቍ11:12:15:16፤ሐሥ24፥9፤15፤20፥24፤1ቆሮ1፥1
1፥2 ሐሥ16፥6፤ፊል4፥21
1፥3 ሮሜ1፥7
1፥4 ማቴ20፥28፤ሮሜ4፥25፤1ቆሮ1፥20፤15፥3፤ገላ2፥20፤ፊል4፥20
1፥5 ሮሜ11፥36
1፥6 ቍ15፤ሮሜ8፥28፤2ቆሮ11፥4
1፥7 ኤር23፥16:36፤ሐሥ15፥24፤ገላ5፥10
1፥8 ቍ11:16፤ሮሜ9፥3፤1ቆሮ15፥1፤2ቆሮ11፥4፤ገላ2፥2
1፥9 ሮሜ16፥17
1፥10 ሮሜ2፥29
1፥11 ቍ8፤1ቆሮ15፥1
1፥12 ቍ1:16፤1ቆሮ2፥10፤11፥23፤15፥3
1፥13 ሐሥ8፥3፤26፥4:5፤1ቆሮ10፥32
1፥14 ማቴ15፥2፤ሐሥ21፥20፤
1፥15 ኢሳ49፥1:5፤ኤር1፥5፤ሐሥ9፥15፤ሮሜ8፥28፤
1፥16 ማቴ16፥17፤ሐሥ9፥15፤ገላ2፥9፤
1፥17 ሐሥ9፥21፤

[u]15 *ወይም ከመወለዴ*

1፥1 *ከሙታንም ባስነሣው፤* ትንሣኤ፣ የክርስትና እምነት ዋና ማረጋገጫ ነው (ሐሥ17፥18፤ ሮሜ1፥4፤ 1ቆሮ15፥20፤ 1ጴጥ 1፥3 ይመ)፤ ጳውሎስ ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን ስላየ ሐዋ ርያ እንዲሆን ተሹሞአል (ሐሥ1፥22 እና ማብ፤ 2፥32፤ 1ቆሮ 15፥8 ይመ):: *ሐዋርያ፤* ሙሉ የውክልና ሥልጣን ተሰጥቶት ለአንድ ተግባር የተላከ መልእክተኛ ማለት ነው (የ1ቆሮ1፥1 ማብ ይመ):: *ከጳውሎስ፤* በዚያን ዘመን የነበሩ ጸሓፊዎች ስማቸውን በመልእክታቸው መጀመሪያ ላይ ማስፈር የተለመደ ነበር:: ስለ ጳውሎስ በበለጠ ለማወቅ የሐሥ9፥1፤ ፊል3፥4-14 ማብ ይመ::

1፥2 *ወንድሞች፤* ክርስቲያኖችን ማለት ነው (3፥15፤4፥12፤ 5፥11፤ 6፥18 ይመ):: *ገላትያ፤* ቃሉ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሦስት ጊዜ ተጠቅሶአል:: የመጀመሪያው በ2ጢሞ 4፥10 ላይ ሲ ሆን፣ ምን እንደሚያመለክት ግን አይታወቅም:: ሁለተኛው ደግሞ በ1ጴጥ 1፥1 ላይ ነው፤ ይህም ጎል የተባለው ሕዝብ ሰፍ ሮበት የነበረውን የትንሿን እስያ ሰሜናዊ ክፍል ያመለክታል:: በመጨረሻም እዚህ ላይ ሲሆን፣ ምናልባት ጳውሎስ ቃሉን የተጠ ቀመው የሮም ግዛት የነበረችውን የገላትያን አውራጃና በመጀ መሪያው ሐዋርያዊ ጕዞው ያለፈበትን በደቡብ በኩል ያለውን ተጨማሪ አካባቢ ለማሳየት ሊሆን ይችላል (ሐሥ 13፥14-14፥23 ይመ):: *አብያተ ክርስቲያናት፤* መልእክቱ የተጻፈው በገላትያ ላሉት አያሌ ማኅበረ ምእመናን ነው::

1፥3 *ጸጋ፤* ከተለመደው የግሪክ ሰላምታ የተወሰደ ክርስቲ ያናዊ ሰላምታ ነው (ዮና 4፥2፤ ኤፌ1፥2 ማብ ይመ):: *ሰላም፤* በዕብራይስጥ የተለመደ ሰላምታ ነው (ዮሐ14፥27፤ 20፥19፤ ኤፌ 1፥2 ማብ ይመ)::

1፥4 *ከዚህ ክፉ ዓለም፤* በአሁኑ ዘመን ያለውን የዓለም ሁኔታ ያመለክታል (የ2ቆሮ4፥4 ማብ ይመ)፤ ሊመጣ ካለው የመ ሲሑ ዘመን ጋር ሲነጻጸር፣ የአሁኑ ዘመን ተለይቶ የሚታወቀው በክፋቱ ነው (ኤፌ2፥2፤ 6፥12):: *ስለ ኀጢአታችን፤* ማቴ1፥21፤ ዮሐ1፥29፤ 1ቆሮ15፥3፤ 1ጴጥ2፥24 ይመ::

*1፥5፤* ስለ ሌሎችም የውዳሴ ቃሎች ሮሜ9፥5፤ 11፥36፤ 16፥27፤ ኤፌ 3፥21፤ 1ጢሞ 1፥17 ይመ::

1፥6 *በክርስቶስ ጸጋ፤* የጠራና ያልተደባለቀ ወንጌል መለኪያ ነው:: *የጠራችሁን፤* እግዚአብሔርን ያመለክታል:: *እንዲህ ፈጥናችሁ፤* በክርስቶስ ካመኑ በኋላ ብዙ ሳይቈዩ ወይም ወዲ ያውኑ ማለት ነው::

1፥7 *አንዳንድ ሰዎች፤* የይሁዲ እምነት ተከታይ የሆኑትን ክርስቲያኖች የሚያመለክት ነው::

1፥8 *ለዘላለም የተረገመ፤* ይህ ሐረግ በግሪክ፣ "አናቴማ" የሚባል ሲሆን፣ ቀደም ሲል በቤተ ጣዖት ስእለትን ለመፈጸም የሚሰጠውን ክፍያ ያመለክታል፤ በኋላ ግን ቃሉ ርግማንን የሚያ መለክት ሆኖአል (ቍ9፤ 1ቆሮ 12፥3፤ 16፥22፤ ሮሜ9፥3 ይመ)::

1፥10 *የክርስቶስ አገልጋይ፤* ቀደም ሲል ጳውሎስ በኀጢ አት የባርነት ቀንበር ሥር ነበር (5፥1)፤ ነገር ግን በክርስቶስ ቤዛ ነት ከኀጢአት ነጻ ከወጣ በኋላ የጽድቅና የእግዚአብሔር ባሪያ ሆነ (ሮሜ 6፥18: 22 ይመ)::

1፥11 *ወንድሞች ሆይ ... እንድታውቁ እፈልጋለሁ፤* ይህ ሐረግ ጳውሎስ የተቀበለውን ወንጌል በተነተነበት በ1ቆሮ15፥1 ላይም ይገኛል:: *የሰበክሁላችሁ ወንጌል፤* በሮሜ2፥16፤ 16፥25 ላይ፣ "የእኔ ወንጌል" ተብሎአል:: ድነት ለሁሉ ነው፤ የሚገኘ ውም ክርስቶስን በማመን ነው::

1፥12 *በመገለጥ ... ተቀበልሁት፤* ኤፌ3፥2-6 ይመ::

1፥13 *በአይሁድ ሃይማኖት፤* በብሉይ በአዲስ ኪዳን መካ ከል ባለው ዘመን የተስፋፋ የአይሁድ እምነት ነው:: ቃሉ ከክ ርስቶስ በፊት በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከተደመሰሰ ውና ሕዝቡ ወደ ባቢሎን ተማርኮ ከተጋዘው ከደቡቡ መንግሥት ከይሁዳ የተወሰደ ነው:: *የእግዚአብሔርንም ቤተ ክርስቲያን፤* በብሉይ ኪዳን፣ "ማኅበር" (ዘኍ16፥21) ወይም "የእግዚአብሔር ጉባኤ" (ዘኍ 20፥4) ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው::

1፥14 *ስለ አባቶቼም ወግ፤* ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል የሚተላለፍና ከተጻፈው ከሙሴ ሕግ ጋር የሚነጻጸር ነው፤ ይህን "የሽማግሌዎች ወግ" ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ (የማቴ 15፥2 ማብ ይመ):: *ቀናተኛ፤* ፊል 3፥6 ይመ::

1፥15 *ከእናቴ ማሕፀን ጀምሮ የለየኝና፤* ኢሳ 49፥1፤ ኤር 1፥5፤ ሮሜ 1፥1 ይመ::

1፥16 *በአሕዛብ፤* ባዕዳንን የሚያመለክት ሲሆን፣ "ሰዎች" ወይም "ሕዝቦች" ማለትም ይሆናል፤ በአጠቃላይ ከአይሁድ ውጭ የሆኑትን ዜጎች ወይም ባዕድ አምልኮ የሚከተሉትን ሰዎች ያመለክታል:: *ከማንም ሥጋ ለባሽ፤* ቃል በቃል ሲወሰድ፣ "ከሥ ጋና ከደም" ማለት ነው:: በተለይም በአዲስ ኪዳን የሰውን ደካ ማነትና አለማወቅ ለማመልከት በብዙ ቦታ ተጠቅሶአል (ማቴ 16፥17፤ 1ቆሮ15፥50፤ ኤፌ6፥12 ይመ):: ጳውሎስ ግን መልእክ ቱን የተቀበለው ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ነው::

1፥17 *ኢየሩሳሌም፤* የአይሁድ ሃይማኖት ማእከልና ክርስት ናም የተጀመረበት ስፍራ ነው:: *ዐረብ አገር፤* በዮርዳኖስ ማዶ

ያው ወደ ዐረብ አገር ሄድሁ፤ በኋላም ወደ
ደማስቆ ተመለስሁ።
18ከዚያም ከሦስት ዓመት በኋላ፣ ጴጥሮስን[ሀ]
አገኘው ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣሁ፤ ከእ
ርሱም ጋር ዐሥራ አምስት ቀን ተቀመጥሁ።
19ነገር ግን ከጌታ ወንድም ከያዕቆብ በቀር፣
ከሐዋርያት ማንንም አላየሁም። 20በምጽፍላ
ችሁ ነገር በእግዚአብሔር ፊት ሐሰት እንደ
ማልናገር አስረግጬ እነግራችኋለሁ። 21ከዚ
ያም በኋላ፣ ወደ ሶርያና ወደ ኪልቅያ
አገር ሄድሁ። 22በክርስቶስ ያሉት የይሁዳ
አብያተ ክርስቲያናትም ፊቴን አይተው አያ
ውቁም ነበር፤ 23እነርሱ ግን፣ "ቀድሞ እኛን
ሲያሳድድ የነበረ ሰው፣ ከዚህ በፊት ሊያጠ
ፋው ይፈልግ የነበረውን እምነት አሁን እየ
ሰበከ ነው" የሚለውን ወሬ ብቻ ሰምተው
ነበር፤ 24በእኔም ምክንያት እግዚአብሔርን
አመሰገኑ።

## ጳውሎስን ሐዋርያት ተቀበሉት

2 ከዐሥራ አራት ዓመት በኋላም፣ ዳግመኛ
ወደ ኢየሩሳሌም ወጣሁ፤ በዚህ ጊዜ
ከበርናባስ ጋር ነበርሁ፤ ቲቶንም ይዤው
ሄጄ ነበር። 2ካገኘሁትም መገለጥ የተነሣ
ወደዚያ ሄድሁ፤ በአሕዛብ መካከል የምሰብከ
ውን ወንጌል ለእነርሱም ገለጥሁላቸው። ይሁን
እንጂ፣ ምናልባት በከንቱ እየሮጥሁ ወይም
ሮጬ እንዳይሆን በመሥጋት፣ ዋነኞች ለሚ
መስሉት ብቻ በግል ይህን አስታወቅኋ
ቸው። 3ከእኔ ጋር የነበረው ቲቶ እንኳ የግ
ሪክ ሰው ቢሆንም፣ እንዲገረዝ አልተገደደም
ነበር። 4ይህ ጉዳይ የተነሣው አንዳንድ ሐሰ
ተኞች ወንድሞች በክርስቶስ ኢየሱስ ያገኘነ
ውን ነጻነት ሊሰልሉና ባሪያዎች ሊያደር
ጉን ወደ እኛ ሾልከው በመግባታቸው ነው።
5ለእነዚህ ሰዎች ለአንድ አፍታ እንኳ አል
ተገዛንላቸውም፤ ይኸውም፣ የወንጌል እው
ነት ከእናንተ ጋር ጸንቶ እንዲኖር ነው።
6ዋነኛ መስለው ስለሚታዩት ሰዎች ማን
ነት እኔን አይገደኝም፤ እግዚአብሔር የሰውን
ፊት አይቶ አያደላም፤ እነዚህም ሰዎች
ለመልእክቴ የጨመሩልኝ ነገር የለም።
7ነገር ግን ጴጥሮስ ለተገረዙት[ሐ] ወንጌልን
እንዲሰብክ ዐደራ እንደ ተሰጠው፣ እኔም
ላልተገረዙት[መ] ወንጌልን እንድሰብክ ዐደራ
እንደ ተሰጠኝ ተገነዘቡ፤ 8ጴጥሮስ ለአይ
ሁድ ሐዋርያ እንዲሆን የሠራ እግዚአብሔር፣
በእኔ የአሕዛብ ሐዋሪያዊ አገልግሎትም
ሠርቶአል። 9እንደ አዕማድ የሚቈጠሩት
ያዕቆብ፣ ጴጥሮስና[ሠ] ዮሐንስም የተሰጠኝን
ጸጋ ባስተዋሉ ጊዜ፣ ለእኔና ለባርናባስ
የትብብር ቀኝ እጃቸውን ሰጡን፤ ከዚያም
እኛ ወደ አሕዛብ፣ እነርሱ ደግሞ ወደ
አይሁድ እንድሄድ ተስማሙ።
10አጥብቀው ዐደራ ያሉን ድኾችን ማሰባ
ችንን እንዳናቋርጥ ብቻ ነው፤ እኔም ይህንኑ
ለማድረግ ጕጕቴ ነበር።

## ጳውሎስ ጴጥሮስን ተቃወመው

11ጴጥሮስ ወደ አንጾኪያ በመጣ ጊዜ፣
በግልጥ ስቶ ስለ ነበር ፊት ለፊት ተቃወ

9፥22
1፥18 ሐሥ9፥22፡ 23፡26፤27፤
1፥19 ማቴ13፥55፤ ሐሥ15፥13
1፥20 ሮሜ1፥9፤ 9፥1
1፥21 ሉቃ2፥2፤ ሐሥ6፥9
1፥22 ሮሜ16፥3፤ 1ተሰ2፥14
1፥23 ሐሥ6፥7፤ 8፥3
1፥24 ማቴ9፥8
2፥1 ሐሥ4፥36፤ 15፥2፤ቆሮ2፥13
2፥2 ሐሥ15፥4፡ 12፤1ቆሮ2፥10፤ 9፥24
2፥3 ቍ1፤ ሐሥ16፥3፤1ቆሮ 9፥21፤2ቆሮ2፥13
2፥4 ሐሥ1፥16፤ 2ቆሮ11፥26፤ ገላ5፥1፡13፤ይሁ4
2፥5 ቍ14
2፥6 ቍ2፤ሐሥ 10፥34፤1ቆሮ 15፥11፤ራእ2፥23
2፥7 ቍ9፡11፡14 ሐሥ9፥15፤1ተሰ 2፥4፤1ጢሞ1፥11
2፥8 ሐሥ1፥25፤ 1ቆሮ1፥1
2፥9 ቍ1፡7፡11፡ 14፤ሐ4፥36፤9፥15፤1 5፥13፤ሮሜ12፥3፤ 1ጢሞ3፥15 ራእ3፥12
2፥10 ሐሥ24፥17
2፥11 ቍ7፡9፡ 14፤ሐሥ11፥19

[ሀ]18 ግሪኩ ኬፋ ይለዋል።
[ሐ]7 ወይም ለአይሁድ
[መ]7 ወይም ለአረማዊያን እንዲሁም ቍ8 እና 9 ይመ
[ሠ]9 ግሪኩ ኬፋ ይላል፤ እንዲሁም ቍ11 እና 14 ይመ

የሚገኘውን የናባትያንን መንግሥት የሚያመለክት ነው፤ ይህም ከደማስቆ በስተ ደቡብ ምዕራብ እስከ ስዊዝ ያለውን አካባቢ ያጠቃልላል። *ደማስቆ፤* በብሉይ ኪዳን ዘመን አራም በመባል የሚታወቀው የሶርያ ጥንታዊ ዋና ከተማ ነው። ጳውሎስ ከኢየሩሳሌም ወደ ደማስቆ ሲሄድ በመንገድ ላይ ክርስቶስን አመነ (ሐሥ 9፥1-9)።

1፥18 *ከሦስት ዓመት በኋላ፤* ወደ ዐረብ አገር ለመሄድ ከተነሣበት ጊዜ ጀምሮ ማለት ነው፤ ሦስቱንም ዓመት ዐረብ አገር መቈየቱን ግን ጥቅሱ አይገልጽም። *ጴጥሮስን፤* ወይም "ኬፋን" ማለት ነው፤ ይህም በአረማይክ ድንጋይ ማለት ነው (ማቴ16፥18 እና ማብ ይመ)፤ የስሙ ትርጕም በዚህ ቃል የተጠራው ሰው ያለውን ባሕርይ ያመለክታል (የዮሐ1፥42 ማብ ይመ)። *ወደ ኢየሩሳሌም ወጣሁ፤* አንዳንዶች ሳውልና በርናባስ ርዳታ ለማድረስ ወደ ኢየሩሳሌም ከተላኩበት ከሐሥ 11፥30 ጋር ቢያመሳስሉትም፣ ይህ ክፍል በሐሥ9፥26-30 ላይ የተጠቀሰውን የጳውሎስን ጕብኝት የሚያመለክት ነው።

1፥19 *ከያዕቆብ፤* በያዕቆብ መልእክት መግቢያ ሥር፣ "ጸሓፊው" የሚለውን ይመ። በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን የሽማግሌዎች መሪ እንደ ነበረ በሐሥ 21፥18 ላይ ተጽፎአል። *ከጌታ ወንድም፤* የሉቃ 8፥19 ማብ ይመ።

1፥21 *ወደ ሶርያና ወደ ኪልቅያ፤* የትንሿ እስያ አውራጃዎች ናቸው። የጳውሎስ የትውልድ ከተማ ጠርሴስ በኪልቅያ አውራጃ ስለሚገኝ ወደዚያ ሄደ (ሐሥ 9፥30 ይመ)።

2፥1 *ከዐሥራ አራት ዓመት በኋላም፤* ጳውሎስ በክርስቶስ ካመነ በኋላ ማለት ሊሆን ይችላል። *ዳግመኛ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣሁ፤* አንዳንዶች በሐሥ11፥30 ላይ የተጠቀሰውን ጕብኝት የሚያመለክት ነው ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ በሐሥ15፥1-4 የተጠቀሰውን የሚያሳይ ነው ይላሉ (የሐሥ12፥1፤15፥2 ማብ ይመ)። *በርናባስ፤* ትርጕሙ የሚያጽናናታ ማለት ነው። የመጀመሪያው ስሙ ዮሴፍ ሲሆን፣ እርሱም ከቆጵሮስ ደሴት የመጣ ሌዋዊ ነበር (ሐሥ 4፥36 ማብ ይመ)፤ በመጀመሪያው ሐዋርያዊ ጕዞ የጳውሎስ ባልደረባ ነበር (ሐሥ 13፥1-14፥28)። *ቲቶ፤* ከአሕዛብ ወገን በክርስቶስ ያመነ ሰው ሲሆን፣ በመጀመሪያ የጳውሎስ ተወካይ ሆኖ ወደ ቆሮንቶስ ሄዶአል፤ በኋላም ከቀርጤስ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን ያደራጅ ዘንድ በዚያ ቀርቶአል (ቲቶ1፥5 ይመ)።

2፥2 *በከንቱ ... ሮጬ እንዳይሆን፤* 1ቆሮ 15፥58፤ ፊል 2፥16 ይመ። *ዋነኞች ለሚመስሉት፤* ጳውሎስ ሥልጣናቸውን በመቀበል ግልጽ አድርጎ የተናገረበት እና ምናልባትም ደግሞ ያዕቆብን፣ ጴጥሮስንና ዮሐንስን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል (ቍ9 ይመ፤ ከቍ6 ጋር ያነጻጽሩ)።

2፥4 *ሐሰተኞች ወንድሞች፤* ከአሕዛብ ወገን የሆኑ ክርስትያኖች መገረዝና የሙሴንም ሕግ መጠበቅ እንደሚገባቸው የሚያስተምሩ ክርስቲያኖች ናቸው (ከሐሥ15፥5፤2 ቆሮ11፥26 ጋር ያነጻጽሩ)። *ነጻነት፤* 5፥1፡13፤ ሮሜ6፥18፡20፡22፤ 8፥2 ይመ። ይህም በገላትያ መልእክት ውስጥ ብዙ ጊዜ የተጠቀሰ ዋና ቃል ነው (3፥28፤ 4፥22-23፡26፡30-31፤ 5፥1፡13 ይመ)። *ሊሰልሉና፤* 2ሳሙ10-3 እና 1ዜና19፥3ይመ።

2፥6 *ዋነኛ መስለው ስለሚታዩት፤* የቍ2 ማብ ይመ። *የሰውን ፊት አይቶ አያደላም፤* ከዘዳ 10፥17፤ 1ሳሙ16፥7፤ ሉቃ 20፥21፤ ያዕ2፥1 ጋር ያነጻጽሩ)።

2፥7 *ላልተገረዙት፤* የጳውሎስ አገልግሎት ላልተገረዙት ወይም ለአሕዛብ ብቻ አልነበረም፤ ስለዚህ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አንድ አካባቢ በሚደርስበት ጊዜ፣ ከሁሉ አስቀድሞ ወደ ምኵራብ ይገባ እንደ ነበር ተጽፎአል (የሐሥ13፥14 ማብ)፤ ይሁን እንጂ በአብዛኛው ራሱን ለአሕዛብ የተላከ ሐዋርያ አድርጎ ይቈጥራል (ሮሜ11፥13 እና ማብ ይመ)።

2፥9 *አዕማድ፤* ለአንድ ድርጅት ሕልውና የጀርባ ዐጥንት የሆኑና እንደ ምሳሌ የሚታዩ ሰዎች የሚጠሩበት ስም ነው። *ያዕቆብ፤* የ1፥19 ማብ ይመ። *ቀኝ እጃቸውን፤* በዕብራውያንና በግሪኮች ባህል፣ ሰዎች የወዳጅነት ቃል ኪዳን ሲያደርጉ የሚፈጽሙት የተለመደ ሥርዐት ነው።

2፥11 *አንጾኪያ፤* የሶርያ ዋና ከተማና ከሦስቱ የሮም መንግሥት ታላላቅ ከተሞች አንዷ ነበረች፤ የጳውሎስም ሐዋርያዊ ጕዞ መነሻ ይህችው ከተማ ነበረች (ሐሥ13፥1-3፤ 14፥26

ምሁት:: 12አንዳንድ ሰዎች ከያዕቆብ ዘንድ
ከመምጣታቸው በፊት፣ ከአሕዛብ ጋር ይበላ
ነበር፤ እነርሱ በመጡ ጊዜ ግን የተገረዙትን
ወገኖች ፈርቶ ከአሕዛብ ራሱን በመለየት
ገሸሽ ማለት ጀመረ፤ 13በርናባስም እንኳ በእ
ነርሱ ግብዝነት እስኪወሰድ ድረስ፣ ሌሎቹም
አይሁድ በግብዝነቱ ተባበሩት:: 14ተግባራ
ቸው እንደ ወንጌል እውነት አለመሆኑን
በተረዳሁ ጊዜ፣ በሁሉም ፊት ጴጥሮስን እን
ዲህ አልሁት፤ "አንተ አይሁዳዊ ነህ፤ ሆኖም
በአሕዛብ ሥርዐት እንጂ በአይሁድ ሥርዐት
አትኖርም፤ ታዲያ አሕዛብ የአይሁድን ሥር
ዐት እንዲከተሉ እንዴት ታስገድዳቸዋለህ?
15"እኛ በትውልዳችን አይሁድ እንጂ፣ 'ኀጢ
አተኞች አሕዛብ' ያልሆን፣ 16ሰው በኢየ
ሱስ ክርስቶስ በማመን እንጂ፣ ሕግን በመጠ
በቅ እንደማይጸድቅ እናውቃለን:: ስለዚህ
ሕግን በመጠበቅ ሳይሆን፣ በክርስቶስ በማ
መን እንጸድቅ ዘንድ እኛም ደግሞ በክር
ስቶስ ኢየሱስ አምነናል፤ ሕግን በመጠበቅ
ማንም አይጸድቅምና::
17"በክርስቶስ ለመጽደቅ ስንፈልግ፣ እኛ
ራሳችን ኀጢአተኞች መሆናችን ግልጽ
ነው፤ ታዲያ ክርስቶስ ኀጢአት እንዲስፋፋ
ያደርጋልን? ፈጽሞ አይደለም!:: 18ያፈረስሁ
ትን መልሼ የምገነባ ከሆነማ ሕግ ተላላፊ
መሆኔን አረጋግጣለሁ:: 19ለእግዚአብሔር እኖር
ዘንድ፣ በሕግ በኩል ለሕግ ሞቻለሁና::
20ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ፤ ከእንግዲህ
እኔ አልኖርም፤ ነገር ግን ክርስቶስ በውስጤ
ይኖራል:: አሁንም በሥጋ የምኖረው ኑሮ
በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን አሳልፎ በሰጠው

2፥12 ሐሥ10፥45 11፥2፤11፥3፤15፥13
2፥13 ቍ1፤ ሐሥ 4፥36
2፥14 ቍ5:7:9: 11:12፤ ሐሥ10፥28
2፥15 1ሳሙ15፥18 ፤ሉቃ24፥7፤ ፊል3፥3:5
2፥16 ሮሜ3፥28፤ 4፥25፤9፥30
2፥17 ቍ15፤ ገላ3፥21
2፥19 ሮሜ6፥10: 11:14፤7፥4፤2ቆሮ5፥15
2፥20 ማቴ4፥31፤ ሮሜ 6፥6፤ 8፥10፤8፥37፤ ገላ1፥4፤1ጴጥ4፥2
2፥21 ገላ3፥21
3፥1 ሉቃ24፥25 ፤ሐሥ16፥6፤1ቆሮ 1፥23፤ገላ5፥7
3፥2 ቍ5:10፤ ዮሐ20፥22፤ሮሜ 10፥17፤ ገላ2፥16፤ዕብ 4፥2
3፥5 ቍ2:10፤ 1ቆሮ12፥10፤ገላ 2፥16
3፥6 ዘፍ15፥6፤ ሮሜ4፥3
3፥7 ቍ9፤ሉቃ3፥8
3፥8 ዘፍ12፥3፤ 18፥18፤22፥18፤26፥4፤ ሐሥ3፥25

በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለኝ እምነት ነው::
21የእግዚአብሔርን ጸጋ አላቃልልም፤ ጽድቅ
በሕግ በኩል የሚገኝ ከሆነማ፣ ክርስቶስ
እንዲያው በከንቱ ሞተ ማለት ነዋ!"ረ

## እምነት ወይስ የኦሪትን ሕግ መጠበቅ

3 እናንተ የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች
ሆይ! ለመሆኑ ማን መተት አደረ
ገባችሁ? ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ
ሆኖ በፊት ለፊታችሁ በግልጥ ተሥሎ
ነበር:: 2ከእናንተ ዘንድ አንድ ነገር ብቻ
ማወቅ እፈልጋለሁ፤ መንፈስን የተቀበ
ላችሁት ሕግን በመጠበቅ ነው ወይስ የተሰ
በከላችሁን በማመን? 3ይህን ያህል የማ
ታስተውሉ ናችሁን? በመንፈስ ጀምራችሁ
በሥጋ ፍጹም ለመሆን ትጥራላችሁን?
4በእርግጥ ለከንቱ ከሆነ፣ ይህን ያህል
መከራ የተቀበላችሁት እንዲያው ነውን?
5እግዚአብሔር መንፈሱን የሚሰጣችሁ፣ በእና
ንተም ዘንድ ታምራትን የሚሠራው ሕግን
ስለ ጠበቃችሁ ነው ወይስ የሰማችሁትን
ስላመናችሁ?
6እስቲ አብርሃምን አስቡ፤ "እርሱ እግዚአ
ብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት::"
7እንግዲህ እነዚያ የሚያምኑት የአብርሃም
ልጆች እንደ ሆኑ አስተውሉ:: 8መጽሐፍ፣
እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንደሚያ
ጸድቅ አስቀድሞ በማየት፣ "አሕዛብ ሁሉ
በአንተ ይባረካሉ" በማለት ወንጌልን ለአብ
ርሃም አስቀድሞ አስታወቀው::

ረ21 አንዳንድ ተርጓሚዎች ትምህርተ ጥቅሱን ከቍ14 በኋላ ያደርጋሉ::

ይመ):: ስቶ፤ ጴጥሮስ ተከትሎት የነበረውን ትክክለኛ *መንገድ* ለቆ፣ በወቅቱ ግዝረትን ከሚደግፉ ወገኖች የሚሰነዘረውን ተቃውሞ ለማርገብ በሐሳባቸው በመስማማቱ ጳውሎስ ተቃወመው::

2፥12 ***የተገረዙትን ወገኖች፤*** ያለግዝረት ድነት ሙሉ አይሆንም ብለው የሚያምኑ የአይሁድ እምነት ተከታይ የሆኑ ክርስቲያኖች ናቸው (ከሐሥ10፥45፤ 11፥2፤ ከሮሜ4፥12 ጋር ያነጻጽሩ)::

2፥13 ***ሌሎቹም አይሁድ፤*** ግርዘት ያስፈልጋል ከሚሉት ጋር ያልተባበሩ፣ ነገር ግን በጴጥሮስ ሁኔታ የተሰነካከሉትን ከአይሁድ ወገን የሆኑ ክርስቲያኖችን ያመለክታል::

2፥14 ***በአሕዛብ ሥርዐት እንጂ፤*** በአይሁድ ልማድ አለመሄዱን፣ በተለይም የተከለከሉ ምግቦችን ይበላ እንደ ነበር የሚያመለክት ነው (ቍ12 ይመ)::

*2፥16፤* የገላትያ መልእክት ዋና ሐሳብ የሚገኘው እዚህ ጥቅስ ላይ ነው፤ ጥቅሱ ሦስት ጊዜ ሕግን በመጠበቅ መጽደቅ እንደማይቻል ሲያመለክት፣ ሦስት ጊዜ ደግሞ በክርስቶስ ማመን ፍጹም አስፈላጊ መሆኑን ይናገራል:: ***ሕግን በመጠበቅ፤*** ጳውሎስ ሕግን መናቁ አይደለም፤ እርሱ ራሱ የእግዚአብሔር ሕግ፣ "ቅዱስ፣ ጻድቅና መልካም ነው" (ሮሜ7፥12) በማለት ሕግን የሚያከብር መሆኑን ገልጾአልና:: የብሉይ ኪዳንን ሕግ መጠበቅ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት መሠረታዊ ነገር ነው በማለት ሕጉን አዛብቶ ለመጠቀም የሚደረገውን ተገቢ ያልሆነ ሙከራ ጳውሎስ ተቃውሞታል:: ***በክርስቶስ በማመን እንጸድቅ ዘንድ፤*** የወንጌል መልእክት መሠረታዊ ሐሳብ ነው (ሮሜ 3፥20-28፤ ፊል 3፥9 ይመ፤ እንዲሁም የሮሜ 3፥24-28 ማብ ይመ):: እምነት ጽድቅን የምናገኝበት መንገድ ሲሆን፣ መሠረቱ ደግሞ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የፈጸመው ሥራ ነው::

2፥19 ***ለሕግ ሞቻለሁና፤*** ቍ20 ይመ፤ የሮሜ 7፥4 ማብ ይመ::

2፥20 ***ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ፤*** 5፥24፤ 6፥14፤ ሮሜ 6፥8-10፤ 7፥6 ይመ፤ የሮሜ6፥7 ማብ ይመ:: ***ስለ እኔ ራሱን አሳልፎ በሰጠው፤*** 1፥4፤ 1ጢሞ2፥6፤ ቲቶ2፥14 ይመ::

2፥21 ***ክርስቶስ እንዲያው በከንቱ ሞተ ማለት ነዋ?*** ወግ አጥባቂነትን ከጸጋ ጋር መደባለቅ፣ ጸጋውን ማቃለልና በመስቀሉ ሥራ ላይ ማፌዝ ነው::

3፥1 ***እናንተ የማታስተውሉ፤*** የአእምሮ ችግር አልነበረባቸውም፤ ነገር ግን መረዳት ሲችሉ፣ ቸልተኞች በመሆናቸው ነው፤ ሉቃ24፥25፤ ሮሜ1፥14፤ 1ጢሞ6፥9፤ ቲቶ3፥3 ይመ:: ***ማን ...?*** ወግ አጥባቂ የሆኑ የአይሁድ እምነት ተከታይ የሆኑትን ክርስቲያኖች ማለቱ ነው:: ***እንደ ተሰቀለ ሆኖ ... ተሥሎ፤*** 1ቆሮ1፥23፤ 2፥2 ይመ:: በአደባባይ እንዲታይ የተደረገ ወይም በግድግዳ ላይ የተለጠፈ ማለት ነው:: ሙሴ በዐላማ ላይ ከሰቀለው የናስ እባብ ጋር ይህን ያነጻጽሩ (ዘኍ21፥9)::

3፥2 ***መንፈስን፤*** ይህን ጨምሮ፣ ጳውሎስ ስለ መንፈስ ቅዱስ በገላትያ መልእክቱ ብዙ ጊዜ ጠቅሶአል::

3፥3 ***በመንፈስ ጀምራችሁ በሥጋ፤*** ድነትና ቅድስና ሁለቱም የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ናቸው:: ***በሥጋ፤*** ደካማውና ያልተለወጠው ፍጥረታዊ ሰው የሚያደርገውን ጥረት ለማመልከት ነው:: ጽድቅን በሥራ ለማግኘት መሞከር፣ ግዝረትንና የመሳሰሉትን ማድረግ የሥጋ ሥራዎች ናቸው::

*3፥4፤* ሐዋርያው ጳውሎስ፣ የሳቱ ሰዎች ወደ እውነተኛው ወንጌል እንዲመለሱ ይመኛል፤ ተስፋም ያደርጋል::

3፥7 ***የአብርሃም ልጆች፤*** አብርሃም፣ በሥጋም በመንፈስም የአይሁድ ሕዝብ አባት ነው (ዮሐ 8፥31:33:39:53፤ ሐሥ7፥2 ሮሜ4፥12 ይመ):: እዚህ ላይ ግን ከአይሁድም ሆነ ከአሕዛብ ወገን የሆኑ አማኞች ሁሉ፣ የአብርሃም መንፈሳውያን ልጆች ተብለዋል (የሮሜ4፥11-12 ማብ ይመ)፤ የአብርሃም ዘር ተብለውም ይጠራሉ (ቍ16፤ ዕብ2፥16)::

3፥8 ***መጽሐፍ ... አስቀድሞ በማየት፤*** የጽሑፉን መለኮታዊ ምንጭ የሚያመለክት ነው (1ጢሞ 5፥18 ይመ)::

3፥9 ***የእምነት ሰው ከሆነው ከአብርሃም፤*** ጳውሎስ ስለ

[9]ስለዚህ በእምነት የሆኑት፣ የእምነት ሰው
ከሆነው ከአብርሃም ጋር ቡሩካን ናቸው::
[10]ሕግን በመጠበቅ የሚተማመኑ ሁሉ
ከእርግማን በታች ናቸው፤ "በሕግ መጻሕ
ፍት የተጻፈውን ሁሉ የማያደርግ የተረገመ
ነው" ተብሎ ተጽፎአልና::
[11]"ጻድቅ በእምነት ይኖራል" ስለ ተባለ፣
ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንደማይ
ጸድቅ ግልጽ ነው:: [12]ሕግ በእምነት ላይ
የተመሠረተ አይደለም፤ ነገር ግን "ሕግ
ጋትን የሚፈጽም ሰው በእነርሱ በሕይወት
ይኖራል" ተብሎአል:: [13]"በዕንጨት ላይ
የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው" ተብሎ ስለ
ተጻፈ፣ ክርስቶስ ስለ እኛ ርግማን ሆኖ
ከሕግ ርግማን ዋጅቶናል፤ [14]ለአብርሃም
የተሰጠው በረከት፣ በክርስቶስ ኢየሱስ
ለአሕዛብ እንዲደርስ ዋጅቶናል፤ ይኸውም
በእምነት የመንፈስን ተስፋ እንድንቀበል
ነው::

## የአራት ሕግና የተስፋ ቃል

[15]ወንድሞች ሆይ፤ ከሰው ዕለታዊ ሕይ
ወት የተለመደውን ምሳሌ አድርጌ ላቅርብ፤
የሰው ኪዳን እንኳ አንድ ጊዜ ከጸደቀ በኋላ
ማንም ሊሽረው ወይም በእርሱ ላይ ሊጨም
ርበት እንደማይችል ሁሉ፣ በዚህም ጉዳይ
ቢሆን እንደዚሁ ነው:: [16]የተስፋውም ቃል
የተነገረው ለአብርሃምና ለዘሩ ነበር፤ መጽ
ሐፍ፣ ለብዙ ሰዎች እንደሚነገር፣ "ለዘሮቹ"
አይልም፤ ነገር ግን ለአንድ ሰው እንደሚ
ነገር፣ "ለዘርህ" ይላል፤ እርሱም ክርስቶስ
ነው:: [17]የምለው እንዲህ ነው፤ ከአራት መቶ

3፥9 ቍ7፤ሮሜ 4፥16፤ 4፥18-22
3፥10 ቍ2:5:13፤ ዘዳ27፥26፤ኤር11፥3፤ሮሜ 4፥15፤ ገላ2፥16
3፥11 ዕብ2፥4፤ ሮሜ 3፥28፤9፥30፤ ዕብ 10፥38
3፥12 ዘሌ18፥5፤ ሮሜ 10፥5
3፥13 ዘዳ21፥23፤ ሐሥ5፥30፤ገላ4፥5
3፥14 ቍ2፤ኢል 2፥28፤ዮሐ20፥22፤ ሐሥ2፥33፤ ሮሜ4፥9:16
3፥15 ሮሜ7፥1
3፥16 ዘፍ12፥7፤ 13፥15፤17፥7:8:10፤ 17፥19፤24፥7፤መዝ 132፥11፤ሚክ7፥20፤ሉቃ1፥55፤ሮሜ 4፥13:16፤9፥4:8፤ ገላ3፥29፤4፥28
3፥17 ዘፍ15፥13: 14፤ዘፀ12፥40፤ ሐሥ7፥6
3፥18 ሮሜ4፥14
3፥19 ቍ16፤ዘፀ 20፥19፤ዘዳ5፥5፤ 33፥2፤ሐሥ7፥53፤ ሮሜ5፥20
3፥20 1ጢ2፥5፤ ዕብ8፥6፤9፥15፤ 12፥24
3፥21 ሮሜ7፥12፤ ገላ 2፥17፤2፥21
3፥22 ሮሜ 3፥9-19፤ 11፥3
3፥23 ቍ25፤ ሮሜ11፥32
3፥24 ቍ19፤ሮሜ 4፥15፤10፥4፤ ገላ2፥16

ሠላሳ ዓመት በኋላ የተሰጠው ሕግ፣ አስ
ቀድሞ በእግዚአብሔር የጸናውን ኪዳን አፍርሶ
የተስፋውን ቃል አይሽርም:: [18]ርስትን
መውረስ በሕግ ቢሆን ኖሮ፣ በተስፋ ቃል
ባልተገኘ ነበርና፤ እግዚአብሔር ግን በጸጋው
በተስፋ ቃል አማካይነት ለአብርሃም ሰጥ
ቶታል::
[19]ታዲያ ሕግ የተሰጠበት ምክንያት ምን
ድን ነው? ሕግ የተጨመረው፣ ከመተላለፍ
የተነሣ ተስፋው ያመለከተው ዘር እስኪ
መጣ ድረስ ነበር፤ ሕጉም የመጣው በመላ
እክት በኩል፣ በአንድ መካከለኛ እጅ
ነበር:: [20]ሆኖም መካከለኛው አንድን ወገን
ብቻ የሚወክል አይደለም፤ እግዚአብሔር ግን
አንድ ነው:: [21]ታዲያ ሕግ የእግዚአብሔርን
የተስፋ ቃል የሚቃወም ነውን? ከቶ አይ
ደለም ሕግ የተሰጠው ሕይወትን ለማስገኘት
ቢሆን ኖሮ፣ በእርግጥም ጽድቅ በሕግ
በኩል በተገኘ ነበር:: [22]መጽሐፍ ግን ዓለም
ሁሉ የኀጢአት እስረኛ መሆኑን ያውጃል፤
ይኸውም በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚ
ገኘው ተስፋ ለሚያምኑት ሁሉ ይሰጥ ዘንድ
ነው::
[23]ይህ እምነት ከመምጣቱ በፊት በሕግ
አማካይነት እስረኞች ሆነን፣ እምነት እስከ
ሚገለጥ ድረስ ተዘግቶብን ነበርን:: [24]ስለ
ዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ
ክርስቶስ የሚያደርሰን ሞግዚታችን ሆነ::
[25]አሁን ግን ያ እምነት ስለ መጣ፣ ከእንግ
ዲህ በሕግ ሞግዚትነት ሥር አይደለንም::

3፥25 ሮሜ7፥4

ዚህ ሐሳብ በሮሜ4 ላይ በስፋት ጽፎአል፤ እንዲሁም ዕብ11፥8-19 ይመ::

3፥10 *ሕግን በመጠበቅ የሚተማመኑ ሁሉ፤* የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታ የማይቀበሉትንና ጽድቅን በሥራ ለማግኘት የሚጥሩትን ወገ አጥባቂዎች ያመለክታል:: *ከርግማን በታች፤* ምክንያቱም በሕግ ሥር ያለ ሰው ሕግን በመጠበቅ ፍጹም ስላይደለ ነው:: የእግዚአብሔር በረከት በነጻ የሚሰጥ እንጂ በራስ ጥረት የሚገኝ አይደለም:: *የተጻፈውን ሁሉ፤* ያዕ2፥10 ይመ::

3፥11 *ይኖራል፤* እዚህና ቍ12 ላይ የተጠቀሰው፣ "ይጸድቃል" ከሚለው ትርጕም ጋር ተመሳሳይ ነው::

3፥13 *ክርስቶስ ... ከሕግ ርግማን ዋጅቶናል፤* 4፥5፤ ሮሜ 8፥3 ይመ:: *በዕንጨት፤* በጥንት ዘመን ግሪኮች ወንጀል የፈጸመን ሰው ሰውነት፣ ሹል በሆነ ቋሚ ዕንጨት ላይ ሰክተው በማቈየት ተሰቃይቶ እንዲሞት ያደርጉ ነበር፤ እዚህ ላይ ግን የሚናገረው ጌታ ስለ ተሰቀለበት መስቀል ነው (ሐሥ5፥30፤ 10፥39፤ 1ጴጥ 2፥24 ይመ)::

3፥14 *ለአብርሃም የተሰጠው በረከት፤* ቍ8፤ ሮሜ4፥1-5 ይመ፤ *የመንፈስን ተስፋ፤* ሕዝ36፥26፤ 37፥14፤ 39፥29፤ ዮሐ 14፥16 ይመ፤ ከኤፌ1፥13 ጋር ያነጻጽሩ::

3፥15 *ወንድሞች ሆይ፤* የ1፥2 ማብ ይመ:: *የሰው ኪዳን፤* በግሪኩ ለአንዴና ለመጨረሻ የሚደረግ ሕጋዊ መሠረት ያለው ኪዳን መሆኑን ጳውሎስ እዚህ ላይ ያመለክታል:: በሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ግን፣ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ለማመልከት ብዙ ቦታ ገብቷል (ማቴ26፥28፤ ሉቃ 1፥72፤ ሐሥ3፥25፤7፥8፤ 2ቆሮ3፥14፤ ዕብ8፥9 ይመ):: ጳውሎስ ያደረገው ንጽጽር ያሰበውን ነገር ለማመልከት ረድቶታል::

3፥16 *የተስፋውም ቃል፤* የሮሜ4፥13፤9፥4 ማብ ይመ::

3፥17 *ከአራት መቶ ሠላሳ ዓመት፤* ዘፀ 12፥40-41 ይመ:: እስራኤላውያን በግብፅ ያሳለፉት ዘመን በዘፍ15፥13 እና በሐሥ 7፥6 ላይ፣ "አራት መቶ ዓመት" ተብሎ በሙሉ ቍጥር ተጠጋግቶ ተገልጾአል::

3፥19 *የተጨመረው፤* ከአብርሃም ዘመን ጀምሮ ለእርሱ የተሰጠው ተስፋ (ዘፍ12፥2-3:7፤ 15፥18-20፤ 17፥4-8)፣ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ላለው ግንኙነት መሠረታዊ ነገር ነበር:: ሕዝቡ ከግብፅ ከወጡ በኋላ ግን፣ በሲና በተደረገው ቃል ኪዳን ውስጥ የገባው ሕግ (ዘፀ19-24) በዚህ የኪዳን ግንኙነት ውስጥ ተጨማሪ ነገር ሆኖአል:: ኤርምያስም የአዲሱን ኪዳን የእግዚአብሔር ተስፋ በጠቀሰ ጊዜ (ኤር31፥31-34)፣ ስለ አሮጌው ኪዳን አውሥቶ ነበር:: *ዘር፤* ክርስቶስን ያመለክታል:: *በመላእክት በኩል፤* ዘዳ33፥2፤ ሐሥ7፥38:53፤ ዕብ2፥2 ይመ::

*3፥20፤* በሙሴ በኩል የተሰጠው ኪዳን፣ እግዚአብሔርና እስራኤል በሙሴ አማካይነት ስምምነት እንዲፈጽሙ የተደረገበት ነው:: ለአብርሃም የተሰጠው ኪዳን ግን፣ ከአንዱ እግዚአብሔር (የዘዳ 6፥4 ማብ ይመ) ጋር በቀጥታ የተደረገ ስለ ሆነ አደራዳሪ አላስፈለገም::

*3፥21፤* ሕግ በራሱ የሚያድን ባይሆንም፣ ሰውን ከእግዚአብሔር የለየውን ኀጢአት ይገልጣል፤ በተስፋው ቃል የተጠቀሰው ድነት ምን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነም ያሳያል፤ ከዚህ የተነሣ ከቃል ኪዳኑ ተስፋ ጋር አይቃረንም::

3፥23 *ይህ እምነት፤* በክርስቶስ ያለውን እምነት የሚያመለክት ነው (ቍ22):: *በሕግ አማካይነት እስረኞች ሆነን፤* የኀጢአት እስረኛ መሆን (ቍ22) እና በሕግ እስረኛ መሆን ተመሳሳይ ናቸው፤ ምክንያቱም ሕግ ኀጢአትን ይገልጣል፤ ለኀጢአትም መኖር ምክንያት ነው (4፥3፤ ሮሜ7፥8፤ ቈላ2፥20 ይመ)::

3፥24 *ሞግዚታችን ሆነ፤* በግሪኩ ይህ አባባል፣ "አስተማሪ" ማለት ነው፤ ይህም አንድን ሕፃን በሄደበት ሁሉ እየተከተለ የሚጠብቀውንና ሥርዐት የሚያስተምረውን አገልጋይ ያመለክታል (1ቆሮ4፥15 ይመ)::

*3፥25-26፤* አማኝ ከእምነቱ የተነሣ የልጅነት መብትና ልዩ ክብር ያለው (4፥1-7፤ ሮሜ8፥14-17) ሙሉ ሰው ሲሆን፣ በእግዚአብሔርም ቤት ወራሽ ነው::

## የእግዚአብሔር ልጆች

[26]ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን
የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ፤ [27]ከክርስቶስ ጋር
አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁላችሁ
ክርስቶስን ለብሳችሁታልና::
[28]በአይሁድና በግሪክ፣ በባሪያና በነጻ ሰው፣
በወንድና በሴት መካከል ልዩነት የለም፤
ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ናችሁ::
[29]የክርስቶስ ከሆናችሁ፣ እናንተ የአብርሃም
ዘር ናችሁ፤ እንደ ተስፋውም ቃል ወራሾች
ናችሁ::

4 እኔ የምለው ይህ ነው፤ ወራሹ ሕፃን
እስከ ሆነ ድረስ፣ ሀብት ሁሉ የእርሱ
ቢሆንም እንኳ፣ ከባሪያ የተለየ አይደለም::
[2]አባቱ እስከ ወሰነለት ጊዜ ድረስ በጠ
ባቂዎችና በሞግዚቶች ሥር ነው:: [3]እኛም
እንዲሁ ገና ልጆች በነበርንበት ጊዜ ከዓ
ለም መሠረታዊ ትምህርት ሥር በመሆን
በባርነት ተገዝተን ነበር:: [4]ነገር ግን የተወ
ሰነው ዘመን በደረሰ ጊዜ፣ እግዚአብሔር
ከሴት የተወለደውን፣ ከሕግም በታች
የተወለደውን ልጁን ላከ፤ [5]ይህም የሆነው
የልጅነትን መብት እናገኝ ዘንድ ከሕግ
በታች ያሉትን ለመዋጀት ነው:: [6]ልጆችም
ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔር፣ "አባ[ፐ] አባት'' ብሎ
የሚጮኽ የልጁን መንፈስ ወደ ልባችን
ላከ::
[7]ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ነህ እንጂ
ባሪያ አይደለህም፤ ልጅም ስለ ሆንህ፣ እግ
ዚአብሔር ወራሽ አድርጎሃል::

## ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች ማሰቡ

[8]እግዚአብሔርን ከማወቃችሁ በፊት፣ በባሕ
ርያቸው አማልክት ላልሆኑት ባሪያዎች ነበ
ራችሁ፤ [9]አሁን ግን እግዚአብሔርን ዐውቃችሁ
ታል፤ ይልቁን ደግሞ በእግዚአብሔር ታውቃች
ኋል:: ታዲያ እንደ ገና ወደ ደካማና ወደማ
ይጠቅም ትምህርት እንዴት ትመለሳላ
ችሁ? ዳግም በእርሱ በባርነት ለመጠመድ
ትፈልጋላችሁን? [10]ልዩ የሆኑ ቀኖችን፣ ወሮ
ችን፣ ወቅቶችንና ዓመታትን ታከብራላ
ችሁ:: [11]ስለ እናንተ በከንቱ የደከምሁ እየ
መሰለኝ እፈራላችኋለሁ::
[12]ወንድሞች ሆይ፤ እለምናችኋለሁ፤ እኔ
እናንተን እንደ መሰልሁ እናንተም እኔን
ምሰሉ:: እናንተ አንዳች አልበደላችሁኝም::
[13]እንደምታውቁት በመጀመሪያ ለእናንተ
ወንጌልን የሰበክሁት፣ በሕመም ምክንያት
ነበር::
[14]ሕመሜ ለእናንተ ፈተና ሆኖባችሁም
እንኳ፣ አልሰለቻችሁኝም፤ ወይም አልተጸየ
ፋችሁኝም፤ ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር
መልአክ፣ እንዲያውም እንደ ራሱ እንደ ኢየ
ሱስ ክርስቶስ አድርጋችሁ ተቀበላችሁኝ::

3፥26 ሮሜ8፥14
3፥27 ማቴ 28፥19፤ሮሜ 13፥14
3፥28 ዘፍ1፥27፤ 5፥2፤ኢሳ2፥29፤ ዮሐ10፥16፤17፥11፤ 1ቆሮ12፥13፤ኤፌ 2፥14፡15፤ቈላ3፥11
3፥29 ቍ16፤ ሉቃ3፥8፤ሮሜ8፥17፤ 1ቆሮ3፥23፤ገላ3፥16
4፥3 ቍ8፡9፡ 24፡25፤ገላ2፥4፤ ቈላ2፥8፡20፤
4፥4 ማር1፥15፤ ሉቃ2፥27፤ዮሐ1፥14 ፤3፥17፤ሮሜ5፥6፤ ኤፌ1፥10
4፥5 ዮሐ1፥12፤ ሮሜ3፥24፤8፥14
4፥6 ሐሥ16፥7፤ ሮሜ 5፥58፥15፡16
4፥7ሮሜ8፥17
4፥8 ቍ3፤2ዜና 13፥9፤ኢሳ37፥19፤ ኤር2፥11፤5፥7፤ 16፥20፤ሮሜ1፥28፤ 1ቆሮ1፥21፤8፥4፡5፤ 15፥34
4፥9 ቍ3፤8፥3፤ ቈላ2፥20
4፥12 ሮሜ7፥1፤ ገላ 6፥18
4፥13 1ቆሮ 2፥3
4፥14 ማቴ10፥40

[ሀ]24 *ወይም ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ*
[ፐ]6 በአረማይኩ *አባት* ማለት ነው::

3፥27 *ከክርስቶስ ጋር ... የተጠመቃችሁ፤* ሮሜ6፥3-11፤ 1ቆሮ 12፥13 ይመ::

*3፥28፤* በክርስቶስ ጋር ያለን አንድነት በዘር፣ በማኅበራዊ ኑሮ ደረጃና በጾታ ልዩነት አይገደብም (ሮሜ10፥12፤ 1ቆሮ12፥13፤ ኤፌ2፥15-16 ይመ)::

*3፥29፤* ክርስቲያኖች እውነተኛ መንፈሳውያን የአብርሃም ልጆች ናቸው::

4፥1 *ሕፃን፤* በ1ቆሮ 14፥20 ላይ "ጉልማሶች" ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ::

4፥2 *በጠባቂዎችና፤* በ3፥24 ላይ እንደ ተጠቀሰው ብቻ ሳይሆን፣ ሰፋ ያለ ትርጒም አለው፤ ማቴ 20፥8፤ ሉቃ 8፥3 ይመ::

4፥3 *ከዓለም፤* እነዚህ የመጀመሪያ ትምህርቶች፣ "አዲስ ፍጥረት" (6፥15) ከሆነው ሰው የሚመነጩ አይደሉም:: *መሠረታዊ ትምህርት፤* የግሪኩ ቃል በመጀመሪያ የነገሮች ቅደም ተከተልን የሚያመለክት ሲሆን፣ ከጊዜ በኋላ ግን መሠረታዊ ነገሮችን ለማመልከት የሚገባ ቃል ሆነ:: በዚህ ዐውድ የተገለጸው ግን በአሪት ሕግ ሥር ስለ ነበረው የአይሁድ እምነት የመጀመሪያ ትምህርት (ቍ5) ወይም በዘልማድ ስለ ነበረው የአሕዛብ እምነት መጀመሪያ ትምህርት (ቍ8) ነው:: *በባርነት፤* የ3፥23 ማብ ይመ::

4፥4 *ዘመን በደረሰ ጊዜ፤* የእግዚአብሔር ልጆች ወራሾች ለመሆን የሚበቁበትንና ወደ ብስለት የሚደርሱበትን ጊዜ ለማመልከት ነው:: *እግዚአብሔር ... ልጁን ላከ፤* ዮሐ 1፥14፤ 3፥16፤ ሮሜ1፥1-6፤ 1ዮሐ4፥14 ይመ:: *ከሴት የተወለደውን፤* ክርስቶስ ፍጹም ሰው መሆኑን የሚያሳይ ነው:: *ከሕግም በታች የተወለደውን፤* ለአይሁድ ሕግ የነበረውን ተገዥነት ያመለክታል::

4፥5 *የልጅነትን መብት፤* በእግዚአብሔር ጸጋ የተገኘውን ማለት ነው፤ በሮሜ 8፥15 ላይ የልጅነት መንፈስ ከባርነት መንፈስ ጋር ተነጻጽሮአል (ከኤፌ1፥5 ጋር ያነጻጽሩ):: እግዚአብሔር በክርስቶስ ያመኑትን አይሁድና አሕዛብ የልጅነትና የወራሽነት ሥልጣን ሰጥቶ ቤተ ሰቡ ያደርጋቸዋል::

4፥6 *የሚጮኽ፤* በግሪኩ ቃል መሠረት፣ በቃላት መግለጽ የማይቻለውንና ከውስጥ የሚወጣውን ጥልቅ ስሜት መግለጫ ነው:: በማቴ 27፥50 ላይ ያለው የኢየሱስ ክርስቶስ የመጨረሻ ጩኸት ይህን ይገልጻል:: *አባ አባት፤* ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ልዩ የሆነ ግንኙነት የሚያመለክት ነው:: *የልጁን መንፈስ፤* አዲሱ "ሞግዚት" (ቍ2)፣ በሮሜ 8፥9 ላይ "የእግዚአብሔር መንፈስ" ተብሎአል (ሮሜ8፥2፤ ኤፌ 1፥13-14 ይመ)::

4፥8 *እግዚአብሔርን ከማወቃችሁ በፊት፤* 1ቆሮ 12፥2፤ 1ተሰ4፥5 ይመ:: *አማልክት ላልሆኑት፤* የገላትያ ሰዎች ጣዖታትን ያመልኩ በነበረ ጊዜ የሚሰግዱላቸውን ጣዖቶች ሁሉ አማልክቶቻቸው አድርገው ይገምቱ ነበር፤ በክርስቶስ ካመኑ በኋላ ግን፣ አማልክቱ ከንቱ መሆናቸውን ተረድተዋል::

4፥9 *እንዴት ትመለሳላችሁ፤* 3፥1-3 ይመ:: *ደካማና፣ ወደማይጠቅም ትምህርት* ፤የቍ3 ማብ ይመ:: *ዳግም ... በባርነት፤* በሥርዐት፣ በመልካም ሥነ ምግባር፣ በሕግ፣ በበጎ ሥራ ወይም ባረጀውና በሞተው ልማዳዊ ሃይማኖት ውስጥ ያለው ወግ አጥባቂነት፣ ሙሉ ሰው ሆኖ በማደግ ያለው የልጅነት ነጻነት ምን እንደ ሆነ በሚያውቁና በተለማመዱ ሰዎች ፊት፣ ወደ ኋላ ወደ ባርነት መመለስ መሆኑን ያመለክታል::

4፥10 *ልዩ የሆኑ ቀኖችንና፤* በራሳቸው ወደ ድነት ወይም ወደ ቅድስና ፈጽሞ ሊያደርሱ የማይችሉትን እንደ ሰንበትና የስርየት ቀን የመሳሰሉትን ነው:: *ወሮችን፣ ወቅቶችንና፤* የወር መባቻ (ዘኍ28፥11-15፤ ኢሳ1፥13-14 ይመ)፣ የፋሲካ በዓል (ዘፀ 2፥18)፣ የበኵራት ቀንን (ዘሌ23፥10) ነው:: *ዓመታትን፤* ሰባተኛውን ዓመት የመሳሰሉትን ነው (ዘሌ 25፥4 ይመ):: ፈሪሳውያን በእግዚአብሔር ፊት ሽልማት ለማግኘት አንድም ሳያስቀሩ እነዚህን ሁሉ ፈጽመዋል::

4፥11 *በከንቱ የደከምሁ፤* ወደ አሮጌው የቃል ኪዳን ሕግ በመመለሳቸው ነው::

4፥12 *ወንድሞች፤* የ1፥2 ማብ ይመ::

4፥13 *በመጀመሪያ ... የሰበክሁት፤* ጳውሎስ በመጀመሪያ ሐዋርያዊ የወንጌል ጒዞው ገላትያን በጎበኘበት ጊዜ ማለት ነው (ሐሥ 13፥14-14፥23):: *በሕመም፤* አንዳንድ ሰዎች ቍ15ና 6፥11 መሠረት በማድረግ፣ ይህ ሕመም የዐይን ሕመም እንደ ሆነ ይናገራሉ፤ ሌሎች ግን የወባ በሽታ ነው ይላሉ::

4፥14 *ተቀበላችሁኝ፤* የአይሁድ እምነት ተከታይ ከሆኑት ክርስቲያኖች ተጽእኖ የተነሣ ለእርሱ የነበራቸውን አመለካከት መቀየራቸውን ያመለክታል::

4፥15 *ያ ሁሉ ደስታችሁ የት ደረሰ?* ወግ በሚያጠብቀው

[15]ለመሆኑ ያ ሁሉ ደስታችሁ የት ደረሰ?
ቢቻላችሁ ዐይናችሁን ቢሆን እንኳ አውጥ
ታችሁ የምትሰጡኝ እንደ ነበራችሁ እመሰ
ክራለሁ። [16]እውነቱን ስለ ነገርኋችሁ ጠላት
ሆንሁባችሁን ?
[17]እነዚያ ሰዎች ወደ ራሳቸው ሊወስዷችሁ
ይተጋሉ፤ ለበጎ ግን አይደለም፤ የሚፈል
ጉት እናንተን ከእኛ ነጥለው የራሳቸው
ሊያደርጓችሁ ነው። [18]ለበጎ እስከ ሆነ ድረስ
ተቈርቋሪ መሆን መልካም ነው፤ ይህም
መሆን የሚገባው ዘወትር እንጂ እኔ
ከእናንተ ጋር ሳለሁ ብቻ አይደለም። [19]የም
ወዳችሁ ልጆቼ ሆይ፤ ክርስቶስ በውስ
ጣችሁ እስኪቀረጽ ድረስ ስለ እናንተ እንደ
ገና ምጥ ይዞኛል፤ [20]ስለ እናንተ ግራ በመ
ጋባት ተጨንቄአለሁና፤ አሁን በመካከላ
ችሁ ተገኝቼ ለየት ባለ ቋንቋ ልናገራችሁ
ምን ያህል በወደድሁ!

### አጋርና ሣራ ምሳሌ መሆናቸው

[21]እናንት ከአሪት ሕግ በታች ለመኖር
የምትሹ እስቲ ንገሩኝ፤ ሕግ ምን እንደ
ሚል አልሰማችሁምን? [22]አብርሃም፣ አንዱ
ከባሪያዪቱ፣ ሌላው ደግሞ ከነጻዪቱ ሴት
የሆኑ ሁለት ልጆች እንደ ነበሩት ተጽፎ
አልና። [23]ባሪያ ከነበረችው ሴት የተገኘው
ልጅ፣ እንደ ሥጋ ልማድ ነበር፤ ከነጻዪቱ
ሴት የተወለደው ግን በተስፋው ቃል መሠ
ረት ነው።
[24]እነዚህ ሴቶች ሁለቱን ኪዳኖች ስለ
ሚያመለክቱ፣ ይህ ሁኔታ እንደ ምሳሌ
የሚታይ ነው። አንደኛዋ ኪዳን ከሲና ተራራ
ስትሆን፣ ለባርነት የሚሆኑ ልጆችን የምት
ወልድ ናት፤ እርሷም አጋር ናት። [25]እንግ
ዲህ አጋር በዐረብ አገር ያለችው የሲናን
ተራራ በመወከል፣ አሁን ያለችውን ኢየሩ
ሳሌም ትመስላለች፤ ከልጇ ጋር በባርነት
ናትና። [26]ከላይ የሆነችው ኢየሩሳሌም ግን
በነጻነት ትኖራለች፤ እርሷም እናታችን ናት።
[27]እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤

"አንቺ የማትወልጂ መካን ሆይ፤
ደስ ይበልሽ፤
አንቺ አምጠሽ የማታውቂ፣
በእልልታ ጩኺ፤
ባል ካላት ይልቅ፣
የብቸኛዪቱ ልጆች በዝተዋልና።"

[28]እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ እናንተም
እንደ ይስሐቅ የተስፋው ቃል ልጆች ናችሁ።
[29]በዚያን ጊዜ እንደ ሥጋ ልማድ የተወለደው፣
ልጅ በመንፈስ ኀይል የተወለደውን አሳደደው፤
አሁንም እንደዚያው ነው። [30]ነገር ግን መጽ
ሐፍ ምን ይላል? "ባሪያዪቱን ከልጇ ጋር
አስወግዳት፤ የባሪያዪቱ ልጅ ከነጻዪቱ ልጅ ጋር
አይወርስምና" ይላል። [31]ስለዚህ ወንድሞች
ሆይ፤ እኛ የነጻዪቱ እንጂ የባሪያዪቱ ልጆች
አይደለንም።

5 ክርስቶስ ነጻ ያወጣን በነጻነት እንድን
ኖር ነው። ስለዚህ ጸንታችሁ ቁሙ፤
ዳግመኛም በባርነት ቀንበር አትጠመዱ።
[2]የምለውን አስተውሉ፤ ትገረዙ ዘንድ ብት

4፥16 አሞ 5፥10
4፥17 ገላ 2፥4:12
4፥18 ቍ 13:14
4፥19 ሮሜ 8፥29፤ ኤፌ4፥13፤ 1ተሰ2፥11
4፥21 ሮሜ 2፥12
4፥22 ዘፍ16፥15፤ 21፥2
4፥23 ቍ 28:29፤ ዘፍ 17፥16-21፤ 18፥10-14፤21፥1፤ ሮሜ 9፥7:8፤ ዕብ11፥11
4፥26 ዕብ12፥22፤ ራእ3፥12፤21፥2:10
4፥27 ኢሳ 54፥1
4፥28 ቍ 23፤ ገላ 3፥16
4፥29 ቍ 23፤ ዘፍ 21፥9
4፥30 ዘፍ21፥10
4፥31 ቍ 22፤ ሮሜ 7፥4
5፥1 ቍ 13፤ማቴ 23፥4፤ዮሐ8፥32፤ ሮሜ7፥4፤1ቆሮ 16፥13፤ገላ2፥4
5፥2 ቍ 3:6: 11:12ሐሥ15፥1

በአይሁድ ሃይማኖት ተጽእኖ ምክንያት በረከታቸውና ደስታ ቸው ጠፍቶባቸዋል። *ዐይናችሁን ቢሆን እንኳ አውጥታችሁ፤* ውድ የሆነውን ነገር እንኳ ሳይቀር ሊያካፍሉት ፈቃደኞች መሆናቸ ውን ለመግለጽ የተጠቀመበት ምሳሌያዊ አነጋገር ነው።

4፥16 *ጠላት ሆንሁባችሁን?* እውነትን መናገር ወዳጅ ያሳ ጣል።

4፥17 *እነዚያ ሰዎች፤* የአይሁድ ተከታይ የሆኑ ክርስቲያ ኖች ናቸው (2፥4:12 ይመ)።

4፥19 *ልጆቼ ሆይ፤* ጳውሎስ በእርሱ አማካይነት ክርስቶስን ላመኑ ሰዎች ያለው ፍቅር ምን ያህል እንደ ሆነ ያመለክታል፤ ሐሥ 20፥37-38፤ ፊል4፥1፤ 1ተሰ2፥7-8 ይመ። እንዲህ ዐይነቱ አገላ ለጽ ከጳውሎስ መልእክቶች እዚህ ብቻ የሚገኝ ሲሆን፣ ዮሐንስ ግን ብዙ ጊዜ ተጠቅሞበታል (ለምሳሌ ዮሐ13፥33፤ 1ዮሐ 2፥1፤ 3፥7)። *ክርስቶስ በውስጣችሁ እስኪቀረጽ ድረስ፤* ይህ የጳውሎስ የአገልግሎት ግብ ነው (ሮሜ 8፥29፤ ኤፌ 4፥13:15፤ ቈላ 1፥27 ይመ)።

4፥22 *ሁለት ልጆች፤* ባሪያዪቱ አጋር እስማኤልን ስትወ ልድ (ዘፍ16፥1-16)፣ እመቤቲቱ ሣራ ደግሞ ይስሐቅን ወለደች (ዘፍ 21፥2-5)።

4፥24 *እንደ ምሳሌ፤* ጳውሎስ በአጋርና በሣራ ምሳሌነት የተጠቀመው፣ ታሪካዊነቱን በሙሉው እንደ ተለዋጭ አድርጎ ለማ ቅረብ ሳይሆን፣ ትምህርተ መለኮታዊ እውነትን ለመግለጽም ጭምር ነው። *ኪዳን፤* የ3፥15 ማብ ይመ። *ከሲና ተራራ፤* እስራ ኤል ይመራበት የነበረውን ሕግ የያዘው አሮጌው ኪዳን የተሰጠ በት ስፍራ ነው። (ዘፀ 19፥2፤ 20፥1-17 ይመ)።

4፥25 *አሁን ያለችውን ኢየሩሳሌም ትመስላለች፤* ኢየሩ ሳሌም የአይሁድ ሃይማኖት ማእከልን የምትወክል በመሆኗ፣ ከሲና ተራራ ጋር ልትመሳሰል ትችላለች። የአይሁድ ሃይማኖት አሁ ንም በሲና ተራራ ላይ በተሰጠው የኦሪት ሕግ ሥር ያለ ሃይማ ኖት ነው።

4፥26 *ከላይ የሆነችው ኢየሩሳሌም፤* በረበናት ትምህርት መሠረት፣ በመሲሑ ዘመን ወደ ምድር የምትወርደው ኢየሩ ሳሌም ከላይ የሆነችው ኢየሩሳሌም ምሳሌ ናት (ከራእ 21፥2 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህም ክርስቶስ የነገሠባትና ክርስቲያኖች ዜጎቿ ሆነው የሚኖሩባትን የእግዚአብሔርን ከተማ የሚያመለክት ነው፤ እርሷም፣ "አሁን ያለችውን ኢየሩሳሌምን" አይደለም (ቍ25)። *እናታችን፤* ክርስቲያኖች የሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም ዜጎች እንደ መሆናቸው መጠን ልጆቿ ናቸው።

*4፥27፤* ነቢዩ ኢሳይያስ ልጆችን ያልወለደች መካን ለነበረ ችውና ለግዞተኛዋ ኢየሩሳሌም የተናገረውን አስደሳች ተስፋ፣ ጳውሎስ የ"ኢየሩሳሌም" ልጆች በሚበዙበት በወንጌል ከሚሆነው የአማኞች መሰባሰብ ጋር አዛምዶ ጠቅሶታል።

4፥28 *የተስፋው ቃል ልጆች፤* በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል መሠረት የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ ናቸው (3፥29፤ ሮሜ 9፥8 ይመ)።

4፥29 *በመንፈስ ኀይል የተወለደውን አሳደደው፤* በዘፍ 21፥9 ላይ ያለውን ሐሳብ የሚያመለክት ነው፤ ከመዝ 83፥5-6 ጋር ያነጻጽሩ። *አሁንም እንደዚያው ነው፤* ሐሥ 13፥50፤ 14፥2-5:19፤ 1ተሰ 2፥14-16 ይመ።

4፥30 *ባሪያዪቱን … አስወግዳት፤* ጳውሎስ የአይሁድ እምነት ተከታይ የሆኑ ክርስቲያኖችን ከቤተ ክርስቲያን እንዲያስ ወጡ የገላትያን ሰዎች ለማስተማር በዘፍ21፥10 ላይ ሣራ የተናገ ረቻቸውን ቃላት መሠረት አድርጎ ተጠቅሞበታል።

4፥31 *የባሪያዪቱ ልጆች አይደለንም፤* አማኞች የተስፋ ልጆችና በእምነት የሚኖሩ ናቸው እንጂ፣ በሕግ ባርነት ሥር አይደሉም (ከ3፥7:29 ጋር ያነጻጽሩ)።

5፥1 *በነጻነት፤* እዚህ ላይ የተጠቀሰው ነጻነት ከሕግ ባርነት ነጻ ስለ መውጣት የሚናገር ነው። *በባርነት ቀንበር፤* ኀጢአ ተኛ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት ሲል የኦሪትን ሕግ ለመፈጸም ቢሞክር፣ ሕጉ በእርሱ ላይ የተጫነ አድካሚ ሸክም ይሆንበታል (ሐሥ 15፥10-11 ይመ)። *አትጠመዱ፤* በጥንታዊው የግሪክ ቋንቋ መሠረት መያዝ ወይም በቍጥጥር ሥር መሆን ማለት እንደ ሆን ይታወቃል።

5፥2 *ትገረዙ ዘንድ፤* እግዚአብሔር እንዲቀበላቸው ይፈ

ፈልጉ፣ ክርስቶስ ፈጽሞ ለእናንተ እንደማ
ይበጃችሁ እኔ ጳውሎስ እነግራችኋለሁ::
3መገረዝ ለሚፈልግ ሁሉ ሕግን በሙሉ
የመፈጸም ግዴታ እንዳለበት እንደ ገና ለእ
ያንዳንዱ በግልጽ እናገራለሁ:: 4በሕግ ለመ
ጽደቅ የምትጥሩ፣ ከክርስቶስ ተለይታችኋል፤
ከጸጋ ርቃችኋል:: 5እኛ ግን ተስፋ የምና
ደርገውን ጽድቅ፣ በመንፈስ አማካይነት በእ
ምነት ሆነን በናፍቆት እንጠባበቃለን::
6በክርስቶስ ኢየሱስ ከሆኑ፣ መገረዝ ወይም
አለመገረዝ አይጠቅምምና፤ የሚጠቅመውስ
በፍቅር የሚገለጽ እምነት ብቻ ነው::

7ሩጫችሁ መልካም ነበር፤ ታዲያ ያሰና
ከላችሁ፣ ለእውነትስ እንዳትታዘዙ የከለ
ከላችሁ ማን ነው? 8እንዲህ ያለው ማባ
በል ከሚጠራችሁ የመጣ አይደለም፤
9"ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ ያቦካል::"
10የተለየ ሐሳብ እንደማይኖራችሁ በጌታ
እታመናለሁ:: ግራ የሚያጋባችሁ ማንም
ይሁን ማን፣ ፍርዱን ይቀበላል::

11ወንድሞች ሆይ፤ እስከ ዛሬ ስለ መገ
ረዝ የምሰብክ ከሆነ፣ ታዲያ እስካሁን ለምን
ያሳድዱኛል? እንደዚያማ ቢሆን ኖሮ፣ መስ
ቀል ዕንቅፋት መሆኑ በቀረ ነበር:: 12ግራ
የሚያጋቡአችሁ ሰዎች የራሳቸውን መግረዝ
ብቻ ሳይሆን ይጐንድሉ! 13ወንድሞቼ ሆይ፤
ነጻ እንድትሆኑ ተጠርታችኋል፤ ነጻነታች
ሁን ግን ሥጋዊ ምኞታችሁን+ መፈጸሚያ

5፥3 ሮሜ2፥25፤ ገላ3፥10፤ያዕ2፥10
5፥4 ሮሜ3፥28 ዕብ 12፥15፤ 2ጴጥ3፥17
5፥5 ሮሜ8፥23:24
5፥6 ሮሜ16፥31 1ቆሮ7፥19፤1ተሰ1፥3 ፤ያዕ2፥22
5፥7 1ቆሮ9፥24፤ ገላ3፥1
5፥8 ሮሜ8፥28
5፥9 1ቆሮ5፥6
5፥10 ቍ 12፤2ቆሮ 2፥3፤ገላ1፥7፤ፊል 3፥15
5፥11 ሉቃ2፥34፤ ገላ 4፥29፤ 6፥12፤
5፥12 ቍ 10
5፥13 ቍ 1:24፤ 1ቆሮ8፥9፤9፥19፤ 2ቆሮ4፥5፤ኤፌ5፥21 ፤1ጴጥ2፥16
5፥14 ዘሌ19፥1፤8፤ ማቴ5+43፤ገላ 6፥2
5፥16 ቍ 18:24: 25፤ ሮሜ8፥2:4-6: 9:14፤2ቆሮ5፥17
5፥17 ሮሜ7፥15 -23፤8፥5-8
5፥18 ቍ 16፤ሮሜ 2፥12፤1ጢሞ1፥9
5፥19 1ቆሮ 6፥18
5፥21 ማቴ15፥19፤ 25፥32፤ሮሜ13፥13
5፥22 ሚል2፥6 ማቴ 7፥16-20፤ ኤፌ5፥9፤ ቈላ3፥12-15

አታድርጉት፤ ይልቁንም አንዱ ሌላውን በፍ
ቅር ያገልግል::

14ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ተጠቃሎአል፤
ይኸውም፣ "ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ"
የሚል ነው:: 15ነገር ግን እርስ በርሳችሁ
የምትነካከሱና የምትበላሉ ከሆነ፣ እርስ በር
ሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ::

### በመንፈስ መመላለስ

16እንግዲህ በመንፈስ ኑሩ እላለሁ፤ የሥጋ
ንም ምኞት አትፈጽሙም:: 17ሥጋ መንፈስ
የማይፈልገውን፣ መንፈስም ሥጋ የማይፈ
ልገውን ይመኛልና፤ እነዚህ እርስ በርሳቸው
ስለሚጋጩ፣ የምትፈልጉትን አታደርጉም::
18በመንፈስ ብትመሩ ግን፣ ከሕግ በታች አይ
ደላችሁም::

19የሥጋ ሥራ ግልጽ ነው:- ይኸውም
ዝሙት፣ ርኵሰት፣ መዳራት፣ 20ጣዖትን
ማምለክ፣ ሟርት፣ ጥላቻ፣ ጠብ፣ ቅናት፣
ቍጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ መለያየት፣ አድመ
ኝነት፤ 21ምቀኝነት፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ እን
ዲሁም እነዚህን የመሰለው ነው:: አስቀ
ድሜ እንዳልሁ፣ አሁንም አስጠንቅቃች
ኋለሁ፤ በእንዲህ ሁኔታ የሚኖሩ ሁሉ የእግዚ
አብሔርን መንግሥት አይወርሱም::

22የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣
ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣

+13 *ወይም ኀጢአተኛ ተፈጥሮአችሁን፤* እንዲሁም ቍ16:17:19 እና 24 ይመ::

ጽሙት የነበር ሥርዐት ነው::

5፥3 *ሕግን በሙሉ የመፈጸም ግዴታ እንዳለበት፡* የብሉይ ኪዳን ሕግ አንድ ወጥ ስለ ሆነ፣ ሁሉንም መታዘዝ አማራጭ የሌለው ግዴታ ነው::

5፥4 *ከጸጋ ርቃችኋል፤* ከመለኮታዊ ፍቅሩ ውጭ መሆናቸውን ይገልጻል፤ ምክንያቱም ሕግን በመጠበቅ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘትና በጸጋው ምሕረትን ማግኘት ሁለቱ የተለያዩ ናቸው (2ጴጥ 3፥17 ይመ)::

5፥5 *ተስፋ የምናደርገውን ጽድቅ፡* እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመን ቅዱሳን ከበደል ነጻ መሆናቸውን የሚሰጠው ቅን ፍርድ፣ ዛሬም በእምነትና ቀዳሽ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ሥራ አማካይነት እንደ ተረጋገጠ የሚያመለክት ነው፤ ይህም ጳውሎስ በገላትያ መልእክት ስለ መጨረሻው ዘመን ከጠቀሳቸው አያሌ ጥቅሶች አንዱ ነው::

5፥6 *መገረዝ ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና፡* ቍ 2፤ 2፥21፤6፥15፤1ቆሮ7፥19 ይመ:: *በፍቅር የሚገለጽ እምነት፤* በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ የተመሠረተ ሕያው እምነት እንጂ (1ተሰ 1፥3)፣ ጊዜያዊ በሆነ ሁኔታ በሐሳብ የሚገለጽ ብቻ አይደለም (ያዕ 2፥18-19 ይመ)::

5፥7 *ሩጫችሁ መልካም ነበር፤* የአይሁድ እምነት ተከታይ የሆኑ ክርስቲያኖች ሳያደናቅፏቸው የነበረውን የሚያመለክት ነው:: ጳውሎስ የክርስትናን ሕይወት ከሩጫ እሽቅድምድም ጋር አመሳስሎ መግለጽ ይወዳል (ለምሳሌ 2፥2፤ ፊል 2፥16፤ 2ጢሞ 2፥5 ይመ)::

5፥8 *ማባበል፤* የአይሁድ እምነት ተከታይ የሆኑ ክርስቲያኖች፣ እውነተኛ አማኞችን ወደ እነርሱ ለመሳብ የሚያደርጉትን ሙከራ ይገልጻል::

*5፥9፤* እዚህ ላይ የአይሁድ እምነት እየተስፋፋ መሄዱን ለመግለጽ የገባ ምሳሌያዊ ንግግር ነው:: ከማቴ 13፥33 በስተቀር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ "እርሾ" የሚል ቃል የሚገኝበት ትምህርት ሁሉ ክፉ ነገርን ወይም የሐሰት ትምህርትን ለመግለጽ የገባ ነው (የማር 8፥15 ማብ ይመ)::

5፥11 *ወንድሞች፤* የ1፥2 ማብ ይመ:: *መስቀል ዕንቅፋት፡* ሮሜ 9፥32-33፤ 1ቆሮ 1፥23 ይመ::

5፥12 *ይጐንድሉ፤* የግሪኩ ቃል፣ "መቍረጥ"፣ "መጐመድ" ወይም "መቀጥቀጥ" ይለዋል:: በፊል 3፥2 ላይ ተመሳሳይ ስለ ሆኑ ሰዎች ሲገልጽ፣ "ሥጋን ከሚቈራርጡ" የሚለውን ቃል ተጠቅሞአል::

5፥13 *ነጻነታችሁን ግን ሥጋዊ ምኞታችሁን መፈጸሚያ አታድርጉት፡* ሮሜ 6፥1፤ 1ጴጥ 2፥16 ይመ:: ዐርነት አንድን ነገር ለማድረግ ፈቃድ ማግኘት አይደለም፤ ነገር ግን እግዚአብሔርንና እርስ በርሳችንን በፍቅር የምናገለግልበት ነው::

5፥14 *ሕግ ሁሉ ...ተጠቃሎአል፤* ሌሎች እንዲያደርጉልህ የምትፈልገውን ነገር ለእነርሱ ማድረግ፣ የሕግንና የነቢያትን መንፈስና ፍላጎት ይገልጻል (ማቴ7፥12፤ ከማር12፥31 ጋር ያነጻጽሩ)::

5፥15 *የምትነካከሱና የምትበላሉ፡* የቍ 13-14 ተቃራኒ ነው:: ሕግን በመጠበቅ በእግዚአብሔርና በሰው ዘንድ ክብርን ለማግኘት መሯሯጥ፣ ተመጻዳቂነትንና አንዱ ሌላውን የመቃወም መንፈስን ያስፋፋል::

5፥16 *ኑሩ፤* ሁልጊዜ መደረግ የሚገባው መሆኑን የሚያመለክት ነው:: በመንፈስ ቅዱስ ኀይል መመላለስ ሥጋዊ ምኞትን ለማሸነፍ ወሳኝ ነው (ቍ 25፤ ሮሜ 8፥2-4 ይመ)::

5፥17 *እርስ በርሳቸው ስለሚጋጩ፡* ሮሜ 7፥15-23፤ 1ጴጥ 2፥11 ይመ::

5፥18 *በመንፈስ ብትመሩ፤* ሮሜ 8፥14 ይመ:: *ከሕግ በታች አይደላችሁም፤* ለድነት ወይም ለቅድስና ሕግን በመጠበቅ፣ እግዚአብሔርን ለማስደሰት የመሞከር እስረኛ አለመሆን ማለት ነው (የሮሜ 6፥14 ማብ ይመ)::

*5፥19-21፤* ስለ ሌሎች ተመሳሳይ ድርጊቶች፤ 1ቆሮ 6፥9-10፤ ኤፌ 5፥5፤ ራእ 22፥15 ይመ::

*5፥22-23፤* ስለ ሌሎች መልካም ባሕርያት 2ቆሮ 6፥6፤ ኤፌ 4፥2፤ 5፥9፤ ቈላ 3፥12-15 ይመ:: የክርስትና መልካም ባሕርያት የሚገኙት ከመንፈስ ቅዱስ እንጂ፣ ሕግን በመጠበቅ የሚመጡ የሥነ ምግባር ውጤት አይደሉም:: በእምነት የሚገኘው ጽድቅ፣ እንደ ተፈለገ በኀጢአት ለመኖር የሚያስችል ነጻነት የሚሰጥ አለመሆኑን ጳውሎስ ገልጾአል:: በአማኙ ሕይወት ውስጥ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ፣ በአማኙ ሕይወት የመልካም ባሕርያት ፍሬዎች እንዲታዩ ያደርጋል::

5፥22 *የመንፈስ ፍሬ፤* ከቍ 19 ጋር ያነጻጽሩ::

23ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው። እንደነዚህ
ያሉትንም የሚከለክል ሕግ የለም። 24የክር
ስቶስ ኢየሱስ የሆኑት ሥጋን ከክፉ ምኞ
ቱና መሻቱ ጋር ሰቅለውታል። 25በመንፈስ
የምንኖር ከሆን፣ በመንፈስ እንመላለስ።
26እርስ በርሳችን እየተጎነታተልንና እየተ
ቀናናን በከንቱ ውዳሴ አንመካ።

## ለሰው ሁሉ በጎ ማድረግ

6 ወንድሞች ሆይ፤ አንድ ሰው በኀጢአት
ውስጥ ገብቶ ቢገኝ፣ መንፈሳውያን
የሆናችሁ እናንተ በገርነት ልትመልሱት
ይገባል። ነገር ግን አንተም እንዳትፈተን
ራስህን ጠብቅ። 2አንዱ የሌላውን ከባድ
ሸክም ይሸከም፤ በዚህም ሁኔታ የክርስቶ
ስን ሕግ ትፈጽማላችሁ። 3አንድ ሰው ምንም
ሳይሆን ትልቅ የሆነ ቢመስለው ራሱን ያታ
ልላል። 4እያንዳንዱ የራሱን ተግባር ይመ
ርምር፤ ከዚያም በኋላ፣ ከሌላ ሰው ጋር
ራሱን ሳያወዳድር፣ ስለ ራሱ የሚመካበትን
ያገኛል፤ 5እያንዳንዱ የራሱን ሸክም ሊሸከም
ይገባዋልና።

6ማንም ቃሉን የሚማር፣ መልካም የሆነ
ውን ነገር ሁሉ ከመምህሩ ጋር ይካፈል።
7አትታለሉ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም።
ሰው የሚዘራውን ያንኑ ያጭዳል። 8ሥጋዊ
ምኞቱን ለማርካት የሚዘራ፣ ከሥጋ[a] ጥፋትን
ያጭዳል፤ መንፈስን ለማስደሰት የሚዘራ
ግን ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል።
9በጎ ነገር ከማድረግ አንታክት፤ ተስፋ
ካልቈረጥን ጊዜው ሲደርስ መከሩን እና
ጭዳለን። 10ስለዚህ ዕድሉ ካለን ለሰው ሁሉ፣
በተለይም ለእምነት ቤተ ሰቦች መልካም
እናድርግ።

## አዲስ ፍጥረት መሆን

11እንዴት ባሉ ታላላቅ ፊደላት በእጄ
እንደ ጻፍሁላችሁ ተመልከቱ።
12ውጫዊ በሆነ ነገር ለመታየት የሚፈ
ልጉ ሰዎች ትገረዙ ዘንድ ሊያስገድዷችሁ
ይጥራሉ፤ ይህንም የሚያደርጉት ስለ ክርስ
ቶስ መስቀል እንዳይሰደዱ ነው። 13እነርሱ
በሥጋችሁ ለመመካት ሲሉ እንድትገረዙ
ፈለጉ እንጂ፣ የተገረዙት ራሳቸው እንኳ
ሕግን የሚጠብቁ አይደሉም። 14ነገር ግን
ዓለም ለእኔ ከተሰቀለበት፣ እኔም ለዓለም
ከተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክር
ስቶስ መስቀል በቀር፣ ሌላው ትምክሕት
ከእኔ የራቀ ይሁን። 15መገረዝም ሆነ አለ
መገረዝ አይጠቅምም፤ የሚጠቅመው አዲስ
ፍጥረት መሆን ነው። 16ይህን ትእዛዝ በሚ
ከተሉ ሁሉ፣ የእግዚአብሔር በሆነው እስራኤልም
ላይ ሰላምና ምሕረት ይሁን።
17እኔ የኢየሱስን ምልክት በሥጋዬ ተሸክሜ
አለሁና፣ ከእንግዲህ ወዲህ ማንም አያስ
ቸግረኝ።

5÷23 ቍ 18፤ ሐሥ 24÷25
5÷24 ቍ 13፡ 16-21፡16፡17፤ ሮሜ6÷6፡7÷5፡18፤ 8÷3-5፡8፡ 9፡12፡13፤13÷14፤ ገላ6÷8፤ቈላ2÷11
5÷25 ቍ 16
5÷26 ፊል2÷3
6÷1 ማቴ18÷15፤1 ቆሮ2÷15፤ 3÷1፤ 2ቆሮ2÷7
6÷2 1ቆሮ9÷21፤ ያዕ 2÷8
6÷3 ሮሜ 12÷3፤ 1ቆሮ3÷18፡8÷2
6÷4 2ቆሮ10÷12፤ 13÷15
6÷5 ቍ 2፤ ኤር31÷30
6÷6 1ቆሮ9÷11፡ 14፤1ጢሞ 5÷17፡18
6÷8 ኢዮ 4÷8፤ ሆሴ 8÷7፤ ሮሜ 6÷23፤ያዕ 3÷18
6÷9 ኢዮ42÷12፤ መዝ126÷5፤1ቆሮ15 ÷58፤2ቆሮ4÷1፤ዕብ 12÷3፤ራእ2÷10
6÷10 ምሳ3÷27፤ ኤፌ 2÷19፤ቲቶ 2÷14፤1ጴጥ4÷17
6÷11 1ቆሮ16÷21
6÷12 ማቴ23÷25፡ 26፤ሐሥ15÷1፤ገላ 5÷11
6÷15 1ቆሮ7÷19፤ 2ቆሮ5÷17
6÷17 ኢሳ44÷5፤ 2ቆሮ 1÷5፤11÷23

[a]8 *ወይም ኀጢአተኛ ተፈጥሮ ለማርካት የሚዘራ፣ ከዚሁ ተፈጥሮ*

5÷23 *ሕግ የለም፤* 1ጢሞ 1÷9 ይመ።

5÷24 *ሥጋን ... ሰቅለውታል፤* 2÷20፤6÷14 ይመ።

5÷25 *እንመላለስ፤* ከቍ 16 ጋር ያነጻጽሩ።

6÷1 *ወንድሞች፤* የ1÷2 ማብ ይመ። *መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ፤* ከ1ቆሮ 3÷1-3 ጋር ያነጻጽሩ። *ልትመልሱት፤* የግሪኩ ግሥ ዐጥንትን መገጣጠም፣ መረብን መጠገን ወይም የተበታተነውን ነገር መልሶ አንድ ማድረግ የሚለውን ትርጕም ይዞ በሌላ ስፍራ ገብቶአል።

6÷2 *አንዱ የሌላውን ከባድ ሸክም ይሸከም፤* ሥነ ምግባራዊ ችግር ላይ ወይም ድክመት ላይ አጽንዖት ያደርጋል (ቍ 1፤ ሮሜ 15÷1-3 ይመ)። *የክርስቶስን ሕግ፤* የ1ቆሮ 9÷21 ማብ ይመ።

6÷4 *እያንዳንዱ የራሱን ተግባር ይመርምር፤* በግል ኀላፊነት ላይ አጽንዖት የሚያደርግ ነው (1ቆሮ 11÷28፤ 2ቆሮ 13÷5 ይመ)።

6÷5 *እያንዳንዱ የራሱን ሸክም ሊሸከም ይገባዋልና፤* እያንዳንዳችን በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂዎች ነን፤ ይህም ሊመጣ ያለውን ፍርድ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል፤ በዚያን ጊዜ እያንዳንዱ ስለ ራሱ በእግዚአብሔር ፊት መልስ ይሰጣል (ሮሜ 14÷12፤ 2ቆሮ 5÷10)።

6÷6 *መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ...ይካፈል፤* ፊል4÷14-19 ይመ።

6÷7 *የሚዘራውን ያንኑ ያጭዳል፤* 2ቆሮ 9÷6 ይመ። ከቍ 8-9 እንደሚያሳየው ሕጉ ለመጥፎ ብቻ ሳይሆን፣ ለመልካም ነገርም ያገለግላል።

*6÷8፤* ሮሜ 8÷13 ይመ። *ጥፋትን፤* 5÷19-21 ይመ። *የዘላለምን ሕይወት፤* ጳውሎስ በ5÷21 ላይ የእግዚአብሔርን መንግሥት ስለ መውረስ ሲናገር፣ እዚህ ላይ ደግሞ የዘላለምን ሕይወት ስለ ማጨድ ይናገራል። እስራኤላውያን የተስፋዪቱን ምድር እንደ ወረሱ፣ የመጀመሪያው በሚወረሰው ነገር ላይ አጽንዖት ሲያደርግ፣ ሁለተኛው ደግሞ ከውርሱ በሚገኘው የበረከት ሕይወት ላይ አጽንዖት ያደርጋል።

6÷10 *በተለይም ለእምነት ቤተ ሰቦች፤* 1ጢሞ 5÷8 ይመ።

6÷11 *ታላላቅ ፊደላት፤* ጽሑፉ ትኵረት እንዲሰጠው ወይም አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ጳውሎስ የማየት ችግር ስለ ነበረው ሊሆን ይችላል (የ4÷13 ማብ ይመ)። *በእጄ፤* እስከዚህ ድረስ መልእክቱን ሌላ ጸሓፊ በቃል እየተነገረው ጽፎለት ይሆናል፤ በኋላ ግን ጳውሎስ ከጸሓፊው ተቀብሎ በገዛ እጁ ጽፎ ያጠናቀቀው ይመስላል።

6÷12 *ትገረዙ ዘንድ ሊያስገድዷችሁ ይጥራሉ፤* ከ2÷3 ጋር ያነጻጽሩ። *እንዳይሰደዱ ነው፤* የአይሁድ እምነት ተከታይ የሆኑ ክርስቲያኖች የመገረዝን አስፈላጊነት (5÷11) ስለሚሰብኩ፣ ክርስትናን ከማይደግፉ አይሁዶች ብዙም ተቃውሞ አይደርስባቸውም ነበር፤ የሚያስቡት ስለ ራሳቸው ብቻ ነውና።

6÷14 *ዓለም፤* እግዚአብሔርን የሚቃወም ሁሉ ማለት ነው። *ዓለም ለእኔ ከተሰቀለበት፣እኔም ለዓለም ከተሰቀልሁበት፤* 2÷19-20፤ 5÷24፤ እንዲሁም የያዕ 4÷4፤ 1ዮሐ2÷15 ማብ ይመ። *ከ ... መስቀል በቀር ሌላው ትምክሕት፤* 1ቆሮ 1÷31፤ 2÷2 ይመ።

6÷15 *አዲስ ፍጥረት፤* ሰው በክርስቶስ በማመን አዲስ ሆኖ በክርስቶስ ይለወጣል፤ እንደ ገናም ይፈጠራል (2ቆሮ 5÷17 ይመ)።

6÷16 *ሰላምና ምሕረት፤* ከመዝ 125÷5፤ 128÷6 ጋር ያነጻጽሩ። *ይህን ትእዛዝ፤* ቍ 14-15 ይመ። *የእግዚአብሔር በሆነው እስራኤልም፤* "እንደ ሥጋ ፈቃድ እስራኤላውያን" ወይም በ1ቆሮ10÷18 በግሪኩ ቃል እንደ ተጠቀሰው፣ "የእስራኤል ሕዝብ" ከሚለው ጋር ሲነጻጸር፣ ክርስቶስን በተቀበሉ አይሁድና አሕዛብ የተዋቀረው የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን፣ እርሱ የአብርሃም ዘርና በተስፋው ቃል መሠረት የሚወርሱት ነው (3÷29 ይመ፤ ከሮሜ 9÷6፤ ፊል 3÷3 ጋር ይነጻጽሩ)። አንዳንዶች ግን ይህ ክርስትናን ለተቀበሉ አይሁዶች ብቻ እንደ ሆነ አድርገው ይገምታሉ።

6÷17 *የኢየሱስን ምልክት፤* በጥንት ጊዜ፣ "ምልክት" ለሚለው የሚተካው የግሪክ ቃል፣ ባሪያን ወይም እንስሳን ለይቶ ለማወቅ በጋለ ብረት መተኮስን ወይም መጠበስን ያመለክታል። የጳውሎስ መሠቃየት (መወገሩ ሐሥ 14÷19፣ መደብደቡ፤ ሐሥ 16÷22፤ 2ቆሮ11÷25፣ መታመሙ፤ 2ቆሮ12÷7፤ ገላ4÷13-14)፣

18ወንድሞች ሆይ፤ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመንፈሳችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን::

6፥18 ሮሜ 16፥20፤ ፊል4፥23፤ 2ጢሞ4፥22፤ፊሞ25

"የክርስቶስ ባሪያ" መሆኑን ያመለክታል (1፥10 ይመ፤ ከ2ቆሮ 4፥10 ጋር ያነጻጽሩ)::

6፥18 **አሜን፤** አብዛኛውን ጊዜ የቃለ ውዳሴ መዝጊያ ወይም በቡራኬ ላይ የሚነገር የስምምነት ቃል ነው::

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ኤፌሶን ሰዎች


## መግቢያ

### ጸሓፊው፣ መልእክቱ የተጻፈበት ጊዜና ቦታ

የመልእክቱ ጸሓፊ ጳውሎስ መሆኑን ራሱ መልእክቱ ይገልጻል (1፥1፣ 3፥1 ይመ፣ ከ3፥7:13፣ 4፥1፣ 6፥19-20 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ መልእክት ኤፌሶንን ጨምሮ ወደ ሌሎች ከተሞችም እንዲደርስ የተጻፈ ዞዋሪ ደብዳቤ ሳይሆን አይቀርም (1፥1:15፣ 6፥21-23 ማብ ይመ)፣ ጳውሎስ የቆላስይስን መልእክት በጻፈበት ጊዜ፣ በ60 ዓ.ም ግድም በሮም እስር ላይ እያለ ይህን ደብዳቤ ጽፎታል (3፥1፣ 4፥1፣ 6፥20 ይመ)።

### የኤፌሶን ከተማ

ኤፌሶን በትንሹ እስያ (በዛሬው ቱርክ) ምዕራብ ክፍል ከሚገኙት ከተሞች እጅግ የታወቀች ከተማ ነበረች። ከተማዋ ወደ ኤጂያን ባሕር በሚፈስው የካይስተር ወንዝ ላይ አንድ ወደብ ነበራት። ታላላቅ የንግድ መንገዶች አቋርጠው በሚያልፉበት ቦታ ላይ የተመሠረተች ስለ ሆነች ኤፌሶን የንግድ ማእከል ለመሆን በቅታለች። ግሪኮች አርጤምስ ሮማውያን ዲያና የሚሏት ጣዖት አምላክ ቤተ መቅደስ በዚችው ከተማ ይገኝ ስለ ነበር ክፉኛ ትኵራራም ነበር (ከሐሥ 19፥23-31 ጋር ያነጻጽሩ)። ጳውሎስ በኤፌሶን ሦስት ዓመት ያህል ተቀምጦ የወንጌል ስርጭት ማእከል አድርጎአት ነበር (የሐሥ 19፥10 ማብ ይመ)፣ በዚያን ጊዜ የነበረችውም ቤተ ክርስቲያን በአንድ ወቅት አድጋ፣ ተስፋፍታ ነበር፣ በኋላ ግን በራእ2፥1-7 ላይ ያለውን ማስጠንቀቂያ መስጥቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ።




**ኤፌሶን በጳውሎስ ዘመን**

እስያ በሮም ግዛት ካሉ የሜዲትራኒያንን ባሕር ከበው ከተቀመጡ አስደናቂ ከተሞች ካሉአቸው አውራጃዎች አንዷ ናት።

በግዛቱ ውስጥ ወደ ምሥራቃዊ አውራጃዎች በየብስም ሆነ በባሕር ለመሄድ ባለው ዋነኛ መስመር የምትገኘው ኤፌሶን በዓለም ላይ ጥቂት አምሳያዎች ያሏት የንግድ ማዕከል ነበረች። በእርግጥም በእስያ አውራጃ ውስጥ እንደዚህች ከተማ ስሟ የገነነና ብዙ ሕዝብ የሚኖሩባት ከተማ የለችም። በዚህ ግዛት ውስጥ እንደ ሮም፣ ቆሮንቶስ አንጾኪያና እስክንድርያ ካሉት የምትመደብ ነበረች።

ወደ የብስ ገባ ያለ ወደብ ያላት ይህች ከተማ ከኤግያን ባሕር 4.8 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ትገኛለች። ኤፌሶን በዓለም ካሉት ሰባት አስደናቂ ሥራዎች አንዱ በሆነው በአርጤምስ (ዲያና) ቤተ ጣዖት በስመ ገናናነት ትታወቃለች። የከተማው ሳንቲሞች ኒዮቆሮስ «የመቅደስ አለቃ» የሚል ጽሑፍ የተጻፈባቸው ነበሩ።

ጳውሎስ በኤፌሶን ለተሰበሰቡ አያሌ ሕዝብ ወንጌልን ሰበከ። ጳውሎስ የከተማውን አብዛኛ ሕዝብ እንዲያውም በእስያ አውራጃ የሚገኙትን ሁሉ በስብከቱ እንደ ለወጠ ብር አንጥረኛው ተቃውሞ አቀረበ (ሐሥ 19:26)። በአዲስ ኪዳን ከተዘገቡት አስደናቂ ክስተቶች በአንዱ ሐዋርያው ጳውሎስ በጨዋታ ስፍራ ከተነሣው ዐመፅ ማምለጡ ነው። በጲዮን ተራራ ቁልቁለት ላይ የተሠራው የጨዋታ ስፍራ 25000 ሰው ሊያስቀምጥ የሚችል ቦታ ነበረው።

ሐዋርያው የሚያውቃቸው ስፍራዎች የአጎራ ገበያ፣ የማግኔሲያን በር፣ የሽንት አዳራሽና የቀርጤስ ጎዳና ናቸው። ጳውሎስ ያስተማረበት የጢራኖስ ትምህርት ቤት ቦታው አይታወቅም።

### መልእክቱ

ኤፌሶን፣ እንደ ሌሎቹ የጳውሎስ መልእክቶች የስሕተት ትምህርትን ወይም ኑፋቄን በተመለከተ በተለይ የሚያወሣው ነገር የለም። ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው የአንባቢዎቹን አድማስ በማስፋት፣

የእግዚአብሔርን የዘላለም ዕቅድና የጸጋውን ስፋት ጥልቀት ይበልጥ እንዲረዱና እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ታላቅ ግብ ማድነቅ እንዲችሉ ነው። ይህ መልእክት ወደ እግዚአብሔር ጥበብ ዕቅ ድና ዐላማ በሚስቡ ድንቅ መግለጫዎች መካከል በተሰበጣጠሩ፣ ስለ እግዚአብሔር በረከት በሚናገሩ ተከታታይ ዐረፍተ ነገሮች ይጀምራል።

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ መጻናችን እኛ ጥቅም እንድናገኝ ብቻ ሳይሆን፣ ለእግዚ አብሔር ውዳሴና ክብርም ይሆን ዘንድ መሆኑን በአጽንዖት ያሳስባል። ዋናውና መጨረሻው የእግዚ አብሔር ዕቅድ፣ "በዘመን ፍጻሜ" በፍጥረተ ዓለም ያለውን ሁሉ በአንድነት አጠቃሎ በክርስቶስ ሥልጣን ሥር ማዋል ነው (1፥10)። ሁሉም ክርስቲያን ይህን ማወቅ ያለበት ዋና ነገር ስለ ሆነ የኤ ፌሶንም ምዕመናን ይህን እንዲገነዘቡ ሐዋርያው ይጸልይላቸዋል (81፥15-23)።

ሐዋርያው በ3፥14-21 ላይም በድጋሚ ይጸልያል፤ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ዐላ ማና ግብ ካስረዳ በኋላ፣ በምን ዐይነት መልክ ተፈጻሚ መሆን እንዳለባቸው በቅደም ተከተል ያስቀም ጣል። ከሁሉ አስቀድሞ እግዚአብሔር በጸጋው እያንዳንዱን ከራሱ ጋር አስታርቆአል (2፥1-10)፣ በሁለ ተኛ ደረጃ እግዚአብሔር የዳኑትን ሰዎች እርስ በርሳቸው አስታርቆአቸዋል፤ በክርስቶስ ሞት በመካከላቸው የነበረው የጥል ግድግዳ ፈርሶአል (2፥11-22)። ይህ ብቻ አይደለም፤ እግዚአብሔር እነዚ ህን የታረቁትን ሰዎች አንድ አካል በሆነችው ቤተ ክርስቲያን አንድ በማድረግ አስደናቂ ሥራ ሠርቶአል። ይህም ለጳውሎስ ከመገለጡ በፊት ሙሉ በሙሉ ያልታወቀ ምስጢር ነበር (3፥1-6)። ጳውሎስ ግን አሁን እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያሰበውን ሐሳብ በተሻለ ሁኔታ ለመግለጽ ችሎአል። ይኸ ውም፣ "ብዙ ገጽታ ያለው የእግዚአብሔር ጥበብ በሰማያዊ ስፍራ ላሉት አለቆችና ባለ ሥልጣናት" የሚገለጽበት መንገድ እንድትሆን ስለፈለገ ነው (3፥7-13)፣ "በሰማያዊ ስፍራ" የሚለው ተደጋግሞ ሲታይ (1፥3፡20፤ 2፥6፤ 3፥10፤ 6፥12)፣ የክርስትና ሕይወት በምድር ብቻ ተወስኖ እንዳልቀረ ያመለክታል፤ የክርስትና ትርጕሙንና ጠቀሜታውን ክርስቶስ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ከተቀመጠበት ከሰማያዊ ስፍራ አንጻር ማየት ይቻላል (1፥20)።

ይሁን እንጂ ይህ ሕይወት የሚኖረው ምድር ላይ ነው፤ ለምን ቢባል የእግዚአብሔር ዕቅድ በአ ማኙ የዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ይገለጣልና። አማኞች አንዱ ሌላውን በማገልገል፣ አንድነትንና ብስለትን እንዲያሳድጉ (4፥1-16)፣ ከሞት ተነሥቶ ወደ ሰማይ ያረገው ጌታ ለቤተ ክርስቲያኑ አባላት "ስጦታን" ሰጥቶአቸዋል። በክርስቶስ ራስነት በምትተዳደረዋ በዚህች ቤተ ክርስቲያን የሚታየው አንድነት በዘመ ናት መጨረሻ ላይ የሚሆነውን "በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ" በክርስቶስ አንድ ማድረግን አስቀ ድሞ የሚያመለክት ነው (1፥10)። አንድነት በልዩነት ያለበት ይህ አዲሱ የቅድስና ሕይወት፣ ክርስቶስ የሌለበት የአሮጌው ሕይወት ተቃራኒ ነው (4፥17-6፥9)። "በጌታ ብርቱዎች" የሆኑ ምእመናን (በተለይ በጸሎት) በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ከፉውን ድል ይነሣሉ (6፥10-20)።

**አስተዋፅኦ**

1. ሰላምታ (1፥1-2)
2. መለኮታዊ ዕቅድ የክርስቶስ ክብርና የበላይነት (1፥3-14)
3. ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ዕቅድና ኀይል እንዲያውቁ (1፥15-23)
4. የእግዚአብሔርን ዐላማ ዳር ለማድረስ የሚኬድባቸው መንገዶች (ም 2-3)
   - ሀ. እያንዳንዱ ሰው በጸጋ የሚያገኘው መዳን (2፥1-10)
   - ለ. አይሁድና አሕዛብ በመስቀሉ አማካይነት በመካከላቸው ዕርቅ መመሥረቱ (2፥11-18)
   - ሐ. አይሁድንና አሕዛብን አንድ ቤተ ሰብ ማድረግ መቻሉ (2፥19-22)
   - መ. የእግዚአብሔር ጥበብ በቤተ ክርስቲያን አማካይነት መገለጡ (3፥1-13)
   - ሠ. የእግዚአብሔርን ሙላት በጥልቀ ለመለማመድ የመጸለይ አስፈላጊነት (3፥14-21)
5. የእግዚአብሔርን ዐላማ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለመፈጸም አስፈላጊው ነገር (4፥1-6፥20)
   - ሀ. አንድነት (4፥1-6)
   - ለ. ብስለት (4፥7-16)
   - ሐ. የግል ሕይወትን ማደስ (4፥17-5፥20)
   - መ. በቤተ ሰብ መካከል መኖር የሚገባው ግንኙነት (5፥21-6፥9)
     1. መመሪያው የሚከተሉትን ይመለከታል (5፥21)
     2. ባልና ሚስትን (5፥22-23)
     3. ልጆችንና ወላጆችን (6፥1-4)
     4. ባሮችንና አሳዳሪዎቻቸውን (6፥5-9)
   - ሠ. ለመንፈሳዊ ውጊያ አስፈላጊው ብርታትና ጥንካሬ (6፥10-20)
6. ማጠቃለያ፤ የመሰናበቻ ሰላምታና ቡራኬ (6፥21-24)

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ የክርስቶስ ኢየ
ሱስ ሐዋርያ ከሆነው ከጳውሎስ፤
በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉ፣ ለታመኑ፣[ሀ]
በኤፌሶን[ለ] ለሚገኙ ቅዱሳን፤
2ከእግዚአብሔር ከአባታችን፣ ከጌታም ከኢ
የሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።

## በክርስቶስ የሚገኝ መንፈሳዊ በረከት

3በሰማያዊ ስፍራ፣ በመንፈሳዊ በረከት
ሁሉ በክርስቶስ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ
ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፤ 4በፊቱ
ቅዱሳንና ነውር አልባ እንድንሆን ዓለም
ከመፈጠሩ አስቀድሞ በእርሱ መርጦናልና።
በፍቅር፣ 5በኢየሱስ ክርስቶስ ልጆቹ እን
ሆን ዘንድ፣ እንደ በጎ ፈቃዱ አስቀድሞ
ወሰነን፤ 6ይኸውም፣ በሚወደው በእርሱ
በኩል በነጻ የተሰጠን ክቡር የሆነው ጸጋው
እንዲመሰገን ነው። 7በእርሱም እንደ እግዚ
አብሔር ጸጋ ባለ ጠግነት መጠን፣ በደሙ
በተደረገ ቤዛነት የኀጢአትን ይቅርታ
አገኘን፤ 8ጸጋውንም በጥበብና በማስተዋል
ሁሉ አበዛልን። 9በክርስቶስ ያቀደውንም
የፈቃዱን ምስጢር እንደ በጎ ሐሳቡ እን
ድናውቅ[ሐ] አደረገ። 10በዘመን ፍጻሜ ይሆን
ዘንድ ያለው ሐሳቡ በሰማይም፣ በምድርም
ያሉትን ነገሮች ሁሉ ራስ በሆነው በክርስ
ቶስ ሥር ለመጠቅለል ነው።
11ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት እንደሚ
ሠራው እንደ እርሱ ዕቅድ አስቀድሞ የተወ
ሰነን እኛ ደግሞ በእርሱ ተመርጠናል፣[መ]

1፥1 ሐሥ9፥13፡18፥19 ፡1ቆሮ1፥1፡2ቆሮ1፥1፡ቈላ1፥2
1፥2 ሮሜ1፥7
1፥3 ቍ20፡2ቆሮ1፥3፡ኤፌ2፥6፡3፥10፡16፥12፡1ጴጥ1፥3
1፥4 ዘሌ11፥44፡20፥7፡2ሳሙ22፥24፡መዝ15፥2፡ማቴ25፥34፡ኤፌ4፥2:15:16፡5፥27፡ቈላ1፥22፡2ተሰ2፥13
1፥5 ቍ11፡ሉቃ12፥32፡ሮሜ8፥14:15:29:30፡1ቆሮ1፥21፡ቈላ1፥19
1፥6 ቍ12:14፡ማቴ3፥17
1፥7 ቍ14፡ሮሜ2፥4፡3፥24:25
1፥9 ቍ11፡ ሮሜ16፥25
1፥10 ማር1፥15፡ሮሜ5፥6፡ገላ4፥4፡ ቈላ1፥20
1፥11 ቍ5:9፡ሮሜ8፥28:29:30፡ኤፌ3፥11፡ዕብ6፥17

[ሀ]1 ወይም ለሚያምኑ
[ለ]1 አንዳንድ የጥንት ቅጆች በኤፌሶን ለሚገኙት የሚለው ሐረግ የላቸውም።
[ሐ]8-9 ወይም ጸጋውን አበዛልን በጥበብና በአእምሮ ሁሉ፣ 9 ... አሳወቀን
[መ]11 ወይም ወራሾች ሆነናል

1፥1 *በእግዚአብሔር ፈቃድ፤* ጳውሎስ በአጽንዖት የሚያ ሳየው በእግዚአብሔር ሥር በመሆን ያለውን ሥልጣን ብቻ ሳይ ሆን፣ በዚህ ምዕራፍና በአጠቃላይ በመልእክቱ ውስጥ በእግዚ አብሔር ሉዓላዊ ዕቅድና ዐላማ ላይ የበለጠ ትኩረት እንደሚያ ደርግ ነው። *ሐዋርያ፤* በተለይ በክርስቶስ የተላከ ማለት ነው (የማር 6፥30፤ 1ቆሮ1፥1፤ ዕብ3፥1 ማብ ይመ)። *በኤፌሶን፤* አማራጭ ትር ጕሙን ይመ። መልእክቱ በኤፌሶን የምትገኝን አንድ ቤተ ክርስቲያንን ጨምሮ፣ ለአያሌ አብያተ ክርስቲያናት የተጻፈ ዟሪ ደብዳቤ ነው (የቍ 15፤ 6፥21-23፤ ሐሥ 19፥10 ማብ ይመ)።

1፥2 *ጸጋና ሰላም፤* ምንም እንኳ እነዚህ ቃላት በብዙዎች መንፈሳዊ ባልሆኑ የሰላምታ ደብዳቤዎች ውስጥ በተለምዶ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቢሆንም፣ ቀጥሎ ያሉት ቃላት እንደ ሚያሳዩት ጳውሎስ መንፈሳዊውን ሁኔታ ለማመልከት ተጠ ቅሞበታል።

*1፥3-14፤* ይህ ክፍል በግሪኩ አንድ ወጥ ዐረፍተ ነገር ሲሆን፣ ብዙውን ጊዜ፣ "ውዳሴ" በሚለው አንድ ቃል ተጠቃለሎ ይጠራል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ያደረገውን ነገር መለስ ብሎ የሚያ መለክትና እርሱንም ለማክበር የሚደረገውን አምልኮ የሚያሳይ ነው። በመጀመሪያ ጳውሎስ ከአብ ያገኘነውን (ቍ3)፣ ከዚያ በኋላ በልጁ በኩል የመጣውንና (ቍ4-13ሀ) በመጨረሻም በመን ፈስ ቅዱስ አማካይነት የተሰጠውን በረከት ይናገራል (1፥13ለ-14)።

1፥3 *በሰማያዊ ስፍራ፤* ይህ ሐረግ በኤፌሶን መጽሐፍ ውስጥ አምስት ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን፣ ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ መክበርና (ስለ ትንሣኤውና በእግዚአብሔር ቀኝ ስለ መቀመጡ) ክርስቲያን ከከበረው በክርስቶስ ጋር ስላለው ኅብረት አጽንዖት የሚሰጥ ነው። መሠረታዊ ርእሰ ጕዳዮችንም ያካተተ ሲሆን፣ ይህም ከሰማያዊ መንግሥትና በዚህ መንግሥት ውስጥ ከሚከናወ ነው የመጨረሻ ሐሳቡ ጋር የተያያዘ ነው። ከዚህ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዐላማ (3፥11) የተነሣ፣ በእግዚአብሔርና በብርቱ መንፈሳዊ ኀይላት መካከል የሚካሄድ ግጭት አለ። ይህም በድነት ታሪክ ላይ ያነጣጠረ ዐላማና ተቃርኖ ነው። ጳውሎስ በቍጥር 3 ላይ ክርስቲያኖች ከከበረው ክርስቶስ ጋር ባላቸው ኅብረት በሰ ማያዊ ስፍራ ካለውና ከዚያ ከመጣው መንፈሳዊ በረከት ሁሉ ተጠቃሚዎች መሆናቸውን ይናገራል። በቍ20-22 ላይ ለቤተ ክርስቲያኑ ጥቅም ሲል ሁሉንም ይገዛ ዘንድ ክርስቶስ በዚያ ስፍራ መክበሩንና በሌሎቹም ኀይላትና አለቆች ላይ ከፍ ማለቱን ይገ ልጻል። ክርስቶስ በ2፥6 ላይ እንደ ተጠቀሰው አሕዛብንና አይሁድን በቤተ ክርስቲያን ወደ አንድ አካል በማምጣት፣ የእግዚአብሔርን የጥበቡን ብዛት በሰማያዊ ስፍራ ላሉት፣ "አለቆችና ባለ ሥልጣናት" በድል አድራጊነት አሳያቸው (3፥11)። ስለዚህ አሁን በዚህ ያለው የቅዱሳን መንፈሳዊ ውጊያ፣ በሰማይ ካሉ እግዚአ ብሔርን ከሚቃወሙ ታላላቅ መንፈሳውያን ኀይላት ጋር እንጂ፣ ከሥጋና ከደም ጋር የሚደረግ አይደለም (6፥12)። *በክርስቶስ፤* ይህ ቃል ከቍ3-12 ላይ ብቻ ዐሥራ ሁለት ጊዜ ይገኛል። ይህም ጳውሎስ ብዙ ጊዜ "የክርስቶስ አካል" በማለት የሚመስለውንና ክርስቶስ ከአማኞች ጋር ያለውን መንፈሳዊ ኅብረት የሚያመለ ክት ነው (ለምሳሌ:- ቍ23፤ 2፥16፤ 4፥4:12:16፤ 5፥23:30 ይመ) *የባረከን ... ይባረክ፤* የአይሁድ ሕዝብ፣ "መባረክ" የሚለውን ቃል የሚጠቀሙት እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን በጎነትና እኛ ለእርሱ የምናቀርበውን ምስጋና ወይም ውዳሴ ለመግለጽ ነው። *የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት፤* ኢየሱስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር ያለው ኅብረት ፍጹም የተለየ ነው (ዮሐ20፥17 እና ማብ ይመ)።

1፥4 *ቅዱሳንና ነውር አልባ፤* በ5፥27 ላይ የተጠቀሱትን ተመሳሳይ ጥምር ቃላት ይመልከቱ። ቅድስና የእግዚአብሔር ምርጫ ውጤት እንጂ፣ ለምርጫው መሠረት አይደለም። ቃሉ በክርስቶስ ምክንያት ለአማኙ የተሰጠውንና ከአማኙ ግላዊ የጽድቅ ኑሮ ጋር የተያያዘውን ቅድስና ያመለክታል (የ1ቆሮ 1፥2 ማብ ይመ)። *ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ፤* ዮሐ 17፥24 ይመ። *መርጦናልና፤* በጳውሎስ መልእክታት ውስጥ፣ ምርጫ የሚለው ሐሳብ ያለማቋረጥ የሚጠቀስ ነው (ሮሜ 8፥29-33፤ 9፥6-26፤ 11፥5:7:28፤ 16፥13፤ ቈላ3፥12፤ 1ተሰ1፥4፤ 2ተሰ2፥13፤ ቲቶ1፥1)። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እንደሚከተለው አጽንዖት ተሰጥቶታል፤ (1) "መርጦናልና" (በዚህ ቦታ)፤ (2) "ወሰነን" (ቍ5)፤ (3) "ተመ ርጠናል" (ቍ11)፤ (4) "አስቀድሞ የተወሰነን" (ቍ11)። *በፍቅር፤* ከ3፥17፤ 4፥2:15-16፤ 5፥2 ጋር ያነጻጽሩ።

1፥5 *ልጆቹ እንሆን ዘንድ፤* የሮሜ 8፥23 ማብ ይመ። *ወሰነን፤* እግዚአብሔር በክርስቶስ የሚያምኑ የቤተ ሰቡ አባል እንዲሆኑና ልጁንም እንዲመስሉ አስቀድሞ ወስኖአል (ሮሜ 8፥29 ያነጻጽሩ)። ይህም ምርጫው (ኤፌ1፥4) በፍቅር መሆኑን (ቍ4)፣ በእርሱም ፍጹም መልካም ፈቃድ ላይ መመሥረቱን (ቍ5:9:11)፣ ዐላማው እግዚአብሔርን ለማክበር መሆኑን (ቍ14) የሚያመለክት ሲሆን ነገር ግን የእግዚአብሔርን ውሳኔ የግሉ ለማ ድረግ ግን ሁሉም ሰው ወንጌልን የማመን ግዴታውን የማያስቀር ነው (ቍ13)።

1፥6 *በሚወደው በእርሱ፤* በክርስቶስ ማለት ነው። *እንዲ መሰገን፤* ቍ12 እና 14 ይመ። መመረጥ ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆን ነው።

1፥7 *ቤዛነት፤* ቍ14፤4፥30፤ ሮሜ3፥24፤ ቲቶ2፥14 ይመ። የኤፌሶን ሰዎች በግሪክና በሮማውያን ዘንድ ያለውን የመቤዠት ልምድ ያውቃሉ፤ ይኸውም ባሮች ዎጆ ከፍለው ነጻ ይወጡ የነበረበት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ኀጢአተኞችን ከኀጢአት ባርነትና ከሕግ መርገም ነጻ ለማውጣት የተከፈለው በዚህ ክፍል "በደሙ" ተብሎ የተጠቀሰው የክርስቶስ ሞት ነው (ገላ3፥13 ይመ)። *በደሙ፤* ከ2፥13፤ 1ጴጥ1፥18-19 ጋር ያነጻጽሩ።

1፥9 *ምስጢር፤* የሮሜ11፥25 ፤ ቈላ1፥26 ማብ ይመ።

1፥10 *ራስ በሆነው ... ሥር ለመጠቅለል፤* ጳውሎስ እዚህ ቦታ የተጠቀመው ቃል የሚያመለክተው የመሪነትን ሐሳብ ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎች ብዙ ነገሮችንም የያዘ ነው። ውጥንቅጡ በወጣና ነገሮች ሁሉ ትርጕም ባጡበት በዚህ ዘመን የሚሰጠው ሐሳብ፣ በክርስቶስ መሪነት ሥር ሁሉም ነገር ትርጕም ወዳለው ኅብረት የመድረሻው ጊዜ የብዙዎቻችን ናፍቆት መሆኑን የሚያመለክት ይመስላል።

1፥11 *በእርሱ፤* ክርስቶስ የእግዚአብሔር ዕቅድ ማእከል ነው፤ ፍጥረተ ዓለም ይሁን ወይም አንድ ክርስቲያን፣ ትርጕም ያለው ሊሆን የሚችለው ከክርስቶስ ጋር ካለው ኅብረት አኳያ ብቻ ነው። በመቀጠልም ጳውሎስ የሚናገረው፣ ስለ መላው ዓለም ሳይሆን ለእግዚአብሔር ጥሪ ምላሽ ስለ ሰጡት ነው።

[12]ይኸውም በክርስቶስ ተስፋ በማድረግ የመ
ጀመሪያ የሆንነው እኛ ለክብሩ ምስጋና
እንሆን ዘንድ ነው፡፡ [13]እናንተም ደግሞ የእ
ውነትን ቃል ይህም የድነታችሁን ወንጌል
በሰማችሁ ጊዜ ወደ ክርስቶስ ተጨምራች
ኋል፤ አምናችሁም፣ በእርሱ በመሆን ተስፋ
ሆኖ በተሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ማኅተም
ታትማችኋል፡፡ [14]ለክብሩ ምስጋና ለመሆን
የእግዚአብሔር የሆኑት እስኪዋጁ ድረስ፣
እርሱ ለርስታችን ዋስትና የሚሆን መያዣ
ነው፡፡

## የምስጋናና የልመና ጸሎት

[15]ስለዚህ በጌታ ኢየሱስ ስላላችሁ እም
ነት፣ ለቅዱሳንም ሁሉ ስላላችሁ ፍቅር ከሰ
ማሁበት ጊዜ አንሥቶ፣ [16]በጸሎቴ እያስታ
ወስኋችሁ ስለ እናንተ ምስጋና ማቅረብን
አላቋረጥሁም፡፡ [17]የክብር አባት የሆነውን
የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስምላክ ይበ
ልጥ እንድታውቁት፣ የጥበብና የመገለጥን
መንፈስ እንዲሰጣችሁ ያለማቋረጥ እለም
ናለሁ፡፡ [18]እንዲሁም በእርሱ የተጠራችሁለት
ተስፋ፣ ይህም በቅዱሳኑ ዘንድ ያለውን ክቡር
የሆነውን የርስቱን ባለ ጠግነት ምን እንደ
ሆነ ታውቁ ዘንድ የልባችሁ ዐይኖች እንዲ
በሩ፣ [19]ለእኛ ለምናምነው ከሁሉ በላይ
ታላቅ የሆነውን ኀይሉን እንድታውቁ እጸ
ልያለሁ፡፡ ይህም ኀይል እንደ እርሱ ታላቅ
ብርታት አሠራር፣ [20]ክርስቶስን ከሙታን ሲያ
ስነሣውና በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀ
ምጠው የታየው፣ [21]ከግዛትና ከሥልጣን፣
ከኀይልና ከጌትነት እንዲሁም በአሁኑ ዘመን
ብቻ ሳይሆን በሚመጣውም ዘመን ቢሆን
ሊሰየም ከሚቻለው ስም ሁሉ በላይ ነው፡፡
[22]እግዚአብሔርም ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዛ
ለት፤ በቤተ ክርስቲያንም፣ በማንኛው ነገር
ላይ ራስ አድርጎ ሾመው፡፡ [23]እርሷም ሁሉን
ነገር በሁሉም ረገድ የሚሞላው፣ የእርሱ
ሙላት የሆነች አካሉ ናት፡፡

## በክርስቶስ ሕያው መሆን

2 እናንተ በበደላችሁና በኀጢአታችሁ ምክን
ያት ሙታን ነበራችሁ፤ [2]በዚህም፣ የዓ
ለምን ክፉ መንገድ ተከትላችሁ፣ በአየር
ላይ ላሉት መንፈሳውያን ኀይላት ገዥ ለሆ
ነውና አሁንም ለእግዚአብሔር በማይታዘዙት ሰዎች
ላይ ለሚሠራው መንፈስ እየታዘዛችሁ ትኖሩ
ነበር፡፡ [3]እኛ ሁላችን በአንድ ወቅት የሥጋ
ችንን ምኞትሠ እያረካን፣ መንገዱንም እየተከ

1፥12 ቆላ6፡14
1፥13 ዮሐ14፥16፡ 17፤ሮሜ16፥3፤ኤፌ 4፥21፡30፤ቈላ1፥5
1፥14 ቆላ6፡7፡12፤ ሐሥ20፥32፤ሮሜ 3፥24፤2ቆሮ5፥5
1፥15 ሐሥ20፥21፤ ቆላ1፥4
1፥16 ሮሜ1፥8፡10
1፥17 ዘፀ28፥3፤ኢሳ 11፥2፤ዮሐ20፥17፤ ሮሜ15፥6፤ፊል1፥9፤ ቈላ1፥9፤ራእ1፥6
1፥18 ቆላ7፡11፤ኢዮ 42፥5፤ሮሜ2፥4፤8፥28 ፤2ቆሮ4፥6፤ቈላ1፥12፤ ዕብ6፥4
1፥19 ኢሳ40፥26፤ ኤፌ 3፡7፤6፥10፤ቈላ 1፥29
1፥20 ቆላ3፤ማር 16፥19፤ሐሥ2፡24
1፥21 ማቴ12፥32፤ ኤፌ3፥10፤ፊል2፥9፡ 10፤ቈላ1፥16
1፥22 ማቴ22፥44፤ ፤28፥18፤1ቆሮ11፥3፤ ኤፌ4፥15፤5፥23፤ቈላ 1፥18፤2፥19
1፥23 ዮሐ1፥16፤ 1ቆሮ12፥27፤ኤፌ3፥1 9፤4፥10
2፥1 ቆላ5፤ቈላ2፥13
2፥2 ቆላ3፡11-13፤

ዮሐ12፥31፤ሮሜ11፥30፤12፥2፤1ቆሮ5፥8፤6፥11፤ኤፌ5፥6፤
ቈላ3፥7፤ቲቶ3፥3፤1ጴጥ4፥3 2፥3 ቆላ2፤ገላ5፥24

ሠ3 ወይም የአርጌውን ባሕርይ ፈቃድ

1፥12 *በክርስቶስ ተስፋ በማድረግ የመጀመሪያ የሆንነው እኛ፤* ምናልባት ብዙ አሕዛብ አማኞች ከመሆናቸው በፊት እንደ ጳውሎስ በክርስቶስ ያመኑትን አይሁድ ሊያመለክት ይችላል፡፡

1፥13 *እናንተም ደግሞ፤* አሕዛብ የነበሩትን አብዛኞዎቹን የኤፌሶንን ሰዎች ሊያመለክት ይችላል፡፡ *አምናችሁም፤* የመ ታተሙ ሁኔታ ከማመን ጋር የተያያዘ ነው፡፡ *ማኅተም ታት ማችኋል፤* በዚያን ዘመን ማኅተም ባለ ንብረትነትን ያመለ ክት ነበር፡፡ ማኅተም የሆነው የመንፈስ ቅዱስ መኖር፣ ለአማኝ የድነቱ ማጽኛ ምልክት ነው፡፡

1፥14 *መያዣ፤* የሮሜ 8፥23 ማብ ይመ፡፡

1፥15 *ከሰማሁበት ጊዜ አንሥቶ፤* ጥቂት ዓመታት ከእነርሱ ጋር ከቈየ ሰው ይህን መስማት ትንሽ ግር ይላል፡፡ ቤተክርስቲያኒቱ እጅግ ሰፊ ስለ ሆነች ወይም የኤፌሶን መልእ ክት ለብዙ አብያተ ክርስቲያናት እንዲደረስ ተብሎ የተጻፈ ከሆነ (የቍ1 ማብ ይመ) እርሱ ከጉበኛቸው አካባቢዎች የመጣ ውን ወሬ ሊያመለክት ይችላል፡፡

1፥16 *በጸሎቴ፤* ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች የጸለ የው ጸሎት፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ ላሉ አማኞች ሁሉ ያለ ውን ከፍተኛ ምኞት ያሳያል፡፡

1፥17 *የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክ፤* የቍ3 ማብ ይመ፤ እግዚአብሔር አብን ያመለክታል፡፡

1፥18 *የተጠራችሁለት፤* ፊል 3፥14፤ 2ጢሞ 1፥9፤ ዕብ 3፥1 ይመ፡፡ *ተስፋ፤* ተጨባጭና እውነተኛነት ያለውን ነገር ይዞአል (ሮሜ 8፥25)፡፡ ይህም አሁን በመንፈስ ቅዱስ መያዣነት የተገኘው የዘላለም ሕይወት ማረጋገጫ ነው (ቍ14)፡፡ *በቅዱሳኑ ዘንድ ያለውን ክቡር የሆነውን የርስቱን ባለ ጠግነት፤* ከእግዚ አብሔር የተቀበልነውን ርስት (ቍ14፤ ቈላ 1፥12) ወይም የእግዚ አብሔር ርስት የሆኑትን ቅዱሳንን ያመለክታል፡፡ *በቅዱሳኑ፤* እግዚአብሔር የራሱ ሕዝብ እንዲሆኑ የጠራቸውን ክርስቲያ ኖች ሁሉ ያመለክታል (ቍ1 እና 15 ይመ)፡፡ ቃሉ ለእግዚአብሔር የመሰጠትን ሐሳብ የያዘ ነው፡፡ *የልባችሁ ዐይኖች፤* ሐሳባችሁ፣ ማስተዋላችሁ ወይም መረዳታችሁ ማለት ነው፡፡

*1፥19፤* በዚህ ቍጥር ጳውሎስ በተለያዩ ቃል በአጽንዖት የሚገ ልጸው፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት የተነሣበት አስገራሚ መለኮታዊ ኀይል (ቍ20) በአማኞችም ውስጥና መካከል የሚሠራ መሆኑን ነው፡፡

1፥20 *በቀኙ፤* ታላቅ ክብርንና ሥልጣንን የሚያሳይ ትእ ምርታዊ አቀራረብ ነው፡፡

1፥21 *ከግዛትና ... ሊሰየም ከሚቻለው ስም ሁሉ፤* በእ ርሱ ዘመን የነበሩ ሰዎች ረቂቅ ፍጥረታትን ጨምሮ መላእክት ንና አጋንንት ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ረቂቅ ኀይላት ይኖራሉ ብለው ያምኑ ነበር፤ ክርስቶስ ግን ከእነዚህ ሁሉ በላይ ነው፡፡ *ከግዛትና ከሥልጣን፣ ከኀይልና ከጌትነት* በጊዜው በነበሩት የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን ዘንድ የመላእክትን የተለያዩ ደረጃዎች ያሳያሉ ተብሎ ይታመንም ነበር (ሮሜ8፥38፤ ኤፌ 3፥10፤ 6፥12፤ ቈላ1፥16፤ 2፥10፡15፤ ቲቶ3፥1 ይመ)፡፡ *በአሁኑ ዘመን ... በሚመጣውም ዘመን፤* ጳውሎስ በዘመኑ እንደ ነበሩት የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን፣ ክፉ የሆነውን የአሁኑን ዘመን መሲሑ የራሱን መንግሥት የሚጠቀለልበትን በምድርም ላይ ፍጹ ምና ጽድቅ የነገሠበት ኅብረ ተሰብ ከሚመሠረትበት ከወደ ፊቱ ዘመን ለይቶ ያስቀምጠዋል፡፡

1፥22 *ከእግሩ በታች፤* መዝ 8፥5-6 የሰውን ፍጻሜ በአ ጽንዖት የሚገልጽ ነው፤ ዕብ 2፥6-9 ደግሞ በመጨረሻ የሰው ልጅ የሆነው ክርስቶስ በሁሉም ነገር ላይ ገዥ እንደሚሆን ያሳያል (ከዕብ 10፥13 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ *ራስ፤* ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በነገር ሁሉ ላይ ራስ ነው (የቍ10 ማብ ይ መ)፡፡

1፥23 *የሚሞላው የእርሱ ሙላት፤* ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሙላት ናት ሲል፣ ሁሉንም በሚሞላው በእርሱ እንደ ተሞላች ለማሳየት ይሆናል፡፡ *አካሉ፤* አንድን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን፣ እውነተኛ አማኞችን ሁሉ የምታካትተ ውን ዓለማቀፋዊቷን ቤተ ክርስቲያን ያመለክታል (2፥16፤ 4፥4፡12፡16፤ 5፥23፡30 ይመ)፡፡

*2፥1-10፤* ጳውሎስ በም1 ላይ ሁሉም፣ "ለክብሩ ምስጋና" እንዲሆኑ ክርስቶስም በአጠቃላይ የሁሉም ነገር ራስ መሆኑን በማ መልከት የእግዚአብሔርን ታላቅ ዐላማና ዕቅድ ጽፏል (1፥10፡ 14)፤ አሁን ደግሞ ከእያንዳንዱ ግለሰብ ድነት በመጀመር እግዚ አብሔር ዐላማውን የሚፈጽምበትን መንገድ መግለጹን ይቀጥላል፡፡

*2፥1፤* ከእግዚአብሔር ሕይወት የተለየውን፣ የቀድሞውን ምግባራቸውንና መንፈሳዊ ሁኔታቸውን የሚገልጽ ነው፡፡

2፥2 *ገዥ፤* ሰይጣንን ማለቱ ነው (ዮሐ 14፥30 ያነጻጽሩ፤ ገዥ ይለዋል)፡፡ *በአየር፤* ሰይጣን በምድር ላይ ብቻ የተወሰነ ጠላት አይደለም (6፥12 ያነጻጽሩ)፡፡ *መንፈስ፤* ሰይጣን፣ ሰው ሳይሆን የተለየ ፍጡር ነው (ከኢዮ1፥6፤ ሕዝ28፥15 ያነጻጽሩ፤ የኢሳ 14፥12-15 ማብ ይመ)፡፡

2፥3 *እኛም ሁላችን፤* አይሁድንና አሕዛብን ያመለክታል፡፡ የማንኛውም ሰው መሠረታዊ ተፈጥሮ በኀጢአት የተበከለ ነው፡፡ *የቍጣ ልጆች፤* 'ቅጣት የሚገባቸው' የሚል ትርጓሜን የያዘ ሐረግ ነው (ሮሜ 1፥18-20፤ 2፥5፤ 9፥22 ይመ)፡፡

2፥5 *በክርስቶስ ሕያዋን አደረገን፤* ይህ እውነት በሮሜ

ተልን በመካከላቸው እንኖር ነበር፤ እንደ
ሌሎቹም የቍጣ ልጆች ነበርን። 4ነገር ግን
በምሕረቱ ባለ ጠጋ የሆነ እግዚአብሔር ለእኛ
ካለው ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ፣ 5በበደላችን
ሙታን ሆነን ሳለ፣ በክርስቶስ ሕያዋን አደ
ረገን፤ የዳናችሁት በጸጋ ነው። 6እግዚአብሔርም
ከክርስቶስ ጋር አስነሣን፤ በክርስቶስ ኢየሱስ
በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን፤
7ይኸውም በሚመጣው ዘመን፣ በክርስቶስ
ኢየሱስ በቸርነቱ የገለጠልንን ወደር የሌለ
ውን የጸጋውን ባለ ጠግነት ያሳይ ዘንድ
ነው፤ 8በእምነት፣ በጸጋ ድናችኋልና፤ ይህም
የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ
አይደለም፤ 9ማንም እንዳይመካ በሥራ አይ
ደለም፤ 10ምክንያቱም፣ እግዚአብሔር አስቀ
ድሞ ያዘጋጀልንን መልካም ሥራ እንድንሠራ
በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር
እጅ ሥራዎች ነን።

## በክርስቶስ አንድ መሆን

11ስለዚህ እናንተ ቀድሞ በትውልድ አሕ
ዛብ የሆናችሁ፣ በአካል ላይ በሰው እጅ
ከተደረገው የተነሣ፣ ራሳቸውን "ተገርዘናል"
በሚሉት፣ "ያልተገረዙ" የተባላችሁ ያን አስ
ታውሱ፤ 12በዚያን ዘመን ከክርስቶስ ተለይ
ታችሁ፣ ከእስራኤል ወገንነት ርቃችሁ፣ ለኪ
ዳኑም ተስፋ ባዕዳን ሆናችሁ በዓለም ላይ
ያለ ተስፋና ያለ እግዚአብሔር እንደ ነበራችሁ
አስታውሱ። 13አሁን ግን እናንተ ቀድሞ
ርቃችሁ የነበራችሁ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆና
ችሁ በክርስቶስ ደም አማካይነት ቀርባች
ኋል።

14ሁለቱን አንድ ያደረገ፣ የሚለያየውንም
የጥል ግድግዳ ያፈረሰ ሰላማችን እርሱ ራሱ
ነውና፤ 15ሕግንም ከትእዛዛቱና ከሥርዐቱ
ጋር በሥጋው ሻረ። ዐላማውም ከሁለቱ
አንድን አዲስ ሰው በራሱ ፈጥሮ ሰላምን ለማ
ድረግ ነው። 16ጥልን በገደለበት በመስቀ
ሉም ሁለቱን በዚህ በአንድ አካል ከእግዚ
አብሔር ጋር አስታረቀ። 17መጥቶም ርቃ
ችሁ ለነበራችሁት ለእናንተ፣ ቀርበው
ለነበሩትም ለእነርሱ ሰላምን ሰበከ፤

2፥4 ዮሐ3፥16
2፥5 ቍ1:8፤መዝ 103፥12፤ዮሐ5፥24፤ ሐሥ15፥11
2፥6 ሮሜ6፥5፤ኤፌ 1፥3:20
2፥7 ሮሜ2፥4፤ቲቶ 3፥4
2፥8 ቍ5፤ሮሜ 3፥24፤9፥30
2፥9 ዘዳ9፥5፤ሮሜ 4፥2፤1ቆሮ1፥29፤ 2ጢሞ1፥9፤ቲቶ3፥5
2፥10 ኢሳ29፥23፤ 43፥7፤60፥21፤ ኤፌ 4፥24፤ ቲቶ2፥14
2፥11 ቍ2፤ቈላ 2፥11
2፥12 ኢሳ14፥11 65፥1፤ገላ3፥17፤ 1ተሰ4፥13
2፥13 ቍ2:17፤ ቈላ1፥20
2፥14 ቍ15፤ዮሐ 14፥27፤1ቆሮ12፥13፤ ኤፌ3፥6
2፥15 ገላ3፥28፤ቈላ 1፥21:22፤2፥14
2፥16 2ቆሮ5፥18፤ ቈላ1፥20:22 2፥17 ቍ13፤ኢሳ 57፥19፤መዝ148፥14፤ሉቃ2፥14

6፥1-10 ላይ በሚገባ ተገልጾአል።

2፥6 *በክርስቶስ ኢየሱስ፤* ከክርስቶስ ጋር ባለን ኅብረት ማለት ነው። *በሰማያዊ ስፍራ፤* የ1፥3 ማብ ይመ።

2፥7 *በሚመጣው ዘመን፤* ከ1፥21 ጋር ያነጻጽሩ፤ ምናልባት በክርስቶስ የሚገኘውን የወደፊቱን ዘላለማዊ በረከት ሊያመለክት ይችላል። *ያሳይ ዘንድ፤* ገልጦ ያሳይ ወይም ያረጋግጥ ዘንድ ማለት ነው። አማኞች ለዘላለም የእግዚአብሔርን ጸጋ የሚያንጸባርቁ ይሆናሉ።

*2፥8፤* የእግዚአብሔርን ጸጋ ለማወቅ የሚረዳ ዋና ክፍል ነው፤ ይህም በጎነቱን፣ እንዲያው የሚሰጠውን ሞገሱን እና ይቅርታ አድራጊ ፍቅሩን ያሳያል። *በእምነት፤* ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ኅብረት ለመፍጠር በክርስቶስ ማመን ብቸኛው መንገድ እንደ ሆነ የሚያሳየውን ሮሜ3፥21-31 እና ማብ ይመ ። እምነት፣ ወንጌልን ማወቅና (ሮሜ 10፥14) የመ ልእክቱን እውነት ማመን እንዲሁም አዳኙን ኢየሱስ የግል መድኀኒት አድርጎ መቀበልን የያዘ ነው (ዮሐ 1፥12)። *ድናችኋል፤* ይህ ቃል ሰፋ ያለ ትርጕም አለው። ይህም ኀጢአተኛ በመሆናችን ምክንያት በራሳችን ላይ ካመጣነው ከእግዚአብሔር ቍጣ መዳናችንንም ጭምር ያመለክታል። ይህም የተፈጸመ ድርጊት መሆኑንና አሁንም የመሥራት ኀይል እንዳለው በአጽንዖት ያሳያል። *ከእናንተ አይደለም፤* የትኛውም የሰው ጥረት ለድነታችን አስተዋጽዖ ማድረግ አይችልም፤ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።

2፥9 *ማንም እንዳይመካ፤* ማንም ለመዳኑ ያደረገው አስተዋፅኦ ኖሮ የሚያሰመ ካው ነገር የለም። *በሥራ አይደለም፤* ማንም "ሕግን በመጠበቅ" ድነትን ሊያገኝ አይችልም (ሮሜ 3፥20:28)፤ ምክንያቱም ሰው ሁሉ በመንፈሱ የሞተ፣ የሰይጣን ምርኮኛ፣ የኀጢአትም ባሪያ የሆነና በእግዚአብሔር ቍጣ ሥር የወደቀ ስለ ሆነ ነው። ድነትን ለማግኘት የሚደረገው እንዲህ ያለው ሥርዐታዊ አቀራረብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተቀባይነት እንደሌለው ተገልጾአል።

2፥10 *አስቀድሞ ያዘጋጀልንን፤* በም1 የታየውን የእግዚአብሔርን ለዐላዊ ዐላማና ዕቅድ የሚያንጸባርቅ ዐቢይ ሐሳብ ነው። *እጅ ሥራዎች፤* የግሪኩ ቃል አንዳንድ ጊዜ፣ "የጥበብ ሥራ" የሚል ሐሳብ የያዘ ነው።

*2፥11-22፤* ጳውሎስ ከግለሰብ ድነት በመጀመር፣ ከእግዚአብሔር ጋር ቀድሞ ጠበኞች የነበሩትን ሕዝቦች ማለትም አሕዛብንና አይሁድን ከራሱ ጋር ብቻ ሳይሆን እርስ በርሳቸውንም በክርስቶስ ወዳስታረቀበት ወደ ሌላኛው የድነት ገጽታ ይሄዳል (ቍ11-16)። ይህም ብቻ ሳይሆን በቍጥር 19-22 እንደ ተገለ ጸውና በም 3 ውስጥ እንደ ተብራራው፣ እግዚአብሔር አሁን የታረቁትን እነዚህን ሕዝቦች በአንድ አካል አዋሕዶአቸዋል።

2፥11 *ስለዚህ፤* በቍጥር 1-10 ላይ ከክርስቶስ ውጭ ያሉ ሰዎች ያሉበትን ሁኔታ ያመለክታል። *እናንተ ... አሕዛብ የሆናችሁ፤* አብዛኞዎቹን የኤፌሶን ሰዎችን ያሳያል (በ 1፥13 ላይ "እናንተም ቀድሞ" ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ)። *"ተገርዘናል" ... "ያልተገረዙ"፤* ወንድ የሆኑ አይሁድ ሕፃናት ሁሉ መገረዝ ይገባቸው ነበር፤ ስለዚህ፣ "በሰው እጅ" በተደረገው ግርዘት የአይሁድ ሕዝብ የሚኰራሩበት ይህ ሥርዐት በአይሁድና በአሕዛብ መካከል የነበረውን ልዩነት በግልጽ የሚያሳይ ነው።

*2፥12፤ በዚያን ዘመን፤* በቍ13 "አሁን ግን" ከሚለው ጋር ሲነጻጸር የድነት ሥራ ከመሠራቱ በፊት ያለውን ጊዜ ያሳያል። *ከክርስቶስ ተለይታችሁ፣ ... ያለ እግዚአብሔር፤* እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚያሳዩት ያላመኑ አሕዛብ ከእስራኤልና ከክርስቶስ ምን ያህል ርቀው እንደ ነበር ነው። *ለኪዳኑም፤* እግዚአብሔር ለራሳቸው ለአይሁድ ሕዝብ እንዲሁም በእነርሱ አማካይነት ለሌሎች በረከትን እንደሚሰጥ የገባውን ቃል ያሳያል (የሮሜ 9፥4 ማብ ይመ)።

2፥13 *አሁን ግን፤* "በዚያን ዘመን" (ቍ12) ከሚለው ጋር የሚነጻጸር ብቻ ሳይሆን፣ "ከክርስቶስ" እና "በክርስቶስ" በሚሉት ቃላት መካከል ያለውንም ንጽጽር ያሳያል። *በክርስቶስ ደም፤* ደሙን ለእኛ እንደ መሥዋዕት ያፈሰሰበትን የክርስቶስን ሥቃይና ሞት ይገልጻል (1፥7)። *ቀርባችኋል፤* ወደ እግዚአብሔር ማለት ነው።

2፥14 *ሁለቱን፤* አማኝ የሆኑትን አይሁድንና አማኝ የሆኑትን አሕዛብን ያመለክታል። *የሚለያየውንም ... ግድግዳ፤* በአይሁድና በአሕዛብን መካከል የነበረው የሃይማኖት ልዩነት ያስከተለውን መለያየት ግልጽ በሆነ ሁኔታ የሚያሳይ አባባል ነው። ይህም በተለይ በቤተ መቅደስ ውስጥ የነበረውን የአይሁድን አደባባይና የአሕዛብን አደባባይ የሚለየውን ግድግዳ ይገልጻል፤ ይህንን ግድግዳ አልፎ በሚሄድ የአሕዛብ ወገን ላይ የሞት ቅጣት እንደሚፈጸም የሚያሳይ ጽሑፍ በግድግዳው ላይ ተጽፎ ነበር። *የጥል፤* በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ያለውን መለያየት ያመለክታል።

2፥15 *ሕግንም፣ ... ሻረ፤* በማቴ 5፥17 እና በሮሜ 3፥31 ላይ የተጠቀሰው ሐሳብ በብሉይ ኪዳን የተገለጠው ሕግ የእግዚአብሔር ቅዱስ ባሕርይ ስለ ሆነ በክርስቶስ መምጣት አልተቀየረም፤ በዚህ ክፍል እንደ ተሻረ የተገለጸው አይሁድን ከአሕዛብ የሚለየውና አሕዛብንም እንደ ርኵስ የሚቈጥረውን፣ "ትእዛዝና ደንብ" ሊሆን ይችላል። *በሥጋው፤* ምናልባት የክርስቶስን ሞት ያሳያል። *አንድን አዲስ ሰው፤* አንድ አካል የሆነውን የአማኞችን ኅብረት፣ ማለትም ቤተ ክርስቲያንን ያመለክታል።

2፥16 *በዚህ በአንድ አካል፤* በቍጥር 15 ላይ፣ "በሥጋው" የሚለውን በመንተራስ፣ በመስቀል ላይ የተሠዋውን የክርስቶስን አካል (በቍ15 ላይ "በሥጋው" ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ) ሊያመለክት ቢችልም፣ ቀደም ብሎ የአማኞች አካል የተባለውን፣ "አንድን አዲስ ሰው" በመባል የተጠቀሰውን ሊያሳይ ይችላል።

2፥17 *ርቃችሁ ... ቀርበው፤* በቃሉ ቅደም ተከተል መሠረት አሕዛብንና አይሁድን በተከታታይ ያመለክታል።

2፥18 *ወደ አብ መቅረብ፤* ወደ አብ የመቅረብ ዕድሉ የተገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩልና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው። ይህም በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ እግዚአብሔር አብ እንደ

18ሁላችንም በእርሱ አማካይነት በአንዱ
መንፈስ ወደ አብ መቅረብ እንችላለንና።
19ከዚህ የተነሣ እናንተ ከቅዱሳን ጋር የአ
ንድ አገር ዜጋ፣ የእግዚአብሔርም ቤተ ሰብ
አባል ናችሁ እንጂ ከእንግዲህ ወዲህ መጻ
ተኞችና እንግዶች አይደላችሁም። 20በሐዋ
ርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፤
የማእዘኑ ራስ ድንጋይም ክርስቶስ ኢየሱስ
ራሱ ነው፤ 21በእርሱ ሕንጻ ሁሉ አንድ ላይ
ተገጣጥሞ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ
እንዲሆን ያድጋል። 22እናንተም ደግሞ እግ
ዚአብሔር በመንፈሱ የሚኖርበት ማደሪያ ትሆኑ
ዘንድ አብራችሁ እየተገነባችሁ ነው።

## ለአሕዛብ ሐዋርያ የሆነው ጳውሎስ

3በዚህም ምክንያት እኔ ጳውሎስ ለእና
ንተ ለአሕዛብ የክርስቶስ ኢየሱስ እስ
ረኛ ሆኛለሁ።
2ለእናንተ ጥቅም ሲባል ስለ ተሰጠኝ የእ
ግዚአብሔር ጸጋ መጋቢነት በእርግጥ ሰምታ
ችኋል፤ 3ቀደም ሲል በአጭሩ እንደ ጻፍ
ሁት፣ በመገለጥ እንዳውቀው የተደረገው
ምስጢር ይህ ነው። 4እንግዲህ ይህን ስታ
ነቡ፣ የክርስቶስን ምስጢር እንዴት እንደ
ማስተውል ለመረዳት ትችላላችሁ። 5ይህም
ምስጢር አሁን ለቅዱሳኑ ሐዋርያትና ነቢ
ያት የተገለጠውን ያህል፣ ባለፉት ዘመናት
ለነበሩ ሰዎች አልተገለጠም ነበር። 6ይህም
ምስጢር አሕዛብ በወንጌል አማካይነት
ከእስራኤል ጋር አብረው ወራሾች፣ አብረው
የአንዱ አካል ብልቶች እንዲሁም በክርስቶስ
ኢየሱስ በሆነው ተስፋ አብረው ተካፋይ መሆ
ናቸው ነው።
7እኔም በኀይሉ አሠራር በተሰጠኝ በእግዚ
አብሔር የጸጋ ስጦታ የዚህ ወንጌል አገል
ጋይ ሆኛለሁ። 8ምንም እንኳ ከቅዱሳን ሁሉ

2፥18 1ቆሮ12፥13፤ ኤፌ3፥12፤4፥4፤ ቈላ1፥12
2፥19 ቍ12፤ ገላ6፥10፤ፊል3፥20
2፥2 ማቴ16፥18፤ ሐሥ4፥11፤1ቆሮ3፥9፡10፡11፤ኤፌ4፥11፤ 1ጴጥ2፥4-8፤ ራእ21፥14
2፥21 1ቆሮ3፥16፡17
2፥22 1ቆሮ3፥16
3፥1 ሐሥ23፥18፤ ኤፌ4፥1፤2ጢሞ1፥8፤ ፊሞ1፡9
3፥2 ቈላ1፥25
3፥3 ሮሜ16፥25፤ 1ቆሮ2፥10
3፥4 2ቆሮ11፥6
3፥5 ሮሜ16፥26፤ ኤፌ4፥11
3፥6 ሕዝ47፥22፤ ሮሜ8፥17፤ ኤፌ2፥15፡16
3፥7 ሮሜ12፥3፤ 1ቆሮ 3፥5፤ኤፌ1፥19 ፤ቈላ1፥29
3፥8 ሐሥ9፥15፤ ሮሜ2፥4፤1ቆሮ15፥9

ሚቀበላቸውና እንደሚወዳቸው፣ እርግጠኞች ሆነውም ወደ እርሱ የመቅረብ ነጻነትና መብት እንዳላቸው የሚያመለክት ነው።

2፥19 *ከዚህ የተነሣ፤* ጳውሎስ በቍጥር 19፥22 ላይ የገለጸው ኅብረት፣ በቍጥር 14-18 ላይ እንደ ተጠቀሰው ክርስቶስ በሞቱ በሠራው ሥራ ላይ የተመሠረተ ነው። *እናንተ፤* በተለይ በኤፌሶን ያሉ አሕዛብ በጳውሎስ ሐሳብ ውስጥ እንዳሉ ይህ ክፍል ያሳያል። *የአንድ አገር ዜጋ፣ ... ቤተ ሰብ፤* ተቀራራቢ የሆኑ ሥዕላዊ መግለጫዎች ናቸው። በጥንት ጊዜ ቤተ ሰው የሚባለው፣ በዛሬ ዘመን አጎትንና አክስትን ከነቤተ ሰባቸው የቅርብ ዘመድ አድርጉ የሚያጠቃልለውንና ከመደበኛው ቤተ ሰብ ሰፋ ያለ ቤተ ሰባዊ መዋቅርን ነው።

*2፥20-21፤* ቤተ ክርስቲያን እንደ ቤተ መቅደስ በተመሰለችበት ሁኔታ፣ ክርስቶስ ዋና የማእዘን ራስ ድንጋይ፣ ሐዋርያትና የአዲስ ኪዳን ነቢያት መሠረት፣ እያንዳንዱ ክርስቲያን ደግሞ ሕንጻው የታነጸበት ድንጋይ ሆነው ቀርበዋል (1ጴጥ 2፥4-8)። ጳውሎስ በ1ቆሮ 3፥11 ላይ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ብቸኛ መሠረት እንደ ሆነ ገልጾአል።

2፥20 *መሠረት፤* በአንድ ላይ ተዋቅሮ የተገነባ ጠንካራ ሥራን የሚያሳይ ዘይቤአዊ አገላለጽ ነው። *ሐዋርያትና ነቢያት፤* የእግዚአብሔርን ቃል በመስበክና በማስተማር መሠረት የጣሉትን ቀደምት ክርስቲያን ሐዋርያትንና ነቢያትን ሊያመለክት ይችላል (1ቆሮ 3፥10-11)። *የማእዘኑ ራስ ድንጋይም፤* በሰብዓ ሊቃናት ውስጥ ኢሳ 28፥16 ላይ ተመሳሳይ ቃል የተጠቀሰ ሲሆን፣ ማእዘኑ "በተፈተነ" ድንጋይ የተሠራ መሠረትን ያመለክታል። ይህም ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ልትሆን የምትችለው፤ እንከን በሌለው የክርስቶስ መንፈስ ለመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት በተሰጠው መገለጥ ላይ ስትመሠረት ነው።

2፥21 *አንድ ላይ ተገጣጥሞ፤* በ4፥16 ላይ ከተጠቀሰው ተመሳሳይ ቃል ጋር ያነጻጽሩ፤ ሁለቱም ክፍሎች በአማኞች መካከል ስላለው የጠበቀ ኅብረት ይናገራሉ። *ያድጋል፤* በመገንባት ላይ ስላለው ሕንጻ የተሰጠው ገለጻ የቤተ ክርስቲያንን ፈጣን እድገት የሚያሳይ ነው። *ቅዱስ ቤተ መቅደስ፤* አሁን ደግሞ ጳውሎስ፣ "ቤተ መቅደስ" የሚለውን ዘይቤአዊ አገላለጽ ይጠቀማል፤ ይህም እግዚአብሔር የእርሱ የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን የመሠረተበትን ዐላማ የሚያመለክት ነው።

2፥22 *ማደሪያ፤* ቤተ ክርስቲያን፣ መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ሰዎች ወይም ማኅበረ ሰብ ናት።

*3፥1-13፤* እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው በጸጋው በማዳን (2፥1-10)፣ በክርስቶስ የመሥዋዕትነት ሞት ከራሱና ከሌላው ጋር ካስታረቀ በኋላ (2፥11-12)፣ በአንድ አካል ማለትም በቤተ ክርስቲያን በእኩልነት አሁን አዋሕዶአቸዋል። በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ ያለው ይህ ሐሳብ በቀደሙት ዘመናት ሙሉ በሙሉ አልተገለጠም ነበር፤ ጳውሎስም ይህን፣ "ምስጢር" ይለዋል።

3፥1 *በዚህም ምክንያት፤* ከዚህ በፊት ባሉት ብዙ ቍጥሮች እንደተገለጸው፣ እግዚአብሔር በሠራው ሥራ ሁሉ ምክንያት ማለት ነው። *እስረኛ፤* በዚህ ጊዜ ጳውሎስ የቁም እስረኛ የነበረ ይመስላል (ሐሥ 28፥16፡30)። *የክርስቶስ፤* ጳውሎስ ሊታሰር የቻለው ክርስቶስን በመታዘዙ ነው። ከዚህ ቍጥር በኋላ ጳውሎስ "ምስጢር" የሆነውን ነገር ወደ ማብራራት ይሄዳል (ቍ4)፤ በቍ 14 ላይ ካቆመበት ሐሳብ እንደ ገና ይቀጥላል።

3፥2 *መጋቢነት፤* ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያንና ለፍጥረተ ዓለም ያለውን ዕቅድ ይገልጻል (1፥3-12 ይመ)፤ ይህንንም ዕቅድ ለማስፈጸም የተለየ ኀላፊነት ተሰጥቶታል። የአሕዛብ ሐዋርያ እንደ መሆኑ መጠን፣ የእግዚአብሔርን የጸጋ መልእክት እንዲናገር ዐደራ አለበት (ገላ 2፥7)። *በርግጥ ሰምታችኋል፤* ጳውሎስ ከዚህ ቀደም በኤፌሶን ለረጅም ጊዜ ቈይታ ስላደረገ ስለ አገለግሎቱ አብዛኛዎቹ የኤፌሶን ክርስቲያኖች ሰምተው ይሆናል፤ ሆኖም ይህ መልእክት በየስፍራው እንዲላክ የተጻፈ ከሆነ በሌላ ቦታ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ስለ አገልግሎቱ ላይሰሙ ይችላሉ።

3፥3 *ቀደም ሲል በአጭሩ እንደ ጻፍሁት፤* ከ1፥9-10 ያለውን ሐሳብ ያመለክት ይሆናል። *ምስጢር፤* በመለኮታዊ መገለጥ ብቻ ሊታወቅ የሚችል እውነት ነው (ቍ5፤ ሮሜ16፥25 ይመ፤ እንዲሁም የሮሜ 11፥25፤ የቈላ 1፥26 ማብ ይመ)። እዚህ ቦታ፣ "ምስጢር" የሚለው ቃል አማኝ የሆኑትን አይሁድንና አሕዛብን በአንድ አካል ማለትም በቤተ ክርስቲያን ያዋሐደውንና በጥበብ የተሞላውን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ያሳያል (ቍ6)። ለጊዜው የተደበቀ ምስጢር እንደ ሆነ ቢታሰብም፣ ከዚያ በላይ እግዚአብሔር የሚሠራው ቀስ በቀስም የሚገለጥ ዕቅድ ነው (ከ1፥9-10፤ ራእ10፥7 ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥4 *የክርስቶስን ምስጢር፤* ለዘመናት ተሰውሮ የነበረውን (ቍ9) አሁን ግን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለሐዋርያትና ለነቢያት የተገለጠውን ምስጢር ጳውሎስ ይናገራል (ቍ5)። ምስጢሩም በ1፥10 ላይ እንደ ተገለጠው በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው። ከአይሁድና ከአሕዛብ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ አዲስ ሕዝብ ለራሱ ፈጥሮአል (1፥4-6፤ 2፥16)።

3፥5 *ቅዱሳን፤* ለእግዚአብሔር አገልግሎት መለየትን ያመለክታል። *ሐዋርያትና ነቢያት፤* የ2፥20 ማብ ይመ። ጳውሎስ ምንም እንኳ የተገለጠው ምስጢር ዋና ተቀባይ ቢሆንም ለሌሎቹም ደግሞ ይህ ተገልጦላቸዋል። *ባለፉት ዘመናት ለነበሩ ሰዎች አልተገለጠም፤* የቍ6 ማብ ይመ።

3፥6 *አብረው ... አብረው... አብረው፤* የቃሉ መደጋገም ቀድሞ ያልታወቀውን ምስጢር የተለየ ገጽታ ያሳያል፤ ይኸውም በአንዱ አካል በቤተ ክርስቲያን፣ አሕዛብ ከአይሁድ ጋር ያላቸውን እኩልነትና መደጋገፍ ያመለክታል። የአሕዛብ ወደ እስራኤል አምላክ መመለስና መዳን፣ በብሉይ ኪዳን አስቀድሞ ተነግሮአል (ሮሜ 15፥9-12)፤ አሕዛብ በክርስቶስ ከሚያምኑ አይሁድ ጋር አንድ በሆነ መሠረት ላይ ሕያው የሆነ ኅብረት ይኖራቸዋል የሚል ግምት አልነበረም። *አብረው ወራሾች፤* የ1፥18 ማብ ይመ።

3፥8 *ከ ... ሁሉ ያነስሁ ብሆንም፤* ከ1ጢሞ 1፥15 ጋር ያነጻጽሩ። ጳውሎስ አሁንም ራሱን ዝቅ አድርጎ በመቍጠር እጅግ ታላቅ ለሆነ አገልግሎት መመረጡን በመገረም ይጽፋል። ምንም እንኳ ስለ ራሱ በሰጠው ግምገማ ብዙዎቻችን ባንስማማም ትሕትናው ግን እውነተኛ ነበር። *የማይመረመረውን፤* እኛ ልናውቀው ከምንችለው በላይ ቢሆንም በጥቂቱም እንኳ ለማድ

ያነስሁ ብሆንም፣ የማይመረመረውን የክር
ስቶስን ባለጠግነት ለአሕዛብ እሰብክ ዘንድ
ይህ ጸጋ ለእኔ ተሰጠኝ። 9እንዲሁም ሁሉን
በፈጠረ በእግዚአብሔር ላለፉት ዘመናት የተሰ
ወረውን የዚህን ምስጢር አሠራር ለሁ
ሉም እገልጥ ዘንድ ተሰጠኝ። 10አሳቡም በአ
ሁኑ ዘመን በቤተ ክርስቲያን አማካይነት
ብዙ ገጽታ ያለው የእግዚአብሔር ጥበብ በሰማ
ያዊ ስፍራ ላሉት አለቆችና ባለ ሥልጣናት
ይታወቅ ዘንድ ነው፤ 11ይህም በክርስቶስ ኢየ
ሱስ በጌታችን በፈጸመው ዘላለማዊ ዕቅዱ
መሠረት ነው። 12በእርሱና በእርሱ ላይ ባለን
እምነት አማካይነት በነጻነትና በልበ ሙሉ
ነት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንችላለን።
13ስለዚህ ክብራችሁ በሆነው ስለ እናንተ
በደረሰብኝ መከራ ተስፋ እንዳትቈርጡ ዐደራ
እላችኋለሁ።

## ለኤፌሶን ክርስቲያኖች የተደረገ ጸሎት

14በዚህም ምክንያት በአብ ፊት እንበረከ
ካለሁ፤ 15ከእርሱም በሰማይና በምድር ያለ
ቤተ ሰብ ሁሉ ስያሜ[ሀ] ያገኛል። 16በውስጥ
ሰውነታችሁ እንድትጠነክሩ፣ ከክብሩ ባለጠ
ግነት በመንፈሱ በኩል ኀይል እንዲሰጣችሁ
እጸልያለሁ፤ 17ይኸውም በእምነት ክርስቶስ
በልባችሁ እንዲያድር ነው። ደግሞም ሥር
ሰዳችሁ፣ በፍቅር ታንጻችሁ፣ 18የክርስቶስ
ፍቅር ስፋቱ፣ ርዝመቱ፣ ከፍታውና ጥልቀቱ
ምን ያህል እንደ ሆነ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር
የመገንዘብ ኀይልን እንድታገኙ ነው። 19እስከ
እግዚአብሔር ሙላት ሁሉ ልክ ደርሳችሁ እን
ድትሞሉ፣ ከመታወቅ በላይ የሆነውን የክር
ስቶስን ፍቅር ታውቁም ዘንድ ነው።
20እንግዲህ በእኛ ውስጥ እንደሚሠራው
እንደ ኀይሉ መጠን፣ ከምንለምነው ወይም
ከምናስበው ሁሉ በላይ እጅግ አብልጦ ማድረግ
ለሚቻለው፣ 21በቤተ ክርስቲያን እንዲሁም
በክርስቶስ ኢየሱስ፣ በዘመናት ሁሉ ከዘላለም
እስከ ዘላለም ለእርሱ ክብር ይሁን፤ አሜን።

## በክርስቶስ አካል ያለ አንድነት

4 እንግዲህ በጌታ እስረኛ የሆንሁ እኔ፣
ለተቀበላችሁት ጥሪ የሚገባ ኑሮ ትኖሩ
ዘንድ እለምናችኋለሁ። 2ፍጹም ትሑታንና
ገሮች ሁኑ፤ እርስ በርሳችሁም በፍቅር እየተ
ቻቻላችሁ ትዕግሥተኞች ሁኑ። 3በሰላም
ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ።
4በተጠራችሁ ጊዜ ወደ አንድ ተስፋ እንደ
ተጠራችሁ ሁሉ አንድ አካልና አንድ መን
ፈስ አለ፤ 5አንድ ጌታ፣ አንድ እምነትና
አንድ ጥምቀት አለ፤ 6ከሁሉም በላይ የሆነ፣

3፥9 ሮሜ16፥25
3፥10 ሮሜ11፥33፤ 1ቆሮ2፥7፤ኤፌ1፥3:2 1፥6፥12፤ቈላ2፥10:1 5፤1ጴጥ1፥12
3፥11 ኤፌ1፥11
3፥12 2ቆሮ3፥4፤ ኤፌ2፥18፤ዕብ3፥14 ፤4፥16፤10፥19:35፤1 ዮሐ2:28፤3፥21፤4፥17
3፥14 ፊል2፥10
3፥16 ቍ፥8፤ሮሜ 2፥4፤7፥22፤ፊል4፥13
3፥17 ሮሜ8፥10፤ ቈላ2፥7
3፥18 ኢዮ11፥8:9፤ መዝ103፥11፤ኤፌ1፥15
3፥19 ኤፌ1፥23፤ ፊል4፥7፤ቈላ2፥10
3፥20 ቍ፥7፤1ነገ 3፥13፤ሮሜ16፥25፤ 2ቆሮ9፥8
3፥21 ሮሜ11፥36
4፥1 ሮሜ8፥28፤ ኤፌ 3፥1፤ፊል1፥27 ፤ቈላ1፥10፤1ተሰ2፥12
4፥2 ቍ፥15:16፤ኤፌ 1፥4፤ቈላ3፥12:13
4፥3 ሮሜ15፥5፤ቈላ 3፥15
4፥4 ሮሜ8፥28፤ 12፥5፤1ቆሮ12፥13፤ ኤፌ2፥18
4፥5 1ቆሮ8፥6

[ሀ]15 ወይም *አባትነት ሁሉ*

ነቅ ከማስተዋላችን ውጭ አይሆንም (ከሮሜ 11፥33 ጋር ያነጻጽሩ)። *እሰብክ ዘንድ፤* የቃሉ ቀጥተኛ ትርጒም "ወንጌልን መስበክ" ሲሆን፣ 'መግለጥ' ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው (ቍ9)። *ጸጋ፤* እዚህ ቦታ ላይ፣ ወደ ኀላፊነት የሚያመጣውን ልዩ ስጦታ ያመለክታል።

3፥10 *በአሁኑ፤* በቍ9 "ላለፉት ዘመናት" ከሚለው ጋር ተነጻጽሮ የቀረበ ነው። *በቤተ ክርስቲያን አማካይነት፤* ፍጹም የማይቻል የሚመስለው እግዚአብሔር የሠራው ሥራ ቤተ ክርስቲያንን የአይሁድና የአሕዛብ ሕያው ኅብረት መሠረት እና የእግዚአብሔር ጥበብ ፍጹም መገለጫ አድርጎአታል። *ብዙ ገጽታ፤* አልማዝ በተለያየ አንጻር ያለው ገጽታ ውበቱ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ይህም የተለያየ ገጽታ ያለውን የእግዚአብሔርን ጥበብ ያሳያል። *በሰማያዊ ስፍራ፤* የ1፥3 ማብ ይመ። *አለቆችና ባለ ሥልጣናት፤* ክርስቶስ ከእነዚህ ሁሉ በላይ ከፍ ከፍ ብሎአል (1፥20-21)። ለዚህ ክፍል የሚሰጡ ሁለት ትርጓሜዎች አሉ፤ የመጀመሪያው መልካም የሆኑትን መላእክት የሚያመለክት ሲሆን፣ እነዚህም እግዚአብ ሔር በቤተ ክርስቲያን በኩል የሚገልጠውን አስደናቂ ጥበቡን የሚያዩ ሊሆኑ ይችላሉ (ከቈላ 1፥16 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ሁለተኛው ደግሞ በጨለማው ዓለም በሰማያዊው ስፍራ ያሉትን መላእክት ሊያመለክት ይችላል (6፥12፤ዳን 10፥13:20-21)።

3፥11 *ዘላለማዊ ዕቅዱ፤* ክርስቶስ አንድ በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ላይ የበላይ (ራስ) መሆኑ ፍጥረተ ዓለምን ለመጠቅለል የሚኖረውን የበላይነት የሚያረጋግጥ ነው (1፥10)።

*3፥14-21፤* እግዚአብሔር በአማኞች ሕይወት እየሠራ ያለውን ነገር በሚመለከት ጳውሎስ ከልቡ ሆኖ እንደሚጸልይ ይገልጻል። የእግዚአብሔር ዋና ስጦታዎች "ኀይል" (ቍ16:18፡ 20) እና "ፍቅር" ናቸው (ቍ17-19)

3፥14 *በዚህም ምክንያት፤* ከቍጥር 1 የቀጠለ ሐሳብ ነው። *እንበረከካለሁ፤* ጳውሎስ በነበረበት ዘመን ሰዎች የሚጸልዩት ቆመው ስለ ነበር፣ ቃሉ ጥልቅ የሆነ ስሜትንና ጥልቅ አክብሮትን ያመለክታል።

3፥15 *ቤተ ሰብ፤* በግሪኩ ይህ ቃል፣ "አባት" ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይነት አለው (አማራጭ ትርጒሙን ይመ)፤ እንዲህ ከሆነ፣ "ቤተ ሰብ" የሚለው ስም አመጣጡ፣ "አባት" ከሚለው ቃል ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር አባታችን ስለ ሆነ፣ እኛም ጸሎታችንን በመታመን ወደ እርሱ ማቅረብ እንችላለን።

3፥17 *በልባችሁ፤* መላውን የውስጥ ማንነታችንን ያመለክታል። *እንዲያድር፤* ሙሉ በሙሉ በቤት ውስጥ መሆንን ያሳያል። ክርስቶስ በኤፌሶን ክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ እንደ ነበረ ያመለክታል (ከሮሜ 8፥9 ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥19 *ሙላት፤* በማንኛውም ረገድ ሙሉ የሆነው እግዚአብሔር ወደ ፍቅሩ ታላቅነት እንድንደርስ ፈቃደኛ መሆኑን ያሳያል። *ከመታወቅ በላይ የሆነውን፤* ከቶ የማይታወቅ ሳይሆን፣ እጅግ ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ ሙሉ ለሙሉ ለማወቅ የማይቻል መሆኑን ያመለክታል።

3፥20 *ኀይሉ፤* 1፥19-21 ይመ። *ከምናስበው ሁሉ በላይ፤* በተወሰነ ደረጃ በዚህ ክፍል ከተጠቀሱት ጒዳዮች ጋር የሚገናኝ ቢሆንም፣ በእነዚህ ብቻ የተ ወሰነ አይደለም።

3፥21 *በቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በክርስቶስ ኢየሱስ፤* አስደናቂ ንጽጽር ነው። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን እጅግ ለተለየ ክብርና ተግባር ጠርቶአታል (ከቍ10፤4፥1 ጋር ያነጻጽሩ)። *ለእርሱ ክብር ይሁን፤* በሕይወት የመኖራችን ዋና ዐላማ ነው (1፥6 እና ማብ ይመ)።

*4፥1-32፤* ይህ ምዕራፍ ጀምሮ የሚጨርሰው፣ እርስ በርስ እንዋደድ ይቅርም እንባባል በሚል ምክር ነው።

*4፥1-16፤* እስካሁን ድረስ ጳውሎስ ያስተማረው፣ እግዚአብሔር አይሁድንና አሕዛብን በቤተ ክርስቲያን አዲስ ወደ ሆነ ኅብረት እንዳመጣና ቤተ ክርስቲያንንም ጥበቡን ሊገልጥባት እንደ ጠራት ነው። አሁን ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ላሉት በአንድነት የሚኖሩበትንና የሚሠሩበትን እንዲሁም በአንድ ላይ ወደ ፍጹምነት የሚያድጉበትን ጸጋ እግዚአብሔር እንዴት እንዳ ዘጋጀ ያሳያል።

4፥1 *እስረኛ፤* የ3፥1 ማብ ይመ። *ጥሪ፤* 3፥10:21 እና ማብ ይመ።

4፥3 *አንድነት ለመጠበቅ፤* ይህ የተገኘው እግዚአብሔር በክርስቶስ ሞት ባደረገው ዕርቅ ነው (2፥14-22 ይመ)። ይህ ኅብረት እንዳይበላሽ ይጠብቁት ዘንድ ክርስቲያኖች ከባድ ኀላፊነት ተሰጥቶአቸዋል። ይህ የመንፈስ አንድነት በሰዎች የሚፈጠር አይደለም፤ ነገር ግን ጳውሎስ በም1-3 እንደ ተጠቀሰው እውነትን ባመኑና ክርስቶስን በተቀበሉት ዘንድ ቀድሞውኑ የነበረ ነው።

4፥4 *አንድ ተስፋ፤* ብዙ ገጽታዎች ቢኖሩትም (ለምሳሌ 1፥5:10፤ 2፥7)፣ ተስፋው ግን አሁንም አንድ ነው፤ ይህም አማኞች ሁሉ ከሚካፈሉት ወደ ፊት ከሚመጣው ከክርስቶስ ታላቅ ክብር ጋር የተቈራኘ ነው።

4፥5 *አንድ ጥምቀት፤* በውስጥ ሰውነት የሚካሄደውንና የማይታየውን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን ሳይሆን (1ቆሮ 12፥13)፣ የውሃ ጥምቀትን የሚያመለክት ነው (የሮሜ6፥3-4 ማብ ይመ)። ጳውሎስ በልቡ የአማኞችን የአንድነት ስሜት የሚገልጽ ሐሳብ ስለያዘ፣ ሊያመለክት የፈለገው እያንዳንዱ አዲስ አማኝ በግልጽ የሚፈጽመውን የቤተ ክርስቲያንን ሥርዐት ነው። የውሃ ጥምቀት

በሁሉም የሚሠራ፣ በሁሉ የሚኖር የሁሉም
አባት የሆነ አንድ አምላክ አለ።
7 ነገር ግን ክርስቶስ በወሰነው መጠን ለእ
ያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጥቶናል። 8 ስለዚህም
እንዲህ ይላል፤

“ወደ ላይ በወጣ ጊዜ፣
ምርኮ ማረከ፤
ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ።”

9 ታዲያ፣ “ወደ ላይ ወጣ” ማለት ደግሞ
ወደ ምድር ታችኛው ክፍል[ሀ] ወረደ ማለት
ካልሆነ በቀር ምን ማለት ነው? 10 ወደ
ታች የወረደውም፣ መላውን ፍጥረተ ዓለም
ይሞላ ዘንድ ከሰማያት ሁሉ በላይ የወ
ጣው እርሱ ራሱ ነው። 11 አንዳንዶቹ ሐዋ
ርያት፣ አንዳንዶቹ ነቢያት፣ አንዳንዶቹም
ወንጌል ሰባኪዎች፣ ሌሎቹ ደግሞ እረኞችና
አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ የሰጠ እርሱ
ነው፤ 12 ይኸውም የክርስቶስ አካል ይገነባ
ዘንድ፣ ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ ለማ
ዘጋጀት ሲሆን፣ 13 ይህም የሚሆነው፣ ሁላች
ንም የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ
ወደሚገኘው አንድነት በመምጣትና ሙሉ
ሰው በመሆን፣ በክርስቶስ ወዳለው ፍጹምነት
ደረጃ እስክምንደርስ ነው።
14 ከእንግዲህ በማዕበል ወደ ፊትና ወደ
ኋላ እየተነዳን፣ በልዩ ልዩ ዐይነት የትም
ህርት ነፋስ፣ በሰዎችም ረቂቅ ተንኰልና
ማታለል ወዲያና ወዲህ እየተንገዋለልን
ሕፃናት አንሆንም። 15 ይልቁንም እውነትን
በፍቅር እየተናገርን፣ ራስ ወደ ሆነው ወደ
እርሱ በነገር ሁሉ እናድጋለን፤ እርሱም
ክርስቶስ ነው፤ 16 ከእርሱም የተነሣ፣ አካል
ሁሉ በሚያገናኘው ጅማት እየተያያዘና
እየተጋጠመ፣ እያንዳንዱ ክፍል የራሱን ሥራ
እያከናወነ በፍቅር ያድጋል፤ ራሱንም ያንጻል።

4፥6 ዘዳ6፥4፤ዘካ 14፥9፤ሮሜ11፥36
4፥7 ሮሜ3፥24፤ 12፥3፤1ቆሮ12:7:11
4፥8 መዝ68፥18፤ ቈላ2፥15
4፥10 ምሳ30፥1-4፤ ኤፌ1፥23፤
4፥11 ቍ8፤ሐሥ 11፥27፤13፥1፤21፥8፤ ሮሜ2፥21፤12፥6:7፣ 1ቆሮ12፥10:28፤13፥ 2:8፤14፥1:26:39፤ ኤፌ2፥20፤3፥5፤ 1ጢሞ1፥7፤2ጢሞ 4፥5፤2ጴጥ3፥2፤ያዕ 3፥1፤ይሁ17
4፥12 ሮሜ14፥19፤ 1ቆሮ12፥27
4፥13 ቍ3:5፤ዮሐ 1፥16፤1ቆሮ2፥6፤ኤፌ 1፥23፤3፥19፤ፊል3፥8፤ ቈላ1፥28
4፥14 ኢሳ57፥20፤ 1ቆሮ14፥20፤ኤፌ6፥1 1፤ያዕ1፥6
4፥15 ቍ2:
16፤ኤፌ1፥4:22 4፥16 ቍ2:15፤1ቆሮ12፥7፤ኤፌ 1፥4፤ቈላ2፥19

[ሀ]9 *ወይም ወደ ምድር ጥልቀት*

ከአሁን ይልቅ በዚያን ጊዜ የክርስቲያኖች ዐይነተኛ መለያ ነበር፤ ይህም ሥርዐት በተለያየ መንገድ የሚፈጸምና ብዙ ጊዜም በቤተ ክርስቲያን ባሉት ፊት ብቻ ይፈጸም የነበረ በመሆኑ ነው።

4፥7 *ጸጋ፤* 3፥7-8 ይመ።

*4፥8፤ የመዝ* 68፥8 ማብ ይመ፤ እግዚአብሔር የሰማያዊው ዙፋን ተምሳሌት ወደ ሆነው፣ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ወደሚገኘው ዙፋኑ በድል አድራጊነት መውጣቱን ይናገራል፤ ጳውሎስ ይህንን ክርስቶስ በድል ወደ ሰማይ ካረገበት ሁኔታ ጋር ያያይዘዋል። *ምርኮ፤* ጳውሎስ እዚህ ላይ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ድል የነሣቸውን ጠላቶች ማመልከቱ ሊሆን ይችላል።

4፥9 *ወጣ ... ወረደ፤* ምንም እንኳ ጳውሎስ ከመዝሙረ ዳዊት በመጥቀስ፣ “ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ” የሚለውን ሐሳብ ቢያሳይም፣ አንባቢዎቹ የክርስቶስን በሥጋ ወደ ምድር መምጣት፣ ከሙታን መነሣትና ማረግ እንዲያስታውሱ ለመምከር ተጠቅሞበታል። አንዳንድ ሰዎች እንደሚያስቡትና አንዳንድ ተርጓሚዎች እንደሚናገሩት ይህ ክፍል ክርስቶስ ወደ ገሀነም እንደ ወረደ ላያመለክት ይችላል።

4፥11 *ሐዋርያት፤* እዚህ ላይ የተጠቀሱት ቤተ ክርስቲያንን በመመሥረት ረገድ ካላቸው ሚና አንጻር ነው (2፥20 ይመ)። ስለ መጀመሪያዎቹ ሐዋርያት አመራረጥ ሐሥ 1፥21-22 ይመ፤ የማር6፥30፤ ሮሜ 1፥1፤ 1ቆሮ 1፥1፤ ዕብ 3፥1 ማብ ይመ። ጳውሎስም ሐዋርያ ነበር (1፥1 ይመ)። *ነቢያት፤* እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ወይም ሳሉበት ሁኔታ መልእክት የሚያስተላልፍባቸው ሰዎች ናቸው (1ቆሮ 14፥3-4ይመ፤ 1ቆሮ 12፥10 ማብ ይመ)። *ወንጌል ሰባኪዎች፤* ሐሥ 21፥8፤ 1ቆሮ 1፥17 ይመ። ሌሎቹ ስጦታ ያላቸው ሰዎች ቤተ ክርስቲያን እንድታድግ በማነጽ ሲያግዙ፣ የወንጌል ሰባኪዎች ግን ቤተ ክርስቲያን በቍጥር እንድታድግና እንድትሰፋ የሚያግዙ ናቸው። በቍ 12 ላይ የተጠቀሰው ዐላማ፣ “ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት” እስከ ሆነ ድረስ፣ ከልዩ ልዩ አገልግሎታቸው መካከል ሌሎች ክርስቲያኖችን በምስክርነታቸው ይጸኑ ዘንድ መርዳትም እንደ ሆነ መገመት ይቻላል። *እረኞችና አስተማሪዎች፤* በግሪኩ ሰዋስው፣ “ሌሎቹ” የሚለው ቃል ሁለቱንም በአንድ ላይ የሚመለከት ነው፤ ይህ ስጦታ ያላቸው ሁለቱ ክፍሎች በጥብቅ የተያያዙ መሆናቸው ግልጽ ነው። የእረኝነት አገልግሎት ያላቸው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከእግዚአብሔር ቃል (ትምህርት) ይመግባሉ። እነርሱም እንደ አስተማሪዎች ልዩ የማስተማር ስጦታ አላቸው (ከ1ጢሞ 3፥2 ጋር ያነጻጽሩ)። *የሰጠ እርሱ ነው፤* ከመዝ 68 የተወሰደው ጥቅስ ፍጹም የሆነ ትርጕም የሚሰጠው፣ ስጦታዎችን የሰጠው ክርስቶስ ወደ ሰማይ ያረገው ጌታ እንደ ሆነ ሲቈጠር ነው።

4፥12 *የክርስቶስ አካል ይገነባ ዘንድ፤* ቍ 16 ይመ። መንፈሳዊ ስጦታዎች ለግል ጥቅም የሚውሉ ሳይሆኑ ለክርስቶስ አካል ማለትም ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ ናቸው። “ይገነባ ዘንድ” የሚለው የ2፥19-22 ምሳሌን ያንጸባርቃል። ሁለቱም ጽንሰ ሐሳቦች ማለትም አካልና ሕንጻ በአንድነት ሲሆኑ ቍልፍ የሆነውን የእድገት ሐሳብ በአጽንዖት ይገልጻሉ። *ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት፤* በቍ 11 ላይ የተጠቀሱት የምእመናንን ሥራ የሚሠሩ ሳይሆኑ፣ ምእመናን ሥራቸውን ራሳቸው እንዲሠሩ የሚያዘጋጇቸው ናቸው።

4፥13 *የእግዚአብሔርን ልጅ ... በማወቅ፤* አንድነት የፍቅር ስሜት ወይም ሃይማኖታዊ ዝንባሌ ብቻ ሳይሆን፣ ስለ እውነትና ስለ እግዚአብሔር ልጅ ሊኖረን የሚገባንን ዕውቀት ያመለክታል። *በማመን፤* በዚህ ቦታ “ማመን” የሚለው ቃል የሚያሳየው ክርስቲያኖች ስለ ክርስቶስ ያላቸውን ጽኑ እምነትና ስለ እርሱ ስለሚሰጡት ትምህርቶች ያላቸውን አመለካከት ነው (በሐሥ 2፥42 “ለሐዋርያት ትምህርት” ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ)። *አንድነት፤* በቍ 1-6 ላይ የተጠቀሰውን ሐሳብ የሚያንጸባርቅ ነው። *በክርስቶስ ወዳለው ፍጹምነት፤* በክርስትና ትምህርት ዕውቀት ማደግን ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር ባለው ግንኙነት የሚገለጸውን የግል ብስለት ሳይሆን (ቍ 2-3 ያነጻጽሩ) ፍጹም ሚዛናዊ በሆነው በክርስቶስ ባሕርይ ማደግን ያሳያል። *እስከ ምን ደረሰ፤* ጊዜን ብቻ የሚያሳይ ሳይሆን ዐላማንም ያመለክታል።

4፥14 *እየተነዳን፤* በባሕር ላይ ወዲያና ወዲህ የሚል ጀልባን ምሳሌ በማድረግ ጠንካራና ጽኑ ያልሆኑ ክርስቲያኖችን የሚያሳይ ቃል ነው። *ትምህርት፤* እንደ አሁኑ ዘመን በቀድሞ ጊዜም በእምነታቸው ያልጠነከሩትን በቀላሉ ከመንገድ የሚያስቱ ዐያሌ የተዛቡ ትምህርቶችና ኑፋቄዎች ነበሩ። *ረቂቅ ተንኰልና ማታለል፤* አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖችን በክርስቶስ ካላቸው እምነት የሚያስቷቸው ሰዎች ባለማወቅና በየዋህነት ሳይሆን ሆን ብለው በክፋትና በማታለል ነው (ከ1ጢሞ 4፥1-2 ጋር ያነጻጽሩ)። *ሕፃናት፤* በቍ 13 ላይ ከተገለጸው ብስለት ጋር ያነጻጽሩ።

4፥15 *እውነትን በፍቅር እየተናገርን፤* እውነተኛና በፍቅር የተሞላ የአኗኗር ሁኔታን ያሳያል። *ራስ ወደ ሆነው ... እናድጋለን፤* ክርስቶስ የአካሉ ማለትም የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ በምሳሌነት በመጥቀስ፣ በቍ 13 ላይ ባለው ሐሳብ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የቀረበ ነው፤ ስለዚህ ጳውሎስ በቅድሚያ የሚናገረው በአንድነት ስለ ሆነው እድገት ነው። የሚገነባው የክርስቶስ አካል ነው (ቍ 12)። በቍ 13 ላይ እንደተገለጸው ሁላችንም በኅብረት ወደ፣ “ፍጹምነት ደረጃ” እናድጋለን።

*4፥16፤ የአካሉ ራስ እየመራው ስለሚያድገው አካል ሁኔታ* ለማስረዳት የቀረበ ጠለቅ ያለ ምሳሌ ነው። የአካል ብልቶች በእድገት ሂደት ውስጥ እርስ በርስ ይረዳዳሉ፤ ይህም በቍ 11-13 የተጠቀሰውን የእግዚአብሔርን ሕዝብ የመደጋገፍ አገልግሎት በሥዕላዊ መልኩ ያቀርባል። *በፍቅር፤* ያለዚህ ወደ ፍጹም እድገትና አንድነት መድረስ አይቻልም (ከቍ 2 ፥ 15 ጋር ያነጻጽሩ)።

*4፥17-5፥20፤* እግዚአብሔር በክርስቶስ ሞት ስላስገኛቸው የቤተ ክርስቲያን መንታ ግቦች ስለ ሆኑት ስለ አንድነትና ፍጹምነት ጳውሎስ አስቀድሞ ተናግሯል። አሁን ደግሞ የእግዚአብሔር በሆኑትም ዘንድ ቅድስና ዋነኛ ጕዳይ እንደ ሆነ ያሳያል።

4፥17 *በአስተሳሰባቸው ከንቱነት፤* ሕይወት ያለ እግዚአብሔር ተስፋ የሚያስቈርጥ፣ ከንቱና ትርጕም የለሽ ነው (ለምሳሌ:- መክ 1፥2፤ ሮሜ 1፥21 ይመ)።

## እንደ ብርሃን ልጆች መኖር

17ስለዚህ ይህን እነግራችኋለሁ፤ በጌታም
ዐደራ እላለሁ፤ በአስተሳሰባቸው ከንቱነት እን
ደሚኖሩት እንደ አሕዛብ ልትመላለሱ አይ
ገባም። 18እነርሱ ከልባቸው መደንደን የተነሣ
ስለማያስተውሉ ልቦናቸው ጨልሞአል፤
ከእግዚአብሔርም ሕይወት ተለይተዋል። 19ኀሊ
ናቸው ስለ ደነዘዘ በማይረካ ምኞት፣ በርኩሰት
ሁሉ እንዳሻቸው ለመኖር ቅጥ ለሌለው ብል
ግና ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል።
20እናንተ ግን ክርስቶስን ያወቃችሁት እን
ደዚህ ባለ መንገድ አይደለም፤ 21በእርግጥ ስለ
እርሱ ሰምታችኋል፤ በኢየሱስም እንዳለው
እውነት በእርሱ ተምራችኋል። 22ቀድሞ ስለ
ነበራችሁበት ሕይወትም፣ በሚያታልል ምኞቱ
የጎደፈውን አሮጌ ሰውነታችሁን አውልቃችሁ
እንድትጥሉ ተምራችኋል፤ 23ደግሞም በአእ
ምሮአችሁ መንፈስ እንድትታደሱ፣ 24እው
ነተኛ በሆነው ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና
እግዚአብሔርን እንዲመስል የተፈጠረውን አዲ
ሱን ሰው እንድትለብሱ ነው።
25ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፣ እያንዳን
ዳችሁ ከባልንጀራችሁ ጋር እውነትን ተነጋ
ገሩ፤ ሁላችንም የአንድ አካል ብልቶች ነንና።
26ተቈጡ፤ ነገር ግን ኀጢአት አትሥሩ፤ በቍ
ጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፤ 27ለዲያብሎስም
ስፍራ አትስጡት። 28ይሰርቅ የነበረ ከእንግ
ዲህ አይስረቅ፤ ነገር ግን ለተቸገሩት የሚ
ያካፍለው ነገር እንዲኖረው በገዛ እጆቹ በጎ
የሆነውን እየሠራ ለማግኘት ይድከም።
29እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎችን የሚያንጽና
ሰሚዎችን የሚጠቅም ቃል እንጂ የማይረባ
ቃል ከአፋችሁ አይውጣ። 30ለቤዛ ቀን የታ
ተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ
አታሳዝኑ። 31መራርነትን ሁሉ፣ ቍጣና
ንዴትን፣ ጭቅጭቅና ስድብን ከማንኛ
ውም ክፋት ጋር ከእናንተ ዘንድ አስወግዱ።
32እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ
እናንተም ይቅር ተባባሉ፤ እርስ በርሳችሁ
ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ።

5 እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔ
ርን ምሰሉ፤ 2ክርስቶስ እንደ ወደደን ራሱ
ንም ስለ እኛ መልካም መዐዛ ያለው መባና
መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር እንደሰጠ
እናንተም በፍቅር ተመላለሱ።
3ማንኛውም የዝሙት ወይም የርኵሰት

4፥17 ሮሜ1፥21፤ ኤፌ2፥2
4፥18 ዘዳ29፥4፤ ሮሜ1፥21፤2ቆሮ 3፥14፤ኤፌ2፥12
4፥19 ሮሜ1፥24፤ ቈላ3፥5፤1ጢሞ4፥2፤ 1ጴጥ4፥3
4፥22 ቍ25፡31፤ ኤር17፥9፤ሮሜ6፥6፤ ቈላ3፥5፡8፡9፤ዕብ 3፥13፤ ያዕ1፥21፤ 1ጴጥ 2፥1
4፥23 ሮሜ12፥2፤ ቈላ3፥10
4፥24 ሮሜ6፥4፤13፥ 14፤ኤፌ2፥10
4፥25 ዘሌ19፥11፤ መዝ15፥2፤ዘካ8፥16፤ ሮሜ12፥5፤ቈላ3፥9
4፥26 መዝ4፥4፤ ማቴ5፥22
4፥27 2ቆ2፥10፡11
4፥28 ሐሥ20፥35፤ ገላ6፥10፤1ተሰ4፥11
4፥29 ማቴ12፥36፤ ሮሜ14፥19፤ኤፌ5፥4 1ቆላ3፥8
4፥30 ኢሳ63፥10፤ ሮሜ8፥23፤ 2ቆሮ1፡22፤5፥5፤ ኤፌ1፥13፤1ተሰ5፥19
4፥31 ቍ22፤ቈላ 3፥8፤1ጴጥ2፥1
4፥32 ማቴ6፥14፡15፤ቈላ3፥12፡13፤1ጴጥ3፥18፤5፥1 ማቴ5፥48፤ ሉቃ6፥36፤ዮሐ1፥12፤5፥2 ቍ25፤ዮሐ 13፥34፤ገላ1፥4፤2፥20፤ዕብ 7፥27፤5፥3 1ቆሮ6፥18፤ ቈላ3፥5

4፥18 *ከልባቸው መደንደን የተነሣ፤* የሞራል ውድቀትን ያመለክታል። *ልቦናቸው ጨልሞአል፤* በአስተሳሰብ ከንቱ የሆነ ሕይወትን ያሳያል።

4፥19 *ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል፤* የፈርዖን ልብ በራሱ ፈቃድና በእግዚአብሔር እንደ ደነደነ (ዘፀ 7፥11 ይመ) አሕዛብ ልባቸውን በማደንደን ራሳቸውን ለረከሰ ሕይወት አሳልፈው መስጠታቸውንና (ሮሜ1፥24፡26፡28) እግዚአብሔር እንዲህ ላለው ሕይወት አሳልፎ እንደ ሰጣቸው ይናገራል።

4፥20 *እናንተ፤* አጽንዖት መስጠቱን ያመለክታል።

4፥21 *በኢየሱስም እንዳለው እውነት፤* ጳውሎስ፣ ክርስ ቶስ የሚለውን ስም ሳይሆን ኢየሱስ የሚለውን ስም መጠቀሙ፣ በኢየሱስ ምድራዊ ኑሮ ውስጥ እውነት የተገለጸ መሆኑን ለማ መልከት ነው።

4፥22 *አሮጌ ሰውነታችሁን፤* ምናልባት ክርስቲያን ከመ ሆን በፊት የነበረውን ሰው ያመለክታል። አሮጌው የኑሮ ሥርዐት የክፉ ምኞት ውጤት ነው።

4፥23 *በአእምሮአችሁ፤* ይህን ከማያምኑ ሰዎች ክፉ ሐሳብ ጋር ያነጻጽሩ (ቍ 17-18)።

4፥24 *እግዚአብሔርን እንዲመስል የተፈጠረውን አዲሱን ሰው፤* አዲሱ ሰው የተፈጠረ ነው፤ በውስጥ የሚኖረውን ክርስቶስን አያሳይም፤ ነገር ግን በአዲስ አማኝ ሕይወት ውስጥ ክርስቶስ የፈጠረውን አዲስ ሰው ያመለክታል፤ ወይም በአዲስ ልደት ጊዜ የሚገኘውን አንድ አማኝ የሚኖረውን አዲስ ባሕርይ አያመለክትም። በአንጻሩ ግን አንድ አማኝ በመለወጥ ጊዜ (ቈላ3፥9-10) የሚለብሰው ብቻ ሳይሆን እንደ ክርስቲያን በተግባርም የሚ ለብሰው አዲስ የኑሮ ዘይቤ ነው (የሮሜ6፥12-13 ማብ ይመ)።

4፥25 *ከባልንጀራችሁ፤* በዚህ ዐውድ ቃሉ ክርስቲያኖችን ሊያመለክት ይችላል። *እውነትን፤* ከቍ 15 ፤ 21 ጋር ያነጻጽሩ።

4፥26 *ተቈጡ፤* ሰዎች በሚለወጡበት ጊዜ ስሜታቸው ከእነርሱ አይወሰድም፤ ነገር ግን ስሜታቸው እየጠራና ንጹሕ እየ ሆነ ሊመጣ ይገባዋል። አንዳንድ ቍጣዎች ወደ ኀጢአት የሚወ ስዱ ሲሆኑ፣ አንዳንዶቹ ግን አይደሉም። *ፀሐይ አይግባ፤* ማንኛ ውም ቍጣ ለረጅም ጊዜ ሊቈይ አይገባም፤ መቈጣት ቢፈቀድም ለዲያብሎስ ዕድል እስከሚሰጥ ድረስ መቈየት እንደሌለበት ያሳያል።

4፥27 *ለዲያብሎስም፤* ራሳችን የምንሠራው ኀጢአት አብዛኛውን ጊዜ ከራሳችን ክፉ ምኞት የሚመነጭ እንጂ ከዲያብ ሎስ በቀጥታ የሚመጣ ፈተና አይደለም። ቢሆንም ሰይጣን በሌ ሎች ላይ እንድንነሣ የሚያደርጉትን፣ እንደ ቍጣ ያሉ ኀጢአቶ ችን በመጠቀም፣ በክርስቲያኖች መካከል መለያየት ሊያመጡ የሚችሉ ታላላቅ ክፋቶች እንዲሆኑ ያደርጋል።

4፥28 *ከእንግዲህ አይስረቅ፤ ... የሚያካፍለው ነገር እንዲ ኖረው ... እየሠራ፤* ኀጢአትን መተው ብቻ በቂ አይደለም፤ ነገር ግን መልካም ነገር መሥራትም ይገባል። ቀድሞ ሌባ የነበረ፣ አሁን እየሠራ የተቸገሩትን ሊረዳ ይገባዋል።

4፥29 *የሚጠቅም ቃል፤* ቀድሞ ሲል ከተጠቀሰው ቍጥር ጋር አብሮ የሚሄድ ተመሳሳይ ምክር ነው። ክርስቲያን ክፉ የሆ ነውን ነገር አለመናገር ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎች እንዲታነጹ የሚረ ዳን ነገር ሊናገር ይገባዋል።

4፥30 *ለቤዛ ቀን፤* 1፥14 ይመ፤ 1ጴጥ1፥5 እና ማብ ይመ። *የታተማችሁበትን፤* የ1፥13 ማብ ይመ። *አታሳዝኑ፤* በቍ29 ላይ በተጠቀሰው፣ "የማይረባ ቃል" እና በቍ31 ላይ በተጠቀሱት ኀጢአቶች ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ ኀይል ብቻ ሳይሆን አካልም (ሰብእና) ያለው ስለ ሆነ የማዘን ስሜት እንዳለው ግሡ ያመለክታል።

4፥31 *መራርነት ... ክፋት፤* እንዲህ ያሉ ነገሮች መንፈስ ቅዱስን ያሳዝናሉ፤ ይህም የአንድን ሰው ንግግር በተመለከተ በቍ20 ላይ ከተጠቀሰው ምክር የሚቀጥል ነው።

4፥32 *ይቅር ተባባሉ፤* ይህ መሠረታዊ የክርስቲያን ባሕ ርይ ቸርና ርኅሩኅ መሆንን ጨምሮ በክርስቶስ ይቅር የመባል ውጤት ሲሆን፣ ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን ለሌሎች የምንገልጽበት መንገድ ነው።

5፥1 *ምሰሉ፤* እግዚአብሔርን የመምሰያ መንገድ አንዱ የይቅር ባይ መንፈስ መያዝ ነው (4፥32)። ጌታችንን ልንመስ ለው የምንችለው ልክ እርሱ እንዳደረገው በማድረግ ነው (ቍ2፤ 4፥32)። ኢየሱስ ለእኛ ያለውን ፍቅርን የገለጠበት መሥዋዕትነት የሚያሳየው የድነትን መንገድ ብቻ ሳይሆን (በም 2 እንደምናየው)፣ ለሌሎች እንዴት መኖር እንደሚገባን ጭምር ነው።

5፥2 *መልካም መዐዛ፤* በብሉይ ኪዳን ዘመን ይቀርብ የነበ ረው መሥዋዕት ጌታን ደስ ከማሰኘቱ የተነሣ፣ ይህም "ደስ የሚ ያሰኘውን መዐዛ" ተብሎ ተገልጾአል (ዘፍ 8፥21፤ ዘፀ 29፥18፡25፡ 41፤ ዘሌ 1፥9፡13፡17)።

5፥3 *የርኵሰት ወይም የስስት ነገር፤* ጳውሎስ በተለይ ሲ ገልጸው ከነበረው ከዝሙት ኀጢአት አጠቃላይ ይዘት ወዳለው እንደ ስስት ወደ መሳሰሉት ኀጢአቶች ትኵረቱን ዘወር ያደር ጋል፤ ዝሙት ምኞትን የሚጨምር ሲሆን ሌሎችንም የስግብግ ብነት ኀጢአቶች ያካትታል። *ክፉ ... አይገኝ፤* ቍ12 ይመ። *ቅዱስ ... ሕዝብ፤* እኛ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነን (2፥21፤ ከ2ቆሮ 6፥16፤ 1ጴጥ 2፥9 ጋር ያነጻጽሩ)።

5፥4 *ተራ የሆነ ንግግር፣ ዋዛ ፈዛዛም፤* ዐውዱ እንዲሁም "የሚያሳፍር" የሚለው ቃል የሚያሳየው ተራ ቀልድን ሳይሆን፣

ወይም የሥሥት ነገር ከቶ በመካከላችሁ አይ
ነሣ፤ ይህ ቅዱስ ለሆነው ለእግዚአብሔር ሕዝብ
አይገባምና:: [4]የሚያሳፍርና ተራ የሆነ ንግ
ግር፣ ዋዛ ፈዛዛም፣ ለእናንተ ስለማይገባ
በመካከላችሁ አይኑር፤ ይልቁንስ የምታመሰ
ግኑ ሁኑ:: [5]ደግሞም ይህን ዕወቁ፤ ማንም
አመንዝራ ወይም ርኩስ ወይም ሥሥታም
ማለት ጣዖት አምላኪ በክርስቶስና በእግዚአ
ብሔር መንግሥት[ª] ርስት የለውም:: [6]ማንም
በከንቱ ንግግር አያታላችሁ፤ ምክንያቱም
የእግዚአብሔር ቍጣ በማይታዘዙ ልጆች ላይ
የሚመጣው በእንደዚህ ዐይነት ነገር ነው::
[7]ስለዚህ እንዲህ ካሉ ጋር አትተባበሩ::
[8]ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁ፤ አሁን ግን
በጌታ ብርሃን ናችሁ:: እንደ ብርሃን ልጆች
ኑሩ፤ [9]የብርሃኑ ፍሬ በበጎነት፣ በጽድቅና
በእውነት ሁሉ ዘንድ ነውና:: [10]እንዲሁም
ጌታን ደስ የሚያሰኘውን ፈልጉ:: [11]ፍሬ
ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር ምንም ዐይነት
ግንኙነት አይኑራችሁ፤ ይልቁን ግለጡት፤
[12]በድብቅ የሚሠሩትን ነገር መናገር ራሱ
አሳፋሪ ነውና:: [13]ብርሃን የበራበት ነገር
ሁሉ ግልጽ ሆኖ ይታያል፤ [14]ምክንያቱም ሁሉን
ነገር እንዲታይ የሚያደርገው ብርሃን ነውና፤
ስለዚህም፣

"አንተ የተኛህ ንቃ፤
ከሙታን ተነሣ፤
ክርስቶስም ያበራልሃል" ተብሎአል::

[15]እንግዲህ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን
እንደ ጥበበኞች እንዴት እንደምትኖሩ
ተጠንቀቁ:: [16]ቀኖቹ ክፉ ናቸውና ዘመኑን
በሚገባ዗ ዋጁ:: [17]ስለዚህ ሞኞች አትሁኑ፤
የጌታ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ አስተውሉ
እንጂ:: [18]በመንፈስ ተሞሉ እንጂ በወይን ጠጅ
አትስከሩ፤ ይህ ብክነት ነውና:: [19]በመዝሙ
ርና በውዳሴ፣ በመንፈሳዊም ዝማሬ እርስ
በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ በልባችሁ ለጌታ ተቀኙ፤
አዚሙም:: [20]በዚህም እግዚአብሔር አብን በጌ
ታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስለ ሁሉ ነገር
ሁልጊዜ አመስግኑ::

5፥4 ቈ-20፤ ኤፌ4፥29
5፥5 ማቴ25፥34፤ ሐሥ20፥32፤ ቈላ3፥5
5፥6 ማር13፥5፤ ሮሜ1፥18፤ ኤፌ2፥2
5፥8 ሉቃ16፥8፤ ዮሐ 8፥12፤ ሐሥ26፥18፤ ኤፌ2፥2
5፥9 ማቴ7፥16-20፤ ሮሜ15፥14፤ ገላ5፥22
5፥10 1ጢሞ5፥4
5፥11 ሮሜ13፥12፤ 2ቆሮ6፥14
5፥13 ዮሐ3፥20፡21
5፥14 ኢሳ26፥19፤ 60፥1፤ ሚል4፥2፤ ዮሐ 5፥25፤ ሮሜ13፥11
5፥15 ቍ-2
5፥16 ኤፌ6፥13፤ ቈላ4፥5
5፥17 ሮሜ12፥2፤ ቈላ 1፥9፤ 1ተሰ4፥3
5፥18 ዘሌ10፥9፤ ምሳ20፥1፤ ኢሳ28፥7፤ ሉቃ1፥15፤ ሮሜ 13፥13
5፥19 መዝ27፥6፤ 95፥2፤ ሐሥ16፥25፤ 1ቆሮ14፥15፡26፤ ቈላ3፥16
5፥20 ቍ-4፤ ኢዮ 1፥21፤ መዝ34፥1፤ ቈላ3፥17፤ ዕብ13፥15

[ª]5 ወይም *የክርስቶስና የእግዚአብሔር መንግሥት በሆነው*

ጸያፍና የማያንጽ ፈዝን ነው:: *የምታመሰግኑ፤* እግዚአብሔር ለሰጠን ነገር ሁሉ አመስጋኞች በመሆን ክፉ ሐሳብንና ንግግርን ልናስወግድ እንችላለን::

5፥5 *አመንዝራ ወይም ርኩስ ወይም ስስታም፤* ቍ 3 ይመ:: *ጣዖት አምላኪ፤* ከቈላ 3፥5 ጋር ያነጻጽሩ:: ስግብ ግብ ሰው ከእግዚአብሔር ይልቅ ብዙ ቍሳቍሶችን ይፈልጋል፤ በእግዚአብሔርም ምትክ ሌሎች ነገሮችን ይወዳል፤ ስለዚህ ጣዖት አምላኪ ይሆናል:: *ርስት፤* በአመንዝራነትና በሌሎች የስስት ኀጢ አቶች የሚኖር፣ እግዚአብሔርን ይበድላል፤ እግዚአብሔርም በመ ንግሥቱ ዕድል ፈንታ እንዳይኖረው ያደርገዋል (የ1ቆሮ 6፥9፡11 ማብ ይመ)::

5፥6 *አያታላችሁ፤* የኤፌሶንን ክርስቲያኖች በርኵሰታ ችሁ ምክንያት የእግዚአብሔር ቍጣ አይመጣባችሁም ብለው አንዳንድ አስተማሪዎች እንደሚያስተምሩ ጳውሎስ ያውቃል:: እንዲህ ያለው ትምህርት በርኵሰት የሚኖር በክርስቶስ መንግ ሥት ርስት ይኖረዋል ብሎ አንድ ሰው እንዲያስብና እንዲስት ሊያደርገው ይችላል::

5፥7 *አትተባበሩ፤* ክርስቲያኖች ምንም እንኳ ክርስቶስ እን ዳደረገው ጤናማ የሆነ ማኅበራዊ ሕይወት መኖር ቢገባቸውም (ሉቃ 5፥30-32፤ 15፥1-2)፣ ኀጢአት ከሞላበት ከማያምኑ ሰዎች የኑሮ ዘይቤ ጋር መተባበር የለባቸውም::

5፥8 *ጨለማ ... ብርሃን፤* ይህ ክፍል በብርሃንና በጨለማ መካከል ንጽጽር ያደርጋል፤ ይህም የእርሱ ማለትም ንጹሕና እው ነት የሆነው "ብርሃን" (1ዮሐ 1፥5) በሕይወታቸው የበራ ብቻ ሳይሆን፣ ጨለማ ለወረሰው ለሰው ባሕርይ ብርሃን የመፈንጠቂያ መንገድ መሆናቸውን ለማሳየት ነው (ማቴ5፥14)::

5፥9 *የብርሃኑ ፍሬ፤* ቅይጥ ተለዋጭ ዘይቤ ቢሆንም፣ ትር ጕሙ ግን ግልጽ ነው:: ብርሃን ፍሬያማ ነው (ብርሃን በዕፀዋት እድገት ላይ የሚያመጣውን ለውጥ ልብ ይበሉ)፤ በእግዚአብሔር ብርሃን የሚኖሩም የመልካም ሥነ ምግባር ፍሬ አላቸው (ከገላ 5፥22-23 ጋር ያነጻጽሩ):: በጨለማ የሚኖሩ ግን፣ እንዲህ ያለ ፍሬ አይታይባቸውም (ቍ 11 ይመ)::

5፥11 *ምንም ዐይነት ግንኙነት አይኑራችሁ፤* ቍ 7 ይመ:: *ግለጡት፤* ብርሃን በባሕርይው በጨለማ ውስጥ ያለውን ይገል ጣል፤ ንጽጽሩም ኀጢአት ምን እንደ ሆነ ያሳያል::

5፥12 *መናገር ራሱ አሳፋሪ ነውና፤* ክርስቲያኖች ሕይወ ታቸው ለሌሎች ብርሃን እንዲሆን በክፋት ውስጥ ሊኖሩ አይገባ ቸውም::

5፥13-14 *ነገር ሁሉ ... እንዲታይ፤* ጳውሎስ እነዚህን ቃላት በመደጋገም ሁሉን የሚገልጠውን የእግዚአብሔርን ብርሃን ባሕርይና ሊቀር የማይችለውን ውጤት በአጽንዖት የሚናገር ይመ ስላል::

5፥14 *አንተ የተኛህ ... ከሙታን፤* የኀጢአተኛን ሁኔታ የሚገልጹ ቃላት ናቸው (ከ2፥1 ጋር ያነጻጽሩ):: *ክርስቶ ስም ያበ ራልሃል፤* ሕይወት በሚሰጠው ብርሃኑ አማካይነት ነው::

5፥15 *ጥበብ እንደሌላቸው ... ጥበበኞች፤* ጳውሎስ በብር ሃንና በጨለማ መካከል ሲያደርገው ከነበረው ንጽጽር፣ በጥበብና በሞኝነት መካከል ወዳለው ንጽጽር ዘወር ይላል::

5፥16 *ዘመኑን፤* ሰነፍ ሰው ለሕይወት ምንም ዕቅድ የለ ውም፤ ክፉ በሆነው ዓለም ለእግዚአብሔር ሊኖር የሚችልበትን አጋጣሚ ሳይጠቀምበት ያመልጠዋል::

5፥17 *ሞኞች ... አስተውሉ፤* ጳውሎስ አሁንም ንጽጽሩን በመቀጠል፣ ሞኝ ሰው ያገኘውን አጋጣሚ በሚገባ ባለመጠቀሙ ጊዜ የሚያመልጠው ብቻ ሳይሆን፣ ከዚህም በላይ የሆነ መሠረ ታዊ ችግር እንዳለበት ያመለክታል፤ ይህ ችግር እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ እንዲሁም ለክርስቲያኖች ያለውን ዐላማ ምን እንደ ሆነ አለማስተዋሉ ነው:: በኤፌሶን መልእክት ውስጥ የእግዚአ ብሔር ዐላማ መሠረታዊ ዐቢይ ርእስ ነው (ም1 ይመ)::

5፥18 *በመንፈስ ተሞሉ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ፤* በግሪኩ የአሁን ጊዜ ግሥ ሲሆን፣ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በየጊዜው የሚከናወን መሆኑን ያመለክ ታል:: እንደ አስፈላጊነቱ መንፈስ ቅዱስ እየደጋገመ ለአምልኮ፣ ለአገልግሎትና ለምስክርነት በኀይል ይሞላናል:: በወይን ጠጅ በመሞላትና በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት መካከል ያለው ንጽጽር ግልጽ ነው:: ሆኖም ጳውሎስ ለማነጻጸር የቻለው በሁለቱ መካከል ተመሳሳይ ነገር ስላለ ነው:: ይህም ወይን ጠጅም ሆነ መንፈስ ቅዱስ በአንድ ሰው ውስጥ በሙላት ሲሆን ያን ሰው በቍጥጥር ሥር የማድረግ ኀይል ያለው በመሆኑ ነው:: ቈላ3፥15-4፥1 ከኤፌ 5፥18-6፥9 ጋር ተመሳሳይ ስለ ሆነ፣ በሁለቱም ክፍል መግቢያ ላይ ጳውሎስ አንድ ዐይነት መሠረታዊ የሆነ ሐሳብ ለማስ ተላለፍ እንዳሰበ መገመት እንችላለን:: በዚህ ክፍል በመንፈስ ስለ መሞላት፣ በቈላስያስ ደግሞ በክርስቶስ የሰላም ግዛት ሥር ስለ መሆንና በክርስቶስ፣ "ቃል" ስለ መሞላት ሲናገር ማለት የፈለገው በእግዚአብሔር ቍጥጥር ሥር ስለ መሆን ነው:: በሁለቱም ክፍ ሎች በቍጥጥር ሥር የመሆን ውጤቱ በመሠረቱ ተመሳሳይ ነው፤ ይህም በደስታ አንድ ላይ ሆኖ እግዚአብሔርን ማመስገንና ጤ ናማ ኅብረትን ከሰዎች ጋር መፍጠር ነው::

5፥19 *በመዝሙርና ... በመንፈሳዊ ዝማሬ፤* ማንኛውም በብሉይ ኪዳን የተጻፈውን ዐይነት መዝሙር ወይም ለእግዚአ ብሔር በቀጥታ የሚቀርብ ውዳሴ ወይም ዘወትር ክርስቲያኖች የሚያቀርቡት ማሕሌት፣ እግዚአብሔርን ለማመስገንና ከፍ ከፍ ለማድረግ የምንጠቀምባቸው መንገዶች ይሆናሉ (ቍ 20):: ሦስቱም ቃላት የተለያዩ የዝማሬ ዐይነቶችን ሊያመለክቱ ይችላሉ::

*5፥21-6፥9፤* በም2-4 በተገለጸው ላይ እግዚአብሔር፣ የሚያ ምኑትን አይሁድንና አሕዛብን በክርስቶስ በኩል ወደ አዲስ ኅብ ረት ያመጣበትን መንገድ ያሳያል:: በ4፥1-6 ላይ የአንድነቱን አስፈላጊነት በአጽንዖት ተናግሯል:: አሁን ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ አማኞች በተለያዩ ማኅበራዊ ጕዳዮች ውስጥ እንዴት ተግባ ራዊ በሆነ መንገድ መኖር እንደሚገባቸው ያመለክታል:: ይህ

21ለክርቶስ ካላችሁ አክብሮታዊ ፍርሀት
የተነሣ አንዳችሁ ለአንዳችሁ ተገዙ::

## ባልና ሚስት

5፥22-6፥9 ተጓ ምብ-ቈላ3፥18-4፥1

22ሚስቶች ሆይ፤ ለጌታ እንደምትገዙ ለባ
ሎቻችሁም ተገዙ 23ክርስቶስ አካሉ ለሆነ
ችውና አዳኟ ለሆናት ቤተ ክርስቲያን ራስ
እንደ ሆነ ሁሉ፣ ባልም የሚስቱ ራስ ነውና::
24እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እን
ደምትገዛ፣ ሚስቶችም ለባሎቻቸው በማን
ኛውም ነገር እንደዚሁ መገዛት ይገባቸዋል::
25ባሎች ሆይ፤ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን
እንደ ወደዳትና ራሱንም ስለ እርሷ አሳልፎ
እንደ ሰጠ፣ እናንተም ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤
26በቃሉ አማካይነት በውሃ አጥቦ በማንጻት
እንድትቀደስ፣ 27እንዲሁም ጒድፍ ወይም
የፊት መጨማደድ ወይም አንዳች እንከን
ሳይገኝባት ቅድስትና ነውር አልባ የሆነች
ክብርት ቤተ ክርስቲያን አድርጎ ለራሱ ሊያ
ቀርባት ነው:: 28ባሎችም እንደዚሁ ሚስቶቻ
ቸውን እንደ ገዛ ሥጋቸው መውደድ ይገባ
ቸዋል:: ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል::
29የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ማንም የለም፤ ይመ
ግበዋል፤ ይንከባከበዋል፤ ክርስቶስም ለቤተ
ክርስቲያን ያደረገው ልክ እንደዚሁ ነው፤
30እኛ የክርስቶስ አካል ብልቶች ነንና:: 31"ስለ
ዚህም ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ከሚ
ስቱም ጋር አንድ ይሆናል፤ ሁለቱም አንድ
ሥጋ ይሆናሉ":: 32ይህ ጥልቅ ምስጢር ነው፤
እኔም ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስ
ቲያን እናገራለሁ:: 33ሆኖም ከእናንተ እያን
ዳንዱ ሚስቱን እንደ ራሱ አድርጎ ይው
ደድ፤ ሚስትም ባሏን ታክብር::

## ወላጆችና ልጆች

6ልጆች ሆይ፤ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፤
ይህ ተገቢ ነውና:: 2"አባትህንና እናት
ህን አክብር" በሚለው ቀዳሚ ትእዛዝ ውስጥ
ያለው ተስፋ፣ 3"መልካም እንዲሆንልህ፣ ዕድሜ
ህም በምድር ላይ እንዲረዝም" የሚል ነው::
4አባቶች ሆይ፤ እናንተም ልጆቻችሁን
አታስቈጧቸው፤ ነገር ግን በጌታ ምክርና ተግ
ሣጽ አሳድጓቸው::

5፥21 ገላ5፥13፤ 1ጴጥ5፥5
5፥22 ዘፍ3፥16፤ 1ቆሮ14፥34፤ኤፌ6፥5፤ቈላ3፥18፤ 2ጢሞ2፥12፤ቲቶ2፥5፤ 1ጴጥ3፥1:5:6
5፥23 ኤፌ1፥22
5፥24 ቊ22
5፥25 ቊ2:28:33 ፤ቈላ3፥19
5፥26 ዮሐ17፥19፤ ሐሥ22፥16፤ዕብ2፥11 ፤10፥10:14፤13፥12፤
5፥27 2ቆሮ4፥14፤ ኤፌ1፥4
5፥28 ቊ25
5፥30 ሮሜ12፥5፤ 1ቆሮ12፥27
5፥31 ዘፍ2፥24፤ ማቴ19፥5፤1ቆሮ6፥16
5፥33 ቊ25
6፥1 ምሳ6፥20፤ ቈላ3፥20
6፥3 ዘፀ20፥12፤ ዘዳ5፥16
6፥4 ዘፍ18፥19፤ ዘዳ6፥7፤ምሳ13፥24፤22፥6፤ቈላ3፥21

የጋራ የኀላፊነት ዝርዝር በቈላ 3፥18-41፤ 1ጴጥ 2፥13-3፥12 ላይ ከተጠቀሱት ጋር ተመሳሳይነት አለው፤ ከሮሜ 13፥1-10 ጋር ያነጻጽሩ::

5፥21 *አንዳችሁ ለአንዳችሁ ተገዙ፤* ከዚህ ቀጥሎ በተከታታይ ለሚመጡት ሐሳቦች መሠረታዊ ጒዳይ ነው:: ጳውሎስ በእያንዳንዱ ግንኙነት፣ እያንዳንዱ ሰው ኅብረቱን ሊያጠነክር የሚያስችለውን የወዳጅነት ዝንባሌ እንዲኖረው የሚረዳውን መንገድ ያሳያል:: የግሪኩ ሰዋሰው እንደሚያሳየው፣ ይህ አንዱ ለሌላው የመገዛት ጒዳይ በቍ 18 ላይ ከመንፈስ ቅዱስ መሞላት ጋር ተያይዞ ቀርቦአል:: "ተሞሉ" ከሚለው (ቍ 18) ትእዛዝ ቀጥሎ "ተነጋገሩ" (ቍ 19)፤ "ተቀኙ" (ቍ 19)፤ "አዚሙ" (ቍ 19)፤ "አመስግኑ" (ቍ 20) እና "ተገዙ" (ቍ 21) የሚሉት ቃላት ይገኛሉ::

5፥22 *ሚስቶች ሆይ፤ ... ተገዙ፤* በቍ 21 ላይ የተገለጸው፣ አንዱ ለሌላው የመገዛት ጉዳይ አንዱ ገጽታ ነው:: መገዛት ማለት የራስን መብት መተው ማለት ነው:: ግንኙነቱ በውትድርና ዓለም እንዳለው ዐይነት ከሆነ፣ 'መታዘዝ' የሚል ሐሳብ የያዘ ከሆነ፣ ከፈቃድ የተነሣ ሳይሆን ከኀይል የተነሣ መሆኑ ነው፤ ነገር ግን ይህን ዐይነቱ ትርጒም ለዚህ አይጠቀስም:: በእርግጥ በዚህ መልኩ፣ "መታዘዝ" የሚለው ቃል ከሚስቶች አኳያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጠቀሰም፤ ሆኖም ልጆችን (6፥1) እና ባሪያዎችን (6፥5) በሚመለከት ተጠቅሶአል:: *ለጌታ፤* ባሉችን በጌታ ቦታ ማስቀመጥ አይደለም:: ነገር ግን ሚስት ለጌታ እንደምትገዛ እንዲሁ ለባሏ መገዛት እንዳለባት የሚያመለክት ነው:: ይህም ለባሏ የበላይነትን በመስጠት (ቍ 23) ባሏን በማክበር (ቍ 33፤ 1ጴጥ3፥12)፣ ባሏን በመውደድ (ቲቶ 2፥4) እና እስከ ሞት ድረስ ከባሏ ጋር ጸንታ በመኖር (ሮሜ 7፥2-3) ከእርሷ የሚጠበቀውን ኀላፊነት ያመለክታል::

5፥23 *ክርስቶስ ... እንደ ሆነ ሁሉ፤* በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በባልና በሚስት መካከል ያለው ግንኙነት በአጠቃላይ ለዚህ ክፍል መሠረታዊ ነገር ነው:: *አካሉ፤* 2፥16፤ 4፥4:12:16 ይመ:: *አዳኟ ለሆናት፤* ክርስቶስ ዋጋ ስለ ከፈለ፣ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ኅብረት እንዲኖረው መብት አለው:: *የሚስቱ ራስ፤* የ1ቆሮ 11፥3 ማብ ይመ:: እያንዳንዱ ቤተ ሰብ መሪ ሊኖረው ይገባል፤ የመሪነቱንም ኀላፊነት እግዚአብሔር ለባል ሰጥቶአል (ቍ 23-33፤ 6፥4)::

5፥25 *ባሎች ሆይ፤* ራስን አሳልፎ የመስጠቱ ጒዳይ፣ አንዱን ወገን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን የእርስ በርስ እንደ ሆነ ጳውሎስ ያሳያል:: *ራሱንም ስለ እርሷ አሳልፎ እንደ ሰጠ፤* የጌታችንን ፍቅር የሚገልጽ ብቻ ሳይሆን ባል ለሚስቱ ደኅንነት ሲል ራሱን ምን ያህል መስጠት እንዳለበት የሚያመለክት ምሳሌ ነው:: ራስን ለሚወዱት ሰው ለሞት አሳልፎ መስጠት ሚስቶች በቍጥር 22 ላይ እንዲያደርጉት ከታዘዙት ይልቅ የበለጠ ራስን የመስጠት መግለጫ ነው:: *ውደዱ፤* ባሎች ሚስቶቻቸውን ሊወዱ፣ ሊመሩ (ቍ 23)፣ በክርስቶስ ነገር ሊመግቡና (ቍ 29)፣ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ በታማኝነት አብረዋቸው ሊኖሩ ይገባቸዋል (ማቴ 19፥3-9)::

5፥26 *በቃሉ አማካይነት በውሃ አጥቦ በማንጻት፤* በእነዚህ ቃላት ውስጥ የጋብቻ ልማዶችን ወይም የቤተ ክርስቲያን ሥርዐቶችን ለማየት ብዙ ሙከራዎች ተደርገዋል:: አንድ ነገር ግን ግልጽ ነው፤ ጌታ ኢየሱስ የሞተው ይቅርታን ለማስገኘት ብቻ ሳይሆን፣ የእርሱ ሙሽራ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ የሆነ አዲስ ሕይወት እንዲኖራትም ጭምር ነው:: የመታጠብን፣ የውሃንና የቃሉን ጽንሰ ሐሳብ ለማጥናት ዮሐ 3:5፤ 15፥3፤ ቲቶ 3፥5፤ 1ጴጥ 1፥23፤ 3፥21 ይመ::

5፥27 *ቅድስትና ነቀፋ የሌለባት፤* 1፥4 ይመ::

5፥28-29 *እንደ ገዛ ሥጋቸው ... ራሱን ይወዳል:: ... የገዛ ሥጋውን፤* ለዚህ አባባልና በእነዚህ ጥቅሶች ላይ የተሰጠው ትምህርት መሠረቱ በቍ 31 የተጠቀሰው ዘፍ 2፥24 ነው:: ባልና ሚስት፣ "አንድ ሥጋ" ከሆኑ በኋላ ባል ሚስቱን መውደድ ማለት የራሱን አካል መውደድ ማለት ነው::

5፥32 *ምስጢር፤* የሮሜ 11፥25 ማብ ይመ:: ክርስቶስ ሙሽራው ከሆነችው ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያደረገው ኅብረት ጥልቅ ምስጢር ያለበትና ከሰው መረዳትም በላይ ነው:: ዋና ምሳሌ ሆኖ የቀረበው የባልና የሚስት ኅብረት ሳይሆን የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ነው::

5፥33 *ይውደድ፤ ... ታክብር፤* በዚህ ክፍል ለተጠቀሰው ሐሳብ ማጠቃለያ ሐረግ ነው::

6፥1 *በጌታ፤* ልጆች ለወላጆቻቸው ቢታዘዙ፣ ለክርስቶስ ማድረግ ከሚገባቸው ነገር አንዱን አደረጉ ማለት ነው፤ የክርስቶስን ምሳሌ ከሉቃ 2፥51፤ እና ዕብ 5፥8 ይመ::

*6፥2፤* አንድ ልጅ አድጎ ሚስት ካገባ በኋላ ከወላጆቹ ጋር ያለው ግንኙነት ይለወጣል (5፥31)፤ ነገር ግን ወላጆቹን ለመንከባከብ ያለበት ኀላፊነት ፈጽሞ አይቀርም (1ጢሞ 5፥4)::

6፥3 *በምድር ላይ፤* ይህ ትእዛዝ በሚገኝበት በዘዳ 5፥16 (ዘፀ 20፥12 ይመ) ላይ የተገባው የተስፋ ቃል (ቍ 2) የሚጠበቀው የተስፋውን ምድር ከንዓንን ለመውረስ ከመጠበቅ አንጻር ነው:: የቀረበው ሐሳብ የኤፌሶንን ክርስቲያኖች በቀጥታ አይመለከትም:: ስለዚህ በዚህ ቦታ የተጠቀሰው በአጠቃላይ መልኩ ነው::

6፥4 *አታስቈጧቸው፤* አባቶች ልጆቻቸውን በሆነ ባልሆነ መቈጣት የለባቸውም፤ በልጆቻችን ላይ የፈለግነውን ሁሉ ለማድረግ መብት አለን የሚሉትንም መተው አለባቸው::

6፥5 *ባሪያዎች፤* ብሉይ ኪዳንም ሆነ አዲስ ኪዳን፣ የልብ ደንዳናነት ውጤት ለሆኑት እንደ ባርነት፣ እንደ መፋታት ለመሳሰሉት ማኅበራዊ ጒዳዮች ሕግጋት አሏቸው (ዘዳ 24፥1-4፤ ማቴ

## ጌቶችና ባሪያዎች

5ባሪያዎች ሆይ፤ ለክርስቶስ እንደምት
ታዘዙ፣ በምድር ጌቶቻችሁ ለሆኑት በአክብ
ሮትና በፍርሀት፣ በልብ ቅንነትም ታዘዙ፤
6ለታይታና ከእነርሱ ሙገሳን ለማግኘት
ሳይሆን እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች የእግዚአ
ብሔርን ፈቃድ ከልብ በመፈጸም ታዘዟቸው።
7ሰውን ሳይሆን ጌታን እንደምታገለግሉ
ሆናችሁ በሙሉ ልብ አገልግሉ፤ 8ምክንያቱም፣
ባሪያም ሆነ ነጻ ሰው ለሚያደርገው በጎ
ነገር ሁሉ ሽልማቱን ከጌታ እንደሚቀበል
ታውቃላችሁ።

9እናንተም ጌቶች ሆይ፤ ለባሮቻችሁ እን
ዲሁ አድርጉላቸው፤ የእነርሱም፣ የእናንተም
ጌታ የሆነው በሰማይ እንዳለ፣ የሰውንም ፊት
አይቶ እንደማያደላ ታውቃላችሁና አታስ
ፈራሯቸው።

## የእግዚአብሔር ጦር ዕቃ

10በተረፈ በጌታና ብርቱ በሆነው ኀይሉ ጠን
ክሩ። 11የዲያብሎስን የተንኰል ሥራ መቋ
ቋም ትችሉ ዘንድ፣ የእግዚአብሔርን ሙሉ
የጦር ዕቃ ልበሱ። 12ምክንያቱም ተጋድሎ
አችን ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን ከዚህ
ከጨለማ ዓለም ገዦች፣ ከሥልጣናትና
ከኀይላት እንዲሁም በሰማያዊ ስፍራ ካሉ
ከርኩሳን መናፍስት ሰራዊት ጋር ነው።
13ክፉው ቀን ሲመጣ መቋቋም ትችሉ ዘንድ
የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር ዕቃ ልበሱ፤ ሁሉን
ከፈጸማችሁ በኋላ ጸንታችሁ መቆም ትችላ
ላችሁና። 14እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት
ዝናር ታጥቃችሁ፣ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳ
ችሁ፣ 15በሰላም ወንጌል ዝግጁነት እግሮቻ
ችሁ ተጫምተው ቁሙ። 16ከእነዚህም ሁሉ
ጋር፣ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች
ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን
ጋሻ አንሡ፤ 17የመዳንን ራስ ቍር አድርጉ፤
የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፤ እርሱም የእግዚ
አብሔር ቃል ነው። 18በጸሎትና በልመና
ሁሉ፣ በማንኛውም ሁኔታ በመንፈስ ጸልዩ፤
ይህንም በማሰብ ንቁ፤ ስለ ቅዱሳንም ሁሉ
በትጋት ልመና አቅርቡ።

19የወንጌልን ምስጢር ለመግለጥ አፌን
በምከፍትበት ጊዜ ሁሉ በድፍረት እንድ
ናገር ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ጸልዩልኝ። 20በሰ
ንሰለት የታሰረ መልእክተኛ የሆንሁት ለዚሁ
ነውና። ስለዚህ መናገር የሚገባኝን ያለ ፍር
ሀት እንድናገር ጸልዩልኝ።

## የመጨረሻ ሰላምታ

21በምን ሁኔታ እንዳለሁና ምን እንደ
ማደርግ ታውቁ ዘንድ ተወዳጅ ወንድምና
በጌታ ታማኝ አገልጋይ የሆነው ቲኪቆስ
ሁሉንም ነገር ይነግራችኋል። 22የእኛን ሁኔታ
እንድታውቁና ልባችሁን እንዲያበረታ ለዚሁ
ስል ወደ እናንተ ልኬዋለሁ።

23ከእግዚአብሔር አብ፣ ከጌታም ከኢየሱስ ክር
ስቶስ ሰላም፣ ፍቅርም ከእምነት ጋር ለወን
ድሞች ይሁን። 24ጌታችንን ኢየሱስ ክርስ
ቶስን በማይጠፋ ፍቅር ለሚወዱ ሁሉ ጸጋ
ይሁን።

6፥5 ኢሳ5፥22፤ ቈላ3፥22፤1ጢሞ6፥1፤ ቲቶ2፥9፤1ጴጥ2፥18
6፥6 ሮሜ6፥22
6፥7 ቈላ3፥23
6፥8 ማቴ16፥27 1ቆሮ3፥24
6፥9 ኢዮ31፥13፡ 14፤ሐሥ10፥34
6፥10 2ሳሙ10፥12 1መዝ27፥14፤ሐጌ 2፥4፤1ቆሮ16፥13፤ ኤፌ1፡19፣2ጢሞ2፥1
6፥11 ቈላ13፤ሮሜ 13፥12፤1ተሰ5፥8
6፥12 ሮሜ8፥38 ፤1ቆሮ15፥50፤ኤፌ1፥ 3፡21፤3፥10፤ዕብ2፥14
6፥13 ቈላ11፤2ቆሮ 6፥7
6፥14 መዝ132፥9፤ ኢሳ11፥5፤59፥17፤ 1ተሰ5፥8
6፥15 ኢሳ52፥7፤ ሮሜ 10፥15
6፥16 ማቴ5፥37፤ 1ዮሐ5፥4
6፥17 ኢሳ49፥2፤ 59፥17፤ዕብ4፥12
6፥18 ማቴ26፥41፤ ሉቃ18፥1፤ሐሥ1፥14 1ሮሜ8፥26:27፤ፊል 1፥4፤4፥6፤ቈላ1፥3
6፥19 ሐሥ4፥29፤ ሮሜ16፥25፤1ተሰ 5፥25
6፥20 ሐሥ21፥33፤ 2ቆሮ5፥20
6፥21 ሐሥ20፥4
6፥22ቈላ2፥2፤4፥7-9
6፥23 ገላ6፥16፤ 2ተሰ3፥16፤1ጴጥ 5፥14

19፥8 ይመ)። እንዲህ ያሉ ሕግጋት እነዚህን የመሳሰሉ ጒዳዮችን የሚያበረታቱ ወይም ቸል የሚሉ ሳይሆኑ፣ ከእግዚአብሔር የተሰጡና በዘመኑ ከነበረው እውነታ ጋር ተግባራዊ የሆነ ግንኙነት ያላቸው ነበሩ።

6፥9 *ጌቶች፤* አሁንም ጳውሎስ በሌላው ወገን ያሉት ማድረግ የሚገባቸውን ነገር በአጽንዖት ያቀርባል (ከ5፥21-6፥4 ጋር ያነጻጽሩ፤ የቲቶ 2፥9 ማብ ይመ)።

*6፥10-20፤* እስከ አሁን ጳውሎስ በኤፌሶን መልእክት የተናገረው ቍሳዊውን ዓለም በተመለከተ ነበር። ከመጀመሪያ አንሥቶ ትኵረት ያደረገው ስለማይታየው ዓለም ሲሆን (የ1፥3 ማብ ይመ፤ በተጨማሪ፣ 1፥10፡20-30፤ 2፥6፤ 6፥10 ይመ)፣ አሁን ደግሞ "በሰማያዊ ስፍራ" (ቍ 12) ከክፉው ጋር ስለሚደረገው መንፈሳዊ ውጊያ ነው።

6፥10 *ብርቱ ... ኀይሉ፤* የሰው ጥረት ዋጋ እንደሌለው እና የእግዚአብሔር ኀይል ግን ማንም ሊቋቋመው እንደማይችል ያሳያል።

6፥11 *የዲያቢሎስን ... ሥራ፤* ክርስቲያኖች ከክፉው ጋር በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ አሉ፤ ይህ መንፈሳዊ ውጊያ የእምነት ጦርነት እንደ ሆነ ተገልጾአል (2ቆሮ 10፥4፤ 1ጢሞ 1፥18-19፤ 6፥12)፤ ይህም ውጊያ እስከሚመጣው ሕይወት ድረስ ይቀጥላል።

6፥12 *ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን፤* ዋና ጠላት እነርሱ እንደ ሆኑ በመቍጠር በተቃዋሚ ሰዎች ላይ በቍጣ በመነሣሣት ሥጋዊ ኀይል መጠቀም ተገቢ እንዳልሆነ የቀረበ ማስጠንቀቂያ ነው። *ገዦች ... ሰራዊት፤* ጳውሎስ አስቀድሞ ከጠቀሳቸው በማይታየው ዓለም ካሉ ኀይላት ጋር ያነጻጽሩ (የ1፥21፤3፥10 ማብ ይመ)። *በሰማያዊ ስፍራ፤* የ1፥3 ማብ ይመ።

6፥13 *መቋቋም ትችሉ ዘንድ ... ጸንታችሁ ቍሙ፤* በዚህ ዐውድ የተጠቀሰው ምሳሌ የክፉውን ግዛት በኀይል መውረርን የሚያመለክት ሳይሆን፣ እያንዳንዱ ወታደር የሚመጣውን ጥቃት ለመቋቋም የሚያደርገውን መከላከል የሚያሳይ ነው።

6፥14 *በእውነት ዝናር፤* በኢሳ11፥5 ላይ በምሳሌነት ከተጠቀሰው ከመሲሑ አለባበስ ጋር ያነጻጽሩ። በውጊያ ድል ማድረግ የሚቻለው ጭካኔ በተሞላበት ኀይል ሳይሆን፣ መሲሑ እንዳደረገው በመልካም ባሕርይ ነው። *የጽድቅንም ጥሩር፤* እዚህም ላይ የጦረኛው ባሕርይ መከላከል ነው። እግዚአብሔር ራሱ ፍትሕን ለማምጣት ሲነሣ፣ የጽድቅን ጥሩር እንደሚለብስ በምሳሌ ተገልጾአል (ኢሳ 59፥17 ይመ)።

6፥15 *እግሮቻችሁ ተጫምተው፤* በኢሳ 52፥7 ላይ የተጠቀሰው መልእክተኛ እግር የሚያንጸባርቀው በባዶ እግር የመሮጥን ልማድ ሲሆን፣ እዚህ ላይ የወንጌሉ መልእክት የቀረበው እንደ ሮማዊ ወታደር ጫማ የሚከላከልና የሚደግፍ መሆኑን ለማሣየት ነው።

6፥16 *የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ፤* በቁጻ የተለበጠ፣ ነበልባል ያላቸውን የሚወረወሩ ፍላጻዎችን እንዲያጠፉ በውሃ ውስጥ የተነከረን ሰፊ የሆነውን የሮማውያንን ጋሻ በምሳሌነት ያመለክታል።

6፥17-18 *የመንፈስንም ሰይፍ ... በመንፈስ ጸልዩ፤* ውጊያው መንፈሳዊ ስለ ሆነ በቃሉና በጸሎት አማካይነት በእግዚአብሔር በመደገፍና በእርሱ ኀይል የሚደረግ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። የመንፈስ ሰይፍ አማኝ ከክፉው ኀይል ጋር ሲዋጋ ለማጥቃት የሚጠቀምበት መሣሪያ ነው።

6፥17 *የመዳንን ራስ ቍር፤* ይህን የሚመስል ምሳሌ በኢሳ 59፡17 ላይ ተጠቅሶአል (የቍ 14 ማብ ይመ)። ቍር የወታደርን ራስ ከመከላከል ባሻገር፣ ወታደራዊ ድልን የሚያመለክት ምሳሌ ነው።

*6፥19፤* ጳውሎስ በወህኒ ተጥሎ ያስብ የነበረው ስለ ራሱ ደኅንነት ሳይሆን ስለ ክርስቶስ መንግሥት አገልግሎት ነው።

*6፥21-23፤* ጳውሎስ በሌሎች መልእክቶቹ ውስጥ የተለያዩ ግለሰቦችን ስም በመጥራት ከሚገልጸው ሰላምታ ለየት ባለ ሁኔታ ሰላምታ በማቅረብ መልእክቱን ይደመድማል። ይህም የኤፌሶን መልእክት ለብዙዎች ክርስቲያኖች እንዲዳረስ ታስቦ የተጻፈ መልእክት መሆኑን ሊያመለክት ይችላል (1፥1 ማብ ይመ)።

6፥21 *ቲኪቆስ፤* የጳውሎስ ተወካይ በመሆን ከቦታ ቦታ የሚዘዋወር ረዳቱ ነበር (ከቈላ 4፥7፤ 2ጢሞ 4፥12፤ ቲቶ 3፥12 ጋር ያነጻጽሩ)።

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

## መግቢያ

### ጸሓፊው፣ መልእክቱ የተጻፈበት ጊዜና ቦታ

የፊልጵስዩስ መልእክት በጳውሎስ እንደ ተጻፈ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ያለማመንታት መስክራለች (1፥1ይመ):: የመልእክቱ ውስጣዊ ማስረጃ የእውነት መለያ ያዘለ ነው:: ጸሓፊው በመልእክቱ ውስጥ ስለ ራሱ የተናገራቸው ብዙ ነገሮች፣ በሌሎች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስለ ጳውሎስ ከምናውቀው ነገር ጋር የሚመሳሰል ነው::

ጳውሎስ መልእክቱን የጻፈው በእስር ቤት ሆኖ እንደ ነበር የታወቀ ነው (1:13-14 ይመ):: አንዳንዶች ጳውሎስ የታሰረው በኤፌሶን በ53-55 ዓ.ም አካባቢ ሳይሆን አይቀርም ይላሉ፤ ሌሎች ደግሞ የታሰረው በ57-59 ዓ.ም ገደማ በቂሣርያ ነው ይላሉ:: ሆኖም ጳውሎስ በ61 ዓ.ም አካባቢ በሮም እስር ቤት ሆኖ ይህን መልእክት እንደ ጻፈ የሚያረጋግጡ የተሻሉ ማስረጃዎች ተገኝተዋል:: ይህም በሐሥ28፥14-31 ሐዋርያው በቁም እስር ላይ እንደ ነበረ፣ ከሚገልጸው ታሪክ ጋር በሚገባ የሚጣጣም ነው:: ጳውሎስ የፊልጵስዩስን መልእክት በጻፈ ጊዜ፣ ሁለተኛውን የጢሞቴዎስ መልእክት በጻፈበት "ማሜርታይን" በተባለው ወህኒ ቤት ውስጥ ሆኖ አልነበረም:: በዚህ ጊዜ ጳውሎስ ለሁለት ዓመት በመኖሪያነት በተከራየው ቤት ውስጥ ሆኖ፣ ወደ እርሱ ለሚመጡ ሁሉ ወንጌልን በነጻነት ገልጦ ያስተምር ነበር::

### የመልእክቱ ዐላማ

ጳውሎስ ይህን መልእክት ሲጽፍ ቀዳሚ ዐላማው የፊልጵስዩስ ሰዎች የእርሱን በሮም መታሰር ሰምተው (1፥5፤4፥10-19) ስለ ላኩለት ስጦታ ለማመስገን ነበር:: ይሁን እንጂ ሐዋርያው ይህንኑ ዕድል በመጠቀም እነርሱ ለነበሯቸው ጥያቄዎች መልስ መስጠትና እግረ መንገዱን የሚያነሣቸው ጒዳዮች ነበሩ (1) ራሱ ስለ ነበረበት ሁኔታ ገልጾላቸዋል (1፥12-26፤4፥10-19)፤ (2) የፊልጵስዩስን ምእመናን በስደት ውስጥ ጸንተው እንዲቆሙና በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ቢያልፉ እንኳ በጌታ ደስ ሊላቸው እንደሚገባ ይመክራቸዋል (1፥27-30፤4፥4)፤ (3) እርስ በርስ ትሑታን እንዲሆኑና አንድነት እንዲኖራቸው (2፥1-11፤4፥2-5)፤ (4) የጢሞቴዎስንና የአፍሮዲጡን መልካም አገልግሎት በፊልጵስዩስ ላለችው ቤተ ክርስቲያን መስክሮላታል፤ (2፥19-30)፤ (5) በመካከላቸው ሆነው የሙሴን ሕግጋት በክርስትናም ውስጥ መጠበቅ አለብን ከሚሉ አይሁድ ክርስቲያኖችና ልቅ አኗኗር በክርስትና ሕይወታችን ላይ ለውጥ አያመጣም ከሚሉ ሰዎች አስጠንቅቋቸዋል (ም 3)::

### የመልእክቱ ተደራስያን

ፊልጵስዩስ በመቄዶኒያው ንጉሥ በዳግማዊ ፊልጶስ ስም የተሰየመች ከተማ ነበረች፤ ዳግማዊ ፊልጶስም የታላቁ እስክንድር አባት ነበረ:: ፊልጵስዩስ የበለጸገች በሮም ቅኝ ግዛት ሥር የነበረች ከተማ ስትሆን፣ የፊልጵስዩስና የሮም ዜጎችም ነበሩ ማለት ነው:: ሮማውያን በመሆናቸው ይመኩ ነበር (ሐሥ 16፥21 ይመ)፤ አለባበሳቸው እንደ ሮማውያን ሲሆን የሚነጋገሩትም በላቲን ቋንቋ ነበር:: ጳውሎስ የክርስቲያኖች አገር በሰማይ ነው ሲል (3፥20-21) ይህን ሁኔታ ተመርኵዞ መሆኑ ጥርጥር የለውም:: ብዙዎቹ የፊልጵስዩስ ነዎሪዎች ጡረታ የወጡ ወታደሮች ስለነበሩ፣ በከተማዪቱ አቅራቢያ መሬት ተሰጥቶአቸው ነበር፤ እነርሱም ጠረፍ ላይ የምትገኘውን የፊልጵስዩስን ከተማ በመጠኑም ቢሆን በውትድርና ያገለግሉ ነበር:: ከተማዋ የሮም ቅኝ ግዛት መሆኗ፣ አይሁድ በዚያ ባለመኖራቸውና ምኵራብ ላለመሥራታቸው ምክንያት ሳይሆን አይቀርም፤ ደግሞም ጳውሎስ በፊልጵስዩስ መልእክቱ ውስጥ አንድም የብሉይ ኪዳን ጥቅስ አለመጠቀሙም በዚሁ ምክንያት ሊሆን ይችላል::

### የመልእክቱ ልዩ ባሕርያት

1. በፊልጵስዩስ መልእክት ውስጥ አንድም የብሉይ ኪዳን ጥቅስ አልተጠቀሰም::
2. አንድ የወንጌል መልእክተኛ ስለ ሥራው አካሄድ በመግለጽ የጻፈው የምስጋና ደብዳቤ ነው::
3. ስለ ጠንካራ ክርስቲያናዊ አኗኗር የሚገልጹ ነጥቦችን ያዘለ ነው፤


   (ሀ) ራስን ዝቅ ማድረግ (2፥1-4)
   (ለ) ወደ አንድ ግብ ለመድረስ ወደፊት መዘርጋት (3፥13-14)
   (ሐ) አለመጨነቅ (4፥6)
   (መ) ሁሉን ለማድረግ መቻል (4፥13)

4. በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ ደስታ የሚናገር መልእክት በመሆን ይታወቃል፤ "ደስታ" የሚለውም ቃል በተለያየ መልኩ አሥራ ስድስት ጊዜ ያህል ተጠቅሶ ይገኛል::
5. መልእክቱ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ ክርስቶስ ከሚያስተምሩ ዋነኛ ክፍሎች አንዱን (2፥5-11) የያዘ ነው::

**አስተዋፅኦ**

1. ሰላምታ (1፥1-2)
2. ስለ ፊልጵስዩስ ሰዎች የቀረበ ምስጋናና ጸሎት (1፥3-11)
3. ጳውሎስ የነበረበት ሁኔታ (1፥12-26)
4. ምክር (1፥27-2፥18)
   (ሀ) ለወንጌል ልንኖረው የሚገባ ሕይወት (1፥27-30)
   (ለ) የክርስቶስን የአገልጋይነት ባሕርይ መከተል (2፥1-18)
5. በወንጌል ሥራ ውስጥ የጳውሎስ ባልደረቦች (2፥19-30)
   (ሀ) ጢሞቴዎስ (2፥19-24)
   (ለ) አፍሮዲጡ (2፥25-30)
6. ልቅ አኗኗርን ለሚያደፋፍሩና ለድነት ሕግንም መፈጸም ያስፈልጋል ለሚሉ መምህራን ማስጠንቀቂያ (3፥1-4፥1)
   (ሀ) የሙሴን ውጪያዊ ሥርዐቶች በክርስትና ውስጥ ከሚያስገቡ አይሁድ ክርስቲያኖች (3፥1-16)
   (ለ) በክርስትና ውስጥ ልቅ አኗኗርን ከሚደግፉ ወገኖች (3፥17-4፥1)
7. የመጨረሻ ምክር፣ ምስጋናና ማጠቃለያ (4፥2-23)
   ሀ) ክርስቲያናዊ አኗኗርን በተመለከተ የተሰጡ ልዩ ልዩ ምክሮች (4፥2-9)
   ለ) ማጠቃለያ፣ ምስክርነትና ድጋሚ ምስጋና (4፥10-20)
   ሐ) የስንብት ሰላምታና ቡራኬ (4፥21-23)

## ፊልጵስዩስ በጳውሎስ ዘመን




ከምሥራቅ ክፍላተ አገራት ወደ ሮም በሚወስደው አውራ ጐዳና ላይ የምትገኘው የሮም ቅኝ ግዥ የሆነችው ፊልጵስዩስ የመቄዶንያ ዋነኛ ከተማ ነበረች፡፡ ይህ ጐዳና የከተማይቱን ፎረም ለእኩል ከፍሉ የሚሄድ ሲሆን፣ የብልጽግናዋና በፖለቲካ አስፈላጊ የመሆኗ ዋና ምክንያት ነበር፡፡ ከ16 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ጳውሎስ በመቄዶንያ ላየው ራእይ ምላሽ በመስጠት ከጢሮአዳ በመርከብ ሲሄድ የናጱሌ ከተማ ትገኛለች፡፡

በመቄዶንያ አውራጃ ዋነኛ የወርቅ ማዕድን የሚገኝባት ከተማ በመሆኗ የተከበረ ታሪክ አላት፡፡ ከተማዋ አስቀድሞ የታላቁ እስክንድር አባት በሆነው በዳግማዊ ፊልጶስ ስም የተሰየመች ስትሆን በኋላም በዩልዮስ ቄሳርና አውግስጦስ ስም ክብር አግኝታለች፡፡ ከየአካባቢው በዚች ከተማ ለመስፈር የመጡ ኢጣሊያኖች ከተማዋን አጥለቅልቀው ፊልጵስዩስን ጠንካራና ብዙ ቋንቋዎች የሚነገሩባት ከተማ አድርገዋታል፡፡ ከትንሽ መንደርነት ወደ ተከበረና ወደምትጠቅም ከተማነት አደገች፡፡ ትልቁ ክብሯ እንደ ሌሎቹ የኢጣልያ ከተሞች እኩል ሕጋዊ መብት ማግኘቷ ነው፡፡

የጨዋታ ሥፍራ፣ የአክሮፖሊስ፣ የመድረኩ፣ የመታጠቢያውና በሐሥ 16:13 ላይ የተጠቀሰው የከተማው መግቢያ ቅስት ፍርስራሽ ተገኝተዋል፡፡ ከከተማው መግቢያ ቅስት ጥቂት ራቅ ብሎ በሚገኘው ወንዝ አጠገብ እግዚአብሔርን ለሚፈሩ ሴቶች ጳውሎስ የሰበከበትና የልድያም ሕይወት የተለወጠበት ቦታ አለ፡፡

1 የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋዮች የሆኑ ጳው
ሎስና ጢሞቴዎስ፤ ከቤተ ክርስቲያን ሽማ
ግሌዎችና[ሀ] ከዲያቆናት ጋር በፊልጵስዩስ
ላሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ቅዱሳን ለሆኑ ሁሉ፤
2ከእግዚአብሔር ከአባታችን፣ ከጌታም ከኢ
የሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።

## ምስጋናና ጸሎት

3እናንተን ባስታወስሁ ቍጥር አምላኬን
አመሰግናለሁ። 4ዘወትር ስለ ሁላችሁ ስጸልይ፣
በደስታ እጸልያለሁ፤ 5ከመጀመሪያው ቀን አን
ሥቶ እስካሁን ድረስ በወንጌል አገልግሎት
ተካፋይ ሆናችኋልና። 6በእናንተ መልካምን ሥራ
የጀመረው እርሱ እስከ ክርስቶስ ኢየሱስ ቀን
ድረስ ከፍጻሜ እንደሚያደርሰው እርግጠኛ
ነኝ።
7በልቤ ስላላችሁ፣ ስለ ሁላችሁ እንዲህ
ማሰቤ ተገቢ ነው፤ በእስራቴ፣ ስለ ወንጌል
ስመከትም ሆነ ወንጌልን ሳጸና ሁላችሁም
ከእኔ ጋር የእግዚአብሔር ጸጋ ተካፋዮች ናችሁና።
8በክርስቶስ ኢየሱስ ፍቅር ሁላችሁንም ምን
ያህል እንደምናፍቃችሁ እግዚአብሔር ምስክሬ
ነው።
9ፍቅራችሁ በጥልቅ እውቀትና በማስተ
ዋል ሁሉ በዝቶ እንዲትረፈረፍ እጸልያለሁ።
10ይኸውም ከሁሉ የሚሻለውን ለይታችሁ
እንድታውቁ፣ እስከ ክርስቶስም ቀን ድረስ ንጹሓ
ንና ነቀፋ የሌለባችሁ እንድትሆኑ፣ 11ለእግዚ
አብሔር ክብርና ምስጋና በኢየሱስ ክርስቶስ
በኩል በሚገኘው የጽድቅ ፍሬ እንድትሞሉ
ነው።

## በጳውሎስ እስራት ወንጌል መስፋፋቱ

12አሁንም ወንድሞች ሆይ፤ በእኔ ላይ የደረ
ሰው ነገር ወንጌል በይበልጥ እንዲስፋፋ
መርዳቱን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ። 13ከዚህ
የተነሣ እስራቴ ስለ ክርስቶስ እንደ ሆነ፣ በቤተ
መንግሥት ዘበኞችና[ለ] በሌሎችም ሁሉ ዘንድ
ታውቆአል። 14በእኔ መታሰር ምክንያት በጌታ
ካሉት ወንድሞች ብዙዎቹ የእግዚአብሔርን ቃል
ያለ ፍርሀት፣ በድፍረት ለመናገር ብርታት
አግኝተዋል።

[ሀ] *ጳጳሳት*
[ለ]13 ወይም በቤተ መንግሥት ሁሉ

1፥1 ሐሥ9፥13፤ 16፥1:12፤2ቆሮ1፥1፤ 1ጢሞ3፥1:8
1፥2 ሮሜ1፥7
1፥3 ሮሜ1፥8
1፥4 ሮሜ1፥10
1፥5 ሐሥ2፥42፤16:12-40፤ፊል4፥15
1፥6 ቍ10፤ መዝ138፥8፤1ቆሮ1፥8
1፥7 ቍ13:14:16:17፤ ሐሥ21፥33፤ 2ቆሮ7፥3፤2ጢሞ1፥13
1፥8 ሮሜ1፥9
1፥9 ኤፌ1፥17፤ 1ተሰ3፥12
1፥10 ቍ6፤ 1ቆሮ1፥8
1፥11 ያዕ3፥18
1፥13 ቍ7:14:17፤ ሐሥ21፥33
1፥14 ቍ7:13:17፤ ሐሥ4፥29፤21፥33

*1፥1-2፤* ጳውሎስ ሌሎች ደብዳቤዎቹን ሲጽፍ እንዳደረገው ሁሉ፣ የዘመኑን የአጻጻፍ ስልት ለመከተል ሦስት ነገር አድርጎአል፤ ሀ) ደብዳቤው ከማን እንደተላከ ገልጾአል፤ ለ) የደብ ዳቤውን ተቀባዮች ለይቶ አሳውቆአል፤ ሐ) ሰላምታ አቅርቦአል፤

1፥1 *አገልጋዮች፤* ሮሜ1፥1፤ ቲቶ 1፥1፤ ፊሞ 1 ይመ። በሌላ አንጻር ይህ አባባል፣ ጳውሎስ የክርስቶስ ሐዋርያ መሆኑን ይገልጻል። *ጢሞቴዎስ፤* ከ1ኛ ጢሞቴዎስ መግቢያ "የመልእክቱ ተደራስያን" የሚለውን ይመ። ጢሞቴዎስ በመልእክቱ ውስጥ የተጠቀሰው የጳውሎስ የሥራ ጓደኛ መሆኑ እንጂ መልእክቱን አብሮ መጻፍ አይደለም። *ሽማግሌዎችና ከዲያቆናት፤* ጳውሎስ ከጻፋቸው መልእክቶች ሁሉ፣ የቤተክርስቲያን መሪዎች የደብዳቤ ተቀባዮች ሆነው የተጠቀሱት እዚህ ላይ ብቻ ነው። *ሽማግሌዎችና፤* የ1ጢሞ 3፥1 ማብ ይመ። *ዲያቆናት፤* የ1ጢሞ 3፥8 ማብ ይመ። *በፊልጵስዩስ፤* ከመጽሐፉ መግቢያ "የመልእክቱ ተደራስያን" የሚለውን ይመ። *ቅዱሳን፤* "በክርስቶስ ኢየሱስ" የሚለው ሐረግ የግለሰብን የሥነ ምግባር ንጽሕና ሳይሆን፣ ከክርስቶስ ጋር በመሆን የሚገኘውን መንፈሳዊ አንድነት የሚያሳይ ነው (ሮሜ 1፥7፤ 1ቆሮ 1፥2 እና ማብ ይመ)።

1፥2፤ በመክፈቻው ላይ የተጠቀሰው የሰላምታ ቃል ባህላዊ ጨዋነትን የሚያሳይ ሳይሆን የክርስቲያኖችም መለያ ነው።

1፥3-4 *አምላኬን አመሰግናለሁ ... ስለ ሁላችሁ ስጸልይ በደስታ፤* ጳውሎስ አንባቢዎች በወንጌል ውስጥ ስላላቸው ተሳትፎ ሁልጊዜ በደስታ እየተሞላ የምስጋና ጸሎት ማቅረብ፣ በደብዳቤዎቹ መጀመሪያ ላይ የሚታይ ልዩ ምልክት ነው (ሮሜ 1፥8፤ 1ቆሮ1፥4፤ ቈላ1፥3፤ 1ተሰ1፥2፤ 2ተሰ1፥3፤ 2ጢሞ 1፥3፤ ፊሞ4 ይመ)።

1፥5 *ከመጀመሪያው ቀን፤* ጳውሎስ ወደ ፊልጵስዩስ የመጣበትን የመጀመሪያ ጊዜ ያመለክታል (ሐሥ 16፥12 ይመ)። *እስካሁን፤* ጳውሎስ በሮም የታሰረበት የመጀመሪያው ጊዜ (ሐሥ 28፥16-31 ይመ) ሊገባደድ አካባቢ ማለት ነው (2፥24 ይመ)። *በወንጌል አገልግሎት ተካፋይ፤* ጳውሎስ ስለ እነርሱ እያመሰገነ የሚጸልየው ወንጌልን ስለተቀበሉ ብቻ ሳይሆን በአገልግሎቱም ከፍተኛ ድጋፍ ስላደረጉለት ነው (4፥15 ይመ)።

1፥6 *በእናንተ ...ሥራ፤* እግዚአብሔር የነጢአት ስርየት በመስጠት ለአንባቢዎቹ ያደረገውን መልካም ነገር ብቻ ሳይሆን፣ በሕይወታቸውም በመሥራት ላይ እንደሆነ ጳውሎስ እርግጠኛ ነው (ቍ11 ይመ)። "ሥራ" የሚለው ቃል እግዚአብሔር እነርሱን ለማዳን የሚያደርገውን ሁሉ ያመለክታል። *እስከ ክርስቶስ ኢየሱስ ቀን፤* ድነታቸው ወደ ፍጻሜ የሚደርስበትን የጌታን ዳግም ምጽአት የሚያመለክት ነው (1፥10፤ 2፥16፤ 1ቆሮ1፥8፤ 5፥5፤ 2ቆሮ 1፥14 ይመ)፤ የድነት ጀማሪ፣ አድራጊና ፈጻሚ እግዚአብሔር ነው።

1፥7 *የእግዚአብሔር ጸጋ ተካፋዮች፤* እስራት ቢሆን ወይም ስደት እንዲህ ዐይነቱን ተካፋይነት ሊከለክል አይችልም። ጳውሎስ በታሰረ ጊዜም እንኳ በአፍሮዲጡ አማካይነት የገንዘብ ስጦታቸውን በመላክና ከጳውሎስ ጋር ያላቸውን አንድነት ገልጸዋል፤ በስደቱም ወቅት አብረውት ቆመዋል።

1፥8 *በክርስቶስ ኢየሱስ ፍቅር፤* ጥልቅና ጽኑ ፍቅር ነው፤ ይህም በመጀመሪያ በጌታ ኢየሱስ ሕይወት የታየ ሲሆን፣ በኋላም ከክርስቶስ ጋር ካለው ኅብረት የተነሣ በጳውሎስ ሕይወት እያደገ የመጣ ነው። ይህም ፍቅር ያለ መከልከል ለሁሉ ሊዳረስ የሚችል ነው።

1፥9 *እውቀትና፤* ፍቅር የሚያድግበት መንገድ ነው (ከቈላ 1፥9 ጋር ያነጻጽሩ)። *በማስተዋል ሁሉ፤* ደጉንና ክፉውን በትክክል በመለየት ማለት ነው። የክርስቲያን ፍቅር ስሜት ብቻ ሳይሆን በዕውቀትና በማስተዋል ላይ የተመሠረተ ነው። *በዝቶ እንዲትረፈረፍ፤* እውነተኛ ፍቅር እያደገና እየበሰለ የሚሄድ ነው። (1ተሰ3፥12፤ 4፥10፤ 2ተሰ1፥3 ይመ)።

1፥10 *ከሁሉ የሚሻለውን ለይታችሁ እንድታውቁ፤* ክርስቲያኖች በሥነ ምግባርም ሆነ በግብረገብ ከሁሉ የላቀውን ተቀብለው ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው። *እስከ ክርስቶስም ቀን፤* በዚያ ጊዜ ግቡ ምን እንደ ሆነ በሚገባ ይታወቃል (የቍ 6 ማብ ይመ)፤ ክርስቲያኖች ክፉም ሆነ ደግ ላደረጉት ነገር መልስ ይሰጣሉ፤ ብድራታቸውንም ይቀበላሉ (2ቆሮ 5፥10 ይመ)። *ንጹሓና ነቀፋ የሌለባችሁ፤* የክርስቲያኖች ግብ በዚህ ዓለም ሕይወታቸው ተጠብቀው፣ በብልሹ ሥነ ምግባር ወይም በመንፈሳዊ ውድቀት ሳይነቀፉ መኖር ነው።

1፥11 *ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና፤* እግዚአብሔር በአማኞች ሕይወት ለሚያደርገው ሁሉ የመጨረሻ ግብ ነው (ኤፌ 1፥6:12፥14 ይመ)። *በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል፤* በክርስቶስ በኩል (ከእርሱ ጋር አንድ በመሆን) በመንፈስ ቅዱስ ሥራ የተገኘ ነው። (ከዮሐ15፥5፤ ከኤፌ2፥10 ጋር ያነጻጽሩ)። ... *የጽድቅ ፍሬ እንድ ትሞሉ፤* ከክርስቲያኖች ሁሉ የሚጠበቅ ነው (ከማቴ5፥20-48፤ ዕብ 12፥11፤ ያዕ3፥18፤ ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም አሞ 6፥12፤ ገላ5፥22 ይመ)።

1፥12 *በእኔ ላይ የደረሰው ነገር፤* የጳውሎስን በእስር መቈየት የሚያመለክት ነው። *ወንጌል ...እንዲስፋፋ፣* የጳውሎስ መታሰር ለወንጌል መሰናከል ከመሆን ይልቅ ወንጌል በበለጠ እንዲታወቅ አድርጎአል።

1፥13 *እስራቴ ስለ ክርስቶስ ... ታውቆአል፤* ጳውሎስ የታሰረው ለወንጌል ካለው ጠንካራ አቋሙ የተነሣ እንጂ ወንጀል ሠርቶ እንዳልሆነ እርሱን በሚያውቁት ሰዎች ሁሉ ዘንድ ግልጽ ነበር። *እስራቴ፤* የታሰረበትን ሰንሰለት ወይም በአጠቃላይ ሥቃዩንና በእስር መቆየቱን የሚያመለክት ነው (ቍ14 ይመ)። *በቤተ መንግሥት ዘበኞችና፤* ጳውሎስን በግል የሚያውቁት ወይም በታሰረበት ወቅት ይጠብቁት ዘንድ የተመደቡ በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ወታደሮችን ያመለክታል (ሐሥ 28፥16:30 ይመ)።

1፥14 *ለመናገር ብርታት አግኝተዋል፤* ሌሎች ሰዎች በእርሱ ምሳሌነት ተበረታትተው ወንጌልን በኀይል መስበክ መቻላቸው በጳውሎስ መታሰር የተገኘ ያልተጠበቀ ውጤት ነው።

15አንዳንዶች ከቅናትና ከፉክክር የተነሣ፣ ሌሎች
ግን ከበጎ ፈቃድ የተነሣ ክርስቶስን ይሰብ
ካሉ:: 16እነዚህ፣ እኔ ለወንጌል ለመሟገት እዚህ
እንዳለሁ ስለሚያውቁ፣ በፍቅር ይህን ያደር
ጋሉ፤ 17እነዚያ ግን በእስራቴ ላይ ሳለሁ መከራ
ሊያጸኑብኝ አስበው በቅንነት ሳይሆን ለግል
ምኞታቸው ሲሉ ክርስቶስን ይሰብካሉ[ሐ]:: 18ታዲያ
ችግሩ ከምኑ ላይ ነው? ቁም ነገሩ በቅንነትም
ይሁን በማስመሰል በማንኛውም መንገድ ክር
ስቶስ መሰበኩ ነው:: በዚህ ደስ ይለኛል::
አዎን፤ ደስ ይለኛል፤ 19በእኔ ላይ የደረሰው
ነገር፣ በጸሎታችሁ አማካይነትና ከኢየሱስ ክርስ
ቶስ መንፈስ በተሰጠኝ ረድኤት ለመዳኔ[መ] እንደ
ሚሆን ዐውቃለሁና:: 20በምንም ዐይነት መንገድ
ዐፍሬ እንዳልገኝ ጽኑ ናፍቆትና ተስፋ አለኝ፤
ነገር ግን እንደ ወትሮው ሁሉ ዛሬም በሕይወ
ትም ሆነ በሞት ክርስቶስ በሥጋዬ እንዲከበር
ሙሉ ድፍረት ይኖረኛል:: 21ለእኔ፣ መኖር ክር
ስቶስ ነው፤ ሞትም ማትረፍ ነው:: 22 ነገር ግን
የትኛውን እንደምመርጥ አላውቅም:: 23በእነዚህ
በሁለቱ እጨነቃለሁ፤ ልሄድ፣ ከክርስቶስም ጋር
ልሆን እናፍቃለሁ፤ ይህ እጅግ የተሻለ ነውና::
24ነገር ግን በሥጋ መኖሬ ለእናንተ ይበልጥ
አስፈላጊ ነው:: 25ይህን በማስተዋል፣ በእምነት
እንድታድጉና ደስ እንዲላችሁ፣ በሁላችሁ ዘንድ
እንደምቈይና እንደምኖር ተረድቻለሁ:: 26እንደ ገና
መጥቼ በእናንተ ዘንድ በምሆንበት ጊዜ በእኔ
ምክንያት በክርስቶስ ኢየሱስ ያላችሁ ደስታ ይበዛል
ችኋል::
27ብቻ ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ ኑሩ፤
ይህ ከሆነ መጥቼ ባያችሁ ወይም በርቀት
ሆኜ ስለ እናንተ ብሰማ፣ ለወንጌል እምነት
እንደ አንድ ሰው ሆናችሁ በመጋደል በአንድ
መንፈስ ጸንታችሁ እንደምትቆሙ ዐውቃለሁ::
28በማንኛውም መንገድ በተቃዋሚዎቻችሁ አት
ሸበሩ፤ ይህ እነርሱ እንደሚጠፉ፣ እናንተ ግን
እንደምትድኑ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ምልክት
ነው:: 29በክርስቶስ እንድታምኑ ብቻ ሳይሆን
ስለ እርሱ መከራ እንድትቀበሉም ይህ ጸጋ
ተሰጥቶአችኋልና፤ 30ቀድሞ እንዳያችሁት አሁ
ንም በእኔ እንዳለ በምትሰሙት በዚያው ዐይ
ነት ተጋድሎ እናንተም እያለፋችሁ ነውና::

1፥16 ቍ7:12
1፥17 ቍ7:13:14፤ ሐ21፥33፤ፊል2፥3
1፥19 ሐሥ16፥7፤ 2ቆሮ1፥11፤ፊሞ22
1፥20 ቍ14፤ሮሜ 8፥19፤14፥8፤ 1ቆሮ6፥20
1፥21 ገላ2፥20
1፥23 ዮሐ12፥26፤ 2ጢሞ 4፥6
1፥27 1ቆሮ16፥13፤ ኤፌ4፥1፤ይሁ3
1፥29 ማቴ5፥11፡ 12፤ሐሥ5፥41፤ 14፥22
1፥30 ቍ13፤ ሐሥ16፥19-40፤

ሐ16:17 አንዳንድ ጥንታዊ ያልሆኑ ቅጆች የቍ16እና17 ቅደም ተከተል አለዋውጠውታል
መ19 ወይም ለትድግናዬ

1፥15 *ከቅናትና ከፉክክር ... ከበጎ ፈቃድ፤* በጳውሎስ መታሰር የተቀሰቀሰው ይህ የወንጌል ስብከት ከሁለት ተቃራኒ ፍላጎቶች በአንዱ ላይ የተመሠረተ ነው::

1፥16 *እነዚህ ... በፍቅር ይህን ያደርጋሉ፤* ከበጎ ፈቃድ የተነሣ የሚሰብኩት ቀደም ሲል በቍ13 ላይ እንደተጠቀሰው፣ ጳውሎስ የታሰረበትን እውነተኛ ምክንያት ስለሚያውቁ፣ እንደ ጳውሎስ በድፍረት የተሞላ ርምጃ ለመውሰድ የተነሣሡ ናቸው::

1፥17 *እነዚያ ግን ... ለግል ምኞታቸው ሲሉ ክርስቶስን ይሰብካሉ፤* ከቅናት የተነሣ ወንጌልን የሚሰብኩ ሰዎች ይህን የሚያደርጉት በቅንነት ሳይሆን፣ ከጳውሎስ ጋር ለመፎካከር በመሆኑ እስራቱ እንዲከብድበት ያደርጋሉ::

1፥18 *በቅንነትም ይሁን በማስመሰል ... ክርስቶስን ይሰብካሉ፤* እነዚህ ሰባኪዎች በጎ ተነሣሥቶት ባይኖራቸውም፣ የእውነት መልእክት ስላላቸው እንደ ስሕተት አስተማሪዎች የሚታዩ አይደሉም:: ወንጌል ከሰባኪው ጋር የማይያያዝ የራሱ የሆነ ዐላማና ተፈላጊነት አለው፤ መልእክቱ ከመልእክተኛው የላቀ ነውና:: *ደስ ይለኛል ...ደስ ይለኛል፤* ጳውሎስ እዚህ ላይ የብርቱ ክርስቲያንን የሕይወት ልምድ ምሳሌነት ይጠቅሳል:: ጳውሎስ ታስሮአል፤ ክርስቲያን ጓደኞቹም በስብከታቸው በችግሩ ላይ ችግር ይጨምሩበት ነበር፤ እርሱ ግን በዚህ ሁሉ ይደሰታል::

1፥19 *ከኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ፤* መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር አብ መንፈስ ብቻ ሳይሆን (ሮሜ8፥9:14፤1ቆሮ2፥10-11:14)፣ የሥላሴ ሁለተኛ አካል የሆነው የክርስቶስም መንፈስ ነው (ሐሥ16፥7፤ሮሜ8፥9፤ገላ4፥6)፤ መንፈስ ቅዱስ በአብና (ዮሐ 14፥16-17:26፤ገላ4፥6) በወልድ የተላከ ነው (ዮሐ15፥26፤16፥7):: *ለመዳኔ፤* የጳውሎስን ከእስር ቤት መፈታት (ቍ25፤2፥24) ወይም ቀጥለው ካሉት ቍጥሮች አንጻር አማኝ በክርስቶስ ሞት የሚያገኘውን መዳን ሊያመለክት ይችላል (ከሮሜ8፥28 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ቍጥር 25 ግን ከእስር ቤት ስለመፈታቱ የሚጠቍም ይመስላል::

1፥20 *ዐፍሬ ... ሙሉ ድፍረት፤* ጳውሎስ በእስራቱ የደረሰበት መከራና ጭቈና ወንጌልንና ክርስቶስን ለማገልገል ያደረገውን ጽኑ ውሳኔ እርግፍ አድርጎ እንዲተው ተፈታታኝ ሁኔታ ይፈጥርበታል:: *በሥጋዬ፤* ክቡር የሆነው ክርስቶስ በመንፈሱ የሚኖርበትና የሚሠራበት ስፍራ ነው (ከሮሜ8፥9-10 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ጳውሎስ በሚያደርገውም ሁሉ ክርስቶስ ይከብራል:: *በሕይወትም ሆነ በሞት፤* ከክርስቶስ የተሰጠው አገልግሎቱ የሚቀጥል ቢሆን ወይም በሞት ምክንያት የሚያቋርጥ ቢሆን ማለቱ ነው::

1፥21 *መኖር ክርስቶስ ነው፤* በእስር ቤት እንኳ ቢሆን፣ ለጳውሎስ ዘላቂ ደስታ ምንጭና ምስጢሩ ክርስቶስ ነው፤ በእርሱም የሕይወትን ትርጕም ሁሉ አግኝቶአልና:: *ማትረፍ፤* በቍጥር 23 መሠረት በሞት የተገኘው ጥቅም "ከክርስቶስ ጋር መሆን" ነው፤ ስለዚህ አሁንም ሆነ ለዘላለም ለጳውሎስ የሕይወቱ ከፍተኛ ነገር፣ ከሁሉ የበለጠ ውድ ሀብቱም ክርስቶስና ከክርስቶስ ጋር ያለው ኅብረቱ እንደሆነ በዚሁ ጥቅስ ገልጾአል::

1፥22 *ፍሬ ያለው፤* የወንጌልን መስፋፋትና የቤተክርስቲያንን መገንባት የሚያመለክት ነው::

1፥23-24 *ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልሆን ... በሥጋ መኖሬ፤* ሁለቱም አማራጮች የሚጠቅሙ ናቸው፤ ምስጢሩ እንደተጠበቀ ሆኖ አማኞች ሲሞቱ፣ ከሥጋ ተለይተው ከክርስቶስ ጋር እንደሚሆኑ ይህ ምንባብ በግልጽ ይናገራል::

1፥23 *ይህ እጅግ የተሻለ ነውና፤* ከሞትን በኋላ ከጌታ ጋር አብረን እንደምንሆንና ግልጽ የሆነ ኅብረት እንደሚኖረን ይህ ጥቅስ ይጠቍማል (ከ2ቆሮ 5፥6:8 ጋር ያነጻጽሩ)::

1፥24 *እናንተ ... አስፈላጊ፤* ጳውሎስ ከራሱ ፍላጎት ይልቅ የተገልጋዮቹን ፍላጎት ያስቀድማል::

1፥25 *እንደምቈይና፤* ከጊዜ በኋላ ጳውሎስ ከእስር ቤት ተፈትቶ ሊሆን ይችላል ("አራተኛው የጳውሎስ ሐዋርያዊ ጕዞ"የሚለውን ከ ይመ):: *በእምነት እንድታድጉና* ክርስትና በደስታ የሚያድጉበትና የሚሻሻሉበት ሕይወት ነው (የቍ 9 ማብ እና በዚያ የተሰጡትን ጥቅሶች ይመ)::

1፥26 *በእኔ ምክንያት በክርስቶስ ኢየሱስ ያላችሁ ደስታ፤* ጳውሎስ በእነርሱ ዘንድ የሰጠው መልካም አገልግሎት፣ የፊልጵስዩስ ሰዎች ክርስቶስ በመካከላቸው የሚሠራውን ሁሉ በደስታ እንዲቀበሉት ጕልህ ምክንያት ይሆንላቸዋል::

1፥27 *ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ፤* ለወንጌል ዐላማና ግብ ምቹ ሆኖ መገኘትን ያመለክታል:: *እንደ አንድ ሰው፤* በወንጌል ላይ ተቃውሞ በሚደርስበት ጊዜ፣ ክርስቲያኖች በመፈላለግ በአንድ ልብ መቆም ይገባቸዋል:: *በአንድ መንፈስ፤* በጋራ ዝንባሌና ዐላማ መያያዝ ማለት ነው::

1፥28 *ምልክት፤* በቤተ ክርስቲያንና በወንጌል ላይ የሚደርስ የማያቋርጥ ተቃውሞ፣ ብቸኛና አማራጭ የሌለውን የድነትን መንገድ የሚጻረር በመሆኑ፣ ይህ ለተቃዋሚዎቹ የጥፋት ምልክት ነው:: በሌላ መልኩ የክርስቲያኖች በእምነት ምክንያት መሰደድ፣ የመዳናቸው እርግጠኝነት ምልክት ነው (2ተሰ 1፥5ይመ)::

1፥29 *መከራ እንድትቀበሉም... ተሰጥቶአችኋልና፤* እንደ ስጦታ ወይም እንደ ልዩ መብት የተሰጠ ነው:: የክርስትና እምነት ከመከራው ጭምር፣ለበረከት የተሰጠ ነው (ከማቴ5፥11-12፤ ከሐሥ5፥41፤ከያዕ1፥2፤ከ1ጴጥ4፥14 ጋር ያነጻጽሩ):: የክርስትና ሕይወት ማመንን ብቻ ሳይሆን፣ መከራ መቀበልንም የሚያጠቃልል ነው::

1፥30 *በዚያው ዐይነት፤* ወንጌልን ከሚቃወሙ ሰዎች ጋር በተፈጠረው ግጭት፣ ከጳውሎስ ጐን መቆማቸውን ያመለክታል:: *እንዳያችሁት፤* ጳውሎስና ሲላስ በመጀመሪያ ፊልጵስዩስን በጐበኙበት ጊዜ፣ የደረሰባቸውን እስራት የሚያመለክት ነው

## ትሕትናን ከክርስቶስ መማር

**2** ከክርስቶስ ጋር ካላችሁ አንድነት
የተነሣ የትኛውም መበረታታት፣
ከፍቅር የሆነ መጽናናት፣ የመንፈስ
ኅብረት፣ ምሕረትና ርኅራኄ ካላችሁ፣
2በአንድ ፍቅር፣ በአንድ መንፈስና
በአንድ ዐሳብ በመሆን ደስታዬን ፍጹም
አድርጉልኝ::
3ሌሎች ከእናንተ እንደሚሻሉ በትሕ
ትና ቍጠሩ እንጂ፣ በራስ ወዳድነት ምኞት
ወይም ከንቱ ውዳሴ ለማግኘት አንዳች
አታድርጉ:: 4እያንዳንዳችሁ ሌሎችን የሚጠ
ቅመውንም እንጂ፣ ራሳችሁን የሚጠቅመውን
ብቻ አትመልከቱ።
5በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረው ያ አስተሳሰብ፣
በእናንተም ዘንድ ይሁን፤
6እርሱ በባሕርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ፣
ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን ሊለቀው እንደ
ማይገባ አድርጎ አልቈጠረውም፤
7ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ፣
በሰውም አምሳል ተገኝቶ፣
ራሱን ባዶ አደረገ፤
8ሰው ሆኖ ተገልጦም፣
ራሱን ዝቅ አደረገ፤
እስከ ሞት፣ ያውም በመስቀል ላይ እስከ
መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ።
9ስለዚህ እግዚአብሔር እጅግ ከፍ አደረገው፤
ከስምም ሁሉ በላይ የሆነውን ስም ሰጠው፤
10ይኸውም በሰማይና በምድር፣ ከምድርም
በታች፣
ጕልበት ሁሉ ለኢየሱስ ስም ይንበረከክ ዘንድ፣
11ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር፣
ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር
ዘንድ ነው::

6 ወይም መልክ
7 ወይም ባሕርይ

1ተሰ2፥2፤ዕብ10፥32
2፥1 2ቆሮ13፥14፤ ቈላ3፥12
2፥2 ዮሐ3፥29፤ሮሜ 15፥5፤ፊል4፥2
2፥3 ሮሜ12፥10፤ ገላ5፥26፤1ጴጥ5፥5
2፥4 1ቆሮ10፥24
2፥5 ማቴ11፥29
2፥6 ዮሐ1፥1፤5፥18፤ 14፥9
2፥7 ማቴ20፥28፤ ዮሐ1፥14፤ሮሜ8፥3፤ 2ቆሮ8፥9፤ዕብ2፥17
2፥8 ማቴ26፥39፤ ዮሐ10፥18፤ሮሜ 5፥19፤1ቆሮ1፥23፤ ዕብ5፥8
2፥9 ኢሳ52፥13፤ 53፥12፤ዳን7፥14፤ ሐሥ2፥33፤ኤፌ 1፥20፡21፤ዕብ 2፥9
2፥10 መዝ95፥6፤ ኢሳ45፥23፤ማቴ 28፥18፤ሮሜ
ቈላ1፥20፤ 2፥11 ዮሐ13፥13

(ሐሥ 16፥19-40 ይመ)::

2፥1 *በክርስቶስ፣* ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆን ማለት ነው:: በጳውሎስ ትምህርት መሠረት እንዲህ ዐይነቱ የግል ኅብረት ለድነት መሠረታዊ ነገር ነው:: በክርስቶስ መሆን ማለት መዳን ማለት ነው:: ይህም ከአዳኙ ከክርስቶስ ጋር በግል የቅርብ ወዳጅነትን መፍጠር ማለት ነው:: መበረታታትን የመሰሉ የድነት ፍሬዎችም የሚመነጩት ከዚሁ ዓይነት ወዳጅነት ነው (3፥8-10፤ ሮሜ8፥1፤ 2ቆሮ 5፥17፤ ገላ 2፥20 ይመ):: *ከፍቅር የሆነ መጽናናት፣* በክርስቶስ ካለው የእግዚአብሔር ፍቅር የሚመጣ የሚያጽናና ዕውቀትና ዋስትና ነው፤ ይህም የዓለምን ኀጢአት ለማስተሰረይና የዘላለም ሕይወት ለማግኘት ክርስቶስ በከፈለው ቤዛነት ተገልጿል (ዮሐ3፥16፤ ሮሜ 5፥8፤ 8፥38-39፤ 1ዮሐ 3፥16፤ 4፥9-10፡16 ይመ):: *የመንፈስ ኅብረት፣* በአማኞች መካከል ያለው ኅብረት በውስጣቸው ካለው ከመንፈስ ቅዱስ የመነጨ ነው (2ቆሮ 13፥14 ይመ):: *ምሕረትና ርኅራኄ፣* ክርስቲያኖች እርስ በርስ መሻከክምና መተሳሰብ ይገባቸዋል (1፥8፤ ቈላ 3፥12 ይመ):: የፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች በጌታ ከመሆናቸው የተነሣ የምክር የመጽናናት፣ የአንድነት፣ የምሕ ረትና የርኅራኄ በረከት ተካፋዮች ሊሆኑ እንደቻሉ ጳውሎስ ገልጿል::

2፥2 *በአንድ ሐሳብ... አንድ ፍቅር... በመንፈስና በዐሳብ አንድ፣* በክርስቲያኖች መካከል ሊኖር በሚገባው አንድነት ላይ አጽንዖት የሚያደርግ ነው:: *በአንድ ሐሳብ፣* በአስተሳሰብ አንድ መሆንን ሳይሆን፣ አብሮ ለመሥራትና አንዱ ሌላውን ለማገልገል ተመሳ ሳይ ዝንባሌ አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል:: የክርስቶስ አሳብ የተባለውም እርሱ ነው (ቍ 5፤ 4፥2፤ ሮሜ 12፥16፤ 15፥5፤ 2ቆሮ 13፥11 ይመ)::

2፥3 *በራስ ወዳድነት ምኞት ወይም ከንቱ ውዳሴ ለማግ ኘት፣* በቤተክርስቲያን ውስጥ ላለው አንድነትና ኅብረት ጠላቶች ናቸው (ከ 1፥17 ጋር ያነጻጽሩ፤ "ራስ ወዳድነት" ከሥጋ ሥራ ዎች እንደ አንዱ ሆኖ የተጠቀሰበትን ገላ 5፥20 ይመ) :: *ትሕ ትና፣* ክርስቲያኖች ሊኖራቸው ለሚገባው አንድነት መሠረት ነው:: ይህም የማይታበየውንና ስለ ራሱም ማንነት ትክክለኛ አመለካከት ያለውን ሰው ያሳያል:: *ሌሎች ከእናንተ እንደሚሻሉ ...ቍጠሩ፣* ሌላው ሰው ሁሉ በችሎታና በዕውቀት ያለውን ለማ መልከት ሳይሆን፣ የክርስቲያን ፍቅር ከግል ጥቅም ይልቅ የሌ ላውን ሰው ጥቅም እንደሚያስቀድም ለማሳየት ነው (ሮሜ 12፥10፤ ገላ 5፥13፤ ኤፌ 5፥21፤ 1ጴጥ 5፥5 ይመ)::

2፥4 *ራሳችሁን የሚጠቅመውን፣* ለሌሎችም የዚያኑ ያህል ማሰብ ከተቻለ፣ ለራስ ማሰብ ተገቢ መሆኑን የሚያሳይ ነው (ከሮሜ 15፥1 ጋር ያነጻጽሩ)::

2፥5 *በክርስቶስ... ኢየሱስ የነበረው ያ አስተሳሰብ፣ በእናንተም፣* የክርስቶስ ማንነትና ሥራው እጅግ ልዩ ቢሆንም (ቍ6-11)፣ ክርስቲያኖች መሥዋዕትነት ያለበት ትሕትናና ፍቅር የተሞላው የክርስቶስ ልብ ሊኖራቸው ይገባል (ቍ 2-4፤ ማቴ 11፥29፤ ዮሐ13፥12-17 ይመ)::

2፥6-11፤ ይህ ክፍል የግጥም ባሕርይ አለው:: ግጥሙም የጥንት ክርስቲያኖች ይጠቀሙበት የነበረ መዝሙር ሲሆን (የቈላ 3፥16 ማብ ይመ)፣በኋላ ግን ጳውሎስ ወስዶ ሳያሻሽለው እንዳልቀረ ይገመታል:: ይህ እውነት ከሆነም ጳውሎስ ለእምነቱ ምን ያህል ራሱን እንደሰጠ ያመለክታል:: ምንባቡ የክርስቶስን መዋረድና (ቍ 6-8) መከበር (ቍ9-11) ይገልጻል::

2፥6 *በባሕርዩ አምላክ፣* ኢየሱስ ፍጹም አምላክ መሆኑን ያረጋግጣል (የሮሜ 9፥5ማብ ይመ):: *ባሕርይ፣* የእግዚአብሔርን አምላካዊ ማንነት በግልጽ የሚያሳይ ነው (አማራጭ ትርጕሙን ይመ):: *ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን፣* ከመለኮታዊ ባሕርይ የሚመነጭ ማዕረግና ልዩ መብት ነው:: *ሊለቀው እንደማይገባ፣* ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ከመገለጡ በፊት በአብ ዘንድ የነበረው ክብሩ ባሕርዩ እንጂ በግድ ወይም በኀይል የወሰደው አለመሆኑን የሚገልጽ ነው፤ ሆኖም ከዚያ ታላቅ ክብር ዝቅ ብሎ ራሱን በማ ዋረድ ወደዚህ ዓለም መምጣት አልከበደውም በሌላ በኩል ደግሞ ይህን ክብር እንደ ሽልማት ገና የሚጨብጠው እንደሆነ ተደርጎም ሊታይ ይችላል::

2፥7 *ራሱን ባዶ አደረገ፣* ጌታ ይህን ያደረገው መለኮት ነቱን በመልቀቅ ሳይሆን፣ ክብሩን በፈቃዱ ትቶ (ዮሐ 17፥5ይመ) ሰው ወደ መሆን ደረጃ ራሱን በማዋረድ ነው (2ቆሮ 8፥9ይመ):: ጌታ ኢየሱስ ፍጹም ሰውና ፍጹም አምላክ ነው:: በሌላ በኩል ራሱን ባዶ አደረገ ሲል መለኮታዊ ባሕርዩን ተወ ማለት ሳይሆን፣ የተለየ መብቱን ይኸውም ለመለኮትነቱ የሚገባውን ከፍተኛ ሥልጣንና ቦታ ለጊዜው ወደ ጐን አደረገ ማለት ሊሆን ይችላል:: *የባሪያን መልክ፣* ምን ያህል ራሱን ዝቅ እንዳደረገ ያመለክታል (ማቴ 20፥28 ይመ)፤ አገልጋይ እንደ መሆኑም መጠን ዘወትር የአብን ትእዛዝ ያከብር ነበር::

2፥8 *ሰው ሆኖ፣* ኢየሱስ በሰው አምሳል ብቻ የተገለጠ አልነበረም (ቍ 7) ነገር ግን እውነተኛውን የሰው ሁኔታና ባሕርይ የራሱ አድርጎአል (ዮሐ 1፥14፤ ሮሜ 8፥3፤ ዕብ 2፥17 ይመ):: *ራሱን ዝቅ አደረገ፣* ቍ7፤ 2ቆሮ 8፥9 ይመ:: *እስከ ሞት፣* የኢየሱስን የታዛዥነቱን ፍጹምነትና ከፍተኛነት በአጽንዖት የሚገልጽ ነው:: *በመስቀል ላይ፣* ኢየሱስ ምን ያህል ራሱን እንዳዋረደ የሚያሳይ ነው፤ ለተረገመ ሰው የሚገባውን ሞት ሞተ (ገላ 3፥13፤ ዕብ 12፥2 ይመ):: በዘመኑ በመስቀል ላይ መሞት በሰው ላይ ከሚፈጸሙት ቅጣቶች ሁሉ የውርደት ቅጣት ነበር:: *ታዛዥ ሆነ፣* ኢየሱስ ራሱን ዝቅ ለማድረጉ ምልክት ነው (ከዕብ 5፥7-8 ጋር ያነጻ ጽሩ):: አገልጋይ (ቍ7) ይታዘዛል ::

2፥9 *ከፍ አደረገው፣* ማቴ 28፥18፤ ሐሥ 2፥33 ይመ፤ ከኢ ሳ 52፥13 ጋር ያነጻጽሩ:: *ከስምም ሁሉ በላይ የሆነውን ስም፣* ይህም መደበኛ ስሙን ሳይሆን፣ ለኢየሱስ የተሰጠውን ሥልጣን ወይም ማዕረግ ማለትም ከፍተኛ የክብር ስፍራውን ያመለክታል (ከኤፌ1፥21፤ ከዕብ 1፥4-5 ጋር ያነጻጽሩ)::

2፥10-11 *ይንበረከክ ዘንድ ... ይመሰክር ዘንድ፣* ከኢሳ 45፥23 ጋር ያነጻጽሩ:: ሰው ሁሉ ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ዐውቆ እንዲያመልከውና እንዲያገለግለው፣ የእግዚአብሔር ሐሳብ ነው:: በመጨረሻም ሰው ሁሉ ወደደም ጠላም የኢየሱስን ጌትነት የሚመሰክርበት ጊዜ ይመጣል (ሮሜ 14፥9 ይመ)::

2፥12 *ስለዚህ፣* በቍ5-11 ላይ የተገለጸውንና ወደር የሌለውን የክርስቶስን ምሳሌነት ያመለክታል:: *ታዛዦች እንደ ነበራችሁ* በጳውሎስ

## እንደ ከዋክብት ማብራት

12ስለዚህ፣ ወዳጆቼ ሆይ፤ ሁልጊዜም ታዛገሮች
እንደ ነበራችሁ ሁሉ፣ አሁንም እኔ በአጠ
ገባችሁ ሳለሁ ብቻ ሳይሆን፣ ይልቁንም አሁን
በሌለሁበት ጊዜ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራ
ሳችሁን መዳን ፈጽሙ፤ 13እንደ በጎ ፈቃዱ
መፈለግንና ማድረግን በእናንተ ውስጥ የሚ
ሠራ እግዚአብሔር ነውና።

14ማንኛውንም ነገር ሳታጕረመርሙና ሳትከ
ራከሩ አድርጉ፤ 15ይኸውም በጠማማና በክፉ
ትውልድ መካከል ንጹሓንና ያለ ነቀፋ፣ ነው
ርም የሌለባቸው የእግዚአብሔር ልጆች ሆናችሁ፣
እንደ ከዋክብት በዓለም ሁሉ ታበሩ ዘንድ
ነው። 16የሕይወትንም ቃል ስታቀርቡ[ሰ]፣ በከ
ንቱ እንዳልሮጥሁ ወይም በከንቱ እንዳልደ
ከምሁ በክርስቶስ ቀን የምመካበት ይሆንል
ኛል። 17ነገር ግን በእምነታችሁ መሥዋዕትና
አገልግሎት ላይ እንደ መጠጥ ቍርባን ብፈስ
እንኳ ከሁላችሁ ጋር ደስ ይለኛል፤ ሐሤትም
አደርጋለሁ። 18እናንተም እንደዚሁ ከእኔ ጋር
ደስ ልትሰኙና ሐሤት ልታደርጉ ይገባል።

## ጢሞቴዎስና አፍሮዲጡ

19ስለ እናንተ ሰምቼ ደስ እንዲለኝ፣ ጢሞ
ቴዎስን ቶሎ ወደ እናንተ ልልክላችሁ በጌታ
ኢየሱስ ተስፋ አደርጋለሁ። 20ስለ እናንተ
ድኅነት የሚገደው እንደ እርሱ ያለ ማንም
የለኝም፤ 21ሁሉም የኢየሱስ ክርስቶስን ሳይሆን
የራሳቸውን ፍላጎት ለሟሟላት ይሯሯጣሉና።
22ነገር ግን እንደምታውቁት ጢሞቴዎስ ማን
ነቱን አስመስክሮአል፤ ልጅ ከአባቱ ጋር እን
ደሚያገለግል፣ ከእኔ ጋር በወንጌል ሥራ አገለ
ግሎአልና። 23እንግዲህ የራሴን የወደፊት ሁኔታ
እንዳጣራሁ ልልከው ተስፋ አደርጋለሁ።
24እኔም ራሴ ቶሎ እንደምመጣ በጌታ ታም
ኛለሁ። 25እንዲሁም ወንድሜን፣ የሥራ ባልደ
ረባዬንና አብሮኝ ወታደር የሆነውን፣ በሚያስ
ፈልገኝ ሁሉ እንዲንከባከበኝ የላካችሁትን፣
የእናንተ መልእክተኛ የሆነውን አፍሮዲጡን
መልሼ እንድልክላችሁ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼ
ዋለሁ። 26እርሱ ሁላችሁንም ይናፍቃልና፤ መታ
መሙን ስለ ሰማችሁም ተጨንቆአል። 27በእር
ግጥም ታሞ ለሞት ተቃርቦ ነበር፤ እግዚአብሔር
ግን ምሕረት አደረገለት፤ በሐዘን ላይ ሐዘን
እንዳይደራረብብኝ፣ ለእኔም ጭምር እንጂ ለእ
ርሱ ብቻ አይደለም። 28ስለዚህ እርሱን እንደ
ገና ስታዩ ደስ እንዲላችሁና የእኔም ጭንቀት
እንዲቀል ልልከው በጣም ጓጕቻለሁ። 29በሙሉ
ደስታ በጌታ ተቀበሉት፤ እንደ እርሱ ያሉት
ንም ሰዎች አክብሯቸው። 30እርሱም እናንተ
ልትሰጡኝ ያልቻላችሁትን አገልግሎት ለማሟ
ላት ሲል ለሕይወቱ እንኳ ሳይሳሳ፣ ለክርስቶስ
ሥራ ከሞት አፋፍ ደርሶ ነበርና።

[ሰ]16 ሰትይዙ

14፥11፤ኤፌ1፥10፤
2፥12 2ቆሮ7፥15
2፥13 ዕዝ1፥5፤ 1ቆሮ12፥6፤15፥10፤ ገላ2፥8፤ኤፌ1፥5፤ ዕብ13፥21
2፥14 1ቆሮ10፥10፤ 1ጴጥ4፥9
2፥15 ማቴ5፥45፡48፤ሐሥ2፥40፤ ኤፌ5፥1፤1ተሰ3፥13
2፥16 1ቆሮ1፥8፤ 9፥24፤1ተሰ2፥19
2፥17 ሮሜ15፥16፤ 2ቆሮ6፥10፤12፥15፤ 2ጢሞ4፥6
2፥19 ቍ23፤ ሐሥ16፥1
2፥20 1ቆሮ16፥10
2፥21 1ቆሮ10፥24
2፥22 1ቆሮ4፥17፤ 1ጢሞ1፥2
2፥23 ቍ19
2፥24 ፊል1፥25
2፥25 ሮሜ16፥3፡9፡21፤2ቆሮ8፥23፤ ፊል4፥3፡18፤ቆላ4፥11
2፥26 ፊል1፥8
2፥28 ቍ25
2፥29 1ቆሮ16፥18፤ 1ጢሞ5፥17

አማካይነት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች የመጣውን የእግዚአብሔ ርን ትእዛዝ ያመለክታል (ሮሜ 1፥5፤ 15፥18፤ 2ቆሮ 10፥5-6 ይመ)። *በአጠገባችሁ ሳለሁ፤* ጳውሎስ ሁለተኛውንና (ሐሥ 16፥12-40) ሦስተኛውን (ሐሥ 20፥1-3፡6) ሐዋርያዊ ጕዞዎች ባደረገበት ጊዜ ለማ ለት ነው። *በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ፤* እግዚአብሔርን የምንፈራው ከጭንቀትና ከሥጋት የተነሣ ሳይሆን፣ እርሱ ለሰጠን ጸጋ ምላሽ እንዲሆን በአንድ ዐላማ ሆነን ከልብ የመነጨ አክብሮት ለማስጠት መሆኑን የሚያመለክት ነው፡ *የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፤* እስከ መጨረሻ መጽናትን የሚያመለክት ነው፤ ሐሳቡ፣ ድነት በሥራ ሳይሆን በእምነት እንደሚገኝ ነው፤ ድነትን እስከመጨረሻ ለማጽናት ደግሞ በመንፈሳዊ ሕይወት መትጋትና ማደግ አስፈላጊ መሆኑን ይገልጻል። ድነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የምንቀበለው ስጦታ ብቻ ሳይሆን፣ አማኙ በመጽናት፣ በመንፈሳዊ ሕይወቱ በማደግና በመብሰል በሚያደርገው የማያቋርጥ ትጋት (ከማቴ 24፥13፤ ከ1ቆሮ 9፥24-27፤ ከዕብ 3፥14፤ 6፥9-11፤ ከ2ጴጥ 1፥5-8 ጋር ያነጻጽሩ)።

2፥13 *መፈለግንና ማድረግን፤* ፈቃድ ወይም እምነትና የእኛ መታዘዝ ተነጣጥለው የሚይታዩ አይደሉም (ከገላ 5፥6፤ ከያዕ 2፥18፡20፡22 ጋር ያነጻጽሩ)።

2፥14-17፤ *መዳናችንን ከፍጻሜ ለማድረስ የሚጠቅሙ* አንዳንድ ነገሮች በዚህ ክፍል ተጠቅሰዋል።

2፥14 *ሳታጕረመርሙ፤* በእግዚአብሔር ፈቃድ አለመርካት እግዚአብሔርን ደስ እንዳናሰኝ የሚያደርገን የጥርጥር ምልክት ነው፤ (ቍ13፤ ከ1ቆሮ 10፥10 ጋር ያነጻጽሩ)። *ሳትከራከሩ፤* ለቤተክርስቲያን እድገትና ለወንጌል መስፋፋት በማይጠቅሙ ጕዳዮች ላይ በመጨቃጨቅ ጊዜ መፍጀት አስፈላጊ አይደለም (2ጢሞ 2፥23፤ ቲቶ 3፥9 ይመ)።

2፥15 *ንጹሓንና ያለ ነቀፋ፤ ነውርም የሌለባቸው፤* በሙሉ ልብና በንጹሕ ሕሊና ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛትን እንጂ ፍጹም መሆንን የሚያመለክት አይደለም። *በጠማማና በክፉ ትውልድ፤* ያላመነውን ዓለም የሚገልጽ ነው (ሐሥ 2፥40፤ ኤፌ 2፥1-3 ይመ ከማቴ 17፥17 ጋር ያነጻጽሩ) *እንደ ከዋክብት... ታበሩ ዘንድ፤* ብርሃን በጨለማ እንደሚያበራ ሁሉ ክርስቲያኖችም በዙሪያቸው ላለው ዓለም ብርሃን ሊሆኑ ይገባቸዋል (ከማቴ 5፥15-16 ጋር ያነጻጽሩ)

2፥16 *በከንቱ፤* ከ1ቆሮ 9፥24-27 ጋር ያነጻጽሩ። *በክርስቶስ ቀን፤* የ1፥6 ማብ ይመ። *የምመካበት፤* ጳውሎስ በግሉ ከፈጸመው ነገር የተነሣ መኩራራቱ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በእርሱ አማካይነት በሠራው ሥራ መተማመኑን ያመለክታል (1ተሰ 2፥19 ይመ)።

2፥17-18 *ደስ ይለኛል ... እናንተም... ደስ ልትሰኙ ... ይገባል፤* የክርስቲያን ደስታ ምን ጊዜም፣ የጋራ ሊሆን ይገባዋል።

2፥17 *እንደሚፈስ የመጠጥ ቍርባን፤* በዘፀ 29፥ 38-41 ላይ እንደተጠቀሰው የብሉይ ኪዳን የመጠጥ ቍርባን በየዕለቱ ይቀርብ ነበር። *ከእምነታችሁ እንደሚመነጭ፤* እውነተኛ እምነት ሕያው ነው፤ የሚሠራም ነው (የቀ 13 ማብ ይመ)። *ብፈስ፤* እንደ ትልቅ የምስጋና መሥዋዕት የሚቈጠረውን የራሱን አገልግሎት አጠቃላይ ሁኔታ ያመለክታል፤ ይልቁንም፣ በሰማዕትነት ሕይወቱን የሚሰጥበትን የወቅቱን እስራቱን ይጠቍማል። ሕይወቱም መሥዋዕትነት በተሞላው የፊልጵስዩስ ሰዎች አገልግሎት ታጅቦ እንደ መጠጥ ቍርባን ይፈሳል።

*2፥19-23፤* በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ያለውን ሁኔታ ተረድቶ እንዲያስታውቀው፣ ጳውሎስ አብሮት በሮም የነበረውን (1፥1 ይመ)
ጢሞቴዎስን ሊልክ ያስባል።

2፥20 *እንደ እርሱ ያለ ማንም የለኝም፤* በቍ4 ላይ ከተሰጠው ምክር አንጻር ሲታይ ጢሞቴዎስ መልካም ምሳሌ ነው።

2፥21፤ በጢሞቴዎስና በሌሎች የጳውሎስ የሥራ ባልደረቦች መካከል የተደረገውን ጕልህ ንጽጽር ያሳያል፤ በንጽጽሩም ወጣቱ ጢሞቴዎስ የተሻለ ሆኖ በመገኘቱ ይመሰገናል።

2፥22 *ልጅ ከአባቱ ጋር፤* በጳውሎስና በጢሞቴዎስ መካከል የነበረው ኅብረት በ1ኛና በ2ኛ ጢሞቴዎስ መልእክቶች ከፍተኛ እድገት አሳይቶአል። *እንደሚያገለግል፤* እንደ ኢየሱስና እንደ ጳውሎስ ጢሞቴዎስም የአገልጋይነት ባሕርይ ነበረው።

2፥24፤ ጳውሎስ በቅርቡ ከእስር ቤት እንደሚፈታ ይገምታል (1፥25 ይመ)።

2፥25-30፤ አፍሮዲጡ ታሞ ለሞት ተቃርቦ ነበር (ቍ 27፡30)፤ አሁን ግን ድኖ ወደ አገሩ ወደ ፊልጵስዩስ ተልኮአል።

2፥25 *መልእክተኛ፤* የግሪኩ ትርጕም ሰፋ ባለ መልኩ፣ "ሐዋርያ" ለሚለው ቃል የሚቆም ሲሆን፣ በዚህ ስፍራ የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ተወካይ የነበረውን አፍሮዲጡን ያመለክታል (ከ2ቆሮ 8፥23 ጋር ያነጻጽሩ)።

2፥27፤ ከ1፥21-26 ጋር ያነጻጽሩ።

2፥28 *ጭንቀት፤* ለክርስትና ሕይወትና ለወንጌል አገልግሎት ያለውን ሸክም ያመለክታል (የ 4፥6 ማብ ይመ፤ ከ2ቆሮ 4፥8፤ 11፥28 ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥1 *ከዚህ በተረፈ፤* ጳውሎስ ወደ መልእክቱ መደምደሚያ በተቃረበ ጊዜ፣ ወደሚቀጥለው ክፍል ለመሸጋገር የተጠ

## በሥጋ አለመመካት

3 ከዚህ በተረፈ ወንድሞቼ ሆይ፣ በጌታ
ደስ ይበላችሁ። ያንኑ ደግሜ ብጽፍላችሁ
እኔ አይሰለቸኝም፤ ለእናንተም ይጠቅማች
ኋል። [2]ከእነዚያ ውሾች ተጠንቀቁ፤ ክፉትን
ከሚያደርጉና ሥጋን ከሚቈራርጡ ሰዎች
ተጠበቁ። [3]እኛ በእውነት የተገረዝን በእግዚ
አብሔር መንፈስ የምናመልክ፣ በክርስቶስ ኢየ
ሱስ የምንመካ፣ በሥጋም የማንታመን ነንና።
[4]ካስፈለገ እኔም በሥጋ የምመካበት አለኝ።
ማንም በሥጋ የሚመካበት ነገር ያለው
ቢመስለው፣ እኔ እበልጠዋለሁ፤ [5]በስምንተኛው
ቀን የተገረዝሁ፣ ከእስራኤል ዘር፣ ከብንያም
ወገን የተወለድሁ ስሆን፣ ከዕብራውያንም ዕብ
ራዊ ነኝ፤ ስለ ሕግ ከተነሣ፣ ፈሪሳዊ ነበርሁ፤
[6]ስለ ቅናት ከሆነ፣ የቤተ ክርስቲያን አሳዳጅ
ነበርሁ፤ ሕግን በመፈጸም ስለሚገኝ ጽድቅ
ከሆነም፣ ያለ ነቀፋ ነበርሁ።
[7]ነገር ግን ይጠቅመኝ የነበረውን ሁሉ
አሁን ለክርስቶስ ስል እንደ ጒድለት ቈጥ
ሬዋለሁ። [8]ከዚህም በላይ ለእርሱ ብዬ ሁሉን
ነገር የተውሁለትን፣ ወደር የሌለውን ጌታዬን
ክርስቶስ ኢየሱስን ከማወቅ ታላቅነት ጋር ሳነ
ጻጽር፣ ሁሉንም ነገር እንደ ጒድለት እቈጥ
ረዋለሁ፤ ለእርሱ ስል ሁሉን አጥቻለሁ፤ ክር
ስቶስን አገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ ጒድፍ እቈጥ
ራለሁ፤ [9]ሕግ በመጠበቅ የሚገኝ የራሴ ጽድቅ
ኖሮኝ ሳይሆን፣ በክርስቶስ በማመን ይኸውም
ከእግዚአብሔር የሚመጣ፣ ከእምነትም በሆነ
ጽድቅ በእርሱ ዘንድ እንድገኝ ነው። [10]ክርስ
ቶስንና የትንሣኤውን ኀይል እንዳውቅ፣ በሥ
ቃዩ ተካፋይ እንድሆንና በሞቱም እርሱን
እንድመስል እመኛለሁ፤ [11]ለሙታን ትንሣኤም
እንድደርስ እናፍቃለሁ።

## ወደ ግብ ለመድረስ መፍጠን

[12]ይህን ሁሉ አግኝቻለሁ ወይም ፍጹም
ሆኛለሁ ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ክርስቶስ
ኢየሱስ እኔን የራሱ ያደረገበትን ያን፣ እኔም
የራሴ ለማድረግ እጣጣራለሁ። [13]ወንድሞች

2፥30 1ቆሮ16፥17
3፥1 ፊል2፥18
3፥2 መዝ22፥16፡ 20፤ራእ22፥15
3፥3 ሮሜ2፥28፡29፤ 15፥17፤ገላ6፥14፡15፤ ቈላ2፥11
3፥4 2ቆሮ11፥21
3፥5 ሉቃ1፥59፤ ሐሥ23፥6፤ሮሜ 11፥1፤2ቆሮ11፥21፡ 22
3፥6 ቍ9፤ሐሥ 8፥3፤21፥20፤ ሮሜ9፥30፤10፥5
3፥7 ማቴ13፥44፤ ሉቃ14፥33
3፥8 ቍ10፤ መዝ73፥25፤ኤር 9፥23፡24፤ዮሐ17፥3፤ ኤፌ4፥13፤2ጴጥ1፥2
3፥9 ቍ6፤ኤር 33፥16
3፥10 ቍ8፤ሮሜ 6፥3-5፤2ቆሮ1፥5
3፥11 ዮሐ11፥24፤ ሮሜ6፥5፤ራእ20፥5፡6
3፥12 ሐሥ9፥5፡6፤ 1ጢሞ6፥12

ቀመበት ቃል ነው፤ ሆኖም ይህ ቃል መልእክቱ መዘጋቱን አያመለክትም (ከ 4፥8 ጋር ያነጻጽሩ)። *በጌታ ደስ ይበላችሁ፤* 4፥4 ይመ። *ያንኑ ደግሜ፤* በሚቀጥሉት ቍጥሮች ውስጥ የተዘረዘረው ሐሳብ ጳውሎስ ቀደም ሲል በፊልጵስዩስ በነበረ ጊዜ በቃል፣ ምናልባትም ደግሞ አስቀድሞ በተጻፈው ደብዳቤ ውስጥ የተካተተ ነው። *ይጠቅማችኋል፤* ስሕተት በበዛበት አካባቢ፣ ነገርን ደጋግሞ መናገር ለዕርግት ይረዳል።

3፥2 *ውሾች፤* በዘመኑ የነበሩ ሐሰተኛ አስተማሪዎች የስሕተታቸውን ከባድነትና የሚያስከትለውን አፍራሽ ተልእኮ አጠንክሮ ለመግለጽ የተጠቀመበት ቃል ነው (ከገላ 5፥15 ጋር ነጻጽሩ)፤ የሚያስተምሩትም ትምህርት፣ ጳውሎስ በገላትያ አብያተ ክርስቲያናት ተቃውሞ ከነበረው ጋር የሚመሳሰል ሳይሆን አይቀርም (ከገላትያ መግቢያ "ወቅትና ዓላማ"የሚለውን ይመ)። *ሥጋን ከሚቈራርጡ፤* ይህም ጠንከር ያለ የሚጐዳ አገላለጽ ነው፤ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ግዝረት ስውነትን በከንቱ ከመቈራረጥ በስተቀር ሌላ ፋይዳ እንደሌለው በመቍጠር፣ ትርጒሙን አጣመው እንዳቀረቡ የሚያመለክት ነው (ከቍ 3 ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥3 *የተገረዝን፤* ትክክለኛው የግርዘት ትርጒም በእውነት እግዚአብሔርን በሚያመልኩና በራሳቸው ሥራ ሳይሆን፣ በክርስቶስ አዳኝነት በሚመኩ አማኞች ሕይወት በተግባር የሚታይ ነው (ከሮሜ 2፥28-29፤ ቈላ 2፥12-13፤ ጋር ያነጻጽሩ፤ እንደዚሁም ዘዳ30፥6፤ ሕዝ36፥26 ይመ)። *የምንመካ ...የማንታመን፤* ሰው በክርስቶስ ወይም በራሱ መመካቱ አይቀርም። *በሥጋም፤* ደካማውን ሰብዓዊ ባሕርይ ያመለክታል። በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ ሥጋ የሚለው ቃል ኃጢአተኛውን ሰው የሚያመለክት ቢሆንም በዚህ ቍጥር ላይ ግን አስተማማኝ ስላልሆነውና ከምንም ሊያድን ስለማይችለው ስለ ደካማው ሰውነታችን ይናገራል።

*3፥4-14፤* በዚህ ስፍራ ለማንም አማኝ መልካም ምሳሌነት ያለው የጳውሎስ የግል ምስክርነት ተጠቅሶአል። ይህም በመልእክቶቹ ስለ ራሱ ከጻፋቸው እጅግ በጣም አስፈላጊ ከሆኑት ክፍሎች አንዱ ነው (ገላ1፥13-24፤1ጢሞ1፥12-16 ይመ፤ከሐሥ22፥1-21፤ 26፥1-23 ጋር ያነጻጽሩ)።

*3፥4-6፤* ጳውሎስ ወደ ክርስትና ከመምጣቱ በፊት የነበረው ትምክህት ከአይሁዳዊነቱ የተነሣ በነበረው ልዩ መብትና በሥራው ሥራ ላይ የተመሠረተ ነው።

3፥5 *በስምንተኛው ቀን፤* ዘፍ17፥12 ይመ። *ከእስራኤል ዘር፤* ጳውሎስ ወደ ይሁዲነት የገባ አሕዛባዊ ሳይሆን በትውልዱ አይሁዳዊ ነበር። *ከብንያም ወገን፤* የአይሁዳዊነት ሥረ መሠረቱም ጥልቅ ስለ ሆነ፣ አሻሚ አይደለም ቅድስቲቷም ከተማ ኢየሩሳሌም፣ ለብንያም ነገድ በተሰጠው ርስት ጠረፍ ላይ ትገኛለች። *ከዕብራውያንም ዕብራዊ፤* በቋንቋ፣ በባሕርይና በኑሮ ዘይቤ ማለት ነው (ሐሥ22፥2-3፤ገላ1፥14 ይመ)። *ፈሪሳዊ፤* ሐሥ22፥3፤23፥6፤26፥5 ይመ።

3፥6 *ሕግን በመፈጸም ስለሚገኝ ጽድቅ፤* ሕግን በመጠበቅ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትና በረከትን ለማግኘት የሚደረገውን ጥረት ለማመልከት ነው (ከቍ 9 ጋር ያነጻጽሩ)። በዚህ መንገድ ጽድቅን ለማግኘት መሞከር ወንጌልን የሚቃረን ስለሆነ ጳውሎስ ተቃውሞታል (ሮሜ3፥27-28፤4፥1-5፤ገላ 2፥16፤3፥10-12 ይመ)። *ያለ ነቀፋ፤* ጳውሎስ ሕግን ከመጠበቅ አንጻር ጥንቁቅና እንከን የማይወጣለት ሰው ነበር።

*3፥7-14፤* ጳውሎስ ትምክህቱ በክርስቶስ ላይ እንደ ነበር ያመለክታል።

3፥7 *ሁሉ፤* በቍ 5-6 የተዘረዘሩ ነገሮች ናቸው። *ይጠቅመኝ ... ጒድለት፤* ወደ ደማስቆ በሚወስደው መንገድ ላይ በጳውሎስ ሕይወት ውስጥ ትልቅ ለውጥ ሆነ (ሐሥ 9፥3-16 ይመ)፤ ራሱን ማእከል ከደረገው ሕይወት ክርስቶስን ማእከል ወዳደረገው ሕይወት ተሸጋገረ።

3፥8 *ክርስቶስ ኢየሱስን ከማወቅ፤* የአእምሮን ዕውቀት ብቻ ሳይሆን፣ ከታላቅነቱ የተነሣ የሰውን ሁለንተና የሚለውጠውን ጌታ በተግባር ማወቅን ያመለክታል፤ ቀጥለው ያሉትም ቍጥሮች ይህንኑ ሐሳብ የሚያብራሩ ናቸው። *እንደ ጒድፍ፤* ጳውሎስ ወደ ክርስቶስ ከመጣ በኋላ እጅግ የከበረ ሕይወት እንዳገኘና ከዚያ በፊት የነበረው ሕይወቱ ግን ውርደት የተሞላና ዋጋ የሌለው እንደ ነበረ ይመሰክራል።

3፥9 *በእርሱ ዘንድ እንድገኝ፤* ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆንን ያመለክታል (የ2፥1 ማብ ይመ፤ ከ1ቆሮ1፥30 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይህም ባለፈው የተደረገ ልምምድ ብቻ ሳይሆን አሁንም ያለ፣ ወደፊትም የሚቀጥል ነው። *ሕግ በመጠበቅ... ጽድቅ፤* የቍጥር 6 ማብ ይመ። *በማመን ... ጽድቅ፤* ከክርስቶስ ጋር ባለን ኅብረት የምናገኘው ትልቁ በረከት ነው (ሮሜ 3፥21-22፤ 1ቆሮ 1፥30፤ ገላ2፥16 ይመ)።

3፥10 *ክርስቶስንና ... እንዳውቅ፤* በቍ8 ላይ እንደተጠቀሰው ይህ ዕውቀት በአእምሮ ደረጃ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የትንሣኤውን ኀይል መለማመድን (ኤፌ 1፥17-20 ይመ)፤ በመከራው ከእርሱ ጋር መተባበርንና (ከሐሥ 9፥16 ጋር ያነጻጽሩ)፤ በሞቱም እርሱን መምሰልን (2ቆሮ4፥7-12፤ 12፥9-10 ይመ) የሚያጠቃልል ነው፤ አማኞች ባመኑ ጊዜ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ተካፋዮች ሆነዋል (ከሮሜ6፥2-13፤ከገላ2፥20፤5፥24፤6፥14፤ከኤፌ2፥16፤ከቈላ2፥12-13፤ 3፥1 ጋር ያነጻጽሩ)። በቍጥር 10 ላይ ግን ጳውሎስ ራሱ የክርስቶስንና የትንሣኤውን ኀይል በሕይወቱ መለማመዱን፣ ለእርሱና ከእርሱም ጋር እስከ ሞት ድረስ እንኳ መከራ እንደሚቀበል ይናገራል።

3፥11 *እናፍቃለሁ፤* ቃሉ ከልብ መጓጓትንና ተስፋ ማድረግን እንጂ ጥርጥርን ወይም እርግጠኛ ያለመሆንን አያመለክትም። *ትንሣኤ፤* እያንዳንዱ አማኝ በግል የሚጠብቀው ታላቅ ተስፋ ነው (ዳን12፥2፤ ዮሐ5፥29፤ ሐሥ24፥15፤1ቆሮ15፥23፤1ተሰ4፥16 ይመ)።

*3፥12-14፤* የክርስትና ሕይወት ከእሽቅድምድም ጋር ይመሳሰላል፤ በሌላም ቦታ ጳውሎስ የሩጫ ውድድርን ለተመሳሳይ ሁኔታ በምሳሌነት ይጠቀማል (1ቆሮ9፥24-27፤1ጢሞ6፥12፤2ጢሞ4፥7-8 እንዲሁም ከማቴ24፥13፤ከዕብ12፥1 ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥12 *እኔን የራሱ ያደረገበትን...የራሴ ለማድረግ፤* የክርስቶስ ግብ የጳውሎስም ግብ ነው። ጳውሎስ በፊቱ ያለውን ግብ ይጨብጥ ዘንድ ክርስቶስ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ያዘጋጅለታል (ቍ14፤ከ2፥12-13 ጋር ያነጻጽሩ)።

ሆይ፤ እኔ እንደ ያዝሁት አድርጌ ራሴን አል
ቈጥርም፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤
ከኋላዬ ያለውን እየረሳሁ ከፊቴ ወዳለው እዘ
ረጋለሁ:: [14]እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ
ወደ ላይ ስለ ጠራኝ፣ ሽልማት ለመቀዳጀት
ወደ ግቡ እፈጥናለሁ::
[15]እንግዲህ እኛ ብስለት ያለን ሁላችን
ነገሮችን በዚህ ሁኔታ ማየት ይኖርብናል፤
በአንዳንድ ነገር የተለያየ አስተሳሰብ ቢኖራ
ችሁ፣ እግዚአብሔር እርሱንም ይገልጥላችኋል።
[16]ሆኖም በደረስንበት በዚያ እንመላለስ።
[17]ወንድሞች ሆይ፤ የእኔን አርአያነት በመ
ከተል ከሌሎች ጋር ተባበሩ፤ እኛ በሰጠናችሁ
ምሳሌነት መሠረት የሚኖሩትንም አስተውሉ።
[18]ምክንያቱም ከዚህ በፊት ደጋግሜ እንደ ነገ
ርኋችሁ፣ አሁንም እንደ ገና፣ ያውም በእንባ
እነግራችኋለሁ፤ ብዙዎች የክርስቶስ መስቀል
ጠላቶች ሆነው ይመላለሳሉ:: [19]መጨረሻቸው
ጥፋት ነው፤ ሆዳቸው አምላካቸው ነው፤ ክብራ
ቸው በነውራቸው ነው፤ ልባቸው ያረፈው በምድ
ራዊ ነገር ላይ ነው:: [20]እኛ ግን አገራችን በሰ
ማይ ነው፤ ከዚያ የሚመጣውንም አዳኝ፣ ጌታ
ኢየሱስ ክርስቶስን በናፍቆት እንጠባበቃለን፤
[21]እርሱም ሁሉን ለራሱ ባስገዛበት ኀይል፣
ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋ
ችንን ይለውጣል::

4 ስለዚህ የምወዳችሁና የምናፍቃችሁ፣
ወንድሞቼ ደስታዬና አክሊሌ የሆናችሁ፣
እንዲሁም ወዳጆች ሆይ፤ በዚህ ሁኔታ በጌታ
ጸንታችሁ ቁሙ::

### የጳውሎስ ምክር

[2]በጌታ አንድ ልብ እንዲኖራቸው ኤዎድ
ያንን እለምናለሁ፤ ሲንጢኪንንም እለምና
ለሁ:: [3]አዎን፤ አንተ ታማኝ የሥራ ባልደረባዬ
ሆይ፤ ወንጌልን በማሰራጨት ረገድ ከእኔና ከቀ
ሌምንጦስ ጋር፣ እንዲሁም ስሞቻቸው በሕይወት
መጽሐፍ ከተጻፉት ከሌሎች የሥራ ጓደኞቼ ጋር
የተጋደሉትን እነዚህን ሴቶች እንድትረዳቸው
እለምንሃለሁ::
[4]ምንጊዜም በጌታ ደስ ይበላችሁ፤ ደግሜ
እላለሁ ደስ ይበላችሁ:: [5]ገርነታችሁ በሁሉ

1ቆሮ13፥10፤
3፥13 ሉቃ9፥62
3፥14 ሮሜ8፥28፤
1ቆሮ9፥24፤ዕብ6፥1
3፥15 1ቆሮ2፥6፤
ገላ5፥10፤ኤፌ1፥17፤
1ተሰ4፥9
3፥17 1ቆሮ4፥16፤
1ጢሞ4፥12
3፥18 ሐሥ20፥31፤
ገላ6፥12
3፥19 መዝ73፥17፤
ሮሜ6፥21፤8፥5:6፤
16፥18፤ቈላ3፥2፤
ይሁ13
3፥20 1ቆሮ1፥7፤
ኤፌ2፥19፤ቈላ3፥1፤
ዕብ12፥22
3፥21 ሮሜ8፥29፤
1ቆሮ15፥43-53፤ኤፌ
1፥19፤ቈላ3፥4
4፥1 1ቆሮ16፥13፤
ፊል1፥8
4፥2 ፊል2፥2
4፥3 ፊል2፥25፤
ራእ20፥12
4፥4 መዝ85፥6፤
97፥12፤ዕን3፥18፤
ማቴ5፥12፤ሮሜ

3፥13 *እየረሳሁ፣* ያለፈውን ሁኔታ አንድ ጊዜ እንደ ተፈጸመ ቈጥሮ ተወው እንጂ በኀጢአት ያሳለፈውን ዘመን ሙሉ በሙሉ ረስቶታል ማለት አይደለም (ቍ4-6 ይመ)::

3፥14 *ሽልማት፣* በግሪኩ አገር በሩጫ እሽቅድምድም ያሸነፈ ሰው ጕንጕን አበባ ይደረግለት፣ አንዳንድ ጊዜም ገንዘብ ይሸለም ነበር፤ ክርስቲያንም እንደዚሁ የዘለዓለም ክብር ሽልማት ይቀበላል:: *ወደ ላይ፣* ትልቁ የጳውሎስ ናፍቆት በዚህ ምድር ያለውን ሳይሆን፣ በላይ በሰማይ ያለውን ለማግኘት ነው፤ ክርስ ቶስ በዚያ ነውና (ቈላ 3፥1-2 ይመ)::

3፥15 *ብስለት፣* በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ያደረጉትንና የተደላደሉትን ያመለክታል (1ቆሮ2፥6፤3፥1-3፤ዕብ5፥14 ይመ):: *በዚህ ሁኔታ፣* ከቍጥር 12-15 እንደ ተገለጸው፣ ገና ያልተወጣ ተራራ ስላለ፣ ቢቃኝ ብሎ ዐርፎ መቀመጥ እንደማይገባ የሚያሳይ ነው:: *የተለያየ አስተሳሰብ፣* አማኞቹ ከቍጥር 12-14 ያለውን ዋና ሐሳብ ከተቀበሉ በኋላ በትናንሽ ነገሮች ላይ የአስተሳሰብ ልዩነት በመካከላቸው ቢፈጠር፣ ምስጢሩን እግዚአብሔር ይገልጽላቸዋል::

3፥16 *በደረስንበት... እንመላለስ፣* የተረዱትን እውነት በተግባር እንዲገልጹ ያሳስባቸዋል፤ እኛም አሁን በያዝነው እውነት እንኖርበት ዘንድ ኀላፊነት አለብን

3፥17 *የእኔን አርአያነት በመከተል፣* ጳውሎስ የክርስቶስን ምሳሌነት እንደተከተለ ሁሉ፣ እነርሱም የእርሱን ምሳሌነት እንዲከተሉ ያሳስባል:: *የሚኖሩትንም አስተውሉ፣* ክርስቲያኖች የሚ ኖሩት ሕይወት፣ ሌሎች ሊከተሉት የሚገባ መልካም ምሳሌነት ያለው መሆን አለበት::

3፥18 *ከዚህ በፊት ... እንደነገርኋችሁ፣* ቍጥር 1 ይመ:: *በእንባ፣* ሐሥ20፥19:31 ይመ:: *የክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ሆነው ይመላለሳሉ፣* ከጳውሎስ ባሕርይና (ቍ10) ከወንጌል እውነት ጋር በብርቱ የሚጻረሩ ናቸው::

3፥19 *ጥፋት፣* የድነት ተቃራኒ ነው:: *ሆዳቸው አምላካቸው፣* ሥር የሰደደ ራስ ወዳድነትን ያመለክታል፤ በሁሉ ነገር ፍላጎታቸውን ያስቀድማሉ:: *በምድራዊ ነገር፣* ሐሳባቸው በሚያልፈው በአሁኑ ሕይወት ላይ የተመሠረተ ነው፤ ለሕግ መታዘዝ እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ፤ በቍ2 ላይ ከተጠቀሱት ወገ አጥባቂዎች ጋር የሚጻረሩ ናቸው::

3፥20 *አገራችን፣* ክርስቲያኖች ለጥቂት ጊዜ በምድር የሚኖሩ መጻተኞች እንጂ የምድር ዜጎች አይደሉም (ከዮሐ 17፥14-16፤ ከ1ቆሮ7፥29-31፤ከ1ጴጥ2፥11 ጋር ያነጻጽሩ):: *በሰማይ፣* ክርስቶስ ባለበትና አማኞች ከክርስቶስ ጋር በአንድነት በሚገኙበት ስፍራ ማለት ነው፤ በቍጥር 19 ላይ "በምድራዊ ነገር" ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ (ኤፌ2፥6፤ቈላ3፥1-4 ይመ):: *ከዚያ ... በናፍቆት እንጠባበቃለን፣* ሮሜ8፥19፤1ቆሮ1፥7፤1ተሰ1፥9-10፤ 2ጢሞ 4፥8 ይመ::

3፥21 *ሁሉን ለራሱ ባስገዛበት ኀይል፣* ክርስቶስ እስከ ሞትም ያውም በመስቀል ላይ እስከ መሞት ድረስ በመታዘዙ (2፥8 ይመ) ያገኘው፣ በትንሣኤውና በዕርገቱ የተቀበለው ኀይሉ ሁሉን የሚገዛና ፍጹም ነው (ማቴ 28፥18፤ 1ቆሮ 15፥27፤ ኤፌ 1፥20-22 ይመ):: *የእርሱን ክቡር ሥጋ እንዲመስል፣* ሮሜ 8፥29፤1ዮሐ3፥2 ይመ:: በክብር የሆነው ክርስ ቶስ ቀደም ሲል የተቀበለውን የትንሣኤ አካል፣ በሚመጣው የትንሣኤ ጊዜ አ ማኞችም ይቀበሉታል (1ቆሮ 15፥20:49 ይመ):: ይህም መለወጥ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ስለሚፈጸም "መንፈሳዊ" ነው (1ቆሮ 15፥44:46 ይመ):: *የተዋረደውን ሥጋችንን፣* በኀጢአት ምክንያት ለድካም፣ ለመ በስበስና ለሞት የተሰጠውን ማለቱ ነው (ሮሜ 8፥10:20-23፤ 1ቆሮ15፥42-44 ይመ):: *ይለውጣል፣* ይህም በትንሣኤ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል የሚፈጸም ነው (ሮሜ 8፥11፤1ቆሮ 6፥14፤ 15፥50-53 ይመ)::

4፥1 *የምወዳችሁና የምናፍቃችሁ፣* የ1፥8፤2፥1 ማብ ይመ:: *ደስታዬና አክሊሌ፣* ይህ እውን የሚሆነው አሁን ብቻ ሳይሆን በተ ለይም ክርስቶስ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ ነው (1ተሰ2፥19 ይመ):: *በዚህ ሁኔታ፣* በም 3 ላይ የተነሣው አሳብ መጠቃለሉን ያመለክታል፤ የፊልጵስዩስ ሰዎች ሐሳባቸውን በላይ በሰማይ ባለው ነገር ላይ በማድረግ (3፥20-21)፣ ሕግ መጠበቅ አያስፈልግም በሚሉ ሰዎች ፊት (3፥18-19) የጳውሎስን ምሳሌነት መከተል ነበረባቸው (3፥17):: *ጸንታችሁ ቁሙ፣* በወቅቱ ስለ ወንጌል ተነሥቶ በነበረው ተቃውሞ ውስጥ፣ ስፍራቸውን ሳይለቁ እንዲ ቆሙ የተሰጠ ማሳሰቢያ ነው (ከ1፥27-30፤ከ1ቆሮ15፥58 ጋር ያነጻ ጽሩ)::

*4፥2-3፣* በኤዎድያንና በሲንጢኪን መካከል የነበረው አለ መግባባት በአደባባይ በሚነበብ ደብዳቤ ላይ መጠቀሱ የነገሩን ክብደት የሚያሳይ ነው፤ ጳውሎስ ግን እነዚህ ሴቶች (ቍ3) ሊ ታ ረቁ እንደሚችሉ እምነት ያለው ይመስላል፤ የተፈጠረውንም ችግር ብልኀት በተሞላው ሁኔታ መታዙ አርአያነት ያለው ነው፤ ይኸውም ሳያዳላ ለሁኔታው ቅርብ የሆኑ ሰዎች ለዕርቁ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ አበረታቶአልና (2፥2 ይመ)::

4፥3 *የሥራ ባልደረባዬ ... የሥራ ጓደኞቼ፣* በወንጌል ሥራ ከሐዋርያው ጋር የተባበሩት (ወንድም ሆነ ሴት) ሁሉም ከእርሱ ጋር እኩል ናቸው እንጂ የበታቾቹ አይደሉም (ከ 2፥25፤ ከሮሜ 16፥3:9:21፤ ከፊሞ 24 ጋር ያነጻጽሩ):: *ከቀሌምንጦስ፣* የዚህ ሰው ስም በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በሌላ ስፍራ አልተጠቀሰም:: *ከሌሎች የሥራ ጓደኞቼ፣* በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቁና በሰ ማይ የምርጦች መመዝገቢያ በሆነው በሕይወት መዝገብ ላይ የተጻፉ ስለ ሆነ፣ ስማቸው በዚህ ስፍራ በዝርዝር አልተጠቀሰም (የራእ 3፥5 ማብ ይመ)::

4፥4 *በጌታ... ደስ ይበላችሁ፣* 3፥1 ይመ:: ምንጊዜም መከራ ንም ጨምሮ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ማለት ነው (ዕን 3፥17-18፤ያዕ 1፥2፤1ጴጥ4፥13 ይመ)::

4፥5 *ገርነታችሁ፣* እንደ ክርስቶስ ለሌሎች ማሰብ ማለት ነው (ከ2ቆሮ 10፥1 ጋር ያነጻጽሩ)፤ በተለይ የቤተክርስቲያን መሪዎች እንዲህ ያለው ባሕርይ ሊኖራቸው ይገባል (1ጢሞ 3፥3፤ ቲቶ 3፥2 ይመ):: *ቅርብ፣* ሮሜ13፥11 ይመ፤ ከያዕ 5፥8-9፤

ዘንድ የታወቀ ይሁን፤ ጌታ ቅርብ ነው::
[6]በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ፣ ከምስ
ጋናም ጋር ልመናችሁን በእግዚአብሔር ፊት
አቅርቡ እንጂ ስለ ማንኛውም ነገር አት
ጨነቁ:: [7]ከማስተዋል በላይ የሆነው የእግዚ
አብሔር ሰላም፣ ልባችሁንና አሳባችሁን በክ
ርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል::

[8]በመጨረሻም ወንድሞች ሆይ፤ እውነት የሆ
ነውን ሁሉ፣ ክቡር የሆነውን ሁሉ፣ ትክክል
የሆነውን ሁሉ፣ ንጹሕ የሆነውን ሁሉ፣ ተወ
ዳጅ የሆነውን ሁሉ፣ መልካም የሆነውን ሁሉ፣
በጎነት ቢሆን ወይም ምስጋና፣ እንደ እነዚህ
ስላሉት ነገሮች አስቡ:: [9]ከእኔ የተማራች
ሁትን ወይም የተቀበላችሁትን፣ የሰማችሁትን
ወይም ያያችሁትን ማናቸውንም ነገር አድርጉ፤
የሰላም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል::

## ላደረጉት ቸሮታ የቀረበ ምስጋና

[10]ከብዙ ጊዜ በኋላ በአዲስ መንፈስ ስለ እኔ
ማሰብ በመጀመራችሁ፣ በጌታ እጅግ ደስ ይለ
ኛል፤ በእርግጥ በተግባር ለመግለጽ ዕድሉ
አልነበራችሁም እንጂ ማሰቡንስ ታስቡልኝ
ነበር:: [11]ይህን የምለው ስለቸገረኝ አይደለም፤
ምክንያቱም በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ያለኝ
ይበቃኛል ማለትን ተምሬአለሁ፤ [12]ማጣትን ዐው
ቃለሁ፤ ማግኘትንም ዐውቃለሁ:: ብጠግብም
ብራብም፣ ባገኝም ሆነ ባጣ በማንኛውም
ሆነ በየትኛውም ሁኔታ ያለኝ ይበቃኛል የማ
ለትን ምስጢር ተረድቻለሁ:: [13]ኀይልን
በሚሰጠኝ በእርሱ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ::

[14]ሆኖም የመከራዬ ተካፋይ ስለ ሆናችሁ
መልካም አድርጋችኋል:: [15]ከዚህም በላይ፣
እናንተ የፊልጵስዩስ ሰዎች ራሳችሁ እንደ
ምታውቁት፣ በመጀመሪያ ወንጌልን በተቀ
በላችሁ ጊዜ ከመቄዶንያ ስነሣ፣ ከእናንተ በቀር
በመስጠትና በመቀበል የትኛውም ቤተ
ክርስቲያን አልተባበረኝም:: [16]በተሰሎንቄ
በነበርሁበት ጊዜ እንኳ፣ በችግሬ ወቅት
ደጋግማችሁ ርዳታ ልካችሁልኛልና:: [17]ይኽ
ውም ትርፉ ለእናንተ እየበዛ እንዲሄድ
እንጂ ስጦታውን ጓጉቼ አይደለም:: [18]የሚ
ያስፈልገኝን ሁሉ፣ ከሚያስፈልገኝም በላይ
ተቀብያለሁ፤ የላካችሁትንም ስጦታ ከአፍሮ
ዲጡ እጅ ተቀብዬ ተሞልቻለሁ፤ ይህም
መዐዛው የጣፈጠ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባ
ይነት ያለውና ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት

12፥12፤ፊል3፥1
4፥5 መዝ119፥151፤ 145፥18፤ዕብ10፥37፤ ያዕ5፥8:9
4፥6 ማቴ6፥25-34፤ ኤፌ6፥18፤1ጢሞ2፥1
4፥7 ኢሳ26፥3፤ ዮሐ14፥27፤ኤፌ3፥19
4፥9 ሮሜ15፥33፤ 1ቆሮ4፥16
4፥10 2ቆሮ11፥9
4፥11 1ጢሞ6፥6:8፤ዕብ13፥5
4፥12 1ቆሮ4፥11፤ 2ቆሮ11፥9
4፥13 2ቆሮ12፥9፤ ኤፌ3፥16፤ቈላ1፥11፤ 1ጢሞ1፥12፤ 2ጢሞ4፥17
4፥14 ፊል1፥7
4፥15 ሐሥ16፥9፤ 2ቆሮ11፥8:9፤ፊል1፥5
4፥16 ሐሥ17፥1፤ 1ተሰ2፥9
4፥17 1ቆሮ 9፥11:12
4፥18 2ቆሮ2፥14፤ ፊል2፥25
4፥19 መዝ23፥1፤ ሮሜ2፥4፤2ቆሮ9፥8
4፥20 ሮሜ11፥36፤

ራእ 22፥7:12:20 ጋር ያነጻጽሩ:: በእግዚአብሔር ትንቢታዊ መርሐ ግብር መሠረት፣ ከዚህ በኋላ የሚጠበቀው ትልቁ ነገር የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ነው:: በአዲስ ኪዳን ከክርስቶስ ልደት እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ያለው ጊዜ የመጨረሻው ዘመን በመባል ይታወቃል (1ዮሐ 2፥18):: በእግዚአብሔር አቈጣጠር አንድ ሺህ ዓመት እንደ አንድ ቀን ነው፤ በዚህ ሁኔታ ለሁሉም ትውልድ የጌታ ምጽአት ቅርብ ነው::

4፥6 *በነገር ሁሉ በጸሎትና፤* በክርስትና ሕይወት ውስጥ ጭንቀትና ጸሎት የሚቃረኑ ነገሮች ናቸው:: *ከምስጋናም፤* ከ ጸሎትና ከምልጃ ጋር የሚቀርብ የጭንቀት ማርከሻ ነው:: *አትጨነቁ፤* ለወንጌል መስፋፋት ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግን ሳይሆን፣ራስ ወዳድ መሆንና ፋይዳ በሌለው ሐሳብ መወጠርን ያመለክታል (2፥28 እና ማብ ይመ፤ 2ቆሮ 11፥28፤ እንዲሁም ማቴ 6፥25-31፤ 1ጴጥ 5፥7 ይመ)::

4፥7 *የእግዚአብሔር ሰላም፤* ከእግዚአብሔር ጋር ከመታረቅ የተነሣ የሚገኝ የውስጥ ጸጥታና ዕረፍት እንጂ፣ ሥነ ልቦናዊ የሆነ የአእምሮ መረጋጋት ብቻ አይደለም:: የኀጢአትን ስርየት ያገኙ ሰዎች እንዲህ ዐይነት ሰላም አላቸው (ከዮሐ 14፥27፤ ሮሜ 5፥1 ጋር ያነጻጽሩ):: ይህም ሰላም የሚገኘው አ ማኙ የሚያስጨንቀውን ነገር ሁሉ በጸሎት ለእግዚአብሔር አሳልፎ ሲሰ ጥና ተመልሶም የማያስበው ከሆነ ነው:: *ከማስተዋል ሁሉ በላይ የሆነው፤* የእግዚአብሔር ፍቅርና ጥበቃ ከሰው መረዳት ሁሉ የሚያልፍ ነው (ኤፌ3፥18-20 ይመ):: *ልባችሁንና ሐሳባ ችሁን...ይጠብቃል፤* በር ላይ ቆሞ ዘብ ከሚጠ ብቅ የታጠቀ ወታደር የበለጠ፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉትን ነፍሳቸውን፣ ሥጋቸውንና መንፈሳቸውን ይጠብቃል (ከ1ጴጥ 1፥5 ጋር ያነጻጽሩ)::

4፥8 *በመጨረሻም፤* የ3፥1 ማብ ይመ:: *እውነት ... ምስጋና፤* የአንድ ሰው አስተሳሰብ በገዛ ራሱ ሕይወት ላይ ተጽዕ ኖ እንዳለው ጳውሎስ ተገንዝቦአል፤ በሰው አእምሮ ስፍራ ያገኘ ማንኛውም ነገር ወዲያውኑም ሆነ ቈይቶ በንግግር ወይም በተግባር መገለጡ አይቀርም:: ጳውሎስ፣ "እንደ እነዚህ ስላሉት ነገሮች አስቡ" ካላቸው በኋላ፣ "ማናቸውንም ነገር አድርጉ" (ቍ9) ብሎ በድጋሚ ይመክራቸዋል:: ከቍ8-9 ያሉት ምግባራት በአንድነት፣ በጎ ምግባርና የተሟላ መንፈሳዊ ሕይወት እንዲኖር አስተዋፅኦ ያደርጋሉ::

4፥9 *ከእኔ ... ያያችሁትን፤* የ3፥17 ማብ ይመ:: *የሰላም አምላክ፤* የ1ተሰ5፥23 ማብ ይመ በቍ7 ላይ "የእግዚአብሔር ሰላም" ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ::

4፥10 *ከብዙ ጊዜ በኋላ ... ዕድሉ አልነበራችሁም እንጂ፤* ለጳውሎስ የሚላከው ስጦታ የዘገየው ከፊልጵስዩስ ሰዎች ስሕተት የተነሣ ወይም ስለ እርሱ ሳያስቡ ቀርተው አልነበረም (ከ2ቆሮ 11፥9 ጋር ያነጻጽሩ):: ጳውሎስ ሮም ከመድረሱ በፊት እግረ መንገዱን ጉብኝት በማድረጉ ወይም ስጦታውን የሚያደርስ መልእክተኛ በወቅቱ ያለመገኘቱ፣ የፊልጵስዩስ ሰዎች ለጳውሎስ የነበራቸውን ፍቅር እንዳይገልጹ ዕንቅፋት ሳይሆን አልቀረም::

4፥11 *በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ያለኝ ይበቃኛል፤* ጳውሎስ ከፊልጵስዩስ በተላከለት ስጦታ ደስ ተሰኝ ቶአል (ቍ 14:18 ይመ)፤ ይሁን እንጂ ሙሉ በሙሉ በእነርሱ ላይ ብቻ አልታመነም (ከ1ጢሞ 6፥6-8 ጋር ያነጻጽሩ)::

4፥12 *ብጠግብም ...ባገኝም...ያለኝ ይበቃኛል፤* ባለጠግነት ራሱ ላለመርካት ምክንያት ሊሆን ይችላል::

4፥13 *ሁሉን፤* እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ማንኛውም ነገር ማለት ነው:: *ኀይልን በሚሰጠኝ በእርሱ፤* በክርስቶስ ለማ ለት ነው:: ለጳውሎስ የመርካቱ (ቍ12) ምስጢርና የዘላቂ ኀይል ምንጩ፣ ሕያው ከሆነውና ከፍ ከፍ ካለው ክርስቶስ ጋር አንድ መሆኑ ነው (በተለይ 2ቆሮ 12፥9-10 ይመ፤ እንዲሁም ዮሐ 15፥5፤ ኤፌ 3፥16-17፤ ቈላ1፥11 ይመ)::

4፥14 *ተካፋይ፤* የፊልጵስዩስ ሰዎች ለጳውሎስ የላኩት ስጦታ የመከራው ተካፋይ የመሆናቸው ምልክት ነው (ከዕብ 10፥33 ጋር ያነጻጽሩ)::

4፥15 *በመጀመሪያ...ጊዜ፤* ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ወንጌል ለመስበክ ሁለተኛ ሐዋርያዊ ጕዞ ያደረገበትን ጊዜ ያሳያል (ሐሥ 16፥12-40 ይመ):: *መቄዶንያ፤* ቤርያና ተሰሎንቄ እንዲሁም ፊልጵስዩስ የሚገኙበት የአሁኗ ግሪክ ሰሜናዊ ክፍል ነው:: *ስነሣ፤* ጳውሎስ በዚህ ጊዜ አቴና እና ቆሮንቶስ ወደሚገኙበት ወደ ደቡብ ማለትም ወደ አካይያ ሄዶ ነበር (ሐሥ 17፥14-16፤18፥1-4 ይመ):: *ከእናንተ በቀር፤* የፊልጵስዩስ ቤተክርስቲያን ቸርነት የተለየና ወደር የማይገኝለት ነው (2ቆሮ 8፥1-5 ጋር ያነጻጽሩ)::

4፥16 *በተሰሎንቄ በነበርሁበት ጊዜ፤* በመቄዶንያ እያለ ማለት ነው (ሐሥ 17፥1-9 ይመ):: *ደጋግማችሁ ርዳታ፤* በአፍሮዲጡ በኩል ወደ ሮም የተላከው ስጦታ፣ ለረጅም ጊዜ ሳያቋርጥ ይላክ ከነበረው ስጦታ ውስጥ የመጨረሻው ነው (ከ2ቆሮ8፥1-5 ጋር ያነጻጽሩ)::

4፥17 *ትርፉ...እየበዛ እንዲሄድ፤* የቍ15 ማብ ይመ:: ጳውሎስ የፊልጵስዩስ ሰዎች በላኩለት ስጦታ እንደተጠቀመ ግል ጽ ነው፤ ሆኖም እነርሱ ጳውሎስን በማገልገላቸው ያገኙት መንፈሳዊ በረከት እጅግ የላቀ ነው::

4፥18 *መዐዛው የጣፈጠ ... ተቀባይነት ያለው...መሥዋ ዕት፤* እዚህ ላይ ብሉይ ኪዳንን መሠረት በማድረግ የተጠቀሰው መሥዋዕት ለኀጢአት ስርየት የሚቀርበው ሳይሆን፣ የምስጋና መሥዋዕት ነው (ከዘሌ 7፥12-15፤ ከሮሜ 12፥1፤ ከኤፌ 5፥2፤ ከዕብ 13፥15-16 ጋር ያነጻጽሩ):: *በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለውና ደስ የሚያሰኝ፤* ክርስቶስ ለእኛ ከሠራው ሥራና (1ጴጥ2፥5 ይመ) እግዚአብሔርም በእኛ ውስጥ ከሚሠራው

ነው። [19]አምላኬም እንደ ታላቅ ባለጠግነቱ መጠን
የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ
ይሞላባችኋል።
[20] ለአምላካችንና ለአባታችን ከዘላለም እስከ
ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።

### የስንብት ሰላምታ

[21]ለቅዱሳን ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ሰላ

ገላ1፥4፤1 ተሰ1፥3፤ 3፥11፡13
4፥21 ገላ1፥2
4፥22 ሐሥ9፥13
4፥23 ሮሜ16፥20፤ ገላ6፥18

ምታ አቅርቡልኝ። ከእኔ ጋር ያሉት ወንድ
ሞችም ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። [22]ቅዱሳንን
ሁሉ፣ በተለይም ከቄሳር ቤተ ሰው የሆኑት ወገ
ኖች ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።
[23]የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመንፈ
ሳችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን[ፐ]።

[ፐ]23 አንዳንድ ቅጆች አሜን የሚለው የላቸውም

*ሥራ* የተነሣ ነው (ፊል2፥13 ይመ)።

4፥19 *አምላኬም፤* ከእግዚአብሔር ጋር በጣም የቅርብ ግንኙነት እንዳለው የሚያመለክት አባባል ነው (ከ1፥3 ጋር ያነጻጽሩ)። *እንደ … ባለጠግነቱ … በክርስቶስ ኢየሱስ፤* እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን ለሚሰጠው በረከት እውነተኛ መለኪያ ነው (ከኤፌ 1፥18፤ 3፥16-20 ጋር ያነጻጽሩ)። *የሚያስፈልጋ ችሁን፤* ጳውሎስ ስለ ራሱ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ስለፊልጵስዩስም ሰዎችም ሸክም ነበርው። *ይሞላባችኋል፤* ጳውሎስን ለመርዳት መሥዋዕትነት ያለበትን ስጦታ ላበረከቱት ቤተክርስቲያን የተሰጠ ተስፋ ነው።

*4፥20፤* ጳውሎስ በቍጥር 19 ላይ የተጠቀሰውን እውነት በሚያስብበት ጊዜ፣ እግዚአብሔርን ከማመስገን ወደኋላ ማለት አይችልም።

*4፥21-22፤* የጳውሎስ መልእክቶች ልዩ ባሕርይ፣ በመጨረሻ ሰላምታ ማቅረብ ነው (ለምሳሌ ሮሜ16፥3-16፡21-23፤ 1ቆሮ16፥19-20፤2ቆሮ13፥12-13፤ቈላ4፥10-12፡14-15፡18 ይመ)።

4፥21 *ለቅዱሳን፤* የ1፥1 ማብ ይመ። ከእኔ ጋር ያሉት ወንድሞችም፣ በርም ያሉ የጳውሎስ የሥራ ባልደረቦች በተለይም ጢሞቴዎስን ያመለክታል (1፥1፤ 14፡16 ይመ)።

4፥22 *ከቄሳር ቤተሰው፤* ከንጉሡ ጋር የሥጋ ዝምድና ያላቸውን ሳይሆን፣ ተቀጥረው በቤተ መንግሥት ውስጥ ወይም ባካባቢው የነበሩትን የንጉሡን ባሪያዎች ወይም ነጻ የወጡትን ሰዎች የሚያመለክት ነው (በ1፥13ላይ "በቤተመንግሥት ዘበኞች" ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ)።

4፥23፤ ጳውሎስ የሚጠቀምበት ልዩ የመዝጊያ ቡራኬ ነው። *ከመንፈሳችሁ፤* የሰው ሁለንተና የሚያሳይ እንጂ አንዱን የሰውነት ክፍል ወስዶ ሌላውን መተው ማለት አይደለም (ከገላ 6፥18፤ 2ጢሞ 4፥22፤ ከፊሞ 25 ጋር ያነጻጽሩ)።

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት
# ወደ ቈላስይስ ሰዎች

**ጸሓፊው፣ መልእክቱ የተጻፈበት ጊዜና ቦታ**

ቈላስይስ እውነተኛ የጳውሎስ ደብዳቤ መሆኑ አጠያይቆ አያውቅም:: የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም የመልእክቱ ጸሓፊ ጳውሎስ መሆኑን አመልክተዋል፤ በ19ኛው ምእተ ዓመት የኖሩ አንዳንድ ሊቃውንት እንደሚያስቡት ከሆነ፣ በዚሁ መልእክት በም 2 ላይ ጳውሎስ የተቃወመው የሐሰት ትምህርት በሁለተኛው ምእተ ዓመት የነበረ የኖስትሳውያንን የኑፋቄ ትምህርት ነው:: ይሁን እንጂ ምዕራፉ በጥንቃቄ ሲተነተን የተተቸው የኖስትሳውያን ትምህርት በ2ኛውና በ3ኛው ምእተ ዓመት ከነበረው ጋር ሲነጻጸር፣ ያነሰ የእድገት ደረጃ እንደ ነበረው መገመት ይቻላል፤ በሁለተኛው ምእተ ዓመት ለነበረው የኖስትሳውያን ትምህርት መሠረቱ በመጀመሪያው ምእተ ዓመት የነበረውና ቤተ ክርስቲያንን ያውክ የነበረው የኑፋቄ ትምህርት ነው:: መልእክቱ በሁለተኛው ምእተ ዓመት ተጻፈ እንዳንል ጳውሎስ እስከዚያ ዘመን ድረስ በሕይወት አልነበረም::

ስለዚህ ይህ መልእክት የተጻፈው ጳውሎስ በሮም (ሐሥ28፥16-31) ለሁለት ዓመት ያህል በገዛ ራሱ ቤት ውስጥ በእስር ላይ በነበረበት በመጀመሪያ እስራቱ ወቅት ሳይሆን አይቀርም:: አንዳንዶች ጳውሎስ ይህን መልእክቱን በኤፌሶን ወይም በቂሣርያ ሳለ እንደ ጻፈው ቢናገሩም አብዛኞቹ ማስረጃዎች ጳውሎስ የእስር ቤት ደብዳቤዎቹን በሙሉ (ኤፌሶንን፣ ቈላስይስን፣ ፊልጵስዩስንና ፊልሞናን) የጻፈው በሮም መሆኑን የሚደግፉ ናቸው:: ቈላስይስም እንደ ኤፌሶንና እንደ ፊልሞና ሁሉ የተጻፈው በ60 ዓ.ም ነው ::

**የቈላስይስ ከተማና ቤተ ክርስቲያኒቱ**

ከጳውሎስ ዘመን ቀደም ብሎ ቈላስይስ ለአያሌ መቶ ዓመታት የትንሿ እስያ (ዛሬ ቱርክ) ዋና ከተማ ነበረች:: ይህች ከተማ በላይከስ ወንዝና ከኤፌሶን ተነሥቶ በኤጂያን ባሕር በኩል ወደ ኤፍራጥስ ወንዝ በሚወስደውና ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ በተዘረጋው በታላቁ የንግድ መተላለፊያ መንገድ ላይ ትገኝ ነበር፤ በመጀመሪያው ምእተ ዓመት ግን ቈላስይስ እየተዳከመች ስለሄደች አነስተኛ የንግድ ከተማ ሆነች፤ ሎዶቅያና ሂራፖሊስ የተባሉ ጎረቤት ከተሞችም ከኀይልና ከጠቀሜታ አኳያ ከቈላስይስ ከተማ ልቀው ተገኙ (4፥13)::

ቈላስይስ በአዲስ ኪዳን እንድትታውቅ ያደረጋት ትልቁ ነገር ጳውሎስ ለሦስት ዓመት በኤፌሶን ባገለገለ ጊዜ ኤጳፍራ የተባለው ሰው የጌታን ቃል ሰምቶ በመለወጡና የወንጌልን መልእክት ለቈላስይስ ሰዎች በማድረሱ ነው (ከ1፥7-8፤ሐሥ19፥10 ጋር ያነጻጽሩ):: በዚህ ዐይነት ሁኔታ ተመሥርታ በማደግ ላይ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ለሐሰት ትምህርት ስለ ተጋለጠች ኤጳፍራ በሮም በእስር ላይ ወደ ነበረው ወደ ጳውሎስ ይሄድ ዘንድ ተገደደ፤ ይህም ለቈላስይስ መልእክት መጻፍ መንሥኤ ሆነ:: በኤጳፍራና በጳውሎስ ምስክርነት ወደ ጌታ የመጡ ሌሎች ክርስቲያኖች በሰጡት አገልግሎት አብያተ ክርስቲያናት በሎዶቅያና በሂራፖሊስም ሳይቋቋሙ አልቀሩም፤ ከእነዚህም መካከል አንዳንዶቹ የቤት ለቤት አብያተ ክርስቲያናት ሲሆኑ (4፥15፤ፊሞ2፥ይመ) ከአማኞቹ የሚበዙት ከአሕዛብ ወገን ነበሩ::

**በቈላስይስ የነበረው ኑፋቄ**

ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ የሚቃወማቸውን የሐሰት ትምህርቶች ግልጽ አያደርግም፤ ሆኖም በመልእክቱ ውስጥ የሰጠው ትንታኔ ኑፋቄው የተለያየ ባሕርይ እንዳለው ያመለክታል፤ ከባሕርያቱም መካከል ጥቂቶቹ:-

1 ***ወግ አጥባቂነት፤*** የምግብና የመጠጥ ሕግጋትን፣ የሃይማኖት በዓላትን (2፥16-17)፣ የግዝረትን ሥርዐት (2፥11፤3፥11) ከመጠበቅ ጋር የተያዘ ነው::
2 ***ብሕትውና፤*** "አትያዝ፣ አትቅመስ፣ አትንካ" (2፥21፤ከ2፥23 ጋር ያነጻጽሩ)
3 ***መላእክትን ማምለክ*** (2፥18 ይመ)
4 ***ክርስቶስን መናቅ፤*** ይህ የክርስቶስን መለኮትነት በተመለከተ በጻፈው ውስጥ ተመልክቶአል (1፥15-20፤2፥2-3፥9)
5 ***የተሰወረ ዕውቀት፤*** በዚህ ኖስትሳዊያን ይመኩ ነበር (2፥18 እና ጳውሎስ "የተሰወረ የጥበብና የዕውቀት መዝገብ ሁሉ በእርሱ ነው" ሲል አጽንኦት ያደረገበትን ይመ)::
6 ***በሰው ጥበብና ወግ መታመን*** (2፥4፥8 ይመ) ናቸው::

ከላይ የተገለጹት ነጥቦች አይሁዳዊና ኖስቲሳዊ ተብለው ሁለት ቦታ ሊከፈሉ ይችላሉ:: ስለዚህ በቈላስይስ የነበረው የኑፋቄ ትምህርት የአክራሪው የአይሁድ ሃይማኖትና ዕንጭጭ የነበረው የኖስትሳውያን ትምህርት ቅይጥ ሊሆን ይችላል ማለት ነው (ከ1ዮሐ መግቢያ ላይ "የኖስትሳውያን ትምህርት" የሚለውን እንዲሁም የ2፥23 ማብ ይመ::)

**ዐላማውና መሪ ሐሳቡ**

የጳውሎስ ዐላማ በቈላስይስ የነበረውን የሐሰት ትምህርት ጤናማ ትምህርት በማስተማር መቃወም ሲሆን፣ ይህን ከግቡ ለማድረስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ምሳሌ መሆኑን (1፥15)፣ ፈጣሪ መሆኑን (1፥16)፣ ከሁሉ በፊት የነበረና ሁሉም በእርሱ የተጋጠመ መሆኑን (1፥17)፣ ከሞት በመነሣት የመጀ መሪያ መሆኑን (1፥18)፣ በአካል የተገለጠ የመለኮት ሙላት መሆኑን (1፥19፤2፥9) እና አስታራቂ መሆኑን (1፥20-22) በመግለጽ ክርስቶስን ከፍ ከፍ ያደርጋል። ስለዚህም ክርስቶስ ፍጹምና ብቁ ነው። እኛም በክርስቶስ ሙላት ተሰጥቶናል (2፥10)፤ በቈላስይስ የነበረው ኑፋቄ ብቃት የሌለውና ፍጹም ማድረግ የማይችል ባዶና አሳሳች የሆነ ሥጋዊ ባሕርይን እንኳ መቈጣጠር የማያስችል (2፥23) ፍልስፍና ነው(2፥8)። የቈላስይስ መልእክት መሪ ሐሳብ የክርስቶስን ፍጹም ብቃት ባዶና ብቃት ከሌለው የሰው ፍልስፍና ጋር አነጻጽሮ ማሳየት ነው።

**አስተዋፅኦ**

**መግቢያ**

1. መግቢያ (1፥1-14)
   ሀ. ሰላምታ (1፥1-2)
   ለ. ምስጋና (1፥1፥3-8)
   ሐ. ጸሎት (1፥9-14)
2. የክርስቶስ የበላይነት (1፥15-23)
3. ጳውሎስ ስለ ቤተ ክርስቲያን ያደረገው መጋደል (1፥24-2፥7)
   ሀ. ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠው አገልግሎት (1፥24-29)
   ለ. ለተደራስያኑ መንፈሳዊ ሕይወት የነበረው ሸክም (2፥1-7)
4. በክርስቶስ በተገኘ ሕይወት ከሰው ሥርዐቶች ነጻ መውጣት (2፥8-23)
   ሀ. ከሐሰት መምህራን እንዲጠበቁ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ(2፥8-15)
   ለ. የሐሰት መምህራንን ለመቃወም የቀረበ ጥሪ (2፥16-19)
   ሐ. ስለ ኑፋቄው ትንተና (2፥20-23)
5. የቅድስና አኗኗር ሥርዓት (3፥1-4፥6)
   ሀ. የአሮጌውና የአዲሱ ማንነት (3፥1-17)
   ለ. የክርስቲያናዊ ቤተ ሰብ መመሪያ (3፥18-4፥1)
   ሐ. ተጨማሪ መመሪያዎች (4፥2-6)
6. የመጨረሻ ሰላምታ (4፥7-18)

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ የክርስቶስ ኢየሱስ
ሐዋርያ ከሆነው ከጳውሎስና ከወንድማችን
ከጢሞቴዎስ፤
2በቈላስይስ ለሚኖሩ፣ በክርስቶስ ለሆኑ
ቅዱሳንና ታማኝ[ሀ] ወንድሞች፤
ከእግዚአብሔር ከአባታችን[ለ] ጸጋና ሰላም
ለእናንተ ይሁን::

## ምስጋናና ጸሎት

3ስለ እናንተ በምንጸልይበት ጊዜ የጌታ
ችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን
ሁልጊዜ እናመሰግናለን፤ 4ምክንያቱም በክር
ስቶስ ኢየሱስ ስላላችሁ እምነትና ለቅዱሳን
ሁሉ ስላላችሁ ፍቅር ሰምተናል፤ 5ይህም የሆ
ነው በሰማይ ተዘጋጅቶ ከተቀመጠላችሁ
ተስፋ የተነሣ ነው፤ ስለዚህ ተስፋ በወንጌል
የእውነት ቃል አስቀድማችሁ ሰማችሁ፤ 6ይህም
ወደ እናንተ ደርሶአል:: ይህንም ወንጌል ከሰ
ማችሁበትና የእግዚአብሔርን ጸጋ በእውነት
ከተረዳችሁበት ቀን ጀምሮ በዓለም ዙሪያ
እየሠራ እንዳለ ሁሉ በእናንተም ዘንድ ፍሬ
እያፈራና እያደገ ነው:: 7ይህንም ስለ እኛ[ሐ]
የክርስቶስ ታማኝ አገልጋይ የሆነው፣ አብሮ
ንም በአገልግሎት የተጠመደው ተወዳጁ
ኤጳፍራ አስተማራችሁ፤ 8ደግሞም በመንፈስ
ስላላችሁ ፍቅር ነገረን::
9ከዚህ የተነሣ እኛ ደግሞ ይህን ከሰ
ማንበት ቀን ጀምሮ እግዚአብሔር የፈቃዱን
ዕውቀት በመንፈሳዊ ጥበብና መረዳት ሁሉ
ይሞላችሁ ዘንድ ስለ እናንተ መጸለይና
መለመን አላቋረጥንም፤ 10የምንጸልየውም
ለጌታ እንደሚገባ እንድትኖሩና በሁሉም
ደስ እንድታሰኙት ነው፤ ይኸውም በመልካም
ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ እግዚአብሔርን በማ
ወቅ እያደጋችሁ፣ 11ታላቅ ጽናትና ትዕግሥት
ይኖራችሁ ዘንድ፣ እንደ ክቡር ጕልበቱ መጠን
በኀይል ሁሉ እየበረታችሁ፣ ደስ እየተሰኛ
ችሁ፣ 12በቅዱሳን ርስት በብርሃን ተካፋዮች
ለመሆን ያበቃንን[መ] አብን እንድታመሰግኑ
ነው:: 13እርሱ ከጨለማ ግዛት ታደገን፤
ወደሚወደው ልጁ መንግሥትም አሻገረን፤
14በእርሱም መዋጀትን[ሠ] አግኝተናል፤ ይህም
የኀጢአት ይቅርታ ነው::

## ክርስቶስ ከሁሉ በላይ

15እርሱ የማይታየው አምላክ አምሳል ነው፤

1፥1 ሐሥ16፥1፤ 1ቆሮ1፥1፤2ቆሮ1፥1
1፥2 ሮሜ1፥7፤ ቈላ4፥18
1፥3 ሮሜ1፥8
1፥4 ሐሥ9፥13፤ ገላ5፥6፤ኤፌ1፥15፤ ፊሞ5
1፥5 ቍ23፤ 1ተሰ5፥8፤ 2ጢሞ2፥15፤ ቲቶ1፥2፤1ጴጥ1፥4
1፥6 ቍ23፤ ዮሐ15፥16፤ሮሜ10፥18
1፥7 ቈላ4፥7:12፤ ፊሞ23
1፥8 ሮሜ15፥30
1፥9 ቍ4፤ሮሜ1፥10፤ ኤፌ1፥15:17፤5፥17
1፥10 ቍ6፤ 2ቆሮ5፥9፤ኤፌ4፥1
1፥11 ኤፌ4፥2፤ ፊል4፥13
1፥12 ሐሥ20፥32፤ 26፥18፤2ጴጥ1፥11
1፥13 ማቴ3፥17፤ ሐሥ26፥18፤ 2ጴጥ1፥11
1፥14 ሮሜ3፥24፤ ኤፌ1፥7
1፥15 ቍ18፤ ዮሐ1፥18፤ 14፥9፤1ጢሞ1፥17፤ ዕብ11፥27

[ሀ]2 ወይም *የሚያምኑ*
[ለ]2 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *ከአባትና ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ*
[ሐ]7 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *እናንተ* ይላሉ::
[መ]12 ወይም *ያበቃችሁን*
[ሠ]14 የቅርብ ጊዜ ቅጆች *በደሙ የሆነ መዋጀት*

1፥1 ***ጳውሎስ፤*** በደብዳቤ መግቢያ ላይ የጸሐፊውን ስም መጻፍ የተለመደ ስለ ነበር ጳውሎስ በመልእክቱ መግቢያ ላይ ስሙን ጠቅሶአል:: ስለ ጳውሎስ በይበልጥ ለማወቅ የሐሥ 9፥1፤ ፊል 3፥4-14 ማብ ይመ:: ***ክርስቶስ፤*** ጳውሎስ በዚህች አጭር ደብዳቤ ውስጥ፣ "ክርስቶስ" የሚለውን የማዕረግ ስም 26 ጊዜ እንዲሁም፣ "ጌታ" የሚለውን 7 ጊዜ መጠቀሙ ምን ያህል ክር ስቶስን ማእከል ያደረገ ሰው እንደ ነበረ ያሳያል:: ***ጢሞቴዎስ፤*** ጳውሎስ፣ የጢሞቴዎስን ስም እዚህ ብቻ ሳይሆን በ2ኛ ቆሮን ቶስ፣ በፊልጵስዩስ፣ በ1ኛ እና በ2ኛ ተሰሎንቄ እንዲሁም በፊልሞና ላይ ጠቅሶታል፤ ይሁን እንጂ በመልእክቱ ውስጥ ደጋግሞ "እኔ" ማለቱ እርሱ ራሱ የዚህ መልእክት ጸሐፊ እንደ ነበረ ያረጋግጣል (በተለይ 4፥18 ይመ)::

1፥2 ***በክርስቶስ፤*** ጳውሎስ ከክርስቶስ ጋር ስላለው መንፈሳዊ አንድነት በቈላስይስ መልእክቱ ላይ 13 ጊዜ ጠቅሶአል (የኤፌ 1፥3 ማብ ይመ):: ***ቅዱሳን፤*** ክርስቶስ በቈላስይስ አማኞች ምትክ ስለ ሞተ የቈላስይስ አማኞች በእግዚአብሔር ፊት ቅዱሳን ናቸው፤ እንዲሁም ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ የተነሣ ሁልጊዜ በየዕለቱ ኑሮአቸው ይቀደሳሉ:: ***ታማኝ፤*** 1፥7፤ 4፥7:9 ይመ:: ***ጸጋና ሰላም፤*** የዮና 4፥2፤ ዮሐ 14፥27:20፥19፤ገላ 1፥3፤ ኤፌ 1፥2 ማብ ይመ::

1፥3 ***እግዚአብሔርን…እናመሰግናለን፤*** ከገላትያ መልእክት በስተቀር እያንዳንዱ የጳውሎስ መልእክት እግዚአብሔርን በማመስገን ይጀምራል (የፊል 1፥3–4 ማብ ይመ):: በቈላስይስ መልእክት ውስጥ ምስጋና ማቅረብ አስፈላጊ መሪ ሐሳብ ነው (ቍ 12፡ 2፥7፤3፥15-17:4፥2 ይመ):: መጽሐፍ ቅዱስ ሰውን ስለ እምነቱና ስላለው ፍቅር አያመሰግነውም፤ የእነዚህ መልካም ሥነ ምግባሮች ምንጭ የሆነውን እግዚአብሔርን ግን ማመስገን እንደሚገባ ያስተምራል:: ***እናመሰግናለን፤*** ይህን ሲል ጳውሎስ ራሱንና ጢሞቴዎስን ማለቱ ነው::

*1፥5፤* ሦስቱ የክርስቲያን ዐይነተኛ መለያዎች የሆኑት እምነት፣ ፍቅር ተስፋ በሮሜ 5፥2-5፤ 1ቆሮ 13፥13፤ ገላ 5፥5-6፤ 1ተሰ 1፥3፤ 5፥8፤ ዕብ 10፥22-24 ላይ በተጨማሪ ተጠቅሰዋል:: ***ተስፋ፤*** መልካም የሆነን ነገር ዝም ብሎ መመኘት ሳይሆን የተረጋገጠ እውነት ነው:: ከተስፋ ስለሚመነጨው ስለዚህ ልዩ እምነትና የፍቅር ሐሳብ ቲቶ 1፥2 ይመ::

1፥6 ***በዓለም ዙሪያ፤*** ከበዓለ ኀምሳ በኋላ ባሉት ሦስት ተከታታይ ዐሥር ዓመታት ወንጌል በልዩ ፍጥነት በእያንዳንዱ የሮም ግዛት እንደ ተዳረሰ ለማሳየት የተጠቀሰ አባባል ነው (ቍ 23፤ ሮሜ 1፥8፤10፥18፤16፥19 ይመ)፡፡ የሐሰት ትምህርት መምህራን ያሠራጩትን ትምህርት በመቃወም ጳውሎስ ክርስትና በአንድ አካባቢ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ዓለም ዐቀፋዊ መሆኑን አስረግጦ ተናግሮአል::

1፥7 ***ኤጳፍራ፤*** የዚያው አካባቢ ተወላጅ ሲሆን (4፥12) ምናልባትም የቈላስይስ ቤተ ክርስቲያን መሥራች እንዲሁም በአቅራቢያ ያሉት የሎዶቅያና የኢያራ (4፥3) ከተሞች ወንጌላዊ ሳይሆን አይቀርም:: ጳዋሎስም ኤጳፍራን እንደሚወደውና እንደሚያደንቀው ሲገልጽ፣ "ከእኔ ጋር የታሰረ" (ፊሞ 23)፣ ከእኛ ጋር አብሮ ባሪያ የሆነ፣ ታማኝ የክርስቶስ አገልጋይ ሲል ጠርቶታል:: ስለ ቈላስይስ ቤተ ክርስቲያን ችግር ለጳውሎስ የነገረውም ሆነ ይህን መልእክት እንዲጽፍ ያደፋፈረው ኤጳፍራ ነው (ቍ 4፥8 ይመ):: ኤጳፍራ የሚለው ስም፣ "ኤጳፍሮድተስ" ከሚለው ስም በአጭሩ የተወሰደ ሲሆን፣ ይህም የተገኘው፣ "አፍሮዳይት" ከምትባለው የግሪክ የፍቅር አምላክ ስም ነው፤ ኤጳፍራም የጣዖት አምልኮን ትቶ ክርስቲያን እንደ ሆነ ስሙ ያመለክታል:: ኤጳፍራና በፊል 2፥25፤ 4፥18 ላይ የተጠቀሰው አፍሮዲጡ ሁለት የተለያዩ ሰዎች ናቸው::

1፥8 ***በመንፈስ ስላላችሁ ፍቅር፤*** የክርስቲያን ፍቅር ምንጩ መንፈስ ቅዱስ ነው::

1፥9 ***የፈቃዱን ዕውቀት፤*** መጽሐፍ ቅዱስን ማወቅ ማለት በውስጡ ያለውን እውነት ሙሉ ለሙሉ መረዳት ማለት ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘውን ዕውቀትና ጥበብ በቅድስና በመኖር በተግባር የሚገለጥ ነው፤ ይህንንም የሚያረጋግጥልን ዕውቀት፣ ጥበብና ማስተዋል ለጌታ እንደሚገባ በመኖር የሚገኝ መሆኑን በተገለጸበት በቍ 10-12 ላይ የተጠቀሰው ሐሳብ ነው::

1፥12 ***በብርሃን፤*** የቅድስና (ማቴ 5፥14፤6፥23፤ ሐሥ 26፥18፤ 1ዮሐ 1፥5)፣ የእውነት (መዝ 36፥9፤ 119፥105፡130፤ 2ቆሮ 4፥6)፣ የፍቅር (ያዕ 1፥17፤ 1ዮሐ 2፥9-10)፣ የክብር (ኢሳ 60፥1-3፤ 1ጢሞ 6፥16) እንዲሁም የሕይወት (ዮሐ 1፥4) ምሳሌ ነው:: በዚህ መሠረት እግዚአብሔር (1ዮሐ 1፥5)፣ ክርስቶስ (ዮሐ 8፥12) እንዲሁም ክርስቲያን (ኤፌ 5፥8) ብርሃን በመባል ይታወቃል:: "የብርሃን መንግሥት"፣ "የጨለማው ግዛት" ተቃዋሚ ነው (ቍ 13)::

1፥14 ***መዋጀት፤*** ከኀጢአት ቅጣት ዐርነት የሚገኘው ክርስቶስ የሰዎችን ሞት ከመሞቱ የተነሣ መሆኑን የሚያመለክት ቃል ነው::

*1፥15-20፤* የክርስቶስን ታላቅነት የሚገልጽ የጥንት ክርስቲያኖች ማኅሌት ሳይሆን አይቀርም (የ3፥16 ማብ ይመ):: እዚህ ላይ ጳውሎስ በቈላስይስ የነበረውን የሐሰት ትምህርት ለመቃወም የተጠቀመበት ሲሆን፣ ይህንንም በሁለት አንጻር አሳይቶአል፤ (1) ክርስቶስ የፍጥረት ሁሉ የበላይ በመሆኑ (ቍ 15-17)፣ (2) ክርስቶስ በመቤዠት ሥራው ታላቅ በመሆኑ ነው (ቍ 18-20)::

1፥15 ***አምሳል፤*** ክርስቶስ በዚህ ስፍራና በ2ቆሮ 4፥4 ላይ "አምሳል" ተብሎ ተጠርቶአል:: በዕብ 1፥3 ላይ ደግሞ፣ "የ … ክብር ነጸብራቅና የባሕርዩ ትክክለኛ ምሳሌ ሆኖ" ተብሎአል::

ከፍጥረት ሁሉ በፊት[ሀ] በኵር ነው፤ [16]ሁሉ
ነገር በእርሱ ተፈጥሮአል፤ በሰማይና በምድር
ያሉ፣ የሚታዩና የማይታዩ፣ ዙፋናት ቢሆኑ
ወይም ኀይላት፣ ገዦች ቢሆኑ ወይም ባለ
ሥልጣናት፣ ሁሉም ነገር በእርሱና ለእርሱ
ተፈጥሮአል:: [17]እርሱ ከሁሉ በፊት ነው፤
ሁሉም ነገር በአንድ ላይ ተያይዞ የጸናው
በእርሱ ነው:: [18]እርሱ አካሉ የሆነችው የቤተ
ክርስቲያን ራስ ነው፤ በሁሉ ነገር የበላይነት
ይኖረው ዘንድ እርሱ የመጀመሪያ፣ ከሙ
ታን መካከልም በኵር ነው:: [19]እግዚአብሔ
ርም ሙላቱ ሁሉ በእርሱ ይሆን ዘንድ
ወዶአልና፤ [20]በመስቀሉ ላይ በፈሰሰው ደሙ
ሰላምን በማድረግ በምድርም ሆነ በሰማይ
ያለውን ነገር ሁሉ በእርሱ በኩል ከራሱ ጋር
አስታረቀ::

[21]ከክፉ ባሕርያችሁ የተነሣ[ለ] ቀድሞ ከእግ
ዚአብሔር የተለያችሁ በአሳባችሁም ጠላቶች
ነበራችሁ:: [22]አሁን ግን ነውርና ነቀፋ የሌለ
ባችሁ ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ሊያቀ
ርባችሁ፣ በክርስቶስ ሥጋ በሞቱ በኩል
አስታረቃችሁ፤ [23]ይህም የሚሆነው በእምነ
ታችሁ ተመሥርታችሁና ተደላድላችሁ በመ
ቆም ከሰማችሁት የወንጌል ተስፋ ሳትናወጡ
ጸንታችሁ ብትኖሩ ነው:: እናንተ የሰማች
ሁትና ከሰማይ በታች ላለ ፍጥረት ሁሉ
የተሰበከውም ወንጌል ይኸው ነው፤ እኔም
ጳውሎስ ለዚህ ወንጌል አገልጋይ ሆንሁ::

### ጳውሎስ ስለ ቤተ ክርስቲያን ያሳየው ትጋት

[24]ስለ እናንተ በተቀበልሁት መከራ አሁ
ንም ደስ ይለኛል፤ ክርስቶስ ስለ አካሉ ስለ
ቤተ ክርስቲያን ከተቀበለው መከራ የጐደለ
ውን በሥጋዬ አሟላለሁ:: [25]የእግዚአብሔርን ቃል
በሙላት እንዳቀርብላችሁ ከእግዚአብሔር በተሰ
ጠኝ ዐደራ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆኛ
ለሁ፤ [26]ይህም ቃል ከዘመናትና ከትውልዶች
ተሰውሮ ምስጢር ሆኖ ቈይቶ ነበር፤ አሁን
ግን ለቅዱሳኑ ተገልጦአል:: [27]ለእነርሱም እግዚ
አብሔር የዚህ ምስጢር ክብር ባለ ጠግነት በአሕ
ዛብ መካከል ምን ያህል እንደ ሆነ ለማሳ
ወቅ መረጠ፤ እርሱም የክብር ተስፋ የሆ
ነው በእናንተ ውስጥ ያለው ክርስቶስ ነው::

[28]እኛም እያንዳንዱን ሰው በክርስቶስ ፍጹም
አድርገን ማቅረብ እንችል ዘንድ፣ ሰውን ሁሉ
በጥበብ ሁሉ እየመከርንና እያስተማርን እር
ሱን እንሰብካለን፤ [29]እኔም በብርታት በውስጤ
በሚሠራው በእርሱ ኀይል ሁሉ እየታገልሁ
ለዚህ ዐላማ እጥራለሁ::

1፥16 ዮሐ1፥3፤ ሮሜ11፥36፤ ኤፌ1፥20፡21
1፥17 ዮሐ1፥2
1፥18 ቈላ 15፡24፤ መዝ89፥27፤ ሐሥ26፥23፤ሮሜ8፥29፤ 1ቆሮ12፥27፤ኤፌ1፥22 ዕብ1፥6፤ራእ1፥5
1፥19 ዮሐ1፥16፤ ኤፌ1፥5
1፥20 ሉቃ2፥14፤ ሮሜ5፥10፤ ኤፌ1፥10፤2፥13
1፥21 ሮሜ5፥10፤ ኤፌ2፥3
1፥22 ቈላ20፤ ሮሜ5፥10፤7፥4፤ 2ቆሮ4፥14፤ኤፌ1፥4፤ 5፥27
1፥23 ቈላ5፡6፡25፤ ሮሜ10፥18፤ 11፥22፤ 1ቆሮ3፥5፤ ኤፌ3፥17
1፥24 1ቆሮ12፥27፤ 2ቆሮ1፥5፤6፥10
1፥25 ቈላ23፤ 1ቆሮ3፥5፤ኤፌ3፥2፤ ዕብ4፥12
1፥26 ሮሜ16፥25
1፥27 ማቴ13፥11፤ ሮሜ2፥4፤8፥10
1፥28 ማቴ5፥48፤ 1ቆሮ2፥6፡7፤ ኤፌ5፥27፤ቈላ3፥16 1፥29 1ቆሮ15፥10፤ 2ቆሮ11፥23፤ኤፌ1፥19፤3፥7፤ ቈላ15፥10

[ሀ]15 ወይም *በላይ*
[ለ]21 ወይም *በክፉ ባሕርያችሁ እንደሚታየው*

ይህ መግለጫ ሁለት እውነቶችን ያሳያል፤ (1) እግዚአብሔር የማይታይ አምላክ መሆኑን "እግዚአብሔርን ያየው ማንም የለም" ዮሐ 1፥18፤ (2) የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ልጁ የሆነውና የሰውን ሥጋ የለበሰው ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ባሕርይ መግለጹ ነው (1፥18፤ 14፥9 ይመ):: *ከፍጥረት ሁሉ ... በኵር*፤ በመጽሐፍ ቅዱስ፣ የበኵር ልጅ የተለየ ጥቅምና መብት እንዳለው ሁሉ ክርስቶስም እንዲሁ በፍጥረት ሁሉ ላይ የተለየ መብት አለው፤ ይኸውም እርሱ የፍጥረት ሁሉ የበላይ ነው፤ ልዑል ነው (ቈላ 16-18)::

1፥16 *ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሮአል*፤ ዮሐ 1፥3 ይመ:: በስድስት ጥቅሶች ውስጥ ብቻ ጳውሎስ ሰባት ጊዜ፣ "ፍጥረት ሁሉ"፣ "ሁሉ ነገር"፣ "ሁሉ" በማለት ክርስቶስ ከሁሉ በላይ መሆኑን በአጽንዖት ገለጸአል:: *ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ኀይላት፣ ገዦች ቢሆኑ ወይም ባለ ሥልጣናት*፤ በቈላስይስ በሚገኘው የኑፋቄ ትምህርት መላእክት የሥልጣን ተዋረድ እንዳላቸው ያስተምር ነበር፤ ያም ሆነ ይህ እነዚህ ኀይላት ሁሉ በክርስቶስ እንደ ተፈጠሩና እርሱም ከእነርሱ በላይ እንደ ሆነ ጳውሎስ አስተምሮአል::

1፥17 *እርሱ ከሁሉ በፊት ነው*፤ በዮሐ 1፥1-2፤ 8፥58 ላይ እንዳለው ዘላለማዊነቱን ያሳያል::

1፥18 በኵር፤ በትንሣኤ አካል ከሙታን መጀመሪያ የተነሣው እርሱ ነው:: ጳውሎስ በሌላ ቦታ፣ "ላንቀላፉት ሁሉ በኵራት ሆኖ በእርግጥ ከሙታን ተነሥቶአል" (1ቆሮ 15፥20) ይላል:: ብዙ ሰዎች ከሙታን ተነሥተዋል (2ነገ 4፥35፤ ሉቃ 7፥15፤ ዮሐ 11፥44፤ ሐሥ 9፥36-41፤ 20፥7-11)፤ ነገር ግን ተመልሰው ሞተዋል::

1፥19 *ሙላቱ*፤ ኖስትሳውያን የሚጠቀሙበትን ቃል ነው፤ በዚህ የኑፋቄ ትምህርት መሠረት ቃሉ የሰዎችን ዕድል ፈንታ የሚቈጣጠሩትን መለኮታዊ ኀይላት የሚያሳይ ነው:: ጳውሎስ፣ "ሙላት" ሲል ግን ኀይሉን በሕርዩን ጨምሮ የእግዚአብሔርን ሁለንተና (ሙላት) የሚያሳይ ነው (2፥9)::

1፥20 *ነገር ሁሉ በእርሱ በኩል ከራሱ ጋር አስታረቀ*፤ ክርስቶስ በሞቱ ሰውን ሁሉ አዳነ ለማለት አይደለም፤ ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ የዘላለም ቅጣት እንዳለና ያመኑ ሰዎች ብቻ ከዚህ እንደሚድኑ ያስተምራል:: አዳምና ሔዋን ኀጢአትን በሠሩ ጊዜ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረው መልካም ግንኙነት መበላሸቱ ብቻ ሳይሆን በፍጥረትም መካከል የተዘበራረቀ ነገር ተፈጠረ (ሮሜ 8፥19-22):: ክርስቶስ በመስቀል ሲሞት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ሰላምን መሠረተ፤ ይህ እውነት ተፈጻሚነትን የሚያገኘው ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ ብቻ ቢሆንም (ሮሜ 8፥21)፣ ክርስቶስ የተበላሸውን ግንኙነት ለማደስ መሠረት ጥሎአል::

1፥22 *በሞቱ*፤ በክርስቶስ ሞት ማለት ነው::

1፥23 *ፍጥረት ሁሉ*፤ የቈላ 6 ማብ ይመ::

1፥24 *ስለ እናንተ በተቀበልሁት መከራ*፤ ጳውሎስ ወንጌልን ለአሕዛብ በሚሰብክበት ጊዜ ማንኛውንም ዐይነት መከራ ተቀብሎአል፤ ይሁን እንጂ እዚህ ላይ የሚያመለክተው እስራቱን ሊሆን ይችላል:: *የጐደለውን...አሟላለሁ*፤ ኀጢአትን ሊያስተሰርይ ከሚችለው ከክርስቶስ መሥዋዕትነት የጐደለ ነገር አለ ለማለት አይደለም፤ ነገር ግን ለኀጢአት ክፍያ ክርስቶስ በመስቀል እንደ ተሠቃየ ሁሉ፣ ጳውሎስም ለጠፋችው ዓለም ይህን የምሥራች በማብሰር የመከራው (የሥቃዩ) ተካፋይ እንደ ሆነ የሚያመለክት ነው::

1፥25 *የእግዚአብሔርን ቃል በሙላት እንዳቀርብላችሁ*፤ የእግዚአብሔር ቃል በሙላት የቀረበላቸው ይመስላል፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ቃል የተላከበትን ዐላማ የሚፈጽመው (ኢሳ 55፥11) በሙላት በሚነገርበት ጊዜ ብቻ ነው:: ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል በሙላት ይሰብክ ዘንድ በሌላ ቦታ እንዳደረገው ሁሉ፣ በቈላስይስም ቤተ ክርስቲያን ይህን ቃል ማሰማት ነበረበት ማለት ነው (ሮሜ 15፥19 ይመ)::

1፥26 *ምስጢር*፤ በተለየ መረዳት ካልሆነ በቀር በሰው ሊታወቅ የማይችል የእግዚአብሔር ዐላማ ነው:: ይህ በጣዖት አምላኪዎች ዘንድ የተለመደ ቃል ሲሆን፣ በሃይማኖታቸው ውስጥ ድብቅ የሆነውን ነገር ዋኖቻቸው ለመነጋገር ሲፈልጉ የሚጠቀሙበት ቃል ነው:: ጳውሎስ ግን ብዙውን ጊዜ ከዚህ ቃል ጋር፣ "ተገልጦአል" (በዚህ ስፍራ)፣ "እንድናውቅ አደረገን" (ኤፌ 1፥9)፣ "እገልጥ ዘንድ" (ኤፌ 3፥9)፣ "አሁን በተገለጠው" (ሮሜ 16፥25) የሚሉትን ቃላት አብሮ በመጥቀስ የተዛባ ትርጕሙን ሙሉ በሙሉ ለውጦ እንዲኖረው አድርጐአል:: የክርስትና ምስጢር የተወሰኑ ሰዎች ብቻ የሚያውቁት ዕውቀት አይደለም፤ ነገር ግን አንድ ጊዜ ተሰውሮ የነበረ፣ አሁን ግን ተገልጦ በይፋ የሚሰበክ መለኮታዊ እውነት ነው::

1፥27 *በአሕዛብ መካከል...በእናንተ ውስጥ ያለው ክርስቶስ ነው*፤ ምስጢሩ ክርስቶስ በአሕዛብ ውስጥ የማደሩ ጉዳይ ነው፤ ቀደም ሲል አሕዛብ እንደ አይሁድ የክርስቶስ አካል በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተሰፋውን ቃል እንደሚካፈሉና አብረው እንደሚወርሱ አልተገለጸም ነበር (የኤፌ 3፥6 ማብ ይመ)::

1፥28 *ፍጹም*፤ ምስጢራዊ ሃይማኖቶችና ኖስትሳውያን የምስጢሩ ወይም የዕውቀቱ ባለቤት ናቸው የሚባሉትን ሰዎች የሚገልጹበት ቃል ነው (የ1ዮሐንስ መግቢያ ላይ "የኖስትሳውያን ትምህርት"

2 ስለ እናንተና በሎዶቅያ ስላሉት እንዲ
ሁም በአካል አይተውኝ ስለማያውቁ ሁሉ
ምን ያህል እየተጋደልሁ እንደ ሆነ እንድታውቁ
እፈልጋለሁ፤ [2]ደግሞም ልባቸው እንዲጽናናና
በፍቅር እንዲተሳሰሩ፣ ፍጹም የሆነውን
የመረዳት ብልጥግና አግኝተው የእግዚአብሔር
ምስጢር የሆነውን ክርስቶስን እንዲያውቁ
እተጋለሁ፤ [3]የተሰወረ የጥበብና የዕውቀት
ሀብት ሁሉ የሚገኘው በእርሱ ዘንድ ነውና።
[4]ማንም ንግግር በማሳመር እንዳያታልላችሁ
ይህን እነግራችኋለሁ። [5]ምንም በሥጋ ከእናንተ
ርቄ ብገኝ በመንፈስ ከእናንተ ጋር ነኝና
በሥርዐት መኖራችሁንና በክርስቶስ ያላችሁን
ጽኑ እምነት እያየሁ ደስ ይለኛል።

**ከሰው ሠራሽ ሥርዐት በክርስቶስ ነጻ መሆን**

[6]እንግዲህ ጌታ ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ
ተቀበላችሁት እንዲሁ በእርሱ ኑሩ፤ [7]በእ
ርሱ ተተክላችሁና ታንጻችሁ፣ እንደ ተማራ
ችሁት በእምነት ጸንታችሁ፣ የተትረፈረፈ
ምስጋና እያቀረባችሁ ኑሩ።
[8]በክርስቶስ ላይ ሳይሆን፣ በሰዎች ልማድና
በዚህ ዓለም መሠረታዊ ሕግጋት ላይ በተመ
ሠረተ ፍልስፍናና ከንቱ ማግባቢያ ማንም
ማርኮ እንዳይወስዳችሁ ተጠንቀቁ።
[9]የመለኮት ሙላት ሁሉ በአካል በእርሱ
ይኖራልና፤ [10]እናንተም የገዥነትና የሥልጣን
ሁሉ ራስ በሆነው በክርስቶስ ሙሉ ሆናችኋል።
[11]በእርሱ ሆናችሁ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ
ተገረዛችሁ፤ በክርስቶስም መገረዝ የሥጋን
ኀጢአታዊ ባሕርይ አስወገዳችሁ፤ [12]በጥምቀ
ትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ፤ እርሱን ከሙ
ታን ባስነሣው በእግዚአብሔር ኀይል በማመን
ከእርሱ ጋር ደግሞ ተነሣችሁ።
[13]እናንተም በበደላችሁና የሥጋችሁን ኀጢአ
ታዊ ባሕርይ ባለ መገረዝ ሙታን ሳላችሁ፣
እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ሕያዋን አደረ
ጋችሁ[#]፤ ኀጢአታችንንም ሁሉ ይቅር አለን፤
[14]ሲቃወመንና ሲጻረረን የነበረውን የዕዳ ጽሕ
ፈት ከነ ሕግጋቱ በመደምሰስ፣ በመስቀል ላይ
ቸንክሮ ከመንገድ አስወገደው። [15]የአለቆ
ችንና የባለ ሥልጣናትንም ማዕረግ በመግፈፍ
በመስቀሉ[+] ድል ነሥቶ በአደባባይ እያዞራቸው
እንዲታዩ አደረገ።
[16]እንግዲህ በምትበሉትም ሆነ በምትጠ
ጡት ወይም በዓልን፣ ወር መባቻንና ሰንበ
ትን በማክበር ነገር ማንም አይፍረድባችሁ፤
[17]እነዚህ ሊመጡ ላሉ ነገሮች ጥላ ናቸውና፤
አካሉ ግን የክርስቶስ ነው። [18]ዐጕል ትሕት
ናንና የመላእክትን አምልኮ የሚወድ ማንም

2፥1 ቈላ1፥29፤ 4፥12፡13፡15፡16፤ ራእ1፥11፤3፥14
2፥2 ሮሜ16፥25፤ ኤፌ6፥22፤ቈላ4፥8
2፥3 ኢሳ11፥2፤ ኤር23፥5፤ሮሜ 11፥33፤1ቆሮ1፥24፡30
2፥4 ሮሜ16፥18
2፥5 ሐሥ20፥21፤ 1ቆሮ5፥4፤ 14፥40፤1ተሰ2፥17፤ 1ጴጥ5፥9
2፥6 ዮሐ13፥13፤ ቈላ1፥10
2፥7 ኤፌ3፥17፤ 4፥21
2፥8 ቍ20፤ ገላ4፥3፤1ጢሞ6፥20
2፥9 ዮሐ1፥16
2፥10 ማቴ28፥18፤ ኤፌ1፥22
2፥11 ሮሜ2፥29፤ ገላ5፥24፤ፊል3፥3
2፥12 ማቴ28፥19፤ ሐሥ2፥24፤ሮሜ6፥5
2፥13 ኤፌ2፥1፡ 5፤4፥32
2፥14 ኤፌ2፥15፤ 1ጴጥ2፥24
2፥15 ቍ10፤ ማቴ12፥29፤ ሉቃ10፥18፤ ዮሐ12፥31፤ኤፌ6፥12
2፥16 ዘሌ23፥2፤ 1ዜና23፥31፤ማር2፥27፡28፤7፥19፤ሮሜ14፥3፡ 4፡5፡ 17፤ገላ4፥10 2፥17 ዕብ8፥5፤ 10፥1 2፥18 ቍ23፤1ቆሮ9፥24፤ ፊል3፥14

[#]13 *አንዳንድ የጥንት ቅጆች አደረገን* ይላሉ።
[+]15 *ወይም በእርሱ*

የሚለውን ይመ)። ነገር ግን በክርስቶስ አማካኝነት አማኝ ሁሉ ፍጹም ነው።

2፥1 *በሎዶቅያ*፤ ይህ መልእክት በዚያ በነበረችው ቤተ ክርስቲያንም መነበብ ነበረበት (4፥16)። ሎዶቅያ ከቈላስያስ 18 ኪ.ሜ. ያህል ርቃ የምትገኝ የአሁኗ ዴንዚሊ።

2፥2 *ምስጢር*፤ የ1፥26 እና የሮሜ 11፥25 ማብ ይመ።

2፥3 *ዕውቀት*፤ ድነት በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ነው የሚለውን የኖስትሳውያንን ትምህርት ለመቃወም ጳውሎስ በዚህ መልእክት (ቍ 2፤1፥9-10) ስለ ዕውቀት በአጽንዖት ይናገራል። ጳውሎስ የእውነተኛው ዕውቀት ባለቤቶች ኖስትሳውያን ሳይሆኑ ክርስቲያኖች ናቸው በማለት ጽፎአል ነው።

2፥5 *በሥጋ ከእናንተ ርቄ ብገኝ፣ በመንፈስ ከእናንተ ጋር ነኝ*፤ በ1ቆሮ 5፥3 ላይ ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው።

2፥6 *በእርሱ ኑሩ*፤ በዚህ መልእክት አማኝ ከክርስቶስ ጋር ያለው መንፈሣዊ አንድነትና የቀረበ ግንኙነት ተደጋግሞ ተገልጾ አል (ለምሳሌ ቍ 7፡10-13፡20፤1፥2፡27-28፡3፥1፡3 ይመ)።

2፥8 *በዚህ ዓለም መሠረታዊ ሕግጋት*፤ ይህ ቃል በቍ 20 እና በገላ 4፥3፡9 ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ የተገለጸ ሲሆን፣ ሐሰ ተኛ፣ ዓለማዊ፣ ሃይማኖታዊ ተራ ትምህርት ማለት ነው። አንድ ሰው ለድነት በክርስቶስ ከማመኑ ጋር ግዝረት፣ መብልና መጠ ጥን እንዲሁም ሃይማኖታዊ በዓላትን እንደ ማክበር ያሉ ቍሳ ዊና ውጫዊ ሥርዐቶችን ከደነገገው ሰው ሠራሽ ሕግና ምስጢራዊ ዕውቀትን ማግኘት እንደሚያስፈልግ የሚያስተምረውን የኑፋቄ ትምህርት ጳውሎስ አጥብቆ ይቃወማል።

2፥9 *የመለኮት ሙላት*፤ የ1፥19 ማብ ይመ። የእግዚአብሔር መለኮታዊ ባሕርይ በክርስቶስ አካል ውስጥ በሙላት እንደሚገኝ ሆን ተብሎ መገለጹ የኖስትሳውያንን ትምህርት በቀጥታ ለመቃወም የተደረገ ነው።

*2፥10-15*፤ ኖስትሳውያንን እንደ ሚሉት፣ ክርስቲያን ጐድ ለት ያለበት ሳይሆን በክርስቶስ ፍጹም መሆኑን ጳውሎስ ይናገራል። ይህም ፍጹምነት የኀጢአትን ባሕርይ ማስወገድን (ቍ 11)፣ ከመንፈሣዊ ሞት መነሣትን (ቍ 12-13)፣ ይቅርታ ማግኘትን (ቍ 13)፣ ከሕግ ዕዳ ነጻ መውጣትን (ቍ 14)፣ ከክፉ መናፍ ስትም ተጽእኖ ነፃ መሆንን (ቍ 15) ይጨምራል።

2፥11-12 *መገረዝ...ጥምቀትም*፤ በአይሁድ እምነት መሠ ረት ግርዘት አንድ ሰው በእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ግንኙነት ውስጥ እንደገባ የሚያሳይ ምልክት ነው። መገረዝ ከጥምቀት ጋር ተያይዞ የሚታይበት ክፍል ይህ ብቻ ቢሆንም፣ አንዳንዶች ይህን የውሃ ጥምቀት እንደ ግርዘት ለክርስቲያኖች የቃል ኪዳን ምልክት ነው ይላሉ።

2፥14 *የዕዳ ጽሕፈት*፤ ይህ የንግድ ስምምነትን የሚያመለክት ሲሆን፣ ተበዳሪ ባለ ዕዳ መሆኑን ለማመልከት አበዳሪው በራሱ እጅ ጽፎ የሚሰጠው ወረቀት ነው። ጳውሎስ ይህ ቃል እያንዳንዱን ሰው የእግዚአብሔር ባለ ዕዳ የሚያደርገውን የሙሴን ሕግ ከሙሉ ሥርዐቶቹ ጋር ለማመልከት ተጠቅሞበታል።

2፥15 *ማዕረግ በመግፈፍ*፤ እግዚአብሔር የደመሰሰው፣ ክርስቲያኖችን የሚቃወመውን ሕግ ብቻ ሳይሆን፣ ሰዎች አካላ ቸውን እንዲያጉሳቍሉና ሐሰተኛ ትምህርቶችን እንዲከተሉ የሚ ያደርጓቸውን ርኩሳን መላእክት ጭምር ነው (ሥልጣናትና ኀይላት 1፥16፤ ኤፌ 6፥12)። ቃሉ በጦር ሜዳ ወታደሮች ሙሉ በሙሉ ድል መሆናቸውን ለመግለጽ ልብሳቸውንና የጦር መሣሪ ያዎቻቸውን መገፈፋቸውን የሚያሳይ ሥዕላዊ ገለጻ ነው። *ድል ነሥቶ*፤ በቁሙ በድል አድራጊነት ይዞ መዞር ማለት ነው፤ ምሳ ሌነቱም አንድ ሮማዊ የጦር ጄኔራል ጠላቶቹን ሙሉ በሙሉ ድል ማድረጉን በከተማ ላለው ሕዝብ ማስረጃ ይሆን ዘንድ ምርኮ ኞቹን በአደባባዮች እየነዳ የሚሄድበትን ሁኔታ የሚያሳይ ነው (2ቆሮ 2፥14 እና ማብ ይመ)። ክርስቶስም እንዲሁ በዲያብሎስና በሰራዊቱ ላይ ድል አድራጊ እንደ ሆነ በማቴ 12፥29፤ ሉቃ 10፥18፤ ሮሜ 16፥20 ላይ ይመ።

2፥17 *ሊመጡ ላሉ ነገሮች ጥላ ናቸውና*፤ የክርስቶስን መምጣት በምሳሌነት የሚያሳዩ የብሉይ ኪዳን ሥርዐቶች በዚህ ስፍራ እንደ ጥላ (ከዕብ 8፥5፤ 10፥1 ጋር ያነጻጽሩ) ተጠቅሰዋል። ስለዚህ አሁን እነዚህን ሥርዐቶች መከተል ሙሉ በሙሉ መፈ ጸማቸውን አለመገንዘብ ነው። በቍ 20-21 ላይ እንደተመከ ተው፣ በቈላስይስ ቤተ ክርስቲያን ይታይ የነበረው ከሰው ከንቱ ሥርዐት ያለመላቀቅ ሁኔታ ግትር ከሆነ አካልን ከማጐሳቈል ሕይ ወት ጋር የተያያዘ ነበር።

2፥18 *ዐጕል ትሕትናን*፤ በመሠረቱ ደስ የሚያሰኝ ትሕ ትና፣ ተገቢ በሆነ ሁኔታ የሚገለጽ ትሕትና እንጂ በውሸት ወይም በግብዝነት የሆነው አይደለም። ጳውሎስ እዚህ ላይ የሚናገረው ታላቅ በሆነው አምላክ ፊት የውሸት ትሕትና የሆነውን ለማ መልከት ሊሆን ይችላል፤ ይህም እግዚአብሔርን ከሰው በላይ ብቻ በማድረግ፣ የፈጠራቸው መላእክት በሚመለኩበት ሁኔታ መመለኩን የሚያሳይ ነው። በሁለተኛው ምእተ ዓመት የነበረው የኖስትሳውያን ትምህርት ከእግዚአብሔር የወጡ መንፈሣዊ ፍጥረታት አሉ፤ በእነርሱም አማካይነት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይቻላል የሚል ነበር። *እንዳያደናቅፋችሁ ተጠንቀቁ*፤ ይህ ቃል

ሰው እንዳያደናቅፋችሁ ተጠንቀቁ። እንደ
ዚህ ያለ ሰው ስላየው ራእይ ከመጠን በላይ
ራሱን እየካበ በሥጋዊ አእምሮው ከንቱ
ሐሳብ ተሞልቶ ይታበያል፤ 19ይህ ሰው፣
አካል ሁሉ በጅማትና በማሰሪያ እየተጋጠመ
ምግብንም እየተቀበለ እግዚአብሔር በሚሰጠው
ማደግ ከሚያድግበት ራስ ከሆነው ጋር ግንኙ
ነት የለውም።
20ለዚህ ዓለም መርሕ ከክርስቶስ ጋር
ከሞታችሁ ታዲያ ለምን እንደዚህ ዓለም
ሰው ለሕጎቹ ተገዢ ትሆናላችሁ? 21“አትያዝ!፤
አትቅመስ! አትንካ!” እንደሚሉት ዐይነት፣
22እነዚህ ሁሉ በሰው ትእዛዝና ትምህርት ላይ
የተመሠረቱ ስለ ሆኑ በተግባር ላይ ሲውሉ
ጠፊ ናቸው። 23እነዚህ ነገሮች በገዛ ራስ ላይ
ከሚፈጥሩት የአምልኮ ስሜት፣ ከዐጉል ትሕ
ትናና ሰውነትን ከመጨቈን አንፃር በእርግጥ
ጥበብ ያለባቸው ይመስላሉ፤ ነገር ግን የሥ
ጋን ልቅነት ለመቈጣጠር አንዳች ፋይዳ የላቸ
ውም።

## የቅድስና ሕይወት መመሪያ

3 እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፣ ክር
ስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ በተቀመጠበት
በላይ ያሉ ነገሮችን እሹ፤ 2አሳባችሁም በላይ
ባለው ላይ እንጂ በምድራዊ ነገር ላይ አይ
ሁን። 3ሞታችኋልና፤ ሕይወታችሁም ከክር
ስቶስ ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ተሰውሮአልና፤
4ሕይወታችሁ[∩] የሆነው ክርስቶስ በሚገለጥ
በት ጊዜ እናንተም በዚያን ጊዜ ከእርሱ ጋር
በክብር ትገለጣላችሁ።
5ስለዚህ ምድራዊ ምኞቶቻችሁን ግደሉ፤
እነዚህም፦ ዝሙት፣ ርኵሰት፣ ፍትወት፣ ክፉ
ምኞትና አምልኮተ ጣዖት የሆነው መጐም
ጀት ናቸው። 6በእነዚህም ምክንያት የእግዚ
አብሔር ቍጣ በማይታዘዙት[†] ላይ ይመጣል፤
7እናንተም ቀድሞ በኖራችሁበት ሕይወት
በእነዚህ ትመላለሱ ነበር፤ 8አሁን ግን ቍጣን፣
ንዴትን፣ ስድብን፣ ሐሜትንና አሳፋሪ ንግግ
ርን የመሳሰሉትንም ሁሉ አስወግዱ፤ 9አሮጌ
ውን ሰው ከሥራው ጋር አውልቃችሁ ስለ
ጣላችሁ እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ።
10የፈጣሪውን መልክ እንዲመስል በዕውቀት
የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችኋል፤
11በዚያ ግሪክ ወይም ይሁዲ፣ የተገረዘ ወይም
ያልተገረዘ፣ አረማዊ ወይም እስኩቴስ፣ ባሪያ
ወይም ጌታ ብሎ ልዩነት የለም፤ ነገር ግን
ክርስቶስ ሁሉም ነው፤ በሁሉም ነው።
12እንግዲህ የተቀደሳችሁና የተወደዳችሁ
የእግዚአብሔር ምርጦች እንደ መሆናችሁ ርኅ
ራኄን፣ ቸርነትን፣ ትሕትናን፣ ጨዋነትንና
ትዕግሥትን ልበሱ፤ 13እርስ በርሳችሁ ተቻ
ቻሉ፤ ከእናንተ አንዱ በሌላው ላይ ቅር የተሰ

2፥19 1ቆሮ12፥27፤ ኤፌ1፥22፤ኤፌ4፥16
2፥20 ቍ8:14:16፤ ሮሜ6፥6፤ገላ4፥3:9
2፥22 ኢሳ29፥13፤ ማቴ15፥9፤1ቆሮ6፥13፤ ቲቶ1፥14
2፥23 ቍ18
3፥1 ማር16፥19፤ ሮሜ6፥5
3፥2 ፊል3፥19:20
3፥3 ሮሜ6፥2፤ 2ቆሮ5፥14
3፥4 1ቆሮ1፥7፤ ገላ2፥20፤1ጴጥ1፥13፤ 1ዮሐ3፥2
3፥5 ሮሜ6፥2፤ 1ቆሮ6፥18፤ገላ5፥19: 21:24፤ኤፌ4፥22፤5፥3:5
3፥6 ሮሜ1፥18
3፥7 ኤፌ2፥2
3፥8 ኤፌ4፥22: 29:31
3፥9 ሮሜ6፥6፤ ኤፌ4፥25
3፥10 ሮሜ6፥4፤ 12፥2፤13፥14፤ 2ቆሮ4፥16፤ ኤፌ2፥10፤4፥23
3፥11 ሮሜ10፥12፤ 1ቆሮ7፥19፤12፥13፤ ገላ3፥28፤ኤፌ1፥23
3፥12 ቍ10፤ 2ቆሮ6፥6፤ገላ5፥22: 23፤ኤፌ4፥2፤ ፊል2፥3
3፥13 ኤፌ4፥2:32

[∩]4 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *የኛ ሕይወት*
†6 *በማይታዘዙት ላይ* የሚለው ሐረግ በአንዳንድ የጥንት ቅጆች ላይ ብቻ የሚገኝ ነው

የውድድርን ሕግ የሚጥስን አንድ ስፖርተኛ ዳኛው ከጨዋታው ውጪ የሚያደርግበትን ሁኔታ ያመለክታል። የቈላስይስ ምእመ ናን በአጕል ትሕትናና በመላእክት አምልኮ እግዚአብሔርን ደስ ስለማያሰኙ፣ ያገኙትን ድነት ሊያስከዷአቸው የመጡት የሐሰት አስማሪዎች መቀበል አይገባቸውም። *ስላየው ራእይ፤* ምናልባት የሐ ሰት አስተማሪዎች አየን የሚሉትን የውሸት ራእይ በተመለከተ ሊሆን ይችላል።

2፥19 *ራስ ከሆነው ጋር ግንኙነት የለውም፤* በቈላስይስ ቤተ ክርስቲያን የነበረው የኑፋቄ ትምህርት የክርስቶስን ፍጹም አምላክ ነት የማይቀበልና ከአምላክነቱ ዝቅ የሚያደርግ ነበር (ቍ 9፤ 1፥19 ይመ)።

2፥20 *መርሕ፤* የቍ 8 ማብ ይመ።

2፥21 *“አትያዝ! አትቅመስ! አትንካ!”፤* ይህ የሐሰት ትም ህርት ምን ያህል አካል የማጐሳቈል ባሕርይ እንዳለው የሚያሳይ ነው። እዚህ ላይ የተጠቀሱት ሕግጋት የብሉይ ኪዳን ሥርዐቶችን እስከ መጨረሻው የመጠበቅን ሁኔታ ይገልጻሉ።

*2፥23፤* በቈላስይስ የነበረው የሐሰት ትምህርት ሰፋ ባለ መልኩ ይህን የሚመስል ነው፦ (1) የሚስብ ሥርዐት ያለው የሃይ ማኖት ትምህርት ነው፤ (2) ይህ ሥርዐት በራሳቸው በሐሰት አስ ተማሪዎች የተፈጠረ እንጂ ምንጩ መለኮታዊ አይደለም፤ (3) የሐ ሰት መምህራኑ ዐጕል ትሕትናን ለማሳየት ይሞክራሉ፤ (4) ትሕ ትናቸውን ለመግለጽ ሰውነታቸውን አላግባብ የመጨቈንን ትም ህርት ያስተጋባሉ። ጳውሎስ እንዲህ ዐይነቱ ልምምድ ሥጋዊ ስሜትን ለመቈጣጠር የሚያስችል ኀይል ስለሌለው ከንቱ ነው ይለዋል። *በገዛ ራስ ላይ ከሚፈጥሩት የአምልኮ ስሜት፤* የሐሰት አስተማሪዎች ከእግዚአብሔር ስላልሆኑ፥ በትምህርታቸው ውስጥ ያለ ውን ሥርዐትና ደንብ የፈጠሩት እነርሱ ራሳቸው ናቸው።

3፥1 *እንግዲህ፤* ይህ ቃል አስተምህሮአዊ የሆነውን የመል እክቱን ክፍል ተግባራዊ ከሆነው ክፍል ጋር የሚያገናኝ ነው፤ በሮሜ 12፥1፤ ኤፌ 4፥1፤ ፊል 4፥1 ላይ ተመሳሳይ ሁኔታ ተጠቅሶ አል። *ከተነሣችሁ፤* ከቍ 1፥10 ያሉት ጥቅሶች ክርስቲያን መሆን ያለበትን የሚያመለክቱና ትእዛዝ የሚሰጡ ሐሳቦች ናቸው። እነ ዚህ አመልካች የሆኑ ዐረፍተ ነገሮች አማኝ በክርስቶስ ያለውን ስፍራ የሚያመለክቱ ናቸው፤ ይኸውም፦ አማኝ ከክርስቶስ ጋር ሞቶአል (ቍ 3)፤ ከክርስቶስ ጋር ተነሥቶአል (ቍ 1)፤ ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአል (ቍ 3)፤ አሮጌውን ሰውነት አውልቆአል፤ (9) አዲ ሱን ሰውነት ለብሶአል (ቍ 10)። ትእዛዝ ሰጪ የሆኑት ዐረፍተ ነገሮች ደግሞ አማኝ ከድነቱ የተነሣ በሕይወቱ ሊታይ የሚገባውን ነገር ያመለክታል። ይህም ክርስቲያን ልቡን በላይ ባሉ ነገሮች ላይ ያደርጋል (ቍ 1-2)፤ ምድራዊ ምኞቱን በሙሉ ይገድላል (ቍ 5)፤ ያልተለወጠውን የእኔነቱን ባሕርይ ያርቃል (ቍ 8)። በአጠቃላይ ክርስቲያን በክርስቶስ ያገኘውን አዲስ ሕይወት በዕለት ኑሮው እንዲገልጽ ተጠርቶአል (ከሮሜ 6፥1-13 ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥4 *በሚገለጥበት ጊዜ፤* የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ያመለክታል።

3፥6 *የእግዚአብሔር ቍጣ፤* የዘካ 1፥2 ማብ ይመ። እግዚ አብሔር ኀጢአትን ፈጽሞ ይቃወማል፤ እንዲሁም ኀጢአትን በሚገባ ይቀጣል።

3፥9-10 *አውልቃችሁ ስለጣላችሁ...ለብሳችኋል፤* አንድ ሰው ያደፈን ልብስ አውልቆ ንጹሑን እንደሚለብስ ክርስቲያንም እንዲሁ ክፉ መንገዶቹን በመቃወም በክርስቶስ መንግሥት ሥርዐት መሠረት እንዲኖር ተጥርቶአል (ቍ 12-14 ይመ፤ ከገላ 3፥27 ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥10 *የፈጣሪውን መልክ፤* የዘፍ 1፥26 ማብ ይመ። *ዕው ቀት፤* 1፥10፤2፥2-3 ይመ። *የሚታደሰውን፤* 2ቆሮ 5፥17 ይመ።

3፥11 *አረማዊ፤* ይህ አጠራር የተሰጠው የግሪክን ቋንቋ ለማ ይናገርና የሰለጠነ አይደለም ለሚባል ሰው ነው። *እስኩቴስ፤* እስኩቴሶች በተለይ በጨካኝነታቸው ከዱር አራዊት እንደማይለዩ ተደርገው ይቈጠሩ ነበር። እስኩቴሶች የመጡት ዛሬ ደቡብ ሩስያ ተብሎ ከሚጠራው ስፍራ ነው። *ክርስቶስ ሁሉም ነው፤ በሁሉም ነው፤* ክርስቶስ የባህልንና የጐሣን ልዩነት ግድግዳ በማፍረስ ሰዎችን አንድ አድርጎአቸዋል። እንዲህ ዐይነቶቹ ልዩነቶች ጠፊ ዎች ናቸው፤ ይህን ማድረግ የሚችለውም ክርስቶስ ብቻ ነው።

3፥12 *የእግዚአብሔር ምርጦች፤* ይህ ስም ለእስራ ኤላውያን (ዘዳ 4፥37) እንዲሁም ለክርስቲያኖች (1ጴጥ 2፥9) ተሰጥቶአል። በጳውሎስ መልእክት ውስጥ በአምላክ የመመረጥ ትምህርት ተደጋግሞ የተሰጠ ነው (የኤፌ 1፥4 ማብ ይመ)፤ ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን ኀላፊነት ወይም ተጠያቂነት አያጣጥልም። በአንጻሩ ደግሞ ክርስቲያን ለዘላለም ሕይወት ስለ ተመረጠ ቅድስና የተሞላበትን ሕይወት ለመኖር ጥረት ማድረግ እንዳለበት ይህ ጥቅስ ያሳያል። እንደ ጳውሎስ ትምህርት የእግዚ አብሔር ሉዓላዊነትና የሰው ኀላፊነት እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሄዱ እውነታዎች ናቸው።

ኝበት ነገር ቢኖር ይቅር ተባባሉ፤ ጌታ ይቅር
እንዳላችሁ እናንተም ሌላውን ይቅር በሉ።
14በእነዚህ ሁሉ ላይ ሁሉን በፍጹም አንድ
ነት የሚያስተሳስረውን ፍቅርን ልበሱት።
15እንደ አንድ አካል ሆናችሁ የተጠራ
ችሁበት የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይንገሥ፤
የምታመሰግኑም ሁኑ። 16የክርስቶስ ቃል በሙ
ላት ይኑርባችሁ፤ እርስ በርሳችሁ በጥበብ ሁሉ
ተማማሩ፤ ተመካከሩ፤ በመዝሙርና በማሕሌት፣
በመንፈሳዊም ቅኔ በማመስገን በልባችሁ ለእ
ግዚአብሔር ዘምሩ። 17በእርሱ በኩል ለእግ
ዚአብሔር አብ ምስጋና እያቀረባችሁ፣ በቃ
ልም ሆነ በተግባር የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ
በኢየሱስ ስም አድርጉት።

## የክርስቲያናዊ ቤተ ሰብ መመሪያ

18ሚስቶች ሆይ፤ በጌታ ዘንድ ተገቢ በመ
ሆኑ ለባሎቻችሁ ታዘዙ።
19ባሎች ሆይ፤ ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤
መራራም አትሁኑባቸው።
20ልጆች ሆይ፤ ይህ ጌታን ደስ የሚያ
ሰኝ በመሆኑ ለወላጆቻችሁ በሁሉም ነገር
ታዘዙ፤
21አባቶች ሆይ፤ ተስፋ እንዳይቈርጡ ልጆ
ቻችሁን አታስመርሯቸው።
22ባሮች ሆይ፤ ሰውን ለማስደሰትና ለታ
ይታ ብላችሁ ሳይሆን በቅን ልብ ጌታን በመ
ፍራት ለምድራዊ ጌቶቻችሁ በሁሉ ነገር
ታዘዙ። 23የምታደርጉትን ሁሉ ለሰው ሳይ
ሆን ለጌታ እንደምታደርጉት ቈጥራችሁ
በሙሉ ልባችሁ አድርጉት፤ 24ከጌታ ዘንድ
እንደ ብድራት የምትቀበሉት ርስት እንዳለ
ታውቃላችሁና፤ የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶ
ስን ነው። 25በደለኛውም የእጁን ያገኛል፤ አድ
ልዎም የለም።

4 ጌቶች ሆይ፤ እናንተም በሰማይ ጌታ
እንዳላችሁ ስለምታውቁ አገልጋዮቻች
ሁን በፍትሕና በቅንነት አስተዳድሯቸው።

## ሌሎች ምክሮች

2ከማመስገን ጋር ነቅታችሁ በትጋት
ጸልዩ። 3እኔ እስረኛ የሆንሁለትን የክርስቶ
ስን ምስጢር ማወጅ እንድንችል፣ እግዚአብሔር
የቃሉን በር እንዲከፍትልን ስለ እኛ ደግሞ
ጸልዩ፤ 4ደግሞም መናገር እንደሚገባኝ
ቃሉን በግልጽ እንድናገር ጸልዩልኝ። 5በውጭ
ካሉት ሰዎች ጋር ባላችሁ ግንኙነት በጥበብ
ተመላለሱ፤ በተገኘውም ዕድል ሁሉ ተጠ
ቀሙ። 6ለእያንዳንዱ ሰው እንዴት መልስ
መስጠት እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ ንግግራ
ችሁ በጨው እንደ ተቀመመ ሁልጊዜ በጸጋ
የተሞላ ይሁን።

## የስንብት ሰላምታ

7ቲኪቆስ ስላለሁበት ሁኔታ በሙሉ ይነግ
ራችኋል፤ እርሱ የተወደደ ወንድምና ታማኝ
አገልጋይ፣ በጌታም አብሮኝ ሎሌ ነው። 8ስላ
ለንበት* ሁኔታ እንድታውቁና ልባችሁ
ንም እንዲያጽናና ለዚህ ጕዳይ ወደ እናንተ
እልከዋለሁ፤ 9እርሱም ከእናንተ ወገን ከሆነው
ከታማኙና ከተወዳጁ ወንድማችን ከአናሲሞስ
ጋር ወደ እናንተ ይመጣል፤ እነርሱም እዚህ
ስላለው ሁኔታ ሁሉ ይነግሯችኋል።
10አብሮኝ የታሰረው አርስጥሮኮስና የበርና
ባስ የአክስቱ ልጅ ማርቆስ ሰላምታ ያቀርቡ
ላችኋል፤ ስለ ማርቆስ መመሪያ ደርሶአችኋል፤

3፥14 ሮሜ15፥5፤ 1ቆሮ13፥1:13
3፥15 ዮሐ14፥27፤ ሮሜ12፥5፤14፥19
3፥16 መዝ47፥7፤ ሮሜ10፥17፤ ኤፌ5፥19፤ቈላ1፥28
3፥17 1ቆሮ10፥31፤ ኤፌ5፥20
3፥18 ኤፌ5፥22
3፥24 ማቴ16፥27፤ ሐሥ 20፥32
3፥25 ሐሥ10፥34
4፥1 ዘሌ25፥43:53
4፥2 ሉቃ18፥1
4፥3 ሐሥ14፥27፤ 21፥33፤ሮሜ16፥25
4፥5 ማር4፥11፤ ኤፌ5:15:16
4፥6 ማር9፥50፤ ኤፌ4፥29፤1ጴጥ3፥15
4፥7 ሐሥ20፥4፤ ኤፌ6፥21:22፤ቈላ1፥7
4፥8 ኤፌ6፥21: 22፤ቈላ2፥2
4፥9 ቍ 12፤ፊሞ10
4፥10 ሐሥ4፥36፤ 12፥12፤19፥29

*8 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *ስለእናንተ...ያውቅ ዘንድ*

3፥15 *የክርስቶጸስ ሰላም* በመራራነትና በጠበኝነት መንፈስ ምትክ ክርስቶስ፣ ብቻ የሚሰጠውንም ሰላም ያመለክታል። ይህ የሰው ልጆችን ግንኙነት በሙሉ ሊገዛ ይገባዋል።

3፥16 *የክርስቶስ ቃል*፤ የቈላስይስ መልእክት በተጻፈበት ዘመን በቃል የተላለፈውን የክርስቶስን ትምህርት ያመለክታል። በሌላ መልኩ ግን ብሉይና አዲስ ኪዳንን ያጠቃልላል። *በመዝሙርና በማሕሌት፣ በመንፈሳዊም ቅኔ*፤ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው ጥንታዊ የሆኑ መዝሙሮች እስከ ዛሬ ድረስ ተጠብቀው የቈዩት በጳውሎስ መልእክታት ውስጥ ነው (1፥15-20፤ ኤፌ. 5፥14፤ ፊል 2፥6-11፤ 1ጢሞ 3፥16)። "መዝሙር" የሚለው በቤተ ክርስቲያን የሚዘምሩትን የብሉይ ኪዳንን መዝሙሮች ያመለክታል (ሉቃ 20፥42፤ 24፥44፤ ሐሥ 1፥20፤13፥33 ይመ)። ደግሞም መዝሙር በአምልኮ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን የሚዘመረውንም ሊያመለክት ይችላል። "ማሕሌት" በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርን ስለማንነቱ ለማወደስ እንደ ተጻፉት መዝሙሮች በተለይም በበዓላት ጊዜ (1ቆሮ 14፥26፤ ዕብ 2፥12 ደግሞም ሐሥ 16፥25 ይመ) የሚደረገው የውዳሴ መዝሙር ነው። "መንፈሳዊ ቅኔ" ደግሞ እግዚአብሔር ያደረገውን ውለታ በመቍጠር ስለ ሥራው እርሱን የምናመልክበት ነው (ራእ 5፥9፤14፥3፤ 15፥3)፤ ይህም በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ላደረገው ነገር ምስጋና ለማቅረብ እንደተጠቀሱት መዝሙሮች ዐይነት ማለት ነው (የኤፌ. 5፥19 ማብ ይመ)።

*3፥18-4፥1*፤ በኤፌ. 5፥22-6፥9 ላይ ያለውን ማብ ይመ።

3፥20 *በሁሉም ነገር*፤ ኀጢአት ከሆነው ነገር በስተቀር በሁሉም ነገር ወላጆችን መታዘዝ አስፈላጊ እንደሆነ ያመለክታል (ሐሥ 5፥29 ይመ)።

*3፥22-4፥1*፤ ጳውሎስ ባርነትን እንደ ክፉ ነገር አይቈጥረውም፤ በጌቶች ላይ የሚደረገውንም ዐመፅ አይቃወምም፤ ከዚህ ይልቅ ባሮችንና ጌቶቻቸውን ጠርቶ በግንኙነታቸው ክርስቲያናዊ የሆነውን መንገድ በማሳየት፣ ሥርዐቱ ፈጽሞ ሊለወጥ የሚችልበትን ሁኔታ ያሳያል። ጳውሎስ ስለ ባሎች፣ ሚስቶች፣ ልጆችና አባቶች ከጻፈው ይልቅ ስለ ባሪያዎች አጥብቆ የጻፈበት ምክንያት ከቲኪቆስ ጋር በመሆን ይህን የቈላስይስ እንዲሁም የፊልሞናን መልእክት ይዞ የሚሄደው አናሲሞስ ስለ ሆነ ነው። የአናሲሞስ ጌታ የሚኖረውም በዚያው በቈላስይስ ነበር።

4፥6 *በጨው እንደ ተቀመመ*፤ ጨው ምግብ እንዳይበላሽ የሚከላከልና መልካም ጣዕም እንዲኖረው የሚያደርግ ነው። የክርስቲያንም ንግግር እንደዚሁ መሆን አለበት (3፥8 እና ኤፌ. 4፥29 ይመ)።

4፥7 *ቲኪቆስ*፤ የኤፌ. 6፥21 ማብ ይመ።

*4፥9-17*፤ አናሲሞስ (ቍ 9)፣ አርስጥሮኮስ (ቍ 10)፣ ማርቆስ (ቍ 10)፣ አጳፍራ (ቍ 12)፣ ሉቃስ (ቍ 14)፣ ዴማስ (ቍ 14) እንዲሁም አክሪጳ (ቍ 17) በፊልሞና መልእክት ላይ መጠቀሳቸው፣ የቈላስይስና የፊልሞና መልእክታት በተመሳሳይ ጊዜና ቦታ እንደ ተጻፉ ያሳያል።

4፥9 *አናሲሞስ*፤ በቈላስይስ ይኖር ለነበረው ፊልሞና ለተባለው ክርስቲያን ባሪያ ነበር። ምናልባትም ከጌታው ከፊልሞና ዘንድ አንድ ነገር ሰርቆ ሳሸሽ አይቀርም (ፊል 18)፤ ይህ ደግሞ በሮማውያን ሕግ መሠረት በሞት የሚያስቀጣ ነበር። ይሁን እንጂ አናሲሞስ ሸሽቶ ሳለ ከጳውሎስ ጋር ተገናኝቶ ክርስቲያን ሆነ (ፊል 10)። አናሲሞስ ክርቲያን ከሆነ በኋላ ወደ ጌታው ወደ ፊልሞና ለመመለስ ፈቃደኛ ስለ ሆነ፣ ጌታው ፊልሞና እንደ ክርስቲያን ወንድም እንዲቀበለው ጳውሎስ መልእክት ጻፈለት (ፊልሞ 16)።

4፥10 *አርስጥሮኮስ*፤ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ስሙ ሦስት ጊዜ የተጠቀሰ የመቄዶንያ ሰው ነበር፣ (1) የኤፌሶን ከተማ በረብሻ ስትታመስ (ሐሥ 19፥29) ከጳውሎስ ጋር የነበረ ሰው ነው፤ ለዚህም ነው በቈላስያስ ታዋቂ ሊሆን የቻለው። (2) እርሱና ቲኪቆስ (ሐሥ 20፥4) ከጳውሎስ ጋር በግሪክ ነበሩ። (3) ጳውሎስ ወደ

እንግዲህ ወደ እናንተ ሲመጣ ተቀበሉት።
[11]ኢዮስጦስ የተባለው ኢያሱም ሰላምታ ያቀር
ብላችኋል። ከተገረዙት መካከል ለእግዚአብሔር
መንግሥት አብረውኝ የሚሠሩት እኔንም
ያጽናኑኝ እነዚህ ብቻ ናቸው፤ እነርሱም አጽናን
ተውናል። [12]ከእናንተ ወገን የሆነው የክርስቶስ
ኢየሱስ አገልጋይ ኤጳፍራ ሰላምታ ያቀርብላች
ኋል፤ እርሱም ፍጹም ጠንክራችሁና ሙሉ
በሙሉ ተረጋግታችሁ በእግዚአብሔር ፈቃድ
ሁሉ ጸንታችሁ እንድትቆሙ ዘወትር ስለ
እናንተ በጸሎት እየተጋደለ ነው። [13]ደግሞም
ስለ እናንተ እንዲሁም በሎዶቅያና በኢያራ
ከተሞች ስላሉት ተግቶ እንደሚሠራ እኔ
እመሰክርለታለሁ። [14]የተወደደው ሐኪሙ
ሉቃስ እንዲሁም ዴማስ ሰላምታ ያቀርቡላች
ኋል። [15]በሎዶቅያ ላሉት ወንድሞች፣ ለን
ምፉን፣ በቤቷም ላለች ቤተ ክርስቲያን
ሰላምታ አቅርቡልኝ።
[16]ይህች መልእክት ከተነበበችላችሁ በኋላ
በሎዶቅያ ላለችው ቤተ ክርስቲያን ደግሞ
እንድትነበብ አድርጉ፤ እናንተም ደግሞ በሎ
ዶቅያ ያለችውን መልእክት አንብቡ።
[17]ለአክሪጳም፣ "በጌታ የተቀበልኸውን አገ
ልግሎት ከፍጻሜ ለማድረስ ተጠንቀቅ" በሉ
ልኝ።
[18]ይህን ሰላምታ በገዛ እጄ የጻፍሁት
እኔ ጳውሎስ ነኝ። እስራቴን አስቡ። ጸጋ
ከእናንተ ጋር ይሁን።

4፥11 ፊል2፥25
4፥12 ቈ1፥7፤ ሮሜ15፥30፤ 1ቆሮ2፥6፤ቈ4፥1፥7፤ ፊሞ23
4፥13 ቈላ2፥1
4፥14 2ጢሞ4፥10፡ 11፤ፊሞ24
4፥15 ሮሜ16፥5፤ ቈላ2፥1
4፥16 1ተሰ3፥14፤ 1ጢሞ4፥13
4፥17 2ጢሞ4፥5፤ ፊሞ2
4፥18 ሐሥ21፥33፤ 1ቆሮ16፥21፤ 1ጢሞ6፥21፤ ዕብ13፥3

ሮም በሄደ ጊዜም አብሮት ነበር (ሐሥ 27፥2)። *ማርቆስ*፤ የማርቆስ ወንጌል ጸሐፊ ነው። በርናባስ ይዘኸው ሂድ ቢለውም እንኳ ማርቆስ በጵንፍልያ (ሐሥ 15፥8) ጥሎን ሄዶአል በማለት ጳውሎስ በሁለተኛዋ የወንጌል ጉዞው ይዞት ሊሄድ አልፈቀደም። አሁን ግን ከዐሥራ ሁለት ዓመት በኋላ በመካከላቸው የነበረው ችግር ስለ ተስተካከለ በዚህ ሥፍራና በፊልሞና 24 ላይ የማርቆስን ሰላምታ ጨምሮ ሲጽፍ ይታያል። ከአምስት ዓመት በኋላም፣ "ማርቆስ ለአገልግሎት ብዙ ይጠቅመኛል" ብሎ ጽፎአል (2ጢሞ 4፥11፤ የሐሥ 15፥39፤ ማብ ይመ)።

4፥13 *ኢያራ*፤ ከሎዶቅያ 10 ኪ.ሜ. ከቈላስይስም ደግሞ 22 ኪ.ሜ. ያህል የምትርቅ በትንሿ እስያ የምትገኝ የአሁኗ የቱርክ ከተማ ናት። ቤተ ክርስቲያኒቱ የተመሠረተችው ጳውሎስ በኤፌሶን በቈየበት በሦስቱ ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደ ሆነ ይገመታል (ሐሥ 19)፤ ይሁን እንጂ የመሠረታት ጳውሎስ ላይሆን ይችላል (ከ2፥1 ጋር ያነጻጽሩ)።

4፥14 *ሉቃስ*፤ ጳውሎስ በተጓዘበት ስፍራ ሁሉ አብሮት በመሆን (የሐሥ 16፥19 ማብ ይመ) በሐዋርያት ሥራ መጽሐፉ ላይ ስለ ጳውሎስ ጽፎአል፤ እንዲሁም ይህ መልእክት በተጻፈበት ከጳውሎስ ጋር በሮም አብሮት ነበር (ሐሥ 28)። *ዴማስ* የክርስቶስ አገልጋይ ሲሆን በኋላ ግን ከጳውሎስን ተለይቶ ሄዶአል (2ጢሞ 4፥10)።

4፥15 *ለንምፉን*፤ ምናልባትም ሎዶቅያ ናት። *በቤቷም ላለች ቤተ ክርስቲያን*፤ በብዙ ቦታ የሚገኙት የጥንት አብያተ ክርስቲያናት የራሳቸው ሕንጻ ስላልነበራቸው ለአምልኮ፣ ለትምህርትና ለስብከት የግለሰቦችን ቤት ይጠቀሙ ነበር። ለምሳሌ ጵርስቅላና አቂላ (ሮሜ 16፥5፤ 1ቆሮ 16፥19)፣ ፊልሞና (ፊል 2) እንዲሁም የዮሐንስ እናት ማርያም (ሐሥ 12፥12)።

4፥16 *ይህች መልእክት ከተነበበችላችሁ በኋላ*፤ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ጳውሎስ የላከውን መልእክት በተሰበሰበ ጉባኤ ፊት ድምፅን ከፍ አድርጎ የማንበብ ልማድ ነበራት። *በሎዶቅያ*፤ የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን የጻፈችው መልእክት ሳይሆን፣ ጳውሎስ ለሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን የጻፈውና የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ለቈላስይስ ቤተ ክርስቲያን እንዲያነቡት የምትሰጠው መልእክት ሊሆን ይችላል። ምናልባትም ይህ ደብዳቤ ቲኪቆስ ከኤፌሶን፣ ቈላስይስና ፊልሞና መልእክታት ጋር ይዞት የሄደው አራተኛ መልእክት ሊሆን ይችላል። ይህም ስፍራ በዛሬዋ ቱርክ የሚገኝ ነው። ምናልባት ይህ መልእክት ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን የተላከው መልእክት ሆኖ ከሎዶቅያ እስከ ቈላስይስ ድረስ ተወስዶ የተነበበ ሊሆን ይችላል።

4፥17 *አክሪጳ*፤ በፊሞ 2 ላይ ጳውሎስ ከእኛ ጋር አብሮ ወታደር ይለዋል።

*4፥18*፤ ጳውሎስ መልእክታቱን በቃል እየነገረ በማስጻፍ (ሮሜ 16፥22 ይመ) አንዳንድ ሰላምታዎችን በገዛ እጁ ይጽፍ ነበር (1ቆሮ 16፥21፤ ገላ 6፥11፤ 2ተሰ 3፥17፤ ፊሞ 19)። በመልእክቱ በመጨረሻ ላይ በገዛ እጁ መጻፉ ለመልእክቱ እርግጠኛነት ዋስትና ይሰጣል።